በመንፈስ ቅዱስ ግብር ሕይወቴ ለምልማ
ብርሃን ለብሳለች ጽድቅን ተሸልማ

68. ቅዱስ ቅዱስ

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር /፪/

ዘበተዋሕዶ /፪/ ይሜለስ /፪/

ትርጉም፡- በአንድነት ሦስት፣ በሦስትነት አንድ
የሚሆን እግዚአብሔር ምስጉን ጽኑዕ ልዩ ነው።

69. ስብሐት ለሥላሴ

ስብሐት ለሥላሴ ለፈጣሪ ኩሉ ዓለም
በመላዕክቲሁ ስቡሕ ዘለዓለም /፪/
ምስጋና ለሥላሴ ለዓለም ሁሉ ፈጣሪ
በመላዕክቱ ነውና ሲመሰገን ኗሪ /፪/

70. አማን በአማን

አማን በአማን /፪/
ኧኸ መንግስተ ሥላሴ ዘለዓለም /፪/

71. ነአምን

ነአምን በአብ ወነአምን በወልድ /፪/
ወነአምን /፫/ ነአምን በመንፈስ ቅዱስ
እናምናለን በአብ እናምናለን በወልድ /፪/
እናምናለን /፬/ በመንፈስ ቅዱስ

72. ንሴብሆ ለሥላሴ

ንሴብሆ ለሥላሴ /፪/
ክበር ተመስገን አምላከ ሙሴ /፪/
የኛ አማላጅ እናታችን /፪/
ነይ ነይ ወደኛ እመቤታችን
ፈጥነሽ ተገኚ መሀከላችን
ና ወደኛ ሚካኤል /፪/
መላከ ምክሩ ለልዑል
ከእግራችን ይውደቅ ሳጥናኤል
ና ወደኛ ገብርኤል /፪/
ከእሳቱ አውጣን ከነበልባል
በክንፍህ ጥላ እንጠለል
ና ወደኛ ዑራኤል /፪/
እንደ ቅዱስ እዝራ ሱቱኤል
ጥበብን ስጠን ማስተዋል
ና ወደኛ በፈረስ /፪/
የልዳው ፀሐይ ጊዮርጊስ
ገድልህን ሰምተን እንፈወስ
ና ወደኛ ተክለሃይማኖት /፪/
እንዲጠብቀን ያንተ ጸሎት
ፀንተን እንድንቆም በሃማኖት

73. ሥላሴን አመስግኑ

ሥላሴን አመስግኑ /፪/
የምድር ፍጥረታት ዘምሩ እልል በሉ
በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ምስጋና ይገባል ከምንም በፊት
ዓለማትን ሁሉ ለፈጠረ ጌታ
ምስጋና ይገባል ከጧት እስከ ማታ
ኪሩቤል ሱራፌል የሚያመሰግኑት
መላዕክት በሰማይ የሚዘምሩለት
እኛም የአዳም ልጆች እንዘምራለን
በሰማይ በምድርም እንጠራሃለን
ብራብ በሥላሴ እጠግባለሁኝ
ብጠማ በአምላኬ እረካለሁኝ
ሥላሴ አምባዬ ክብሬም ናቸውና
ሁሌም ይመሩኛል በሕይወት ጎዳና

74. ኦ ሥሉስ ቅዱስ

ኦ ሥሉስ ቅዱስ ተመስገን /፪/
ዓለማትን የፈጠርህ እግዚአብሔር ተመስገን
አዳም ሳይፈጠር በዙፋንህ ነበርክ
በአንድነት ሦስትነት እየተመሰገንክ
መላዕክትን ፈጠርህ ስምህን ሊጠሩ
በምስጋና ጸንተው ካንተ ጋር ሊኖሩ /፪/
የሰው ልጅን ፈጠርህ ክብርህን እንዲወርስ
አንተን በማመስገን ሕይወቱ እንዲቀደስ
እኛም ልንጠራህ ባይገባን እንኳን
በምስጋና ቆመን ደጅህን አንኳኳን
የዓለም ሁሉ ንጉሥ የዓለሙ ፈጣሪ
ፍጥረትን በሙሉ አውሎ አሳዳሪ
ሥላሴን ላወድስ ሥሉስ ቅዱስ ልበል
በዓለም ከመክበር በቤታቸው ልጣል
ዮርዳኖስን ልሁን ሥላሴን ልያቸው
በአንድነት ሦስትነት ቅዱስ ልበላቸው
ትባረክ ትቀደስ ነፍሴ በሥላሴ
በአባቶቼ አምላክ በአብርሃም በሙሴ

75. ምስጋና አምልኮ

ምስጋና አምልኮ ስግደት ውዳሴ
ይገባል በሉ ሰዎች ለቅድስት ሥላሴ
ዘለዓለም ዓለም ቅዱስ ነህ
አምሳያ ወደር የሌለህ
መተማመኛም ሆነኸኛል
ሥላሴ ባንተ ደስ ይለኛል
ዘመናት በእጁ በመዳፉ
ሁሌም የእርሱ ነው ድሉ ሰልፉ
የእሳት መድረክች ያሉት ጌታ
የማያልፍ ነው የማይረታ
የታመነ ነው የተፈራ
የጽድቅን ፀሐይ የሚያበራ
ዓለሙ ጸንቷል በሥላሴ
ትዘምርለት ለርሱ ነፍሴ
አብርሃም አምኖ ተሰደደ

በእርጅናው ወራት ልጅ ወለደ
የተስፋውን ቃል ፈፀመለት
ሥላሴ በሉ በቀን በሌሊት

76. እኔስ እዘምራለሁ

እኔስ እዘምራለሁ ለሥላሴ /፪/
ፈጥሮኛልና በስጋ በነፍሴ
እኔስ እዘምራለሁ ለሥላሴ
ሥሉስ ቅዱስ ተብለህ የምትመሰገን
ሰውን ከመከራ ከሞት የምታድን
ነፍሴ ትገዛልህ ትንበርከክልህ
ቅዱስ ፈጣሪዬ አንተን ታመስግንህ
በመሐሪነትህ ጠብቀህ ያኖርከን
በማዳን ችሎታህ ለዚህ ያበቃኸን
ላንተ ለአምላኬ ምስጋና አቀርባለሁ
ስምህን ለዘለዓለም ሁሌም እጠራለሁ
አብርሃም ለአምላኩ በቀና ቢታዘዝ
ሥላሴ ገቡና ቤቱን ባረኩለት
ሣራንም ጎበኟት በእርጅናዋ ጊዜ
ይስሀቅን ሰጧት ዘለዓለም ሥላሴ

77. በስመ ሥላሴ

ኃይልየ ሥላሴ ወጸወንየ ሥላሴ /፪/

እኸ በስመ ሥላሴ /፪/ እቀጠቅጥ ከይሲ /፪/

ትርጉም፡- ሥላሴ ኃይሌና መጠጊያዬ ናቸው።
በሥላሴ ስም እባቡን /ዲያብሎስን/ እቀጠቅጣለሁ።

78. አማኑኤል ጌታዬ

አማኑኤል ጌታዬ ሆይ
በምህረትህ ተቀበለኝ
ኃጢአት እኔን ልጅህን ዳግም እንዳይገዛኝ /፪/
ኃይልህን አንተ አልብሰኝ

79. ሴስዩነ ከመ መና

ሴስዩነ ከመ መና ስሉስ ቅዱስ
ሰላመክሙ ዳዕና
እማሕበርነ /፪/ እየባህ ሙስና /፪/

80. ኃይሌ ብርታቴ

ኃይሌ ብርታቴ ክብሬ ሞገሴ /፪/
የዘለዓለሙ የአብርሃሙ ሥላሴ /፪/
ተመረጠች ነፍሴ አንተን ለማወደስ
ከላይ ከአርያም ከሥላሴ መቅደስ
በአንድነት ሦስትነት በዙፋኑ ሞልቶ
የሚሳነው የለም ለሥላሴ ክቶ
ከመንገድ ዳር ልቁም የወደቀን ላንሳ
የተራበ ላብላ የታመመ አልርሳ
እንደ አብርሃም አድርገኝ እንደ ደጉ አባት
ቤቴ እንዲሞላ ባንተ በረከት
ጠፈርን በውሃ በጥበብ የሰራ
እኔስ ይገርመኛል የሥላሴ ስራ
ኑና ተመልከቱ ተአምራት ሲሰራ
ሰዎች እልል በሉ ወላድ ሆነች ሣራ
አብ አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ወዶናል
ወልድም በተዋህዶ እኛኑ መስሎናል
ኃይሉ ተገለጠ የመንፈስ ቅዱስ
በቅዱሳን አድሮ ሲያድን ሲፈውስ

81. ምስጋና በዳዊት በገና

ምስጋና በዳዊት በገና
ውዳሴ ለቅድስት ሥላሴ
ይገባል ለአምላከ ሙሴ /፪/
በረከት ፀጋው ፈሰሰ
የትውልድ እንባ ታበሰ
ሲገባ ከድንኳናችን
ሳቅ ደስታ ሞላ በአፋችን
የእሳት ዙፋን ዘርግቶ
መቅደሱን በልብሱ ሞልቶ
ይመሰገናል ዘለዓለም
ሕይወት ነው ሥላሴ ለዓለም
ዓለምን በቃሉ ፈጥሮ
ጠላትን በእሳት አስሮ
ታላቅ ነው ነግሦ ይኖራል
በስልጣን ያስተዳድራል
የክብሩ ፀዳል ወረደ
በሰማይ አንጎደጎደ
ፍጥሩቱ ለክብሩ ይገዛል
ሥላሴ ሕዝቡን ያበዛል

82. ለጌታዬ

ለጌታዬ ለእግዚአብሔር
ስላደረገልኝ ምን እከፍለዋለሁ
ምስጋና ነው እንጂ /፪/ ሌላ ምን እላለሁ /፪/

83. ምሥጋና ለሥላሴ

ምስጋና ለሥላሴ /፪/
ለነአብርሃም አምላክ ለነ ሙሴ
ምስጋና ለሥላሴ
በረቂቅ ጥበቡ ሁሉን ለፈጠረ
ከፍጥረታት በላይ ሰውን ላከበረ

እንዘምር ለክብሩ ለቅድስት ሥላሴ
ምስጋና ይገባል ክብርና ውዳሴ
ለማይመረመር ለሥላሴ አኗኗር
ፀንቶ ለሚኖረው በጌትነት ዙፋን
በእውነት እንቀኝ ከልብ እናመስግን
በፍፁም ሃይማኖት እንደ አባቶቻችን
እንዲህ በወደደን በእግዚአብሔር አብ
በልጁ በኢየሱስ በወልደ ማርያም
እናምናለን በእውነት በመንፈስ ቅዱስ
ፀንተን በተዋሕዶ በሥጋም በነፍስ
ሦስት ሲሆኑ አንድ አንድ ሲሆኑ ሦስት
በሥላሴ ምስጢር ፀንተናል በእምነት
እፁብ እፁብ እንበል ለዚህ ድንቅ ነገር
ምስጋና እናቅርብ ለስሙም እንዘምር

84. ሃሌሉያ በሉ

ሃሌሉያ /፪/ በሉ
ለእግዚአብሔር ሰዎች እልል በሉ
እንዘምርለት እናቅርብ ውዳሴ
ታላቅ ነውና ዘለዓለም ሥላሴ
ታናናሾች ስንሆን እርሱ ከፍ አረገን
በእጆቹ አሰማምሮ ፈጥሮ አከበረን
ይክበር ለዘለዓለም በሰማይ በምድር
ፍጥረታት ዘምሩ ለኃያሉ እግዚአብሔር
ማዳኑ ድንቅ ነው ቸርነቱ ብዙ
ለክፉ አይሰጠንም ሰፊ ነው ትዕግስቱ
ባሮቹን ያየናል በፍቅር ዓይኖቹ
ሁሌ ይጎበኘናል በምህረት እጆቹ
በሕይወት ኑሮአችን ከእኛ ጋር ነውና
መግባት መውጣታችን ይጠብቃልና
በሄድንበት ሁሉ ከቶ አይለየንም
ቅርብ ነው ስንጠራው ይመስገን ዘለዓለም
ከሁሉ አስበልጦ እኛን ይወደናል
ከአፈር አንስቶ በእጆቹ ሰርቶናል
ውብ አድርጎ ፈጠረን አምላክ በአምሳሉ
ስለ ድንቅ ውለታው እጹብ እጹብ በሉ

85. ዘሰማየ ገብረ

ዘሰማይ ገብረ /፪/ ወምድረ ሣረረ
አልቦ ዘይመስሎ ለአምላክነ /፪/
ሰማይን የዘረጋ መሬትን ያፀና
ኃያል ጌታ ሕያው አምላክ
ያላንተ ማን አለና

የእናታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ዝማሬዎች

86. እናት አለኝ

እናት አለኝ የምታብስ እንባ

አያታለዉ ስወጣ ስገባ

<u>ኪዳነ-ምህረት</u> /፫/ አምባ መጠጊያ ናት /፪/

ሄዋን ሰታኝ ከበለሱ ፍሬ
እራቆቴን ብቆምም አፍሬ
ልብሴን ይዘሽ ወደኔ መተሻል
ደጓ እናቴ ቤቴን አድምቀሻል

ለዘላለም ንፅሕት በመሆኗ

ከእኔ ጋር ነዉ ህያዉ ቃልኪዳኗ

ደስተኛ ነኝ ሐዘኔን አልፌ

አፅናኝ ሆና የመስቀል ስር ትርፌ

ከጥፋቱ ዉኃ ማረፊያ
መርከቤ ነሽ ከሞት ማምለጫዬ
የአምላክ እናት ምልጃሽ ሆኖኝ ክብሬ
በህይወት አለዉ ጥልቁን ተሻግሬ

በእናትነት ህይወቴን ጎብኝታዉ

ልቤ አረፈ ተነቅሎ በሽታዉ

ሰንሰለቴ ከእጄ ተቆረጠ

መራራዬ በልጅሽ ጣፈጠ

87. ለማርያም

ለማርያም /፪/
እንዘምራለን ለዘለዓለም /፪/
የተዘጋች ደጅ ለዘለዓለም
ሕዝቅኤል ብሏል ››
ንጽሕት ናት በእውነት ››
በፍፁም ድንግል ››
አብነት አርገን ››
እኛም እሱን ››
<u>በፍፀም ፍቅር እንዘምራለን</u> /፪/
የዋሂት ርግብ ለዘለዓለም
ሰላም አብሳሪ ››
ለጨለማ ሕይወቴ ››
ብርሃንን አብሪ ››

እማፀንሻለሁ ››
ድንግል ለነፍሴ ››
አደራ ቅድስት አንቺ ነሽ ዋሴ /፪/
እጅግ የበዛ ነው ለዘለዓለም
ያለኝ ፍቅር ››
አይወሰንም ››
አይነገርም ››
በእርሷ ደስ ይለኛል ››
ሀሴት አደርጋለሁ ››
ስሟን እየጠራሁ እዘምራለሁ /፪/
ነይ ነይ ስላት ለዘለዓለም
ቀንና ሌሊት ››
አትለየኝም ››
ለኔስ ቅርቤ ናት ››
እፁብ እፁብ ብለው ››
አመሰገኗት ››
ክብሯን ሊገልፁት ቢያጥራቸው ቃላት /፪/

88. ለእናታችን ቅድስት

ለእናታችን ቅድስት የዓለም ርኅርኅት /፪/

እንስገድላት /፪/ በእውነት ለአምላክ እናት /፪/

89. እመቤታችን

እመቤታችን ለአንቺ እናቀርባለን ምስጋና

አንቺ የወለድሽው ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት ሆኗልና

ምእመናን ስለአወቁ ደግነትሽን በሙሉ

ወደ አንቺ ሁል ጊዜ ይማልዳሉ

ከፈጣሪሽ አማልጂን እያሉ /፪/

90. ማርያም እመቤቴ

ማርያም እመቤቴ የአምላክ እናት

ማደሪያ የሆንሽው ዙፋን ለመለኮት

ከሴቶቹ ሁሉ አንቺ ነሽ

የተባረክሽ የነፃሽ በእውነት

ከቶ እንደምን ቻልሽው መድኃኔዓለምን

ሰማይና ምድር የማይችሉትን

ድንግል እናታችን ለዚህ የተመረጥሽ

ለምኝልን ለኛ ምሕረትን ከልጅሽ /፪/

የነቢያት ሞገስ የሐዋርያት

የሰማዕታት አክሊል የጻድቃን እናት

የእኛ መመኪያችን የኃጥአን ተስፋ

ወልድን በመውለድሽ ኃዘናችን ጠፋ /፪/

ቅዱሳን በገነት ሲያመሰግኑሽ

መላእክት በሰማይ ሲያገለግሉሽ

እኛም የአዳም ልጆች ከመሬት ሆነን

ሰአሊለነ ቅድስ እንልሻለን /፪/

91. የሲና ሐመልማል

የሲና ሐመልማል የሙሴ ጽላት /፪/

የሲሎንዲስ ጥበብ ዕፀ መድኃኒት /፪/

አሁን በምን በምን እንመስልሻለን

እፁብ ድንቅ እያልን እናወድስሻለን

ያረጁ ፍጥረታት የታደሱብሽ /፪/

የሕይወት መሰላል ማርያም አንቺ ነሽ /፪/

የነቢያት ትንቢት የልባችን ተስፋ /፪/

በአንቺ መመኪያነት ማኅበራችን ይስፋ /፪/

92. እመቤታችን ለአንቺ

እመቤታችን ለአንቺ ሰላምታ ይገባሻል /፪/

ከሴቶች ሁሉ /፫/ ተመርጠሻል

ሐርና ወርቁን እያስማማች ስትፈትል

ተበሰረላት /፫/ የመመረጥ ክብር

እያረጋጓት የሰማይ መላእክት

ቤተመቅደስ ኖረች /፫/ አሥራ ሁለት ዓመት

መንፈስ ቅዱስም እንደቀረባት አውቆ /፪/

ሰገደላት /፫/ ዘካርያስ ታጥቆ

93. የፍቅር እናት

የፍቅር እናት የሰላም /፪/
ይናፍቀኛል ስምሽ ሳልጠራው ስቀር ማርያም
በሕይወቴ ውስጥ በኑሮዬ
ቅደሚ ከፊት ከኋላዬ
ተደላደለ ልቤ
አንቺ አለሽና ከአጠገቤ
ምኞቴም ይስመር ድብቅ ህልሜ
ልለፍ ወጀቡን ተቋቁሜ
የጌታዬ እናት ነሽ
ኃይልን ያደርጋል ፀሎትሽ
እንዴት እቀራለሁ ከመንገዴ
አደራ እናቴ አስቢኝ
ለሚያስጨንቀኝ ጠላት
ለሚሳድደኝ አትስጪኝ
ትናንትም ዛሬም አመስጋኝ ነኝ
የለም ለነገ የሚያስፈራኝ
ሜዳ ይሆናል ተራራ
ልጅሽ ስላለ ከእኔ ጋራ

94. ማርያም

ማርያም ማርያም ድንግል ማርያም
ርህርህተ ሕሊና /፬/ ማርያም

95. ምስራቀ ምስራቃት

ምሥራቀ ምስራቃት ሙፅአ ፀሐይ
እግዝእትነ ዘመና ሙዳይ
ዘመና ሙዳይ ማርያም ዘመና ሙዳይ /፪/

96. ሰአሊለነ ቅድስት

ሰአሊለነ ቅድስት እንልሻለን /፪/
እንደ ኤፍሬም እንደ አባታችን
ለምኚልን እመቤታችን /፪/
ተስፋቸው ነሽና ለፍጥረት ዓለም
እየተመኩብሽ እስከ ዘለዓለም
ኃጢአታቸው ተደምስሶላቸው
ባንቺ ፀሎት ዳነች ሕይወታቸው /፪/
ስምሽም ስልጡን ነው በእግዚአብሔር መንበር
ቃልኪዳን ገባልሽ ዓለሙን ሊምር
ባንቺ ፀሎት ይተማመናሉ
ጠዋት ማታ ቅድስት ሆይ ይላሉ /፪/
ዓለም ስትዋጋን በምኞት ስለት
ነፍሳችን ስንደክም ሲከብዳት ኃጢአት
ጨልሞብን ግራ ሲገባን
ብርሃናችን ነይ እናታችን /፪/
የልባችን ሐዘን እጅግ ከብዶብናል
ከበለሱ በታች በፍርሃት ወድቀናል
እንደ ኤልሳቤጥ እንደ ዘመድሽ
ደስ አሰኚን ይሰማን ድምፅሽ /፪/

97. ትሕትናሽ

ትሕትናሽ ግሩም ነው ደግነትሽም /፪/
እናቱ ሆነሻል ለመድኃኔዓለም /፪/
ንጽህት ስለሆንሽ እመቤት /፪/
እንከን የሌለብሽ ››
የፍጥረታት ጌታ ››
ባንቺ አደረብሽ ››
የድንግል መመረጥ ››
ዜናው አስገረመን ››
እሳቱን ታቀፊች ››
የማይቻለውን ››
ምርኩዜ ልበልሽ እመቤት /፪/
ጥላ ከለላዬ ››
ጋሻዬ ነሽ አንቺ ››
ለኔስ መመኪያዬ ››
በዓለም እንዳልጠፋ ››
ሕይወቴ መሮብኝ ››
እንደወይን አጣፍጪው ››
ማርያም ድረሺልኝ ››
የምስራቅ ደጃፍ ነሽ እመቤቴ /፪/
የሁላችን ደስታ ››
እሙ ለፀሐይ ጽድቅ ››
የሁሉ ጠበቃ ››
ድንግል የድል አክሊል ››
ድንግል የጽድቅ ሥራ ››
ድንግል መሰላል ነሽ ››
የተዋህዶ ተስፋ ››

98. የጌታዬ እናት

የጌታዬ እናት ማርያም
የበረከት ምንጭ የሰላም
መከራው በዝቶ ተጨንቀናል
ድንግል ነይልን ተማጽነናል
ቀባሪ ሲያጡ አዛውንቱ
ሜዳ ሲወድቁ ህፃናቱ
እሳት ሰደዱ እንዲቆም
አማልጂን ድንግል ማርያም
የራቀው ሰላም እንዲቀርበን
ፍቅር አንድነት እንዲከበን
ከልጅሽ ጋራ ነይልን
ኑሮአችን መልካም እንዲሆን

ውሃ የሌለው ምንጭ ሆነናል
መሬት ታቅፈን ዘር አጥተናል
የኢትዮጵያ እናት እመቤት
ሁሉን ባርኪልን በረድኤት
ድፍረት ጭካኔ አመጽ ሞልቷል
በጎ ደግ ሰው ከዓለም ጠፍቷል
ማን መልካም ነገር ያሳየናል
ወደ ማደሪያሽ አቅንተናል

99. ኦ ማርያም

ኦ ማርያም በእንተዝ ናፈቅረኪ ወነአብየኪ
እስመ ወለድኪ ለነ መብልዓ ጽድቀ ዘበአማን
ወስቴ ሕይወት ዘበአማን

100. መንክር ግርማ

መንክር ግርማ ኃይለ ልዑል ፀለላ
አማን /፪/ መላዕክት ይኬልልዋ /፪/
በሚያስደንቅ ግርማ የልዑል ኃይል ጋረዳት
በእውነት /፪/ መላዕክት አመሰገኗት /፪/

101. ይቄድስዋ

ይቄድስዋ <u>መላዕክት</u> /፪/ ለማርያም
በውስተ ውሳጤ መንጦላዕት ወይብልዋ
በሐኪ ማርያም ሐዳሴዩ ጣዕዋ
በቅድስናሽ በክብርሽ መላዕክት ሲሰግዱልሽ
እኛም ያንቺ ልጆች በሥጋ በምድር ሆነን
ሰአሊ ለነ ቅድስት እመቤቴ እንልሻለን
ፍህም እሳት በማሕፀንሽ ለዘጠኝ ወር የተሸከምሽ
የኢያቄም ፍሬ ንፅህት ሆይ ደስ ይበልሽ
እያልን እንደ ገብርኤል በምስጋና እንዘምርልሽ
ከቅድስት ሃና ተገኝተሽ ለድኅነት ምክንያት
የሆንሽ
ከፍጡራን ሁሉ ለክብር የተመረጥሽ
ድንግል ሆይ ልጆችሽን ጠብቂን ባርኪሽ
ቀድሰሽ

102. እመቤቴ የአምላክ እናት

እመቤቴ የአምላክ እናት
ላመስግንሽ ቀን ከሌሊት
ለልጅሽም ክብር ውዳሴ
ታቀርባለች ዘውትር ነፍሴ /፪/
ልቤ ተነሳሳ ተቀኘ ለክብርሽ
በፍፁም ትህትና ሊያመሰግንሽ
ጽዮን መጠጊያ ነሽ የአብርሃም ድንኳን
የታጠረች ተክል እመብርሃን
የለመለመች መስክ አምላክ የመረጣት
የፅላቱ ኪዳን ታቦቱ ድንግል ናት
የሰማይ የምድር ንግስት ነሽና
ክብር ይገባሻል ዘውትር ጠዋት ማታ
አደራሽን ማርያም የሁሉም እናት
በምልጃሽ አስቢኝ ኋላ ስራቆት
ያንን የእሳት ባሕር አሻግሪኝ ድንግል ሆይ
እንዳልወድቅ እንዳልሞት ከቶ እንዳላይ
ስቃይ

103. አንደ ወይን

እንደወይን /፪/ እንደ ዘለላ
ስምሽ የጣፈጠ ተአምርሽ ያማረ /፪/ ድንግል
ማርያም

104. እንድናለን

እንድናለን እኛስ እንድናለን /፪/
እንድናለን ድንግል አንቺን ይዘን
በፍፁም ቸርነት እንድናለን
ስለወደደን ››
እንዳንጠፋበት ››
ድንግልን ሰጠን ››
የልባችን ደስታ እንድናለን
እኛስ አግኝተናል ››
በአማላጅነቷ ››
ፈጣሪ ምሮናል ››
ምርኩዝ አንቺን ይዘን እንድናለን
ስንቅ አንቺን ሰንቀን ››
በድንግል መሪነት ››
ጽድቅን እንወርሳለን ››
የምታማልደን እንድናለን
ድንግልን ሰጥቶናል ››
የእሳቱን ባሕር ››
በእርሷ ተሻግረናል ››

105. አንቺው ነሽ ተስፋው

አንቺው ነሽ ተስፋው ለአዳም ኪዳነ ምህረት
በተሰደደ ጊዜ ከገነት በተሰደደ ጊዜ

106. ወዳጄ ሆይ

ወዳጄ ሆይ እንሆ ውብ ነሽ
የታተመች ፈላሽ እንከን የሌለሽ
የተዘጋች መቅደስ ንጽህት አዳራሽ
ሕዝቅኤል ያየሽ የምሥራቋ በር
ማንም ያልገባባት ከአምላክ በስተቀር

የልዑል ማደሪያ አማናዊት መቅደስ
ስለንጽህናሽ ምስጋናን እናድርስ
ሁለቱን የሆንሽ እናትና ድንግል
ማሕደረ መለኮት ወላዲተ ቃል
ያለ ዘርአ ብዕሲ በሕቱም ድንግልና
አምላክን የወለድሽ ሐመልማለ ሲና
ምሥራቀ ምሥራቃት ድንግል ሆይ አንቺ ነሽ
ጨረቃን የምትመስል ፀሐይን የወለድሽ
የማለዳ ብርሃን ለዓይን የምታሳሺ
ጽዮን እናቴ ሆይ ከጎኔ አትሸሺ

107. ማርያም ንጽሐት

ማርያም ንጽሕት ድንግል ማዕምንት
ወላዲተ አምላክ ሰዓሊተ ምህረት ለውሉደ ሰብዕ
ለአሊለነ ሀበ ክርስቶስ ወልድኪ
ይስረይ ኃጢአተነ ለአሊለነ ቅድስት
ማርያም ንጽህት ድንግል ታማኝ
አምላክን የወለድሽው ምህረት አማላጅ
አማልጂን ከልጅሽ ከክርስቶስ
ይቅር እንዲለን ቅድስት ሆይ ለምኚልን

108. ማርያም ተዐቢ

ማርያም ተዐቢ እምኩሉ ፍጥረት
ኢያውአያ እሳተ መለኮት /፪/
ማርያም ትበልጣለች ከሁሉም ፍጥረት
አልጎዳትም የመለኮት እሳት /፪/

109. ስምሽን ጠርቼ

ስምሽን ጠርቼ መቼ አፍራለሁ
ማርያም ብዬ መች እወድቃለሁ
የምጽናናበት ስምሽ ነውና
ድንግል ሆይ ላቅርብ ላንቺ ምስጋና
ጨለማ ውጦኝ በጠላት ሀገር
ለዘመናትም ስረገጥ ስኖር
ዲያብሎስ ማርኮ ሲያሰቃየኝ
የዓለሙን መድኃን ወለድሽልኝ
ከአባቶቼ ርስት ከሀገር ወጥቼ
ባሕዛብ ሀገር ስኖር ተሸጩ
ደርሰሽ አጽናንተሽ አከበርሽኝ
ብቸኝነቴን አስረሳሽኝ
ድንኳኑ ሞልቶ ሰው ታድሞ
አስተናባሪው በጭንቀት ቆሞ
ምን አቀርባለሁ ብዬ ስቸገር
ምልጃሽ ደርሶልኝ ዳንኩኝ ከማፈር
ያሰብኩት ሃሳብ ደመና ሆኖ
ቢበተንብኝ እንደ ጉም ተኖ
ይሆናል ያልኩት ሳይሆን ቢቀርም
በእመአምላክ እኔስ ተስፋ አልቆርጥም
እናት አባቴ ባያስታውሱኝ
ይህች ዓለም ንቃ ገፍታ ብትተወኝ
አንቺ ካለሽኝ ምን እሆናለሁ
አውሎ ነፋሱን ባሕሩን አልፋለሁ
ጠላቴ ደርሶ ቢያንገላታኝም
መከራ አብዝቶ ቢያስጨንቀኝም
አላቋርጥም ያንቺን ምስጋና
ውለታሽ ድንግል አለብኝና
ክፉዎች ደርሰው ቢዝቱብኝም
አንቺን መውደዴን አያስተውኝም
በአሕዛብ መሀል ስምሽን ስጠራ
መከታ ሁኚኝ እናቴ አደራ
ጠላቴ ደርሶ ቢያንገላታኝም
መከራ አብዝቶ ቢያስጨንቀኝም
አላቋርጥም ያንቺን ምስጋና
ውለታሽ ድንግል አለብኝና

110. ማርያም

ማርያም /፫/ ደስ ይበልሽ በገብርኤል ሰላምታ
<u>ባንቺ ስላደረ የዓለም ሁሉ ጌታ</u> /፪/
የአምላክ ቸርነቱ ፈቃዱ ሲሆን
ጨለማ ተገፎ ሲወጣ ብርሃን
መድኃኒት ሲመጣ ሰይጣን እንዳፈረ
የዜናው አብሳሪ ገብርኤል ነበረ
በቤተ መቅደስ ተቀምጣ ድንግል
ሐርና ወርቁንም አስማምታ ስትፈትል
ገብርኤል /፪/ ዜናዊ ሐዲስ
የአምላክን መወለድ ሥጋን በመልበስ
ገብርኤል ሲያበስራት ድንግል ስትሰማ
በእርሷ ላይ አደረ የመለኮት ግርማ
እውነተኛ መልዓክ መሆኑን ስላየች
ይሁንልኝ ብላ ቃሉን ተቀበለች

111. የጠሩሽ

የጠሩሽ አንቺን ተማጽነው የዳኑብሽ
የበላኤሰብ እመቤት የአምላክ እናት
ድንግል አዛኝቱ ማርያም ቅድስት
በቃልኪዳንሽ ብዙዎች ድነዋል
በምልጃሽም ጽድቅን አግኝተዋል
<u>የአምላክ ቸርነቱን አይተዋል</u> /፪/
የእሳቱን ባሕርን ባንቺ ተሻግረዋል
የሰይጣንን ፆር ባንቺ ድል ነስተዋል
<u>ለሰማያዊው ክብር በቅተዋል</u> /፪/
ነፍሳቸውም ጽድቅን አግኝታለች
ሕይወታቸውም ባንቺ ትድናለች
<u>ድንግል ሆይ አትጣይን ትላለች</u> /፪/
እኛ ባንቺ እንታመናለን

የአምላክ እናት አሳስቢ እንላለን
በአማላጅትሽ እንድናለን /፪/
እኔም በአንቺ እታመናለዉ
የአምላክ እናት አትርሺኝ እላለዉ
በአማላጅነትሽ እንድናለዉ /፪/
ምዕመናንም ባንቺ ያምናሉ
የአምላክ እናት አሳስቢ ይላሉ
በአማላጅነትሽ ይድናሉ /፪/

112. ኢያቄም

ኢያቄም ወሐና እናት አባትሽ
ቤተ እግዚአብሔር ወስደው ስዕለት የሰጡሽ
መና ከሰማያት የወረደልሽ
ፍጹም ድንግል የሆንሽ ማርያም አንቺ ነሽ
ኦ ወላዲተ አምላክ ማርያም አንቺ ነሽ /፪/

113. በምን በምን

በምን በምን እንመስላት ድንግል ማርያምን /፪/
ምሳሌ የላትም /፪/ ክብሯን የሚመጥን /፪/
የሙሴ ጽላት ነሽ የምህረት ቃል ኪዳን
የያዕቆብ መሰላል የአብርሃም ድንኳን
የብርሃን መውጫ የኖህ ድንቅ መርከብ
የመላዕክት እህት የሩሩሀን ርግብ /፪/
የሰሎሞን አክሊል የአሮን በትር
የዕዝራ መሰንቆ የጌድዮን ፀምር
ድንግል እመቤት ናት የጻድቃኖች በር
ሆና የተገኘች የአምላክ ማሕደር /፪/
የቅዱሳን እናት የዓለም ንግስት
ችላ ተሸከመች መለኮት እሳት
ብርሃን ትሁነን ጨለማን ገላልጣ
አማልዳ ታስምረን ከዚህ ዓለም ጣጣ /፪/
ከማር ይጣፍጣል የድንግል መዓዛ
አምላክን አቅፋለች በሁለት እጇ ይዛ
ዓለም ሁሉ የዳነው በልጅሽ ነውና
እናታችን ጽዮን ይድረስሽ ምስጋና /፪/

114. ጽላት ዘሙሴ

ጽላት ዘሙሴ እፀ ጳጦስ ዘሲና /፪/
ፀናፅል /፩/ ዘ አሮን ካሕን
አልፈያለሁና እመቤቴ ያንሁሉ መከራ
ከኔ ጋር ስለሆንሽ እመቤቴ ስምሽን ስጠራ /፪/
በዚያ በጭንቅ ቀን ድንግል
እጅግ በሚያስፈራ ››
ማን ያድነኝ ነበር ››
ስምሽን ባልጠራ ››
በሞትና ሕይወት ››
መካከል ብሆንም ››
ተአምርሽ አነሳኝ ››
ማርያም አልተውሽኝም ድንግል አልተውሽኝም
እጅግ የከበደ ነበር እመቤቴ ያገኘኝ ፈተና
ታሪክ ሆኖ ቀረ እመቤቴ ባንቺ ዳንኩኝና /፪/
ዙሪያው የሚያስፈራ ድንግል
ፅኑ ነው ገደሉ ››
በዚያ የወደቁ ››
እንዴት ይተርፋሉ ››
ስምሽ ድጋፍ ሆኖ ››
ከስር ተነጠፈ ››
በሚያስደንቅ ምስጢር ››
ሕይወቴ ተረፈ /፪/

115. ምስለ ወልድኪ

ምስለ ወልድኪ አማኑኤል እም አምላክ ንኢ ማርያም
ንኢ /፬/ ማርያም እመ አምላክ ማርያም ንኢ
አምላክን የወለድሽ በቤተልሔም /፪/
ሰላም ለማርያም

116. ሙሴ ዘርእየ

ሙሴ ዘርእየ /፪/ በደብረ ሲና
ሐመልማላዊት እፅ
ሙሴ ያያት /፪/ በደብረ ሲና
የለመለመች እፅ የለመለመች /፪/

117. ድንግል ማርያም

ድንግል ማርያም የወርቅ መሰላል ነሽ
መሰላል ነሽ የወርቅ መሰላል ነሽ
ሰውና አምላክን ያገናኘሽ
አባታችን ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ /፪/
አሸልቦት እንቅልፍ ተኝቶ ከጤዛ
ከምድር እስከ ሰማይ የምትደርስ መሰላል
ምሳሌሽን አየ ማርያም ድንግል
መላዕክት ሲወጡ ሲወርዱ ከሰማይ /፪/
እንዳየ ያዕቆብ ተኝቶ መንገድ ላይ
ተስፋ አድርጎ ሲኖር የሰላሙን ዘመን
ይኸው ተፈፀመ ባንቺ በእናታችን
ባንቺና በልጅሽ ሆነልን ሰላም
ባንቺ ተፈፀመ የያዕቆብ ሕልም
ሰውና መላዕክት ተለያይተው ሲኖሩ
በልጅሽ መወለድ በአንድ ላይ ዘመሩ

118. እናታችን ጽዮን

እታችን ጽዮን ይድረስሽ ምስጋና
መጠጊያ ማረፊያ ጥላችን ነሽና
ከገነት ብንወጣ ማረፊያ ሆንሽን
ምህረት ደመና ውሃ ሰጠሽን
የሕይወት እንጆራ አመጣሽልን
በአስራትም በአደራ ላንቺ ተሰጠን

የኤልሳቤጥ አጽናኝ የጭንቅ ቀን ደራሽ
የኃጢያታችን ብዛት ዳገት ሳይሆንብሽ
ምስራችን ደስታን ይዘሽልን መጣሽ
ማርያም ስንልሽ ድረሺልን ፈጥነሽ
ውለታሽ ብዙ ነው ከልብ የማይጠፋ
ስምሽ መጽናኛ ነው አዝኖ ለተገፋ
በእንተ ማርያም ብሎ ለለመነ
የሰማይ የምድሩ ማንም አልጨከነ
በትራችን አንቺ ነሽ የምትደግፊን
ባሕረ እሳትን የምታሳልፊን
ጽርሃ ሥላሴ ነሽ ማሕደረ መለኮት
ሁል ጊዜ አንጠግብሽም እንላለን ብጽዕት

119. እንደ ኤልሳቤጥ

እንደ ኤልሳቤጥ ላመስግንሽ
ፊትሽ ወድቄ ልሳለምሽ
የጌታዬ እናት የኛ እመቤት
አዛኝ ነሽ ከልብ ፍፁም የዋሕት
ርሕራሔሽ ያስደንቀኛል
ስለኃጢአቴ ምልጃሽ ቀድሟል
የሰላምታሽ ድምጽ ደስ ያሰኘኛል
ከትካዜዬ ያሳርፈኛል
ድምጽሽ ሲሰማኝ ልቤ ይረካል
ሐዘኔ ቀርቶ ፊቴ ይፈካል
በእናትነት አንቺን የሰጠን
ቸሩ አምላካችን ይክበር ይመስገን
የሁሉ እመቤት የሁሉ አጽናኝ
የለበው መድኃኒት ከአምላክ አገናኝ
ዛሬም በልቤ ደስታን ጨምረሽ
እንደ ኤልሳቤጥ ሰላም ልበልሽ
ከሴቶች መካከል መርጦ ቀድሶሻል
ትውልዱ ሁሉ ብፅዕት ይሉሻል
በልዩ ውዳሴ ያመሰግኑሻል
ድንግል ንግስታችን በቀኙ ቆመሻል

120. ቃልን ለመውለድ

ቃልን ለመውለድ ከአብ ዘንድ ሞገስ ያገኘሽ /፪/
የሃና ልጅ ነሽ የኢያቄም እፁብ ድንቅ ነሽ /፪/
እሾህ ኩርንችት ሆነ ኑሮዬ
የልጅሽ ፍጥረት ተጎሳቁዬ
ሞገድ ማዕበል እንዳይጎዳኝ
ሰላላ ክንዴን ደግፊልኝ
ቆሜ ልሳለም ከስዕልሽ ፊት
ፍቅር ትሕትናን እንድማርበት
ላደግድግና ልሳለምሽ
የጌታዬ እናት ልሁን ባሪያሽ
የዳዊት ልጅ ሆይ ቁሚ ከጎኔ
ወደ መስቀሉ ይመልከት ዓይኔ
የሌዊ ልጅ ሆይ አይዞህ/ሽ በይኝ
የሥጋ ድካም እንዳይጎዳኝ

121. ንጽሕተ ንጹሐን

ንጽሕተ ንፁሐን ከዊና ከመታቦተ ዘዶር ዘሲና
ውስተ ቤተ መቅደስ ነበረት በድንግና ነበረት
ሲሳያ ሕብስተ መና ወስቴሀኒ ስቴ ጽሙና

122. የድኅነታችን ፊደል

የድኅነታችን ፊደል በክብር የተፃፈባት
ማርያም የቃል ማደሪያ እንቁ መዝገባችን ናት
ሰማያዊ ጠል ረቦባታል
ከጥማታችን አርክቶናል
በስደት ሆነን በክፉ ቀን
ማርያም ብለናል እንዳይጨንቀን /፪/
የብስራት ቀንበጥ ይዛ በአፏ
የሰላሟ ርግብ ታየን ክንፏ
በልዩ ሕብር በእርሷ ጸጋ
ቀስተደመናው ተዘረጋ /፪/
የርሕራሔ መገኛ ናት
ከመስቀሉ ስር ያገኘናት
ፊቷ ጠውልጓል በእንባዋ
ማዘል ይችላል ትከሻዋ /፪/
የብዙ ብዙ በሚሆኑ
ዙፋኑን በክብር የከደኑ
በመላዕክቱ ታጅባለች
የመዳናችን ምልክት ነች /፪/

123. ክነፈ ርግብ

ክነፈ ርግብ በብሩር ዘግቡር
ወገበዋቲሐኒ ሀመልማለ ወርቅ
አንቲ ምስራቅ ወወልድኪ ፀሐየ ፅድቅ አማን በአማን
አማን በአማን /፪/ ኢየሐልቅ ኪዳንኪ ወላዲተአምላክ
እንደ ርግብ ክንፍ በብርም እንደተሰራ
ጎኖችሽም የወርቅ ሐመልማል
አንቺ ምሥራቅ ነሽ ልጅሽም
የጽድቅ ፀሐይ እውነት በእውነት
እውነት በእውነት /፪/
አያልቅም ቃል ኪዳንሽ የአምላክ እናት

124. ሰላም ለእመቤቴ

ሰላም ለእመቤቴ ሰላም ለማርያም
አምላክን የወለድሽ በቤተልሔም /፪/
ሰላም ለማርያም

125. ከሊባኖስ

ከሊባኖስ /፪/ ከልጅሽ ጋራ ነይ እመ አዶናይ
ከሊባኖስ ወደ እኛ ነይ
ጥበቃሽ ዘወትር ከሊባኖስ
እንዳይለየኝ ››
በሄድኩበት ሁሉ ››
ማረፊያ ሁኚኝ ››
እኔን ባሪያሽን ከሊባኖስ
ድንግል አትርሺኝ ››
በጽድቅ ሰሌዳ ››
ስሜን ጻፊልኝ ››
ነፍስና ሥጋዬን ከሊባኖስ
አደራ እልሻለሁ ››
በልጅሽ ጽኑ ፍቅር ››
ተማጽኜሻለሁ ››
ከአንበሶች መኖሪያ ከሊባኖስ
ከነብሮች ተራራ ››
መጥተሽ አስደስቺኝ ››
እህቴ ሙሽራ ››
የልብስሽ መዓዛ ከሊባኖስ
የሊባኖስ ሽታ ››
ሮማን ናርዶስ ነሽ ››
እናቱ ለጌታ ››
እመቤቴ ስልሽ ከሊባኖስ
ስምሽን ስጠራ ››
ፈጥነሽ ድረሺልኝ ››
ከቅዱሳን ጋራ ››

126. የሕይወት መሠረት

ሰላም ሰላም ለኪ ማርያም ሰላምለኪ
የሕይወት መሠረት ሰላም ለኪ
የፍጥረት አለኝታ ››
ድንግል አደራሽን ››
ሁኚልን መከታ ››
በላኤሰብዕ ዳነ ሰላም ለኪ
ብዙ ነፍሳት በልቶ ››
ያንቺን ስም ለጠራ ››
ጥርኝ ውሃ ሰጥቶ ››
እኛም እንከተል ሰላም ለኪ
በጎ ምግባር ይዘን ››
በሰላም በጤና ››
እንኖራለን ››
ተማጽነንብሻል ሰላምለኪ
በአማላጅነትሽ ››
ድንግል ሆይ አደራ ››
አማልጂን ››

127. ደስ ይበልሽ

ደስ ይበልሽ /፪/ ማርያም ንጽህት ድንግል
ደስ ይበልሽ ከሴቶቹ ሁሉ የተባረክሽ ነሽ
ሰላም እልሻለሁ ማርያም ድንግል
እንደ ብስራታዊው እንደገብርኤል
ላንቺ የተሰጠሽ ሁለት ድንግልና
አንደኛው በሥጋ ሴላው በህሊና
ከዓለም ሁሉ ሴቶች ንጽሕት በመሆንሽ
ሰማያዊ ምስጢር የተገለጸልሽ
የልዑል ማደሪያ ለመሆን የበቃሽ
የጌታችን እናት በጣም ደስ ይበልሽ
የተነበየልሽ ሕዝቅኤል ነቢዩ
የተዘጋችው በር ብሎ በራዕዩ
ሳይከፍት ገብቶ ወጣ የእስራኤል ጌታ
ደግሞም ለዘለዓለም ኖራለች ተዘግታ
ማርያም ስትጎበኝት ወደቤቷ ገብታ
ኤልሳቤጥ ዘመረች በመንፈስ ተሞልታ
በማኅፀኗ ያለው ዘለለ በደስታ
እኛንም ትጎብኘን ከጧት እስከ ማታ /፪/

128. ለማርያም ድንግል

ለማርያም ድንግል መንበረ ተድላ /፪/
ወሪዶ ገብርኤል ምድረ ገሊላ
ትወልዲ ወልድ ለድንግል ይቤላ
አዲስ ዜና ይዞ ለማርያም ድንግል
ሰማያት ሰንጥቆ መጣ ገብርኤል
ድንግል ካንቺ ጋራ ጌታ ስለሆነ
ምክንያት አንቺ ሆነሽ ዓለም ሁሉ ዳነ
መዝገብ ጽድቅ ነሽ ምስጋና ይገባሻል
ሰማያዊ ጌታን ድንግል ሆይ ወልደሻል
መመኪያና ሞገስ ለኛ ልትሆኚን
በስለት ወለዱሽ ሃናና ኢያቄም
በማይደክም ልሳን በመላዕክት ዜማ
ትመሰገናለች የኛ እናት በራማ
ጌታችን ተጸንሶ በማኅፀኗ ሳለ
የመላዕክት ዝማሬ ትሰማ ነበረ
የነቢያት ትንቢት ፍጻሜ አገኘ
ገብርኤል ተልኮ መድኃኒት ተገኘ
ንጹሕ ዘር ከሆነች ከእመቤታችን
በፈቃዱ ወርዶ ተወለደልን

129. ነይ ነይ

ነይ ነይ ማርያም ወላዲተ አምላክ
የጻድቃን እመቤት መላዕክት እህት
ሁላችሁ እመኗት ከልብ
አማላጅ ናትና በእውነት
እናመስግናት እናወድሳት
አማላጅ ኪዳነ ምህረት

130. ምንተኑ

ምነተኑ አአሰየኪ እሴተ
በእንተ ኩሉ ዘገበርኪ ሊተ
የቅዱሳን ተስፋ የትንቢት ምዕራፍ
የስደተኞች ስንቅ የምህረት ደጃፍ
የፍጥረት መመኪያ ምክንያተ ድኂን
ለኔም ለመንገዴ ስለሆንሺኝ ብርሃን
የዓለም ኑሮ ማርኮኝ ልቤ ሲዋልል
በፈተና ብዛት በሕይወት ስዝል
ለሥጋዬ ፈቃድ ከቶ ስላለተውሽኝ
ለነፍሴ ሰላምን ስላስገኘሽልኝ
በኃጢአት መጎስቆሌን ድካሜን ሳታይ
በሐዘን በችግሬ ከእኔ ሳትለይ
ከመከራ አዘቅት ባንቺ ስለወጣሁ
ለብዙ ውለታሽ ምን እከፍልሻለሁ

131. ኪዳነ ምሕረት

ኪዳነ ምሕረት እመቤት
የዓለም ሁሉ መድኃኒት
ቅድስተ ቅዱሳን ንጽሕት
አንቺ ነሽ የአምላካችን እናት
ጌታ አንቺን ፈጠረሽ ልዩ አድርጎ
በሚያስደንቅ ምስጢሩ ተዋሕዶ
ለልዑል ማደሪያነት የተመረጥሽ
ያለሕማም ወለድሽው ድንግል ሆነሽ
እናትነት ድንግልና አስተባብረሽ ይዘሻልና /፪/
እናትም ድንግልም እመብርሃን
ንጽሕተ ንጹሀን እኛን አማልጂን

132. በውዳሴሽ ልትጋ

በውዳሴሽ ልትጋ ስምሽ ግርማ አለው /፪/
እመቤት ኧኸ እመቤቴ ስልሽ እውላለሁ
ከልቤ አቀርባለሁ ምስጋና ለስምሽ
መታመኛዬ ነው ጽኑ ቃልኪዳንሽ
በሰላምታ ድምጽሽ ያልጸና ማን አለ
ጽንሱ በማኅፀን በደስታ ዘለለ
ማርና ወተት ነው የስምሽ ስያሜ
እመቤቴ ስልሽ ይቀላል ሸክሜ
ቅኔ ማኅሌቱ ሰዓታት መዝሙሩ
ያመሰግኑሻል ምድርና ጠፈሩ
እናቱ ነሽና አንቺ ለአዶናይ
ማለድኩኝ ከፊትሽ ይቅርታውን እንዳይ
ሰዓሊለነ ብዬ ይኸው ተምሬአለሁ
በአንቺ ተደግፌ ነገም እኖራለሁ
ነይ ነይ እልሻለሁ እንደ ካሕናቱ
በሰዓታት ጸሎት ቆሜ በሌሊቱ
ዝም አልልም እኔ አወድስሻለሁ
የዓለምን መከራ እረሳብሻለሁ

133. አንቲ ዘበአማን

አንቲ ዘበአማን /፪/ ረከብኪ ፀጋ
ክብረ ድንግል የአቢ ክብራ ለማርያም
በግሸን ተራራ ዘበአማን
በክብር ተቀምጠሽል ››
ታላቁን በረከት ››
በእጅሽ ጨብጠሻል ››
እንሰግድልሻለን ››
የፀጋ ስግደት ››
እመቤቴ ማርያም ››
የጌታዬ እናት ››
ልሂድ ወደ አምባሰል ዘበአማን
ወደጊሸን አንባ ››
አድርጊኝ እንደ ሀፃን ››
ወደቤትሽ ልግባ ››
ልረፍ ከመስቀሉ ››
ከእግርሽ ስር መጥቼ ››
የዓለምን ጫጫታ ››
ሁሉንም ረስቼ ››
እሩቅ ነው መንገዴ ዘበአማን
ብርቱ ነው ዳገቱ ››
ንገሪው ለልጅሽ ››
የእርሱ ነው ጉልበቱ ››
ሳልረግፍ እንደ አበባ ››
ሳልመጣ በአልጋዬ ››
ሕይወቴን አደራ ››
ነፍስና ስጋዬን ››
ያመሰግኑሻል ዘበአማን
ዓለም ዘለዓለም ››
ስምሽ ይጣፍጣል ››
ድንግል ማርያም ››
በተሰጠሽ ፀጋ ››
በአንቺ አማላጅነት ››
ለልጆችሽ ይብዛ ››
ዕድሜና በረከት ››

134. ክንፉ ፀለላ

ክንፉ ፀለላ /፫/
ተፈስሒ ለድንግል ይቤላ /፪/

135. ማኅደረ መለኮት

ማኅደረ መለኮት
ማርያም እመ ብዙሐን /፪/

136. እመቤታችን

እመቤታችን ማርያም ሀገራችንን ጠብቂልን በምልጃሽ
ከመናፍቃን (ከክንድያን) ከጠላት ሰይጣን ሰውረሽ

እንድትጠብቂን በምልጃሽ

137. ማርያም ማርያም ብዬ

ማርያም ማርያም ብዬ ስምሽን ልጥራዉ

አይደክመኝም እኔ ብደጋግመዉ

አሁንም ጠራሁሽ አላስችልህ ቢለኝ

አዉቀዋለዉ ስምሽን እናቴ ስትወልደኝ /፪/

ገና በማህፀን በእናቴ የምጥ ቀን
ደጋግሜ ሰማዉ ሲጠሩ ስምሽን
በሰከንዳት እድሜ የማዉቃት አንዲት ቃል
ልቤ ላይ ያለዉ ስም ማርያም ማርያም
ይላል /፪/

ሔዋን ምጧ ቀሎ ልጆቿን ታቀፈች

በአማላጅነትሽ እናቴም ታመነች

በተወለድኩበት በመጀመሪያዉ ቀን

ስምሽን እየሰማዉ ወጣዉ ከማህፀን /፪/

ከቃልኪዳን ስም ጋር አደኩኝ አብሬ
ምልጃሽ ሳይለየኝ አለሁ እስከዛሬ
የሕይወቴን ፊደል ካንቺ ላይ ቆጠርኩኝ
በልጅሽ አምኜ ዳግም ተወለድኩኝ /፪/

የክፉ ቀን ስንቁ ያዘልኩሽ በልቤ
የሕይወቴ ምግብ የእንጃራ መሶቤ

እንደ ትላንትናዉ ዛም እጠራሻለዉ

የመስቀል ስር ክብሬን እንዴት እረሳለዉ

የመስቀል ስር ክብሬን እንዴት እተዋለዉ

138. የያሬድ ዉብ ዜማ

የያሬድ ዉብ ዜማ ድንግል እመቤቴ ስጦታዬ ነሽ

በምን አንደበቴ እንዴትስ ባለዉ ቃል ማርያም
ልበልሽ /፪/

ምድርና ሰማዩ ታምርሽን ይንገሩ
ፍጥታት በሙሉ ስላንቺ ይመስክሩ
ተነግሮ የማያልቅ ድንቅ ነዉ ስራሽ
ድንግል ሆይ እናቴ አምሳያም የለሽ
ማርያም ድንግል እረዳቴ
የምትደሽልኝ ነኝ ስልሽ በጭንቀቴ
ታምርሽንም በዓይኔ አይቻለዉ
ፂዮን ሆይ ስልሽ እጠግባለዉ

የእግዚአብሔር ጥበቡ በአንቺ ተገለጠ

የአዳም ዘር በሙሉ ከሞት አመለጠ

የመዳን ምክንያት ማርያም አንቺ ነሽ

ለፍጥረቱ ሁሉ መሰላል የሆንሽ

ነገን ባላዉቅ እኔን ቢስፈራኝ

አንቺ ካለሽኝ በፍፁም አልወድቅም

ከጎንሽም እንድቆም ለምሥጋና

ማርያም ልበልሽ በትጎትና

ትዉልዱ በሙሉ ለምሥጋና ይቁም
በአንቺ ስለሆነ የቀረለት መርገም
አዳም ከእነ ልጁ በሰማይ በምድር
ማርያም /፪/ ይበል ተዓምርሽ ይናገር
ጠለማውም ከፊቴ ተገፈፈ
ማሪያም በምልጃሽ ልቤ አረፈ
ከጎኔ ነሽ ስልሽ እፅናናለዉ
እሳት ገደሉን ሁሉንም አልፈዋለዉ

139. እመቤቴ ጥላ

እመቤቴ ጥላ ከለላዬ ረዳቴ የገነት ሙሽራ /፪/

የገነት ሙሽራ /፫/ ማርያም የልዑል ማደሪያ /፪/

140. በአምሳለ ፆፍ

በአምሳለ ፆፍ /፪/ ፀአዳ ርግብ ትመስል ማርያም
ድንግል /፪/

ይእቲኬ ደመና ቀሊል ማርያም ድንግል እሙ
ለእግዚአብሔር /፪/

ትርጉም፡- ድንግል ማርያም እንደ ነጭ ርግብ የወፍ አምሳያ ትመስላለች ይህቺውም ድንግል ማርያም ፈጣኗ ደመና የእግዚአብሔር እናት ናት

141. ይእቲ እሞሙ ለሰማዕት

ይእቲ እሞሙ ለሰማዕት ወእኅቶሙ ለመላእክት

ቃልኪ አዳም ይጥዕመኒ አምአስካለ ወይን

ትርጉም ፡- የሰማታት እናታቸዉ የመላዕክት እህታቸዉ ያማረ ቃልሽ ከወይን ፍሬ ይልቅ ይጣፍጠኛል

142. በጽሐ ሠናይ

በጽሐ ሠናይ ወአልፀቀ ዘመን /፪/ ወበዓላ ለቅድስት ማርያም /፪/

እንተ በላዕሌሃ ተመርዓወ ቃል አንጺሑ ሥጋሃ ላዕለሃ ሀደረ

ትርጉም፡- ቃል ሥጋዋን አንጽቶ ያደረባትና የተሞሸረባ የቅድስት ድንግል ማርያም የክብረ በዓሏ ዘመን ወቅት በሰላም ደረሰ ገባ።

143. ዘየሀይድ ዓይነ

ዘየሀይድ ዓይነ /፪/ ልበሰ ክበር ለቢሶ ዳዊት /፪/

ቅድመ ታቦተ ሕግ ኀለየ ቅድመ ታቦተ ሕግ /፪/
ትርጉም፡- ዳዊት ዓይን የሚሰውር /የሚያብረቀርቅ/ ልብስ ለብሶ በታቦተ ሕግ /ታቦተ ጽዮን/ ፊት ዘመረ

144. እመ ብርሃን

እመ ብርሃን ወእመ ሕይወት /፪/

ማርያም ዘበአማን /፬/ ኧኸ

ትርጉም፦ የብርሃን እናት የሕይወት በእውነት ድንግል ማርያም ናት

145. ለመኑ እነግር ኃዘነ ልብየ

ለመኑ እነግር ኃዘነ ልብየ እንበሌኪ ማርያም እግእትየ /፪/

ወፍጡነ /፪/ ስምዕኒ ጸሎትየ /፬/

ትርጉም፡- እመቤቴ ማርያም ሆይ የልቤን ሀዘን ከአንቺ በቀር ለማን እነግራለሁ ፈጥነሽ ጸሎቴን ስሚ።

146. ኦ ድንግል

ኦ ድንግል አኮ በተላህዮ ዘልህቂ ከመ አዋልደ

ዕባራዉያን እለ ያገዝፉ ክሳዶን /፪/

147. እንዘ ዘልፈ

እንዘ ዘልፈ ትነብር ውስተ ቤት እግዚአብሔር /፪/

አስተርአየ መልአክ ዘኢኮነ /፪/ ከመቀዲሙ ኢኮነ /፪/

ትርጉም፦ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ዘወትር ስትኖር እንደፊተኛው ያልሆነ መልዓክ ተገለጠላት

148. በሰላም ንዒ

በሰላም ንዒ /፪/ ማርያም /፪/

ትናዝዘኒ /፪/ ኀዘነ ልበየ

ምስለ ሚካኤል /፪/ ወገብርኤል

ምስለ ሱራፌል /፪/ ወኪሩቤል

ምስለ ዑራኤል /፪/ ወሩፋኤል

149. አስተርእዮ በሰማይ ኮነ

በሐዋርያት ሁሉ አዘኑ ተከዙ

በስብሐት በማህሌት ሥጋዋን ገነዙ

አስተርእዮ በሰማይ ኮነ አስተርእዮ /፪/

በክብር በስብሐት መላእክት በራማ

እያመሰገኗት በጥዑም ዜማ

የማትፈቅጂ ድንግል የኃጥአንን ሞት

በአማላጅነትሽ አቆይን ጥቂት

የምታምር ርግብ ሰሎሞን አለሽ

ሥጋሽን ለመልበስ ወልድ መረጠሽ

ሞትንስ መሞትን ለሁሉም ይገባል

የድንግል መሞት ግን በጣም ያስደንቃል

150. ኪዳንኪ ኮነ

ኪዳንኪ ኮነ /፪/ ኪዳነ ምሕረት /፬/

ለኃጥአን ተስፋነ ለኃጥአን ቤዛነ ኪዳንኪ ኮነ /፬/

ትርጉም፡- ቃል ኪዳንሽ የምሕረት ቃል ኪዳን ሆነ ለኃጥአን ተስፋቸው ሆነ

151. ፀቃውዕ

ፀቃውዕ /፬/

ይውኅዝ እምከናፍሪሃ /፬/

ትርጉም፡- የማር ወለላ /ጣፋጭ ነገር/ ከከናፍሮቿ ይፈስሳል/ ከእመቤታችን

152. ዕፀ ጳጦስ ዘሲና

ዕፀ ጳጦስ ዘሲና ማርያም

የኖኅ ድንቅ መርከብ ተስፋው የአዳም

አምላክ ያስቀረልን ንፅሕቷ የአዳም ዘር

እናወድስሻለን እንድናገኝ ባንቺ ክብር

ወርቅ ተጎናጽፈሽ በልዑል ቀኝ የምትቆሚ

ምሳሌ የሌለሽ አዛኙቱ እኛን ሰሚ

የአቤል የዋህነት የሴት ቸርነት

የሴም ቡራኬው ነሽ የአብርሃም እንግድነት

የይስሐቅ መዓዛ የያዕቆብ መሰላል

የአሮን ካህን ልብስ የወርቅ ጸናጽል

የሳሙኤል ሙዳይ የጌዴዎን ፀምር

የኢያሱ ሐውልት የአሮን በትር

የሰሎሞን አክሊል የአሚናዳብ ሠረገላ

የኤልሳዕ ማሰሮ የኃጥአን ከለላ

153. ክብረ ቅዱሳን

ክብረ ቅዱሳን ይእቲ /፪/ ማርያም /፪/

ሙዳየ መና ግሩም ሙዳየ መና /፪/

ትርጉም፡- የቅዱሳን ክብር የመና ሙዳይ ማርያም አንቺ ነሽ

154. የአቢ ክብራ

የአቢ ክብራ ለማርያም ክብራ ለማርያም
እም ሃና ወኢያቄም <u>ይሴኒ ላህያ</u> /፪/ ለማርያም

155. ክብረ ቅዱሳን

ክብረ ቅዱሳን ይእቲ /፪/ ክብረ ቅዱሳን

ሙዳየ መና ግሩም ሙዳየ መና /፪/

የቅዱሳኑ ክብር ነሽና

እንሰጥሻለን ቅኔ ምሥጋና

የወለድሽልን የህይወት መና

ዝናም ያለብሽ ታናሽ ደመና

ትህትና ልብስሽ ፍቅር ዉበትሽ

ፅንስ ያዘልላል ሰላምታ ድምፅሽ

እሳቱን ወልደሽ እሳት ታቅፈሻል

ሳንዘምርልሽ መቼ ይመሻል

የፀሐይ መዉጫ ምሥራቅ ሆነሽ

ታላቁን ብርሃን አየንብሽ

አትጨልምም ህይወታችን

ልጅሽ ስላለ ፀሐያችን

ሰአሊለነ ሰላም ለኪ

ተማህፀነ በኪዳንኪ

ንኢ ርግብየ ምስለ ወልድኪ

ሰማይ ወምድር ያወድሱኪ

156. ዕፀ ጳጦስ ይእቲ

ዕፀ ጳጦስ ይእቲ እንተ በአማን ይብልዋ ቅድስተ ቅዱሳን /፪/

ሰአሊ ለነ ማርያም እም አምላክ አንቀጽ ብርሃን /፪/

ትርጉም፡- ቅድስተ ቅዱሳን የሚሉሽ ዕፀ ጳጦስ በእውነት አንቺ ነሽ ይሏታል። ለምኝልን ማርያም የአምላክ እናት የብርሃን መውጫ

157. ነይ ነይ

ነይነይ ማርያም ነይ ነይ
ድንግል ሆይ ነይ ነይ
ያን የእሳት ባሕር ከቶ እንዳላይ
በተራራማው በኤፍሬም ሀገር
እንግዳ የሆንሽ በኤልሳቤጥ በክብር
ነይልኝ እናቴ /፪/ ካንቺ ጋር ልኑር
ዓለም ከብዶብኝ ተጨንቄአለሁ
ሐዘን በዝቶብን ብቸኛ ሆኛለሁ
ኧረ ነይ ድንግል ሆይ /፪/ እጠራሻለሁ
ምሥጢር የገለጽሽ ለሕርያቆስ
ፈጥነሽ ያማለድሽ በቤተ ዶኪማስ
ነይልኝ ወደኔ /፪/ ልቤ ይፈወስ
ጥበብ አንቺ ነሽ የሲሎንዬስ
ነይ ብሎ የጠራሽ ሉላማጢስ
አትጥፊ ድንግል ሆይ /፪/ በእጅሽ ልዳሰስ
ድንግል ቀርባለች ጩኸቴን ሰምታ
የኃጢአቴ ገመድ እስሩ ተፈታ
አከብራታለሁ /፪/ ልጇ በእልልታ

158. ለሳውል ወኬፋ

ለሳውል ወኬፋ /፬/

አክሊሎሙ /፪/ ትኩነነ ተስፋ /፬/

ትጉርም፡- የጴጥሮስና የጳውሎስ አክሊላቸው ድንግል ማርያም ተስፋ ትሁነን።

159. የዓለም ንግሥት የሆንሽው

የዓለም ንግሥት የሆንሽው

ድንግል ማርያም እናቴ

ታመስግንሽ አንቺን ሁል ጊዜ ሕይወቴ

ማርያም ባርኪኝ እመቤቴ እሰግድ ለኪ

እንዳልንገላታ ጠብቂኝ በኃጢአት ዓለም ጎዳና

ደግሞም እንድመገብ ሰማያዊ መና

ማርያም የአዳም ጤና እሰግድ ለኪ

ተሸጬ ስኖር ልጅሽ በኃጢአት ዓለም ከተማ

የሚያወጣኝ ጠፍቶ የእናት ልጅ ወንድም

ወጣሁኝ በልጅሽ ደም እሰግድ ለኪ

የአንቺ መንገላታት ሁሉ ጊዜ ያሳዝነኛል ሲወራ

ማርያም ነፍሴን አደራ እሰግድ ለኪ

160. አፈ ንህብ

አፈ ንህብ ማቱሳላ ወልደ ሔኖክ እምአፈ ልምላሜ

ቡሩክ አፈ መልአክ /፪/

ቀሰመ ጽጌ /፪/ ጽጌኪ እመ እምላክ

ትርጉም፡- አፈንብ የተሰኘ የሄኖክ ልጅ ማቱሳላ

የአምላክ እናት ሆይ ከቡሩክ ልምላሜ አበባሽ ቀሰመ

161. መዓዛ አፈዋት

መዓዛ አፈዋት ማርያም /፪/ ጽጌ መንግሥት ቡርክ /፪/

ጽጌ /፪/ ዘሰሎሞን ወዳዊት አብርሃ ወአጽብሐ /፪/

ትርጉም፡- በጎ መዓዛ ያለሽ ሽቱ /ቅመም/ የተባረክሽ
የመንግሥት /የክብር/ አበባ ማርያም የሰሎሞን የዳዊት
የአብርሃና የአብጽሃ ክብራቸው ነሽ፡፡

162. መላዕክት ይብልዋ

መላዕክት ይብልዋ /፪/ ለማርያም
ኧኸ ሰላም ለኪ /፬/ ይብልዋ ለማርም
ቅዱሳን ይብልዋ /፪/ ለማርያም
ሰማዕታት ይብልዋ /፪/ ለማርያም

163. ፀሐይኑ ንብለከ

ፀሐይኑ ንብለከ /፪/ ወልደ ማርያም ንብለከ /፪/

በመኑ በአምላለ መኑ ናስተማስለከ /፬/

ፀሐይኑ ንብለኪ /፪/ ወላዲተ ቃል ንብለኪ /፪/

በመኑ በአምላለ መኑ ናስተማስለኪ /፬/

164. እንበለ ምግባር

እንበለ ምግባር ባሕቱ እመ ኢይፀድቅ አነ /፪/

ቦኑ ለከንቱ ኪዳንኪ ኮነ ቦኑ ለከንቱ ኪዳንኪ ኮነ /፪/

ትርጉም፡- ምንም እንኳ ሥራዬ ለዚያ የሚያበቃ

ባይሆን መንግሥት ሰማያትን የምወርሳት

ካልሆነ እመቤቴ ሆይ ቃል ኪዳንሽ ለከንቱ ነውን፡፡

165. ለምኝልን ማርያም

ለምኝልን /፪/ ማርያም ለምኝልን /፪/

የንፁሐን አክሊል /፪/ የቅዱሳን ብርሃን /፪/

166. መሠረት ሕይወት

መሠረት ሕይወት ማርያም ወጥንተ

መድኃኒት ዘእምቀዲሙ /፪/

ለወልድኪ /፪/ አምላለ ደሙ /፪/

ትርጉም፡- ቅድመ ዓለም የነበረ መድኃኒት ከሚባል

የተገኘሽ የሕይወት መሠረት ማርያም አንቺ ነሽ

መሠረትነትሽም የልጅሽ የደሙ ምሳሌ ነው፡፡

167. እንተ በምድር

እንተ በምድር ስረዊሃ
ወበሰማይ አዕፁቂህ /፪/
ሐረገወይን /፪/
ድንግል ሐረገወይን

168. ርግብዬ

ርግብዬ /፪/ ማርያም እሙ ለእግዚእየ

በቀለመ ወርቅ ጸአፊ ስምዬ

በዓምደ ብርሃን ጸአፊ ስምዬ

በቀለመወርቅ ጸአፊ ስምዬ

የተመረጥሽ ጌጤ ፈርጤ ሽልማቴ
የክብሬ አክሊል ነሽ ለኔ እመቤቴ ርግብዬ
ወደአንቺ እጮሃለሁ በችግሬ ጊዜ
እንድታርቂልኝ የልቤን ትካዜ ርግብዬ

የማትፈርሺ መቅደስ ንፅሕት አዳራሽ

የመለኮት እሳት በማሕፀንሽ የያዝሽ ርግብዬ

የድኅነቴ ምክንያት የሕይወቴ ፋና

የችግር ደራሽ ርኅርኅተ ኅሊና ርግብዬ

ስጠራ ስምሽን ከጧት እስከ ማታ
ፈጥነሽ ድረሽልኝ እንዳልንገላታ ርግብዬ
የነቢያት ትንቢት የሰማዕታት አክሊል
ምዕራገ ጸሎት የወርቅ መሰላል ርግብዬ

ምርኩዝ መደገፊያ የሃይማኖት በትር

ሆነሽ የተገኘሽ የሕይወት ማኅደር ርግብየ

መንገዴ ጨልሞ ወድቄ እንዳልቀር

ደግፈሽ አሻግሪኝ ያን የኃጢአት ባሕር ርግብዬ

169. ኦ ርህርህተ

ኦ ርህርህተ ህሊና አፍቅሮተ ሰብ ለማዳ /፪/
ለእለ ጌሰሙ /፬/ ትመስል /፫/ እንግዳ

170. የብርሃን መውጫ

የብርሃን መውጫ የሕይወት መሰላል

የተነበየላት ነቢዩ ሕዝቅኤል /፪/

የሰሎሞን አክሊል የአሮን በትር

ሆና የተገኘች የአምላክ ማኅደር /፪/

የዳዊት መሰንቆ የጌዴዎን ጸምር

አፍርታልናለች ያለ ወንድ ዘር /፪/

እስኪ እናመሰግናት ያለ ወንድ ዘር /፪/

ቅድስት እናታችን ስብሕት ወቡርክት

አንቀፀ ብርሃን ምዕራገ ሕይወት

አዘክሪ ድንግል ለልጅሽ በእውነት

በድኅና እንዲያደርሰን ለመጪው ዓመት /፪/

171. ምክሆን ለደናግል

ማርያም ድንግል ምክሆን ለደናግል

ይእቲኬ ቤተ ምስአል ዘአስተአጸቡ ታቀልል

ለኩሉ ፍጥረት ትተነብል በአክናፈ መላእክት
ትትኬለል

ይእቲ ተዐቢ እምኪሩቤል ወትደፈፍድ እምሱራፌል

እኮ የምልጃ ቤት ናት

የሚያስጨንቀውን የምታቃልል

ለፍጥረት ሁሉ ትማልዳለች በመላእክት

ክንፎችም ትጋረዳለች እርሷ ትበልጣለች

ከኪሩቤል ደግሞም ትልቃለች ከሱራፌል

172. ኪዳነ ምሕረት እመቤት

ኪዳነ ምሕረት እመቤት /፪/
ነይልን /፪/ ካለንበት
ከሰማያት በላይ ካለው ከማደሪያሽ /፪/
ዝማሬ ከሞላው ከዘለዓለም ቤትሽ
የምድር ፍጥረታት ማርያም /፪/ ሲሉሽ /፪/
የቃል እናት እመቤቴ ነይ በሰረገላሽ /፪/
ከፀጥታው ወደብ ከፍቅር አውድማ /፪/
ከሰላሙ መንደር ከእውነት ከተማ
ሰዓሊለነ ቅድስት ውዳሴሽ ሲሰማ /፪/
ከሚካኤል ከገብርኤል ጋር ነይልን ከራማ /፪/
ዘርፋፋው ቀሚስሽ ይውረድ ከሰማያት /፪/
እንባችን ይታበስ ባንቺ አማላጅነት
የጽዮን ዝማሬ ተሞላች ነፍሳችን /፪/
ንኢ /፫/ እንበል እንደ አባቶቻችን /፪/
ፍጥረታት ሊድኑ በአማላጅነትሽ /፪/
የዘለዓለም ኪዳን አማኑኤል ሰጠሽ
ትውልድ ይህን አምኖ ብፅዕት ይልሻል /፪/
እናቴ መመኪያዬ ምርኩዜ ሆነሻል /፪/
የልብን ሲያዋዩሽ ሰምተሽ ዝም አትዪም /፪/
ችግረኛን አይቶ ልብሽ አይጨክንም
ከአይን ጥቅሻ ፈጥነሽ ትደርሺለታለሽ /፪/
ከሐዘን ከመከራ ታሳርፊዋለሽ /፪/

173. ቅንኡ

ቅንኡ ለእንተ ተአቢ ጸጋ
መድኃኒት ለነፍስ /፬/ መድኃኒት ኪዳነ ምህረት

174. ዳግሚት አርያም

የአባ ሕርያቆስ ድርሳነ ቅዳሴው

የእነ አባ ኤፍሬም ኃይለ ጸሎታቸው

ማርያም ድንግል ነሽ የእምነት ሙዳያቸው

ወይነ ሕይወት ክርስቶስ የተመላብሽ

ጽዋዐ መድኃኒት ነው የሌለብሽ

የማይቻለውን በማኅፀን የቻልሽ

ምንኛ ድንቅ ነው መቅደስነትሽ

አርፌም አልተኛ ዙፋኔን ትቻለሁ

የያዕቆብን አምላክ ማደሪያ ካላየሁ

ብሎ የናፈቀሽ ዳዊት አባትሽ

ኢያቄም ወሐና ገና ሳይወልዱሽ

እንደምን ታደሉ ሐናና ኢያቄም

የእነርሱ ናትና ዳግሚት አርያም

በሥጋዊ ፈቃድ ሊያስገኙሽ ያልቻሉ

የእግዚአብሔር ስጦታ መድኃኒተ ኩሉ

የድኅነት ምልክት የምእመናን ዓርማ

ተናጋሪ ገነት የጻድቃን ከተማ

ማኅደረ መለኮት የአብ ቃል መገኛ

የሕይወት ውኃ ምንጭ የአዳም ዘር መዳኛ

175. አትለይን

አትለይን /፪/ ድንግል ሆይ ድረሽልን /፪/

ከዲያብሎስ እጅ አንቺ አድኝን

ምሕረት ከልጅሽ ለምኝልን

176. ማርያምስ

ማርያምስ ተኃቱ እመትካት ውስተ

ከርሱ ለአዳም ከመባሕርይ ጸዐዳ

እስመ በአንቲአሃ ወበእነተ አዝማዲሃ

ተሰቀልኩ ዲበ ዕፅ ይቤ መድኃኔዓለም

ማርያምማ ታበራለች ከጥንት ጀምሮ በአዳም

ባሕርይ ውስጥ እንደ ነጭ ዕንቁ በአዳም

እርሷን ደስ ይበላት ብሎ ስለወገኖቿ

ተሰቀልኩ አለ በእንጨት መስቀል ላይ
መድኃኔዓለም

177. አማናዊት ኪዳን

አማናዊት ኪዳን የሰው ልጆች ተስፋ

ድንግል ሆይ አማልጅን በሞቀት እንዳንጠፋ

የአባቶች ነቢያት ተስፋ ትንቢታቸው

የሐዋርያትም ጣዕመ ስብከታቸው

የሰማዕታት እናት የጻድቃን እመቤት

ደግሞም እጎታቸው ለሰማይ መላእክት

የነቅዱስ ኤፍሬም ድንቅ ድርሰታቸው

የነ ቅዱስ ያሬድ ድጓ ዝማሬያቸው

የእምነታቸው ቅመም አንቺ ነሽ በእውነቱ

የአባ ጊዮርጊስም ጸሎተ ሰዓታቱ

የአባ ሕርያቆስ ምሥጢረ ቅዳሴ

የመነኮሳት ስንቅ የኤፍሬም ውዳሴ

የሊቃውንት አበው የምሥጢር ቋንቋቸው

የደናግል ተስፋ የጽድቅ አክሊላቸው

ሁኝልን መመኪያ በሞት እንዳንሰጋ

በዚች ዓለም ፈቃድ ከቶ አንወጋ

ስለሌለን ተስፋ በዚህ ዓለም ስንኖር

አስታርቂን እመአምላክ ከቸሩ ልጅሽ ጋር

178. ፍስሐ ወሰላም

ፍስሐ ወሰላም የኀሉ ምስሌነ /፪/

ድንግል ማርያም እምነ /፬/ ኧኸ

ትርጉም:- ደስታና ሰላም ከእኛ ጋር ይሁን ድንግል
ማርያም እናታችን ናትና::

179. ንዒ ሀቤነ

ንዒ ሀቤነ ኦ ድንግል

ምስለ ወልድኪ መድኃኒነ

ከመ ትባርኪ ላዕሌነ

ነይ ከአምላክሽ ጋር ከልጅሽ

ይቅር እንዲለን በምልጃሽ

ንዒ ድንግል /፪/ ከልጅሽ ከአማኑኤል

የሐና የኢያቄም መልካም ተክል

የሐዋርያት ስብከት የሰማዕታት አክሊል

ነይ ድንግል /፪/ ነይልን ፈጥነሽ ድንግል

አሕዛብ ነገሥታ ይገዙልሻል

የናቁሽም ሁሉ ይሰግዱልሻል

የእግዚአብሔር ከተማ /፪/ ድንግል ሆይ

ጽዮን ይሉሻል

180. ፍቅርኪ መፅሐፍ

ፍቅርኪ መፅሐፍ /፬/

ለዘያነብቦ /፫/ ፍቅርኪ መፅሐፍ /፪/ ኧኸ

ትርጉም፡- ለሚያነበው ሰው ፍቅርሽ መፅሐፍ ነው።

181. በአልባሰ ወርቅ

በአልባሰ ወርቅ /፪/ ፀዓዳ ርግብ ትመስል ማርያም ድንግል /፪/

ይእቲኬ ማርያም ድንግል እምደመና ቀሊል እሙ ለእግዚእ /፪/

ትርጉም፡- ድንግል ማርያም ወርቅን ተጎናጽፋ ነጭ ርግብን ትመስላለች። እርሷም ማርያም የጌታ እናቱ ከደመና ይልቅ ፈጣን ናት።

182. ኦ ድንግል ደስ ይበልሽ

ኦ ድንግል ደስ ይበልሽ

ቅድስት ደስ ይበልሽ

ገብርኤል በቃሉ ደስታን ያሰማሽ

ኦ ንፅሕት ደስ ይበልሽ

የዘለዓለም አምላክ እናት ስለሆንሽ
ኦ ንፅሕት ደስ ይበልሽ
ከፍጡራን ሁሉ በላይ ስለሆንሽ

ኦ ንፅሕት ደስ ይበልሽ

የነገስታት ንጉስ ዙፋን ስለሆንሽ
ኦ ንፅሕት ደስ ይበልሽ
የድኅነቴ ዓርማ ልዩ ምልክቴ

ለእኔም ነሽ እናቴ እመቤቴ

የድኅነቴ ዓርማ ልዩ ምልክቴ

ልዩ ነሽ እናቴ እመቤቴ

የምታማልጂን ከቸሩ አባታችን
ለእኛ እናታችን እመቤታችን /፪/
የምታማልጂን ከቸሩ አምላካችን
ለእኛም እናታችን አስታራቂያችን
ስለዉድ ሀገርሽ ስለ ኢትዮጲያ

ለልጆችሽ አሳስቢ ብለሽ ሃሌሉያ

ድንግል ሆያ አሳስቢ ብለሽ ሃሌሉያ /፪/

ስለዉድ ሀገርሽ ስለ ኢትዮጲያ

ለልጅሽ አሳስቢ ብለሽ ሃሌሉያ

183. ከፈጣሪ በታች

ከፈጣሪ በታች ከፍጡራን በላይ /፪/

ማን አለ እንዳንቺ ድንግል ንፁህ በዓለም ላይ /፪/

ኦ ድንግል ማርያም ዘለዓለም /፪/

መኩሪያ ነሽ መመኪያም

አምላክ ለማደሪያ መርጦ ያዘጋጀሽ /፪/

ፂዮን የተባለች ሀገር ድንግል ሆይ አንቺ ነሽ /፪/

በሐሳብሽ ድንግል ድንግል በስጋሽ /፪/
ከፍጥረታት ሁሉ ላንቺ ምሳሌም የለሽ /፪/
ፍቅሩ ለዘላለም የማይጠገበዉ /፪/

ከስም ሁሉ በላይ ጣፋጭ ድንግል ያንቺ ስም ነዉ/፪/

በእዝራ መሰንቆ በዳዊት በገና /፪/
ይገባሻል ላንቺ ድንግል ሁል ጊዜ ምሥጋና
እስኪ ልያዝና ደጋፊ ምርኩዜን

እስኪ ልያዝና የርሃብ መድኃኒቴን

ወደአምላኬ ቤት ልሄድ ልቀጥል ጉዞዬን /፪/

ለፍርድ ስጠራ በደለኛዉ እኔ /፪/
የእኔ መማፀኛ ድንግል ቁሚልኝ ከጎኔ

184. እናት አለኝ

እናት አለኝ እኔስ እናት አለኝ

ሲጨንቀኝ ሲጠበኝ የምታዕናናኝ

እናት አለኝ እኔስ እናት አለኝ

የተቀኘላት እዝራ በመሰንቆ
እናትነቷን ንፅህናዋን አዉቆ
ያመሰገናት ዳዊት በበገና
አትለየኝም እናቴ ናትና /፪/

ሳለቅስ ስተክዝ ወድቄ ከፊቷ

አቅፋ አፅናናቺኝ እኔን ከደረቷ

ታስታርቃለች ሁሌ ለኃጥአን

ትማፀናለች በእንባ ዝክር ልጇን /፪/

የአዳም ተስፋ ናት ድንግል እናታችን
መርጦ ያደረባት ክርስቶስ ጌታችን
ታማልዳለች ዛሬም ለዘላለም
የአምላክ እናት የፍጥረታ ሰላም /፪/

185. ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም

ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም

ድንግል ማርያም /፪/

ንፅሕተ ንፁሐን ማርያም

ድንግል ማርያም /፪/

ታማልዳለች ከልጇ ከመድኃኒዓለም /፪/

ታማልዳለች ከልጇ /፪/ ከመድኃኒዓለም

ታማልዳለች /፬/ ልጄ ሆይ ይቅር በል እያለች

አባቶቻችን ነቢያት ወሐዋርያት
ፃድቃን ወሰማዕታት
ያማልዳሉ በእዉነት ያማልዳሉ /፪/
ያማልዳሉ በእዉነት /፪/ ያማልዳሉ
ሰባቱ ሊቃነ መላእክት ሚካኤል ወገብርኤል

ሩፋኤልና ፍኑኤል

ሰራዊታቸዉን ሁሉ

ሰባቱ ሊቃናት መላእክት አፋኒን ራጉኤልና ሳቁኤል

ሰራዊቶቻቸዉም ሁሉ

ያማልዳሉ ከክፉም ይጠብቃሉ /፪/

ያማልዳሉ ከክፉም /፪/ ይጠብቃሉ

ያማልዳሉ /፬/ ከክፉም ይጠብቃሉ

በዱር በገደል በበረሀ በዋሻም ያሉ /፪/
ያማልዳሉ በእዉነት ያማልዳሉ /፪/
ያማልዳሉ በእዉነት /፪/ ያማልዳሉ
ያማልዳሉ /፬/ አምላክ ሆይ ይቅር በል እያሉ

186. እጎትየ መርዓት

እጎትየ መርዓት ቅድስት /፪/
እም ዘመዶሙ ለካህናት /፬/

187. እጎትየ ይብልዋ

እጎትየ ይብልዋ መላእክት በክብር /፪/
ለማርያም ድንግል /፬/

188. አምላክ ለእኛ ብሎ

አምላክ ለእኛ ብሎ ቃል ኪዳን የሰጣት /፪/
የኃጥአን አማላጅ ድንግል ማርያም ናት /፬/
እንደ አማለድሽው በላዔ ሰብእን /፪/
እኛንም እባክሽ አደራ አማልጅን /፬/
ምሕረት እንድናገኝ ከአምላካችን /፪/
አማላጅ ሁኝልን እመቤታችን /፬/
ከአንቺ በተገኘው በመልካሙ ፍሬ /፪/
ዓለም ተቀድሷል ነጻ ወጥቷል ዛሬ /፬/
ስምሽ ግርማ ያለው ኪዳነ ምሕረት /፪/
የሰዎች አማላጅ የጌታዬ እናት /፬/
ካህናት በከበሮ ሲያመሰገኑሽ /፪/
እኛም በእልልታ እንዘምርልሽ /፬/

189. መርሕ ዘገነት

መርሕ ዘገነት መርሕ ዘገነት /፪/
አንቺ ነች /፪/ ኪዳነምሕረት
ቅድስት እመቤቴ ጌታዬ እናት
ሆነሽ የተገኘሽ ንጽሕት ቅድስት
አንቺ ነሽ . . .
የሲና ሐመልማል የሰው ልጅ ሕይወት
አንቺን የመረጠ ይክበር መለኮት
አንቺ ነሽ. . .
አዘክሪ ድንግል ለልጅሽ በእውነት
በደኅና እንዲያደርሰን ለመጪው ዓመት
አንቺ ነሽ. . .

190. ሰላም ለኪ

ሰላም ሰላም ለኪ ማርያም ሰላም ለኪ /፪/

የሕይወት መሠረት ሰላም ለኪ
የፍጥረት አለኝታ ሰላም ለኪ
ድንግል አደራሽን ሰላም ለኪ

በላዔ ሰብእ ዳነ ሰላም ለኪ
ብዙ ነፍስ አጥፍቶ ሰላም ለኪ
የአንቺን ስም ለጠራ ሰላም ለኪ
ጥርኝ ውኃ ሰጥቶ ሰላም ለኪ
ተማጽነንብሻል ሰላም ለኪ

በአማላጅነትሽ ሰላም ለኪ

ድንግል ሆይ አደራ ሰላም ለኪ

አማልጅን ከልጅሽ ሰላም ለኪ

እኛ ብንከተል ሰላም ለኪ
በጎ ምግባርን ሰላም ለኪ
በሰላም በጤና ሰላም ለኪ
እንኖራለን ሰላም ለኪ
የልቦናቸው በር ሰላም ለኪ

ለተዘጋባቸው ሰላም ለኪ

እንዲያመሰግኑሽ ሰላም ለኪ

ድንግል ሆይ እርጃቸው ሰላም ለኪ

191. አማን በአማን

አማን በአማን /፪/ ኪዳንኪ /፪/
ኪዳንኪ ኢየሐልቅ /፬/
ትርጉም፡-እውነት በእውነት /፬/
አያልቅም ቃልኪዳንሽ /፬/

192. አማልጂን ከልጅሽ

ማርያም /፪/ ድንግል ማርያም /፪/
አማልጅን ከልጅሽ /፪/ ከመድኃኔዓለም /፪/
ኃጢአተኞች ከኃጢአት እንፈውስ
በማርያም ድንግል /፪/ ክብርን አገኘን
በማርያም ድንግል /፪/ አክሊል አገኘን

193. አዳም ንባብኪ

አዳም ንባብኪ ርግብ ሠናይት /፪/
በልባስ ወርቅ /፪/ ንኢ /፪/ ኪዳነምሕረት /፪/
ትርጉም፡- ነገርሽ (አነጋገርሽ) በጣም ጥሩ ነው።
ወርቅ ለብስሽ ነይ

194. እንበለ ምግባር

እንበለ በምግባር ባሕቱ እመ ኢይጸድቅ አነ /፪/
ቦኑ ለከንቱ ኪዳኒኪ ኮነ ቦኑ ለከንቱ ኪዳነኪ ኮነ /፪/
ትርጉም፡- ያለበጎ ሥራ የምንጸድቅ መንግሥተ
ሰማያትን የምንወርስ ካልሆነ እመቤቴ ቅድስት
ድንግል ማርያም ሆይ ቃል ኪዳን ኪዳንሽ ለከንቱ
ነበርን

195. አመ ወርኃ ነጊድ

አመ ወርኃ ነጊድ የጎልቅ ወይፀራህ ሴጥ /፪/
በገጸ ፈጣሪ ቤዛ ይኩነኒ ኪዳንኪ
በገጸ ፈጣሪ ቤዛ ይኩነኒ ኪዳን /፬/
ትርጉም፡- በእለተ ምፅአት ጊዜ ኪዳንሽ
በፈጣሪ ፊት ቤዛ ይሁን።

196. ልቤን አነሣሥቶ

ልቤን አነሣሥቶ ያመለክተኛል
የአምላክን እናት እመናት ይለኛል /፪/
እመን /፬/ የአምላክ እናት አዛኝቷን /፪/

197. አንቺ የወይን ሐረግ

አንቺ የወይን ሐረግ ድንግል ልምላሜሽ የበዛ
ምግብ ሆኖ ተሰጠን ፍሬሽ ለእኛ ቤዛ
በአንቺ ሰማይነት ድንግል የወጣው ፀሐይ
ብርሃን ነው /፪/ ለጻድቃን ስሙም አዶናይ
ፊደል ትመሥያለሽ ድንግል ወንጌል ትወልጂያለሽ
ለመላእክት የማይቻል ነበልባሉን የቻልሽ
የመሶብ ምሳሌ ድንግል የኮከብ መገኛ
በሥጋችን በነፍሳችን እንዳንራብ አንቺ አለሽን ለእኛ

198. የአምላክ እናት

የአምላክ እናት ነይልን እኛ ልጆችሽን ባርኪን
ከአንዱ ልጅሽ /፪/ ፈጥነሽ አማልጅን /፪/

ስምሽን ሲጠሩ በሽተኞች ሁሉ
በአንቺ አማልጅነት ፈውስን ያገኛሉ /፪/

በኃጢአት በሽታ ታምሞ የሚሰቃየው

የአዳም ዘር ተስፋው በአንቺ እኮ ነው /፪/

ከሀዲው ቢበዛ አንቺን ቢረሳሽ
አንቺ አዛኝ ነሽ ጥላቻ የለሽ /፪/

ለጻድቃን አይደል ለኃጥአን ታለቅሻለሽ
በአማልጅነትሽ ዘውትር ታስቢያሽ /፪/

199. ማርያምሰ ተሀቱ

ማርያምሰ ተሀቱ እምትካት ውስተ ከርሱ /፪/
ለአዳም ከመባሕርይ ጸዓዳ
እስመ በእንቲአሃ ወበእንተ አዝማዲሃ
ተሰቀልኩ ዲበ እጽ ይቤ መድኃኔዓለም /፪/
ትርጉም፡- ማርያምማ ታብራለች ከጥንት ጀምሮ
በአዳም ባሕርይ ውስጥ እንደ ነጭ እንቁ በአዳም
ባሕርይ እርሷን ደስ ይበላት ብሎ ስለወገኖቿ
ተሰቀልኩ አለ በእንጨት መስቀል ላይ መድኃኒዓለም

200. እመአምላክ ሙሽራ ነሽ

እመአምላክ ሙሽራ ነሽ
ለቃል ማደሪያ ለመሆን የበቃሽ
ኸኸ /፫/
አስራ ሁለት ዓመት ቤተ መቅደስ የኖርሽ
የመመረጥ ጸጋ ከጌታ ያገኘሽ

በአብሣሪው መልአክ እጹብ ድንቅ ዜና
ከሰማይ መጣልሽ አቋርጦ ደመና
በስድስተኛው ወር ተልኮ ገብርኤል
ቤተመቅደስ ገባ ሊያበስራት ለድንግል

በልዩ ሰላምታ ሰላም ለኪ አለሽ
የክርስቶስ እናት በጣም ደስ ይበልሽ
መላእክት በሰማይ ያመሰግኑሻል
ክብር ለአምላክ እናት ይድረሳት ይሉሻል

በማሕፀንሽ ቢያድር የሠራዊት ጌታ
ለመሆን ተመረጥሽ የአምላክ ቅድስት ቦታ
የፈጣሪ እናት መሆንሽን ተረድቶ
ሰላም ላንቺ ይሁን አለሽ እጅ ነሥቶ

201. ወእንዘ ትፈትል

ወእንዘ ትፈትል /፪/ ወርቅ ወሜላተ ገብርኤል
ግብተ/፪/
ወይቤላ /፪/ እስመ ረከብኪ ሞገሰ በጎበ እግዚአብሔር

202. በክቡር ዙፋኑ

በክቡር ዙፋኑ መርጦ ያስቀመጠሽ
ለእኛ ለኃጢአተኞች ተስፋቸን አንቺ ነሽ
በፍጹም ትኅትና ቤተመቅደስ ያደግሽ
የአማኑኤል የጌታዬ የፈጣሪዬ እናት በምን
እንመስልሽ
ቃና ዘገሊላ ሠርግ ደግሠው
አንቺን ከነልጅሽ በክብር ጠርተው
ሰዎች ተረብሸው በጣም ተደናግጠው
ወይኑ በማለቁ በፍርሃት ተውጠው
ወይኑ በመሀል ላይ ማለቁን ሰምተሽ
ድንጋጤአቸውን እመቤቴ አይተሽ
ወደ ልጅሽ ሄደሽ ብጠይቂላቸው
ጋኑን ውኃ ሙሉ ብሎ አዘዛቸው
የሚላችሁን አድርጉ ብለሽ
ሰዎቹን ከሀፍረት ከጭንቀት ፈታሽ
ድንግል እመቤቴ ቤዛዊተ ዓለም
በመከራ ደራሽ እንደአንቺ የለም
ውኃውን ወደ ወይን አጣፍጦ ቀይሮ
የዶኪማስንም እፍረቱን ሠውሮ
እድምተኞች ሁሉ እስከሚደነቁ
አምላክ ከእነርሡ ጋር መሆኑን እወቁ

203. ሰላም ለኪ

ሰላም ለኪ /፪/ ማርያም ሰላም ለኪ
ሰላም ለዝክርኪ ማርያም ለኪዳንኪ
ሰላም ለአንቺ ይሁን የኤልሣቤጥ ሰላምታ ሰላም ለኪ
አምላክ የመረጠሽ ሰላም የፍጥረት አለኝታ ሰላም
ለኪ
የልባችን ደስታ የተገለጸልሽ ሰላም ለኪ
የአማኑኤል እናት ምስጋና ይድረስሽ ሰላም ለኪ
ንጽሕተ ንጹሐን እንከን የሌለብሽ ሰላም ለኪ
መዓዛሽ ያማረ ጸጋን የተሞላሽ
ልቤ ተደሰተ ዜናሽን ሲሰማ ሰላም ለኪ
እጎቴ ሙሽራዬ የዳዊት ከተማ
ስምሽን ለልጅ ልጅ
እስቲ እኔ ልናገር ሰላም ለኪ
ከአንቺ ያገኘሁት
አለ ብዙ ነገር ሰላም ለኪ
ሰላም ለኪ ድንግል
እሰግድልሻለሁ ሰላም ለኪ
የአንቺን ቅድስና
ለዓለም እነግራለሁ ሰላም ለኪ

204. ድንግል ማርያም

የእኛ አማላጅ
ድንግል ማርያም የእኛ አማላጅ /፪/
ከአብርሃም ዘር የተመረጠች
በድንግልና ጌታን ወለደች

መሶበ ወርቅ የመና ሙዳይ
ቤቴልሔም ሆይ እሙ ለፀሐይ
የካህናቱ ወርቅ ማእጠንት
የዕጣን መያዣ ነሽ ልዩ ፍጥረት

የመለኮት አትሮኖስ የኮሬብ ተራራ
የወርቅ መቅረዝ የአሚናዳብ ሰረገላ
ንጹሕ የሠርግ ቤት የአብርሃም ድንኳን
የአምላክ ማደሪያ ታቦተ ጽዮን

የአቤል የዋኅት የሴም ቸርነት
የዮሴፍ አጽናኝ ርግብ የዋህት
የአቤል ፀናፅል የጌድዮን ፀምር
የሠሎሞን ጥበብ የዳዊት መዘሙር

205. አንቀፀ ብርሃን

አንቀፀ ብርሃን ድንግል ማርያም
ሰማያዊ ዙፋን የመድኃኔዓለም /፪/
ሰማይና ምድር የማይችሉትን
ኸረ እንደምን ቻልሽው ፍሀም መለኮትን /፪/
የእሳት መጋረጃ ወዴት ተጋረደ
ልዑል በጥበቡ ካንቺ ተዋሐደ /፪/
የኪሩቤል አምሳል እመብርሃን ናት
ሰማያዊ ንጉሥ የከተመባት /፪/
የመለኮት ዙፋን ድንግል በመሆንሽ
ሚካኤል ገብርኤል ሰግደው ዘመሩልሽ
ሩፋኤል ራጉኤል ሰግደው ዘመሩልሽ

206. ልዩ ክብር

ልዩ ክብር የተሰጠሽ ንጽሕት ወቡርክት
የነብያት ሀገራቸው እህተ መላእክት
እናመሰግናት /፪/ እናወድሳት
ከሴቶች ሁሉ ደንግል ልዩ ናት

እናመሰግናት ክብር የበዛ ነው
‹‹ ፍጹም ነው ኪዳኗ
‹‹ ለምና ታሰታርቀን
‹‹ ርኅርኂተ ኅሊና
‹‹ የክፉ ቀን ደራሽ
‹‹ መሸሸጊያ ታዛ
‹‹ የሰላም ሠገነት
‹‹ የነፍሳችን ቤዛ

እናመሰግናት የተስፋ ፀሐይ ናት
‹‹ ሽልማቴ ዘውዴ
‹‹ የዓይኔ ብርሃን
‹‹ አጽናኝ ናት ዘመዴ
‹‹ የርግብ ምልክት
‹‹ የአዲስ ዘመን ብሥራት
‹‹ የድኅነት ዓርማ
‹‹ ትንቢተ ነቢያት

እናመሰግናት የአዳም በረከት
‹‹ የዘለዓለም ቤቱ
‹‹ የሐዘኑ መርሻ
‹‹ ማረፊያ ርስቱ

‹‹ ይገባታልና

‹‹ ወዳሴና ክብር

‹‹ ሆና ተገኝታለች
‹‹ ሀገረ እግዚአብሔር

እናመሰግናት የልዑል ዘፋኑ
‹‹ መንበረ ጸባኦት
‹‹ የኪሩቤል ሞገስ
‹‹ መንፈሳዊ ታቦት
‹‹ በልዩ ዝማሬ
‹‹ እንደ መላእክት
‹‹ ስሟን እናወድስ
‹‹ እንበላት ቅድስት

207. እምብርሃን መመኪያችን

የአዳም ተስፋው አለኝታችን
እመብርሃን መመኪያችን
እመብርሃን የአባቶቻችን
‹‹ ቃና ለዛቸው
‹‹ በችግር ጊዜ
‹‹ መንገድ መሪያቸው
‹‹ ምን ብዬ ልጥራሽ
‹‹ ላወድስሽ
‹‹ የምግባር ደሀ
‹‹ ባዶ ልጆሽ

እመብርሃን የቅዱሳኑ
‹‹ ጣእመ ዜማቸው
‹‹ አንቺ ነሽና
‹‹ ውብ ደስታቸው
‹‹ የእኛ ሥጦታ
‹‹ የድል አክሊል ነሽ
‹‹ በአማልጅነት
‹‹ ለታመነብሽ

እምብርሃን የይስሐቅ መዓዛ
‹‹ በፍናኖተ ሎዛ
‹‹ የያእቆብ መሰላል
‹‹ የአቤል የዋኅት
‹‹ የሴት ቸርነት
‹‹ የኢያሱ ሐውልት
‹‹ የሕይወት ውኃ
‹‹ የሳሙኤል ዘይት
‹‹ ርግብ ሠናይት
‹‹ ንግሥተ ሰማይ

እመብርሃን መልካሚ ርግብ
‹‹ የኖሕ መልክቱ
‹‹ የኀጥአን ተስፋ
‹‹ የልብ ብርታቱ
‹‹ ምሥራቻችን
‹‹ ውስጣችን ያለሽ
‹‹ በምድር በሰማይ
‹‹ አምሳያም የለሽ

208. ኅሥዓ ልብየ

ኅሥዓ ልብየ ቃለ ሠናየ /፪/
ወአነ አይድአ ቅዳሴሃ ለማርያም /፬/

እኔስ የማርያምን ውዳሴዋን እናገራለሁ
እንደ አባቴ ዳዊት በበገና እዘምራለሁ
ቀን ከሌሊት ሳልል ለምስጋና እተጋለሁ
ምርኩዜ ነሽና እመቤቴ በአንቺ እመካለሁ

ኦ እመቤቴ በእውነት እንወድሻለን
የእውነተኛ መብልን ክርስቶስን ወለደሽልን
ምክንያተ ድኂን ሆይ ድንግል ማርያም የአምላክ መገኛ
በአማላጅነትሽ በመታመን እንጮሃለን እኛ
ምሕረትን አድይን ኪዳነምሕረት የዓለም መዳኛ

ስለቸርነትሽ እመቤቴ ለእኔ እናቴ ነሽ
ስለ ንግሥትነትሽም እምቤቴ ነሽ
ዝናባት ሳያጠጡት አየራትም ሳያሳድጉት
ሰማያዊ እንጀራ የሰጠሽን ቤተልሔማዊት

ቃና ዘገሊላ በሠርግ ቤት በዚያ ተገኝተሽ ሳለሽ
ውኃውን ወደ ወይን በአንቺ ምልጃ እንዳስለወጥሽ
ዛሬም የእኔ ሕይወት ወይኑ አልቆ ባዶ ሆኗልና
አንቺ የአምላክ እናት ንጽሕት ቅድስት ርኅርኂተ ኅሊና
ሕይወቴን ቀድሰሽ እመቤቴ ሙይው በምስጋና

209. እሰይ ተከበረች

እሰይ ተከበረች በዛሬዋ እለት ድንግል ማርያም
የአምላክ እናት /፪/
የምሥራች እልል በሉ የአዳም ልጆች ሁሉ
የምሥራች እልል በሉ ክርስቲያኖች ሁሉ /፪/

210. የጽድቅ በር ነሽ

የሙሴ ጽላት
አክሊለ ሰማእታት ምእራገ ጸሎት
የጌታዬ እናት ንጹሕ አክሊላችን
ሐመልማለ ሲና እመቤታችን /፪/

እመቤታችን ለእኛ መርኩዝ ነሽ
‹‹ ከለላም ሆንሽ
‹‹ የእሳት ሙዳይ
‹‹ እሳት ታቀፍሽ
‹‹ በብርሃን ተከበሽ
‹‹ ወርቅ ለብሰሽ
‹‹ ከሴቶች ሁሉ
‹‹ አብ መረጠሽ

እመቤታችን ድንግል ሆይ ልጆችሽ
‹‹ ዘወትር ይጠሩሻል
‹‹ ስምሽን ለልጅ ልጅ
‹‹ ያሳስቡልሻል
‹‹ በተሰጠሽ ጸጋ
‹‹ በአማላጅነትሽ
‹‹ ምሕረትን አሰጪን
‹‹ ከመሐሪው ልጅሽ

እመቤታችን ያልታረሰች እርሻ
‹‹ ዘር ያልተዘራባት
‹‹ የሕይወትን ፍሬ
‹‹ ሰጠችን የእኛ እናት
‹‹ የተሰዋው መሲህ

‹‹ እናቱን ወደዳት
‹‹ በቀኙ ቆማለች
‹‹ ድንግል እመቤት ናት

እመቤታችን የእውነት ደመና
‹‹ ዝናብ የታየባት
‹‹ ወዳናለች ድንግል
‹‹ የታተመች ገነት
‹‹ ክብር ለሆነችው
‹‹ ኑ እንዘመርላት
‹‹ ደስ ይበልሽ እንበል
‹‹ ለብርሃን እናት

211. ድንግል እመቤቴ

ድንግል እመቤቴ የሕይወቴ ረዳት
የኑሮዬ ጣዕም ዋልታ መሠረት
እለምንሻለሁ /፪/ ፍጹም በረከት /፪/

ትጎትናሽ ሲታሰብ ድንግል እመቤቴ
በሰዎች ልቡና ድንግል እመቤቴ
ግርምትን ይፈጥራል
ልብ ይመስጥና
ጽዮን መጠጊያ ነሽ
የአብርሃም ድንኳን
የታጠረች ተክል
እመብዙኃን

ከሚካኤል ጋር ድንግል እመቤቴ
ፈጥነሽ ድረሺልኝ
ቅዱስ ገብርኤል ይምጣ
ክብርሽን ያብስረን
ከድንግል ጋር ሆነህ
ኡራኤል ፈጥነህ ና
ሩፋኤል፤ ራጉኤል

ንኡ በደመና
በደማችን ሰርጻኤል
ፍቅሯ የማርያም
ምስክር ነን እኛ
እስከ ዘለዓለም
በአባቶችሽ ፈንታ
ልጆች ስላለን
ስምሽን ለልጅ ልጅ
እንዘክራለን

212. ሠላም ለኪ እምነ ጽዮን

ማርያም ቅድስት የሕይወት ብርሃን
ሰላም ለኪ እምነ ጽዮን
ሰላም ልበልሽ ተንበርክኬ
በንጽሕናሽ ተማርኬ
መርከብ የኖኅ አዳራሽ
ሰላም ለኪ ልበልሽ

ድንግል የአብርሃም ድንኳን
ሰላም /፪/ ሐረገ ወይን
ያእቆብ ያየሽ መሰላል
የሰሎሞን ክብር አክሊል

ጽላተ ሙሴ የኦሪት
የአሮን በትር መድኃኒት
የኖኅ ርግብ የኢያቄም
የነቢያት ተስፋ የአዳም

እሳተ መለኮትን የያዝሽ
ልዑል አምላክን የወሰንሽ
ቤተ መቅደስ የልዑል
ሰላም ለኪ እም ወድንግል

213. የጌታዬ እናት ጸለየች

የጌታዬ እናት ጸለየች
ማርያምም እንዲህ እያለች /፪/

ነፍሴ ጌታዬን ታከብረዋለች
መንፈሴም በአምላኬ ሐሴት ታደርጋለች
የእኔን የባሪያውን ትኅትና
የእስራኤል አምላክ ተመልክቷልና /፪/

ትውልድ ሁሉ ብፅእት ይሉኛል
እርሱ ታላቅ ሥራ አድርጎልኛል
ስሙም ቅዱስ ነው ምሕረቱም
ለትውልድ ትውልድ ለዘለዓለም /፪/

ኃይልን አድርጓል ጌታ በክንዱ
ትእቢተኞች ተዋረዱ
ገዢዎች ከዙፋን ስለተጣሉ
ትሁታን ደግሞ ከፍ ከፍ አሉ /፪/

ባለጠጎችም ሲያጡ ሲራቡ
ድሆች በምሕረት ጥቂት ጠገቡ
ለአባቶቻችን እንደማለ

ምሕረቱን አስቦ እኛን ተቀበለ /፪/

214. እሴብሕ ጸጋኪ

እሴብሕ ጸጋኪ አምላክነ ዘወለደኪ /፪/
ንጉሥነ ዘወለድኪ
ውዳሴ ወግናይ አሥርቱ ቃላት
ቀድሞ ናት ድንግል ንጽሕት በእውነት
ገብርኤል በቃሉ እያጫወታት
ዘኮንኪ ይሏታል ጽርሐ ቅድስት
ናስተማስለኪ ተቅዋመ ማኅቶት
አንቺ እግዝእተ ኩሉ የሁሉ እመቤት
ናስተማስለኪ በእፀ ገነት
በትረ አሮን ጣትዋ የምትፈትልበት
ለኪ ይደሉ እያሉ መቅደስ አስገቧት
መላእክት ወረዱ ሊያመሰግንዋት
በመቅደስ እንድትኖር ስትሰጥ ብጽዓት
ዘካርያስ ነበር ሊቀ ካህናት
ወሬ ሆኖ ቀረ የምቀኞች አድማ
ሆናለች እሷማ የልዑል ከተማ

215. ታማልደናለች

ታማልደናለች /፬/ ማርያም /፪/ ቤዛዊተ ዓለም /፪/
ሚካኤል መልአከ ሊቀ መላእክት /፪/
ዘአውረድከ /፪/ መና ከደመና /፪/
ገብርኤል መልአክ አብሣሬ ትስብእት /፪/
ዘአብሠራ /፪/ ለማርያም ንጽሕት /፪/
ሩፋኤል መልአክ ሊቀመላእክት /፪/
ዘአብርሀ /፪/ ዓይኑ ለጦቢት /፪/
ኡራኤል መልአክ ለእዝራ ነቢይ /፪/
ዘአስተዮ /፪/ ጽዋአ ልቡና /፪/
ሰሎሞን ይቤላ /፬/
ርግብየ ሠናይትየ ሰሎሞን ይቤላ /፪/
ገብረ መንፈስ ቅዱስ /፬/
ሐዋርያ /፪/ ዘእስክንድርያ /፪/
ተክለሃይማኖት /፬/
ሐዋርያ /፪/ ዘኢትዮጵያ
ብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ
አእማደ /፪/ ቤተ ክርስቲያን /፪/

216. አብሠራ

አብሠራ ገብርኤል ሊቀ መላእክት /፪/
ኸኸ ወይቤላ /ፍ/ ትወልዲ ወልድ /፪/
ትርጉም ሊቀ መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ልጅ
ትወልጃለሽ ብሎ ለእመቤታችን አበሠራት

217. ወይቤላ

ወይቤላ ውእቱ መልአክ ሰላም ለኪ /፪/
ሰላመ ዚአየ የሀሉ ምስሌኪ /፪/
የሀሉ ምስሌ

218. በዝናበ ንጽሕኪ

በዝናበ ንጽሕኪ ሐረገወይን ፀገየ /፪/
ወሮማን /፪/ ወሮማን ሐዋዘ ፈረየ /፪/
እመቤቴ ማርያም ሆይ አንቺን የማይበት /፪/
ምን ዓይን አለኝ /ፍ/ ፍቅርሽ አይለየኝ /፪/
ለአዳም ተስፋ የሆንሽው ማርያም እመቤቴ /፪/
አማልጅን ቶሎ ብለሽ /፫/ ሳልጠፋብሽ ልጅሽ /፪/
የዳዊት መሰንቆ ነሽ የኢያሱ ሐውልት
በምን እንመስልሽ /፫/ ወደርም የለሽ /፪/
እመቤቴ ጥላዬ ሁኚልኝ ከለላዬ /፪/
ያለአንቺ ማን አለኝ /፫/ አለሁሽ በይኝ /፪/
አዳምና ሔዋን ከገነት ተሰደው /፪/
ማርያም አንቺ ነሽ /፫/ የመዳን ተስፋቸው
የእግዚአብሔር አብ ሙሽራ ወልድን የወለድሽ
የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ንጽሕት አዳራሽ
የሰሎሞን አክሊል የታጠረች ተክል
የአሮን ካህን ልብስ /፫/ የወርቅ ጸናጽል

219. እንደ ኤልሳቤጥ

እንደ ኤልሳቤጥ ላመስግንሽ
ፊትሽ ወድቄ ልሳለምሽ
የጌታዬ እናት የእኛ እመቤት
አዛኝ ነሽ ከልብ ፍጹም የዋህት

ርኅራኄሽ ያስደስተኛል
ስለ ኃጢአቴ ምልጃሽ ይቀድማል
የሰላምታሽ ድምፅ ደስ ያሰኘኛል
ከትካዜዬም ያሳርፈኛል

ድምጽሽ ሲሰማኝ ልቤ ይረካል
ሐዘኔ ቀርቶ ፊቴ ይፈካል
በእናትነት አንቺን ለሰጠን
ቸሩ አምላካችን ይክበር ይመስገን

የሁሉ እቤት የሁሉ አጽናኝ
የዓለም መድኃኒት ከአምላክ አገናኝ
ዛሬም በልቤ ደስታ ጨምረሽ
እንደ ኤልሳቤጥ ሰላም ልበልሽ

ከሴቶች መካከል መርጦ ቀድሶሻል

ትውልድ ሁሉ ብጽእት ይሉሻል
በልዩ ውዳሴ ያመሰግኑሻል
ድንግል ንግሥታችን በቀኝ ቆመሻል

የሰላምታሽ ድምጽ ልቤ ሲሰማ
ነፍሴን ደስ አላት ቀለላት ሽክሚ
ድንግል ለክብርሽ ስንበረከክ
እጅሽ ይዘርጋ ለመባረክ

220. በኃጢአት ያደፈ

በኃጢአት ያደፈ ሆኗል ሰውነቴ
አብቂኝ ለንስሓ አማልጅኝ እናቴ

በኃጢአት ያደፈ በኃጢአት ብዛት
ልቤ ሲታወክ በኃጢአት ያደፈ
ተብትቦ ሳይጥለኝ በኃጢአት ያደፈ
የኃጢአቴ ድር በኃጢአት ያደፈ
በጣጥሰሽ ጣይልኝ በኃጢአት ያደፈ
የኃጢአቴን መጥመድ በኃጢአት ያደፈ
ድንግል ሆይ አማልጅኝ በኃጢአት ያደፈ
አርቂኝ ከዚህ ጉድ በኃጢአት ያደፈ

በኃጢአት ያደፈ መቆም አቅቶናል
በደሌ በዝቶብኝ በኃጢአት ያደፈ
እማፀንሻለሁ በኃጢአት ያደፈ
ልመናዬን ስሚኝ በኃጢአት ያደፈ
ኃጢአቴን መሸከም በኃጢአት ያደፈ
እኔ አልቻልኩምና በኃጢአት ያደፈ
እናቴ ሆይ ስሚኝ በኃጢአት ያደፈ
ድንግል በጽሞና በኃጢአት ያደፈ

221. ያመሰገናት

ያመሰገናት /፫/ እዝራ በመሰንቆ
እናትነቷ ንጽሕናዋን አውቆ
ያመሰገናት /፫/ ዳዊት በመዝሙር
አምባ መጠጊያችን የአምላክ ማኅደር
ያመሰገናት /፫/ ኤፍሬም በውዳሴው
ለምኚልን አላት ፍቀሯ ስለገባው
ያመሰገናት /፫/ አባ ሕርያቆስ
ምሳሌ አጣላት በመንፈስ ሲቀድስ
ያመሰገናት /፫/ አባ ጊዮርጊስ
እናትነትዋን ፍቅሯን ሊያስታውስ
ያመሰገኗት /፫/ ካህናት በክበሮ
ልብን በሚመስጥ በሐዘን እርሮ
እናመሰግናት /፫/ ሆነን በአንድነት
እመቤታችንን እመምሕረት
አማላጃቸንን እመምሕረት

222. ኦ ድንግል

ኦ ድንግል አምላል ወትንቢት /፪/ ለነቢያት /፪/
ሞገሶሙ ለሐዋርያት /፬/
ትርጉም- ድንግል ሆይ የሐዋርያት ሞገስ
የነቢያት ትንቢት አንቺ ነሽ

223. በመኑ በአምሳለ መኑ

በመኑ በአምሳለ መኑ ናስተማስለኪ /፪/
እመቤቴ የእኛ አማላጅ አዛኝቷ ኦ ድንግል
ምልእተ ውዳሴ /፪/
ትርጉም:- በምን አረ በምን በምን እንመስልሻለን
እመቤቴ የእኛ አማላጅ አዛኚቷ ኦ ድንግል ጸጋን
የተመላሽ::

224. የኖኅ ቃል ኪዳኑ

የኖኅ ቃል ኪዳኑ ምልክት ዓርማው
የመዳኑ ምሥጢር የሰላም ተስፋው
እመቤቴ አንቺ ነሽ ቀስተ ደመናው /፪/

አንቺ የአሮን በትር ሳይተክላት ያደገች
የማክሰኞ እርሻ ያለዘር ያፈራች
የሲና ሐመልማል የተዋሕዶ ምሥጢር
ክብርት እመቤቴ ሀገረ እግዚአብሔር /፪/

የዳዊት መሰንቆ ያሬድ ጽናጽል
የደካሞች ምርኩዝ የሰሎምን አክሊል
ሰላሜ ተስፋዬ የሐዘኔ ደራሽ
የጽዮን ተራራ መሸሸጊዬ ነሽ/ /፪/

የኤልሳእ ማሠሮ ጨው የተገኘብሽ
የሕዝቅኤል ራእይ ንጽሕት አዳራሽ
አንቺ የአዳም ተስፋ የመዳኔ ብስራት
አንቀጸ ብርሃን የአማኑኤል እናት /፪/

225. ማርያም ፊደል

ማርያም ፊደል የሁሉ መማሪያ /፪/
በንጽሕና በንጽሕና ተጽፋለችና /፪/

226. አስታርቂኝ

አስታርቂኝ ድንግል ማርያም /፪/
ከልጅሽ /፫/ ከመድኃኔዓለም

አስታርቂኝ ኃጢአትን ሰርቼ
አስታርቂኝ ጫካ ውስጥ ቆሜአለው

አስታርቂኝ ሥራዬ አሳፍሮኝ
አስታርቂኝ ዘወትር አነባለው
አስታርቂኝ ልጄ አዳም ብሎ
አስታርቂኝ አምላኬ ሲጠራ
አስታርቂኝ እነሆኝ ለማለት
አስታርቂኝ አንደበቴ ፈራ

አስታርቂኝ ሀብትን ተካፍዬ
አስታርቂኝ ከገዛ አባቴ
አስታርቂኝ ከቤቴ ኮበለልኩ
አስታርቂኝ ይሻለኛል ብዬ
አስታርቂኝ ገፍቼ ወጥቼ
አስታርቂኝ የቤቴን ገበታ
አስታርቂኝ ልበላ ተመኘሁ
አስታርቂኝ የእንስሳት ገፈራ

አስታርቂኝ ወደ አባቴ ልሂድ
አስታርቂኝ አሁን ተነሥቼ
አስታርቂኝ ይቅርታ ልጠይቅ
አስታርቂኝ እግሩ ስር ወድቄ
አስታርቂኝ ልጅነቴ ቀርቶ
አስታርቂኝ አድርገኝ ባርያህ
አስታርቂኝ ከሞያተኞችህ
አስታርቂኝ እንደ አንዱ ቆጥረህ

አስታርቂኝ ገና ሩቅ ሳለው
አስታርቂኝ አባቴ አይቶኝ
አስታርቂኝ ወደኔ ሮጦ
አስታርቂኝ አቅፎ ነው የሳመኝ
አስታርቂኝ ጠፍቶ የነበረው
አስታርቂኝ ተገኝልኝ አለ
አስታርቂኝ ሞቶ የነበረው
አስታርቂኝ ደግሞ ሕያው ሆነ

227. ደስ ይበለን

ደስ ይበለን በጣም ደስ ይበለን /፪/
በረከቱን ለኛ ስለሰጠን

በጨለማ ስኖር ደስ ይበለን
በኃጢአት ተከበን ››
የሕይወትን ብርሃን ››
ጽድቁን አበራልን ››
ወደ ምሥራቅ እንይ ››
ፀሐይ ወዳለበት ››
ጨለማው ልባችን ››
ጎህ እንዲገባበት ››

የፀሐይ እናቱ ደስ ይበለን
ማርያም እመቤቴ ››
እለምንሻለሁ ››
እስከ እለተሞቴ ››
የልቤ ማረፊያ ››
የዘለዓለም ቤቴ ››
አንቺ ነሽ ተስፋዬ ››
እፀ መድኃኒቴ ››

የግሽኗ ንግሥት ደስ ይበለን
የአምላክ እናት ››
ሆና ተገኝታለች ››
ለሚመኩባት ››
በልቼ ጠጥቼ ››
የምረካብሽ ››
ጎጆ ማረፊያ ››
ማርያም አንቺ ነሽ ››

ፀዓዳ እመቤቴ ደስ ይበልን
ሐመልማለ ሲና ››
የሕዝቅኤል ደጃፍ ››
የሙሴ ደመና ››
የተዋበች እንቁ ››
የደጎች አዝመራ ››
በማኅፀንሽ ፍሬ ››
ሕይወታችን በራ ››

228. በሐዘኔ

በሐዘኔ ደራሽ ነሽ በጭነቀቴ
በችግሬ ደራሽ ነሽ
የአምላኬ እናት የጌታዬ እናት
ድንግል እመቤቴ ወላዲተ ቃል /፪/

መልካሚቱ ርግብ ድንግል እመቤቴ
ማርያም እናቴ ነሽ ድንግል እመቤቴ
ከፍጥረታት ሁሉ ድንግል እመቤቴ
ገናና ነው ክብርሽ ድንግል እመቤቴ
የሐዘኔ መጽናኛ ድንግል እመቤቴ
እንባን አባሽ ነሽ ድንግል እመቤቴ

ዋሻ መጠለያ ድንግል እመቤቴ
ዘለዓለም ቤቴ ድንግል እመቤቴ

መንገድ ስሄድ ስንቁ ድንግል እመቤቴ
መጠጤ ነሽ ምግቤ ድንግል እመቤቴ
እምአምላክ ስጠራሽ ድንግል እመቤቴ
ይጠፋል ረሀቤ ድንግል እመቤቴ

የእናትነትሽ ድንግል እመቤቴ
ፍቅርሽን አየሁት ድንግል እመቤቴ
ጎጆዬን ስትሞይው ድንግል እመቤቴ
ባዶ የሆነውን ድንግል እመቤቴ
አንቺ እያለሽልኝ ድንግል እመቤቴ
ምን እሆናለሁኝ ድንግል እመቤቴ

229. የገነት ደጃፍ

የገነት ደጃፍ ማርያም ነሽ
የወርቅ መሰላል ድንግል ነሽ
የአምላክ እናት ማርያም ነሽ
ክብርና ውዳሴ ለአንቺ ይገባሻል
አምላክ አንቺን ወዶ ባርኮ ቀድሶሻል

የተዘጋች በር የታተመች ገነት
ድንግል እና እናት ሰማያዊት ንግሥት
የመለኮት እናት እሳትን ያዘለች
የአደራ እናታችን እመቤታችን ናች

የሰማይ መላእክት እያሸበሸቡ
ሰላም ለኪ ብለው ድንግልን ከበቡ
እኛም ክቡር ወዳሴ ዝማሬ ምስጋና
ለእርሷ እናቀርባለን ይገባታልና

እኔስ አነሳለሁ ስሟን ለዘለዓለም
ከሴቶች መካከል ከቶ እንደርሷ የለም
በድንግል ውዳሴ ነፍሴ ትረካለች
ምስጋና ሲጀመር ድንግል ትመጣለች

230. ማርያም እንወድሻለን

ማርያም እንወድሻለን /፪/
ስለወለድሽ የሕይወት ምግብን /፪/
ማርያም እንወድሻለን

ድክመቴን አትይ ማርያም
በኃጢአት መውደቄን ማርያም
ተስፋዬ አንቺ ነሽ ማርያም
እስከ እለተ ሞቴ ማርያም

ላልጠላሽ ምያለሁ ማርያም
ከስርሽ ላልጠፋ ማርያም
ገጸ በረከቴ ማርያም
የሕይወቴ ዋስትና ማርያም

የምእመናን ውበት ማርያም
ዘወድ አክሊላችው ማርያም
ድንግል አንቺ እኮ ነሽ ማርያም
የመንገድ ስንቃቸው ማርያም

ምሥክር ነኝ ለአንቺ ማርያም

አንደ ነቢያቱ ማርያም

ስጦታ መሆንሽን ማርያም

ለአዳም ልጆች ሁሉ ማርያም

ሞገስና ጸጋ ማርያም
በጌታ ፊት ያለሽ ማርያም
ከሰይጣን መሸሻ ማርያም
ዋስ ጠበቃቸን ነሽ ማርያም

እንዴት ነበር ያኔ ማርያም
ጌታን ስትወልጂው ማርያም
የእረኞቹ ደስታ ማርያም
የመላእክት ዝማሬ ማርያም

231. በሐዘኔ በጭንቀቴ

በሐዘኔ በጭንቀቴ መጽናኛዬ ነሽ ረዳቴ
እመአምላክ አደራ ድንግል እመቤቴ /፪/

ለዓለም ተዘርግቶ እጄ ባዶ ሆናል
የራሴ ላይ አክሊል ተሸቀንጥሮ ወድቋል
ከኤልዛቤል ሸሽቼ መጣሁኝ ወደ አንቺ
የጎሰቆልኩትን እኔን ተመልከቺ

የእግሬ መሰናከል ለዓለም ደስታ ነው
ተስፋ ቢስ መሆኔ ለጠላቴ ድል ነው
የደስታ መመንጫ የኤሳቤጥ ዘመድ
አንዳልሠናከል ምሪኝ በመንገድ

ምድር ትለኛለች ተስፋ ቢስ ብቸኛ
ሳለቅስ ሳነባ አይታኛለችና
ከቤተ መቅደሱ ለእኔ ዘመድ አለኝ
በሐዘኔ ሰዓት አይዞህ የምትለኝ

ከአመድ የወደቀ ትንሽ ገንዘብ አለሽ
ልብሽ ራርቶልኝ ፈልጊኝ አጥብቀሽ

እምነቴ እንዳይደክም እንዳልጠፋ ልጅሽ
አድጌአለሁና ከደጅ ሰላምሽ

232. ማርያም ኩኒ

ማርያም ኩኒ ለሕይወትየ ጸወኖ /፪/
እስመ ተማኅጸንኩ አንሰ ተማኅጸንኩ /፪/
በኪዳንኪ /፪/ ተማኅጸንኩ
ማርያም ሁኚ ለሕይወቴ አምባ በምልጃሽ
እማጸንሻለሁ ተማጽኜሻለሁ /፪/
በቃል ኪዳንሽ /፪/ በሚያድነው ቃል ኪዳንሽ
አምላክ ስለሰጠሽ የምሕረት ቃል ኪዳን
ጻድቃንን ለማትጋት ኃጥአን ለማዳን
የምሕረትን ምጽዋት እለምንሻለሁ
ይቅርታን ለማግኘት እጀን ዘርግቻለሁ
የሊቀ ካህናቱ የክርስቶስ እናት
ለምኚልን ቅድስት ለኃጢአቴ ሥርየት
በሥጋም በነፍስም ይቅር አስብይኝ
ከበደሌ እዳ ንጹሕ አድርጊኝ
ማርያም በስምሽ በቃል ኪዳንሽ
አምኜ ቆሜአለሁኝ ኃጥእ ባርያሽ
ንስሓ ሣልገባ እንዳልሞት አደራሽ
ለዚህ እድል አብቂኝ ከልጅሽ አማልደሽ
በቃል ኪዳንሽ አምኜ ስጠራሽ
ድንግል አትለይኝ በረድኤትሽ
ፍቅርሽን በልቤ ጣእምሽ በአንደበቴ
እንዲያድር አድርጊ ፅዩን እመቤቴ

233. ሰላም ለኪ ማርያም እመአምላክ

ሰላም ለኪ ማርያም እመአምላክ /፪/
ወልድኪ ይቤውአኪ ውስተ ሕይወት
ወመንግሥተ ክብር /፬/

234. እስኪ ላግንሽ

እስኪ ላግንሽ እመቤቴ ማርያም
እስቲ ላድንቅሽ ንጽሕት ቅድስት ማርያም
መመኪያ ርስቴ ነሽና እናቴ /፪/
አዛኝት ማርያም ክብርሽ ልዩ ነው
ለተቸገረ ስምሽ ስንቅ ነው
መደኃኒቴ ነሽ እጠራሻለው
ከእግርሽ ወድቄ እሰግድልሻለው
የኤዶም ወንዝ የገነት ፈላሽ
ምክንያተ ድኅነት ሰው የዳነብሽ
ንጹሑን በግ ጌታን ያስገኘሽ
አብርሃም ያየሽ እፀ ሣቤቅ ነሽ
እያሸበሸብኩ ልዘምርልሽ
ልዝረፍ ቅኔውን ነይ ላወድስሽ
የቅዱስ ጊዮርጊስ ምስጋና አንቺ ነሽ
ዳዊት በመዝሙር የዘመረልሽ
አእላፍ መላእክት ዙሪያሽን ከበው
ሲያመሰግኑሽ በሰማይ ያየው
እፁብ ድንቅ ነው ግሩም ተአምር
ዘርዝሬ አልጨርስ ያንቺን ክብር

235. ናርዶስ ቀጺመታት

ናርዶስ ቀጺመታት አሉ በልብሶችሽ መሀል /፪/
የገነት ሽቱ ነሽ /፪/ ማርያም ድንግል
የከበርሽ ነሽ አንቺ ከፍጥረት
መዓዛሽን ወድጿል ጌታ ፀባኦት
ጠላት እንዳይከሠኝ ከጎኔ ሁኝና
ነውሬን ሸፍኝው እናቴ ነሽና
ገሊላዊት ድንግል የገነት ፈሣሽ
የቆሠለችውን ሕይወቴን ፈውሽ
ሰአሊ ለነ ቅድስት በቀን በሌሊት
ለአፌ ጥበብ ነሽ ቅኔ ማኅሌት
ሁልጊዜ ድኅነትን የምንለምንሽ
ለእግዚአብሔር ፊት ሞገስን ያገኘሽ
ክርስቲያኖች ሁሉ ተስፋ የሚያደርጉሽ
ለዓለም የሚበቃ ምልጃ ቃልኪዳንሽ

236. ልዑል ሠምራ

ልዑል ሠምራ ዳዊት ዘመራ /፪/
በቤተመቅደስ ተወክፋዋ /፪/
ልዑል መረጣት ዳዊት ዘመረላት /፪/
በቤተመቅደስ ተቀበሏት /፬/

237. እንዘ ዘልፈ

እንዘ ዘልፈ ትነበር ውስተ ቤተ እግዚአብሔር /፪/
አስተርዓየ መልአከ ዘኢኮነ /፪/ ከመቀዲሙ ኢኮነ /፪/
ትርጉም፡- ዘወትር በቤተ እግዚአብሔር
እየተቀመጠች ሳለ እንደ ፊተኛው ያልሆነ መልአክ
ታያት

238. መሶበ ወርቅ

መሶበ ወርቅ ዘመና እግዝእትና ማርያም ቅድስት /፪/
ቅድስተ ቅዱሳን ይብልዋ ካህናት /፬/

ትርጉም፡- መና ያለባት የወርቅ መሶብ የሆነችውን
እመቤታችንን ማርያምን ካህናት ከቅዱሳን ይልቅ
ቅድስት ነሽ እያሉ ያመሠግኗታል፡፡

239. እመቤቴ ማርያም

እመቤቴ ማርያም ሆይ እለምንሻለሁ
ከልጅሽ አማልጅን /ፒ/ ከፊትሽ ቆሜአለሁ
እባክሽ አማልጅኝ የአምላክ እናት ድንግል
ምን ጊዜም አይጠፋም /ፒ/ ከአዳም ልጅ በደል
በደላች ብዙ ነው ልመናችን ትንሽ
ምሕረትን ጠይቂልን /ፒ/ ድንግል ከልጅሽ

240. የሰማይ የምድር

የሰማይ የምድር የአርያም ንግሥት
አንቺ ነሽ እመቤት የአምላክ እናት
ኸኸ ድንግል አማልጅኝ
ኸኸ ቅድስት ተራጂን
የሔዋን ተስፋዋ የአዳም ዘር ሕይወት

የድኅነቱ ምክንያት አንቺ ነሽ ንጽሕት

የኦሪት መጽናኛ የሐዲስ ኪዳን በር

የወንጌል መሠረት የአምላክ ማኅደር

የአብርሃም ድንኳን የምሥጢር ዋሻው
እናትና ድንግል ሁለቱን ሆንሽው
የኤፍሬም ውዳሴ የያሬድ ውብ ዜማ
የማትጠልቂ ፀሐይ የሃይማኖት ሻማ

241. ውትቀውም ንግሥት

ውትቀውም ንግሥት /፪/ በየማንከ /፪/
ኸኸ በአልበስ ወርቅ /ፒ/ ዑጽፍት በአልባሰ ወርቅ
/፪/
ትርጉም፡- ንግሥቲቱ የወርቅ ልብስ ተጎናጽፋ
በቀኝህ ትቆማለች

242. ሰአሊ ለነ ማርያም

ስአሊ ለነ ማርያም ሰአሊለነ /፪/
አክሊለ ንጹሐን /፪/ ሰአሊለነ /፬/
ለምኝልን ማርያም ለምኝልን /፪/
የንጹሐን አክሊል /፪/ ለምኝልን /፬/

243. ሰላም ሰላም

ሰላም ሰላም /፪/ ማርያም ድንግል
ልመናሽ ለሚያምኑት ድኅነት ያሰጣል /፪/
ደቀ መዛሙርቱ በሐሳብ ሲዋኙ
በጽኑ ጸማቸው ምልክት አገኙ
ለእኛ ወገኖችሽ ኃጢአት ላደከመን
ከልጅሽ ይቅርታን ድንግል ለምኝልን
በሐና በኢያቄም እመቤታችን
በዚህች ቀን ባርኪልን ማኅበራችንን

መዝሙር በእንተ ቅድስት አርሴማ ሰማዕት

244. ጽኑ ሰማዕት

ጽኑ ሰማዕት የእምነት አርበኛ
አርሴማ ነይ ነይ ወደኛ
ነይ ነይ ቴዎድሮስ አትናስያ
›› በስለት ያገኙሽ
›› ብሉይን ከሐዲስ
›› ጠንቅቀሽ የተማርሽ
›› በፍጹም ትሕትና
›› በጸሎት የተጋሽ
›› አርሴማ ልዩ ነሽ
›› አምላክ የመረጠሽ
ነይ ነይ ውበትም ሐሰት ነው
›› ደም ግባትም ከንቱ
›› ንብረት ትዳር ሁሉ
›› ሐላፊ ውዕቱ
›› ንግስት መባልን
›› በፍጹም ሳትሻ
›› ዓለምን በመናቅ
›› ገባች ወደ ዋሻ
ነይ ነይ አረመኔው ንጉሥ
›› ቢያሰቃይሽ
›› ሕይወቴ ክርስቶስ
›› ነው ብለሽ ሰበክሽ
›› አንገትሽን ለሰይፍ
›› አሳልፈሽ ሰጠሽ
›› ክብርሽም ተገልጾ
›› ለዓለም አበራሽ

ነይ ነይ አርዕያ እንድትሆኝን
ነይ ነይ ለኛ ለሁላችን
›› ፈጽመሽ አሳየሽ
›› ታላቅ ተጋድሎሽን
›› ይህን ዓለም ድል መንሳት
›› አቅቶናልና
›› አርሴማ አትለዪን
›› በእምነት እንድንፀና

245. አርሴማ ቅድስት

አርሴማ ቅድስት /፫/
ኧኸ ሰማእት /፫/ አርሴማ ቅድስት

246. አርሴማ

አርሴማ አርሴማ ቅድስት ሰማእት /፪/
ምሕረት ለምኝልኝ ከዓለም መድኃኒት
የዓለም አሸንክታብ ሳይስብሽ ጽድቅን
የመረጥሽ የጌታ አገልጋይ አርሴማ
ቅድስት አንቺ ነሽ
መስቀል ተመርኩዘሽ በዓላማሽ የጸናሽ
አርሴማ ቅድስት
ተቀዳጅተሽ አክሊል ሙሽራ ሆነሽ ሰማእት
የዚህ ዓለም ደስታ ርስት ጉልት ንብረት
ሣይስብሽ
ዘላለማዊ ሕይወት ክብር ጸጋ ስለመረጥሽ
የዓለም መድኅን አማኑኤል በእውነት
አከበረሽ
በእግዚአብሔር ዘንድ በፍቅር /፪/ አድገሽ
የሰማእታት አክሊል በረከት ሆነሽ ተሸላሚ

247. ሰማዕት

ሰማዕት /፫/

አርሴማ ቅድስት /፪/

የምሥጋና ዝማሬዎች

248. ተነሱ እንዘምር

ተነሡ እንዘምር /፪/

በአንድት ሆነን በእልልታ /፪/ ኧኸ /፫/

ምስጋና በሰማይ ምስጋና በምድር /፪/

ለኃያሉ ጌታ ለልዑል እግዚአብሔር

አሥፈሪ ነው ያልነው ብዙ ነገር ነበር

ሁሉንም አለፍነው እግዚአብሔር ይመስገን

ሕዝቦች ደስ ይበለን ሕይወታችን ድኗል

ሰይጣን ጠላታችን አፍሮ ተመልሷል

ሰማይ ዙፋንህ ነው ምድር መረገጫህ

በዚህም በዚያም ቢሆን በሁሉም አንተው ነህ

በሄድንበት ሁሉ ትከተለናለህ

ከፅንቅፋት ከድንጋይ ትሠውረናለህ

ስለመልካም ሥራህ አለብን ውለታ

ለማይነገረው የማዳን ስጦታ

ተመስገን እንበልህ ከጧት እስከ ማታ

ሌላ ምንም የለም የምንከፍልህ ጌታ

አምላክ ሆይ ስምህን ብንጠራው ብንጠራው

አልጠገብ አለን ምንኛ ጣፋጭ ነው

አቤት ያንተ ሥራ ያንተ ልግስና

ቢነገር አያልቅም ስምህ ነው ገናና

መልስ እንድናዘጋጅ ቶሎ ሳንጠራ

ሳለ አንደበታችን ምስጋናህን ያውራ

ምስጋና በሰማይ ምስጋና በምድር

እስከ ዘለዓለም ለስምህ እንዘምር

249. እልል ደስ ይበለን

እልል እልል ደስ ይበለን ልመናችንን

አምላክ ሰማን /፪/

እናመስግነው /፬/ ይገባዋል ሁሉን ፈፃሚ

ነው ኧኸ /፫/

250. ንጉሥ ዉእቱ

ንጉሥ ውእቱ ንጉሠ ሠላም /፬/

አምላክነ /፪/ መድኃኔዓለም /፪/

ንግሥት ይእቲ ንግሥተ ሰላም /፬/

ማርያም /፪/ ኪዳነ ምሕረት /፪/

ትርጉም፡- አምላካችን መድኃኒዓለም

የእውነትና የሰላም ንጉሥ ነው የምህረት

ቃል ኪዳን ድንግል ማርያም የሰላም

ንግሥት ናት

251. አማን በአማን

አማን በአማን አማን በአማን

አማኑኤል ተመስገን

ለዚህ ፍቅርህ ምን ልክፈልህ

ድብቁን ኃጢያት አንተ ብትገልጠዉ
ይቅር ብለኸኝ ባትሸፋፍነዉ
እንደ ሰዉ በቀል ቢኖርህ ጌታ
የእኔስ ኃጢያቴ የለዉም ቦታ

በየደቂቃዉ ኃጢያት ስሰራ

ስሰርቅ ስበድል አንተን ሳልፈራ

አንተ ግን ፊትህ ምንም ቢቀየም

በቁጣህ በትር አልገረፍከኝም

ምሕረትህን ልከህ አድነኝ ዛሬ
ታክቶኛልና በሓጢያት መኖሬ
ዓለም በኃጢያት እየሳበችኝ
በፍቅርህ ደስታ መኖር አቃተኝ

የኃጢያት ኑሮ ጣፋጭ ቢመስልም

ዉጤቱ መሮ ፍፁም አይጥምም

እንደ በደሌ ስላልከፈልከኝ

ተመስገን እንጂ ሌላ ምን አለኝ

252. እምኹሉ ይኄይስ

እምኹሉ ይኄይስ በሥላሴከ ተአምኖ /፪/
በወላዲትከ /፪/ ወበ ወላዲትከ ተማኅፀኖ /፪/
ከሁሉም /፪/ ሥላሴን ነው ማመን ማመስገን /፪/
ወልድን በወለደች /፪/ ድንግል አማላጃችን በእርስዋ
እንማፀን /፪/

253. ታቦተ ሕጉ

ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር በካህናት ህፅርት
ወበመንፈስ ቅዱስ ክልል /፪/
ንጉሥኪ ጽዮን ኢይትመዋዕ ለፀር ወኢየኃድጋ
ለሀገር /፪/
የሕግ ጽላቱ ለእግዚአብሔር በካህናት የታጠረች
በመንፈስ ቅዱስ የተከለለች /፪/
ንጉሠሽ ጽዮን አይሸነፍም ለጠላት ሀገሪቱንም
አይተዋትም /፪/
ትርጉም፡- 1. ሰሙ፡- ለጽዮን ለእሥራኤል ዘሥጋ
ወርቁ፡- ጽዮን ቤተክርስቲያን ንጉሠሽ ክርስቶስ
ስትፈተኚ ቢያይም መንግስት ሰማያትን ከመስጠት
አይተዉም
2. አማናዊት ጽዮን ማኅደረ መለኮት ድንግል
ማርያም ናት

254. ድዉይ ነን አንተ አድነን

<u>ድዉይ ነን አንተ አድነን</u>
<u>መጻጉን የፈወስክ በልዩ ሥልጣንህ</u> /፪/
<u>እኛም ተይዘናል በነፍስ በሽታ</u>
<u>አድነን የሰራዊት ጌታ</u> /፪/

255. ኩሉ ይሰግድ

ኩሉ ይሰግድ ለሥላሴ /፪/ ኩሉ ይሰግድ /፪/
ወይትቀነይ ኩሉ ለመንግሥተ ሥላሴ ለሥላሴ ኩሉ
ይሰግድ /፬/
ትርጉም፡- ፍጥረት ሁሉ ለሥላሴ ይሰግዳል ለሥላሴ
መንግሥት ፍጥረት ሁሉ ይገዛል።

256. ሰላም ዘአብ

ሃሌሉያ /፪/ ሰላም ዘአብ ወፍቅር ዘወልድ ሃይማኖት
ዘመንፈስ ቅዱስ /፪/
ድኅድር ማዕከሌክሙ አምላከ ሰላም ሰላም /፪/ የሀሉ
ምስሌክሙ
ሃሌ ሉያ /፪/ የአብ ሰላም የወልድ ፍቅር ሃይማኖት
የመንፈስ ቅዱስ
ይደር በመካከላችሁ የሰላሙ አምላክ ሰላም /፪/
ከእናንተ ጋር ይሁን /፪/

257. ስብሐት ለአብ

ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ
ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ
ለአብና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስም

ምስጋና ከማቅረብ ከቶ አንወሰንም /፪/
ዛሬም ወደ ፊትም ደግሞም ለዘለዓለም
ከዚህ ከማራኪው ከአስጨናቂው ዓለም
የጠራ ይድናል የፈጣሪውን ስም
በእውነት ያለ ሀሰት ያለ ጥርጥር
ከቶ መድኃኒቱን የሚጠላ የለም
ኑሮአችን እንዲያምር አንድነታችንም /፪/
ሊኖረን ይገባል ፍቅርና ሰላም
ያልከውን አስበህ እናንተ ሁላችሁ
ሁለት ሦስት ሆናችሁ በስሜ ካላችሁ /፪/
እኔም እገኛለሁ በመካከላችሁ
አቤቱ አምላክ ሆይ እንለምንሃለን
እንድትገኝልን በመካከላችን /፪/
ይኸው ተገኝተናል ሁለት ሦስት ሆነን

258. የቅዱሳን አበዉ /ተዋሕዶ/

የቅዱሳን አበው አሠረ ፍኖት
የጽድቅ አክሊላቸው የሰማዕታት
ተዋሕዶ የቀናች ሃይማኖት
አንቺ ነሽ የነበርሽ ከጥንት
ሚጠት የሌለብሽ ውላጤ ጎድረት
ትድምርት የማትዪ ቱሳኔ ፍልጠት
ተዋሕዶ የቁርሎስ ትምህርት
በእውነት ንጽሕት ሃይማኖት
ከተራራ ጫፍ ላይ የተሠራች መንደር
እንዴት ይቻላታል ከሠው ልትሠወር
ተዋሕዶ ከፍ ከፍ ያልሽ ነሽ
በእውነት አቻ የሌለሽ
ወልደ አብ ወልደ ማርያም ኢየሱስ ክርስቶስ
ብለሽ አስተማሪ ቀጥተኛ መንገድ
ተዋሕዶ እውነተኛ ሃይማኖት
በእውነት መንገድ የድኅነት

259. በማስተዋል እንዘምር

እግዚአብሔር ለምድር ሁሉ ንጉሥ ነውና
በማስተዋል እንዘምር እናቅርብለት ምስጋና /፪/
ቅዱስ ዳዊት በተመስጦ ሲዘምር
በሳኦል ላይ ዘወትር የሚያድር
ርኩስ መንፈስ ይለቀው ነበር
ቅዱስ ጳውሎስ በአደባባይ መሠከረ
በእስር ቤትም ሆኖ በማስተዋል ዘመረ
ከልብ በማመስገኑም የወኅኒው በር ተሰበረ
አስተውሎ የሚዘምር ቅዱስ ያሬድን አንዘንጋ
አልታወቀውም ደሙ ሲፈስ በጦር እግሩ ሲወጋ
በተመስጦ ደርሷልና ከአልፋና ኦሜጋ
ከፈጣሪ ዘንድ እንዲደርስ ጸሎታችን
በማስተዋል እናመስግን የእውነት ይሁን ዝማሬአችን
በማስተዋል እንዘምር ከልብ ይሁን ምስጋናችን

260. ይትባረክ

ይትባረክ እግዚአብሔር አምላክ እሥራኤል
ዘገብረ ዐቢየ ወመንክረ ባሕቲቱ
ወይትባረክ ስመ ስብሐቲሁ ቅዱስ
ወይምላዕ ስብሐቲሁ ኵሉ ምድረ ለይኩን ለይኩን
ትርጉም፡- የእሥራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ
ታላቅ ድንቅ ሥራ ብቻውን የሠራ ቅዱስ ስሙ
ይባረክ ምስጋናው ምድርን ሁሉ ይምላ ላይ ይሁን
ይሁን

261. የእዉነት ብርሃን

ብርሃን የእውነት ብርሃን ጨለማን ያጠፋ
ሞተ ነፍስን የሻረ ክርስቶስ የዓለም ተስፋ
ስለ ሰው ፍቅር ስለ ሰው ልጅ ክብር
ሥጋን ለብሶ ሰው ሆነ ከአዳም ልጅ ዘር
ምን ዕፁብ ድንቅ ነው ላሰበው
ምን ግሩም ድንቅ ነው የፈጣሪ ሥራው
እርሱ አምላክ ሲሆን የዓለም መድኅን

ተቀብሏልና ፍዳና ሞትን ዓለምን ሁሉ ለማዳን

262. እንኳን ደስ አላችሁ

እንኳን ደስ ያላችሁ /፮/
መልእክት ዮሐንስ ሀ ሁ ብላችሁ
ፊደል ቆጥራችሁ ከእነ የኔታ ጠዋትና ማታ
ተመላልሳችሁ ለዚህ በቃችሁ
የአምላክ ቸርነት ረቂቅነት
ይህ ነው ችሮታው ከህፃንነት እስከ አዋቂነት
ዓመታት ቆጥሮ ለዲፕሎም /ዲግሪ/መብቃት
የተዋሕዶ ልጆች እናንተ ሁላችሁ
የዕውቀት ካባ ጃኖ ለብሳችሁ ደስ ማለታችሁ
አደራ እንዳትረሷት ቤተ ክርስቲያንን
አንዲት ተዋሕዶ አደራችሁን

263. አንደበቴም ያውጣ

አንደበቴም ያውጣ የምስጋና ቅኔ
የአምላኬን ማዳን አይቻለሁ በዓይኔ
በገባኦን ሰማይ ፀሐይን ያቆመ
ዛሬም ጎብኝቶኛል እየደጋገመ
ወጥመድ ተሰበረ እኔም አመለጥኩኝ
ከኃጢአት ፍላፃ ከሞት አተረፈኝ
የአናብስቱን አፍ በኃይሉ የዘጋ
የዳንኤል አምላክ ይኖራል ከእኔጋ
በዳዊት ምስጋና በያሬድ ዝማሬ
ከቅዱሳን ጋራ ልዘምር አብሬ
እርሱን ሳመሰግን ሚልኮል ብትስቅብኝ
ለጌታዬ ክብር እዘምራለሁኝ
አስፈሪው ነበልባል እሳቱ ቢነድም
ለጣኦት እንድንሰግድ ነገስታት ቢያውጁም
ሁሉም ቢተወኝም ቢጠላኝም ዓለም
ፅናት ይሆነኛል ጌታ መድኃኔዓለም

264. ስለማይነገር ስጦታው

ስለማነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን
ቸል ያላለን አምላክ ስንጓዝ ማዕበሉን አቋርጠን
ስለማይነገር ስጦታው እግዜአብሔር ይመስገን
የሕይወት እስትንፋስ ዘራብን ሕያው እንድንሆን
ይሕን ያደረገ አምላካችን እግዚአብሔር ይመስገን
ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን
ንፋስን ገስፆ መዕበል አቁሞ የሚያሻግር
የዓለም ፈተና ቢበዛ እርሱ መጠጊያችን
ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን
ዳግም እንዳንሞት በሞቱ ሞትን የረታልን
የምንመካበት ትንሳኤው ሰላሙን የሰጠን
ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር
ይመስገን
ከሲኦል እስራት ተፈተን ነፃ የወጣንበት
መስቀሉን ለሰጠን አምላካችን እንዘምር በእውነት
ስለማይነገር ስጦታው እግዜአብሔር ይመስገን

265. ንሴብሆ ለእግዚአብሔር

ንሴብሆ /፪/ ለእግዚአብሔር
ስቡሐ ዘተሰብሀ /፪/
እናመሰግነው /፪/ እግዚአብሔርን
ምስጉን ነው የተመሰገነ /፪/
ባሕሩን ተሸገርን ወንዙ ደረቅ ሆነ
በጠላታችን ላይ ድሉ የኛ ሆነ
ከባርነት ቀንበር ፍፀም ነፃ ወጣን
ሕይወት የሚሰጠን መና ነው ምግባችን
አስፈሪ ነው ያልነው ብዙ ነገር ነበር
ሁሉንም አለፍነው አምላካችን ይክበር
ሕይወታችን ቢዝል ፈተና ቢበዛ
ኃይላችን ጌታ ነው የዓለሙ ቤዛ
ከአለት ላይ ውሃ ፈልቆ እንጠጣለን
ይህን ታላቅ ጌታ ኑ እናመስግነው
ሕዝቦች ደስ ይበለን ሕይወታችን ድኗል
ሰይጣን ጠላችን አፍሮ ተመልሷል

266. ኩሎ ዘፈቀደ

ኩሎ ዘፈቀደ ገብረ እግዚአብሔር
በሰይማኒ ወበ ምድርኒ ወበባሕርኒ ወበ ኩሉ ቀላያት /፪/

267. እናመስግነው

እናመስግነው /፪/
አምላካችን ውለታው ብዙ ነው /፪/
ከኃጢአት ገደል ከሞት ቤት ለይቶ
መንግስቱን የሰጠን ከሲኦል አውጥቶ
ዘለዓለማዊ ቤት ታላቅ ሀብት ያደለን
መቼም የማይተወን ታላቅ አባት አለን
ፍጡራን ቢንቁኝ መጎስቆሌን አይተው
ወዳጆች ቢሸሹኝ ተስፋ ቢስ ነው ብለው
እውነተኛው ረዳት አምላኬ መች ተወኝ
ሁለት እጁን ይዞ ልጁ ተነስ አለኝ
ሞታችንን ሞቶ ሕይወቱን ላደለን
ለቸሩ ክርስቶስ ምን እንከፍለዋለን

ለታላቅ ውለታው ጌታ ለዋለልን
በእልልታ እንዘምር በአንድነት ሆነን

268. ኢየሱስ ቅዱስ

ኢየሱስ ቅዱስ ፍፁም መድኃኔዓለም
የዓለም መምህር /፪/
እኛን ለማሻገር ከክብር ወደ ክብር
ከሰማይ ወረደ /፬/ በፍቅር እስከ መቃብር

269. አድርገህልኛልና

አድርገህልኛልና በቸርነትህ
አመሰግንሀለሁ እልል እልል
ለዓለመ ዓለም አማኑኤል
እገዛልሀለሁ መድኃኔዓለም /፪/
ቀኑ ጨልሞብኝ ዙሪያው ገደል ሆኖ
የችግር አረንቋ ፊቴ ተደቅኖ
ረዳት ያጣሁኝ በመሰለኝ ጊዜ
ፈፅሞ አራክልኝ የልቤን ትካዜ
አምላኬ ጉልበቴ ኃይሌ መመኪያዬ
ጠላት ማሳፈሪያ የእምነት ጋሻዬ
እንደማትተወኝ አሁን አውቄያለሁ
ካለኝ ነገር ይልቅ በአንተ ታምኛለሁ
ጥቂቷን አብዝተህ ለምትመግብ ጌታ
የምመልስልህ ባላገኝ ስጦታ
በቀንም በለሊትም ሁሌም ለሚያበራ
መንክር ለባህሪህ እፁብ ላንተ ሥራ
አምላክ ሆይ ምስጋና ላንተ ይገባሀል
ለምስኪኗ ጎጆ በረከት ሰጥተሀል
ደሀ ነኝ አልልም ሀብቴ አንተ ነህና
ማሰሮዬ ሞልቷል ላይጎል እንደገና

270. ይለመነናል

ይለመነናል አምላክ አብርሐም
ይታደገናል መድኃኔዓለም /፪/
ለፍጥረት ሁሉ እጹን የዘረጋ
ቸር እረኛ ነው አልፋና ኦሜጋ
አብርሃም ይስሃቅን ያዕቆብን አስበሕ
የማልክላቸውን ቃልኪዳን አስታውሰህ
ደካማ ለሆነው ሥጋ ሰልጥኖብን
አትመልስ ጌታ የምህረት ዓይንህን
ከሰማያት ሰማይ ይድረስ ጩኸታችን
እንዘን እናልቅስ ስለበደላችን /፪/
ባይመለከተን አምላክ አብርሃም
በፍቅር እጆቹ መድኃኔዓለም
ባይዘረጋልን አምላክ አብርሃም
የምህረት እጆቹ መድኃኔዓለም
ሕዝበ እስራኤል ሁሉ ለአምላክ ዘምሩ
አድኖናልና በሚያስደንቅ ፍቅሩ /፪/
ምንም እንኳን ክሕደት ቅጥፈት ቢበረታ
ስለ አብርሃም ብለህ አልተውከንም ጌታ
ለቅዱሳን ያለህ ቃል ኪዳን ሲፀና
ቀስተ ደመናህን አይተነዋልና
ቃል ኪዳኑ ግሩም አምላክ አብርሃም
ምህረቱ የበዛ መድኃኔዓለም
ርስት ጉልታችን አምላክ አብርሃም
የሕይወታችን ቤዛ መድኃኒዓለም
ሳይፀየፍ ጌታ ያደፈ ኃጢአቴን
ከማጥ ውስጥ አወጣት ታደጋት ሕይወቴን /፪/

271. እናመስግን

እናመስግን አማኑኤልን የሞተልንን ጌታ
በሞቱ ሞቱን ሻረልን እንዳንረታ /፪/

272. ስምህ በሁሉ

ስምህ በሁሉ ተመሰገነ
ከክብር በላይ ክብርህ ገነነ
አንተን ማመስገን ያስደስተናል
ስምህን ማክበር ግብራችን ሆኗል
አምላክ ተመስገን በሰማያት
ስምህ ይወደስ በፍጥረታት
ከህፃናት አፍ ምስጋና ይውጣ
አንተን ማመስገን ይሁን የእኛ ዕጣ /፪/
በምግብ እጦት ብንሰቃይም
ማህሌትህን አናቋርጥም
የመከራ ዶፍ ቢወርድብንም
እንዘምራለን ለአምላካችን ስም /፪/
ሰማዩ ዝናም ደመና ቢያጣም
ፍቅርህ በእኛ ውስጥ አላቋረጠም
ቸርነትህን እንጠብቃለን
ካንተ ደጅ ጌታ/አምላክ/ የት እንሄዳለን /፪/
አምላክ ተመስገን ……..

273. መድኃኔዓለም አዳነን

መድኃኔዓለም አዳነን በማይሻር ቃሉ
ኧኸ ደስ ይበለን /፪/ እልል በሉ /፪/
አዳነን በማይሻር ቃሉ
እናታችን ቅድስት የአምላክ እናት
ኧኸ እንስገድላት /፪/ እንስገድ /፪/
በእውነት ለአምላክ እናት
ፃድቃን ሰማእታት ወሐዋርያት
ኧኸ ያማልዱናል /፪/ መላዕክት /፪/
በእውነት በላይኛው ቤት
ተዋሕዶ ሃይማኖት እንከን የሌላት
ኧኸ እንከተላት /፪/ እስከሞት /፪/

በእውነት ያለፍርሃት

274. ተናገሩ

ተናገሩ ድንቅ ሥራውንም መስክሩ
ተዓምሩን ለዓለም ንገሩ /፪/
ድንቅ ሥራውን መስክሩ

275. ኖላዊ ትጉኅ

ኖላዊ ትጉኅ ዘኢትነውም /፪/

ማኅበረነ /፪/ ዕቀብ በሠላም /፬/

ትርጉም:- የማታንቀላፋ ትጉህ እረኛችን /፪/

ጠብቅልን በሰላም ማኅበራችንን /፪/

276. አ አባ ቅዱስ ዕቀቦሙ

አ አባ ቅዱስ ዕቀቦሙ /፪/

በስምከ ወበኃይልከ ዕቀቦሙ

ከመይኩኑ አሐደብነ ከማነ /፪/ ከመይኩኑ /፪/

ትርጉም፡ ቅዱስ አባት ሆይ እነዚህን የሰጠኸኝን
እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው

277. መድኃኔዓለም ክርስቶስ

መድኃኔዓለም ክርስቶስ በቀራንዮ ስቁል
በለኒ መሐርኩከ/መሐርኩኪ
በእንተ ማርያም ድንግል
እስመ ሔር አልቦ እንበሌከ ቃል ኧኸ

278. ኑ የእግዚአብሔርን

ኑ የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራውን እዩ /፪/
<u>የአምላክን ቸርነት ፍቅሩንም ቀምሰናል</u>
<u>በነገሮች ሁሉ ሲረዳን አይተናል</u> /፪/
ተአምርህን አይቶ ማነው ያልወደደህ
የሞት አዋጅ ስትሽር ፍሰሀን ተክተህ
መረጥኩህ ለነፍሴ ለዘለአለሙ ኑሮ
ማን መቆም ይችላል ካንተ ተሰውሮ
የስጋዬን ህመም የነፍሴንም እየው
በከሀሊነትህ ያሻህን አድርገው
የወደድከው ይሁን ፈቃድህ ይፈፀም
አትተኛምና ባርያህን ለመጥቀም
ምንም ባይኖረንም ብንሆን ባዷችንን
በረከቱን ሰጥቶ ሞልቷል እጃችንን
ቅንጣት ባይኖረንም አከናውኖልናል
የሀብታችን ምንጮች ሳይነጥፉ ቀድተናል
ወደ ደጅህ መግቢያ ይጎለሀ መቃኑን
በፊቴ ያለውን አልፌ ባሕሩን
የግፍን እንጀራ ነፍሴ ተፀይፋ
መኖርን ወደደች አንተን ተደግፋ
ኃጢአቴን አንጽቷል የዘመናት ሸክሜን
በፍቅር አፅንቶኛል አሳርፎት ልቤን
ድንቅ ነው ማዳኑ ቃላት የማይገልፀው
አፌን በሳቅ ሞላው ምስጋና ይድረሰው

279. እግዚአብሔር የሀበነ

እግዚአብሔር የሀበነ ልሳነ ጥበብ
እግዚአብሔር የሀበነ ልሳነ
ከመናእምር ሕጋ /፪/ ለቤተክርስቲያን /፪/

280. ቸርነቱ

ቸርነቱ በኛ ላይ ስለበዛ
ይክበር ይመስገን መድኃኔዓለም የዓለም ቤዛ /፪/

281. እንደ እግዚአብሔር ያለ

አንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለምና /፪/
እልል በሉ ቁሙ ለምስጋና /፪/
ባሕር ተከፈለ እስኪታይ መሬቱ
ፈርኦን ወደቀ አልሰራም ትምክህቱ
ደካሞችም ጸንተው ተራመዱ
ኃይለኞችም ይኸው ተዋረዱ
የኢያሪኮ ቅጥር የማይደፈረው
ይኸው ፈራረሰ የሰው እጅ ሳይነካው
ኃይለኞችም ቢበረታቱብን
እንፀናለን በእርሱ ተደግፈን
የተወረወረው የጠላታችን ጦር
ሜዳ ላይ ወደቀ ጋሻ ሆኖ እግዚአብሔር
ለሥላሴ ይድረስ ምስጋናችን
ተሸነፈ አዳኝ ጠላታችን
ባሕር ላይ ሲራመድ ሞገስ አለው እርሱ
በግርማው ሲነሳ ፀጥ ይላል ንፋሱ
የድንግል ልጅ እኛ የምናመልከው
ከሀሊ ነው የለም የሚሳነው

282. እውነተኛው ሰላም

እውነተኛው ሰላም ያለው ከቤትህ ነው /፪/

እርዳኝ አልናወፅ እለምንህለሁ /፪/
ኃጢአቴን ሳስበው ልቤ ይጨነቃል
ካንተ መለየቴ ነፍሴን አድክሚታል
ወዳንተ መልሰኝ እኔ እመለሳለሁ
እውነተኛው ሰላም ያለው ከቤትህ ነው
ለቅዳሴው ፀሎት ዘውትር እንዳልተጋሁ
አደባባይ ቆሜ ስምህን እንዳልጠራሁ
ተሰነካክዬ ወድቄያለሁና
እርዳኝ አማኑኤል በኃይማኖት ልጽና
ዓይኔ እንባን ያምንጭ ላልቅስ ስለ ኃጢአቴ
የንሰሐ ትሁን ቀሪዋ ሕይወቴ
በመዳኔ ሰዓት በዛሬዋ ዕለት
ፍቅርህን አስቤ መጣሁ ከአንተ ፊት
ጌታ ሆይ ፀፀቴን እንባዬን ተቀበል
አባትሽ/ህ ነኝ በለኝ እኔም ልጅ ነኝ ልበል
ዘይት ሳላዘጋጅ ድንገት መጥተህብኝ
በርህን በመዝጋት ከደጅ አታስቀረኝ

283. ኃይል የእግዚአብሔር ነው

ኃይል የእግዚአብሔር ነው
ማዳን የእግዚአብሔር ጥበብ የእግዚአብሔር
አንመካም በጉልበታችን
እግዚአብሔር ነሠው የኛ ኃይላችን

284. ያልጠፋነው

ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሳ ነው /፪/
ቸርነቱ ከቶ አያልቅምና
ርሕራሔው ከቶ አያልቅምና
ይገባዋል ክብርና ምስጋና
ፈታኝ ሲያንገላታን በባሕር ስንሔድ
ማዕበል ተነስቶ ያየሥጋ ሞገድ
ሕይወት ስትመዘን ልባችን ሲናወጥ
ለጠላት ሳይተወን አደረገልን ጸጥ
ስለሆነ ሩሕሩህ ፈጥኖ የማይቀየም
በንሰሐ እንቅረብ አንሂድ ወደ ዓለም
ምስክር ነንና አይተናል ማዳኑን
በእርሱ ተማርከናል ቀምሰን ቸርነቱን
በበደልነው በደል ማረን እንላለን
ካንተ ተለይተን ወዴት እንሄዳለን
ዓለም የማያውቀው የማይመረምረው
በውስጣችን አለ እኛ የምናመልከው
ከእንግዲህ አልፈልግም የሸንጋይ ምላስ
ቃልህ ይቆጣጠረኝ በስጋም በነፍስ
አንተ ካከበርከኝ ማን ያዋርደኛል
አይኔን ከሰው አንሳው አሁንስ ታክቶኛል

285. እግዚአብሔርን ጠራሁት

እግዚአብሔርን ጠራሁት በሐዘኔ ግዜ /፪/
አወጣኝ ከጭንቀት ከሐዘን ከትካዜ /፪/
የልመናዬን ድምጽ እርሱ ሰምቷልና
ጆሮውን ወደኔ አዘንብሏልና
በዘመኔ ሁሉ ስጠራው እኖራለሁ
ጎስቋላ ብሆንም ምስጋና አቀርባለሁ /፪/
እንደ ቃልህ መሄድ መራመድ ተስኖኝ
የኃጢአቱ መንገድ ማዕበሉ ገፍቶኝ
ወደ እርሱ ስማጸን ደግሞም ስጸጸት
አላሳፈረኝም መጣ በምሕረት /፪/
በበዛው ምሕረቱ ያለፈውን ትቶ
በፍቅሩ ጎበኘኝ አልተወኝም ከቶ
ሊቀበለኝ ወዶ ፊቱን አበራልኝ
ማን ይቃወመኛል እግዚአብሔር ካለልኝ /፪/
ኖኅን እንዳዳንከው እኛንም አድነን
ከቀስቱ እንድናመጥ ምልክትን ስጠን
በትርህ ምርኩዝህ እነርሱ ያጽናኑን
አንተ ከእኛጋር ነህ አንፈራም ክፉውን /፪/

286. ልቤ በእግዚአብሔር

ልቤ በእግዚአብሔር ፀና /፪/
አፌን አላቀቅሁኝ ለስሙ ምስጋና
በጠላቶቼ ላይ አፌ ተከፈተ
ማዳኑን አይቼ ልቤ ተመሰጠ
እንደ እግዚአብሔር ያለ ረዳት ማን አለ
ደካማ ባርያውን ስለተቀበለ
ጠግበው የነበሩ እንጀራን ተራቡ
ተርበውም ሳሉ እረኩ ጠገቡ
መች ጎድሎብኝ ያውቃል አንተን ተደግፌ
በእጆቼ በረከት ተሞልቷል መዳፌ
እግዚአብሔር ይገድላል እንዲሁም ያድናል
የኃይለኞቹን ቀስት ሰብሮ ይታደጋል
መካኒቱ ሃና ወለደች ሰባት
ሥራህ ይገርመኛል በቀን በሌሊት
ምስኪኑን ከጉድፍ ያነሳል ከምድር
ይዘረጋለታል የክብርን ወንበር
ተመከረ ልቤ ሃናን ተመልክቶ
እግዚአብሔር ለጋስ ነው ለጠበቀው ከቶ

287. እግዚአብሔር

እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው
የሚያስደነግጠኝ የሚያስፈራኝ ማነው /፪/
አምላኬ መመኪያዬ ነው

288. ቅዱስ

ቅዱስ /፫/ እግዚአብሔር
ፀባኦት ፍፁም ምሉዕ
ሰማያተ ወምድረ /፪/ ቅድሳት ስብሐቲከ

289. እናመሰግንሀለን

እናመሰግንሀለን /፪/
እንደ አባቶቻቸን በማሕሌት እንጠራሀለን
እንደ ቅዱሳኑ ለክብርህ እንዘምራለን
ለአምላክ ውዳሴ ለፈጣሪ ክብር
ማለዳ ተነስተን ምስጋና ስንጀምር
የአባቶች ዝማሬ ቅኔ መወድሱ
ሲሰማ ደስ ይላል በቤተ መቅደሱ
ሥርዓተ ሰማይ በምድር ተሰምቶ
በአባቶች ልቦና የአምላክ ጥበብ ሞልቶ
ዝማሬው ፈለቀ ከታላቁ መቅደስ
በጥዑመ ዜማ ፈጣሪ ሊወደስ
ድምፁ ቀሰቀሰን ለአታት ቅዳሴው
የያሬድ ፀናፅል መሰንቆ በገናው
የፅዮን ደናግል ለመዝሙር ተነሱ
ሥሉስ ቅዱስ በሉ ስሙን አወድሱ
ማህሌቱ ሲቆም ሰአታት መዝሙሩ
ቅዱሳን መላዕክት አብረው ሲዘምሩ
ፍጹም ተመሰጠች ነፍሳችን በደስታ
ለምስጋና ስትቆም ከቅዱሳን ተርታ

290. እግዚአብሔር ይመስገን

በወጅብ በአውሎ ውስጥ በመከራዬ ቀን /፪/
ረድቶኛልና እግዚአብሔር ይመስገን
አድኖኛል እና እግዚአብሔር ይመስገን

291. እስመ አልብነ

እስመ አልብነ ረዳኤ በጊዜ ምንዳቤ ወሐዘን
እስመ ዘእንበሌከ ባዕደ ኢነአምር
እስመ ዘእንበሌክ ባዕደ ኢነአ

292. እግዚአብሔር ይመስገን

እግዚአብሔር ይመስገን
ይሕችን ቀን ቀድሶ ለሰጠን ኧኸ
ከያለንበት ሰብስቦ /፪/ ለዚህ ያደረሰን /፪/

293. ፈተና ወጀብ

ፈተና ወጀብ ቢበዛ
አይተናል ሕዝቡን ሲያበዛ
በሕይወት አንዴ ተክሎናል
እግዚአብሔር መች ይተወናል /፪/
ፍቅር ነው የናርዶስ ሽቶ
ወደደን ተሰቅሎ ሞቶ
ነጎድጓድ መብረቅ ቢሆንም
በሕይወት አለን አሁንም /፪/
መኪንንት ደጁን ክፈቱ
የፀጋው ፈልቷል ዘይቱ
ተራግፏል ሸክማችን
ምህረቱ ቢፈስልን /፪/
ተጽናንቷል አርፏል ልባችን
በእሳት ታጥሯል ቅጥራችን
አንወድቅም አንሸነፍም
ይዞናል የአምላካችን ስም /፪/
ሕይወት ነህ የጽድቅ ጥላ
ያውቅሀል ቃል የተመላ
ኦ አንተ ጣፋጭ ምግባችን
እግዚአብሔር ቸር አምላካችን /፪/

294. ኃይልን በሚሰጠኝ

ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ /፪/
ፈተና ቢገጥመኝ ለበጎ ነው ብዬ አልፋለሁ /፪/
በሰንሰለት አስረው በወሕኒ ቢጥሉኝ
መከራን አብዝተው እጅግ ቢያስጨንቁኝ
ለበጎ ነው ብዬ ተስፋ አድርጌሀለሁ
ይሁን አንተ ያልከው እገዛልሃለሁ
ትናንትናም ዛሬም አንተ ያው አንተነህ
ፍቅርህ አይቀየር ወረትም የለብህ
ስምህን መጥራቴ ሞገስ ሆኖልኛል
ጠላቴ ቢፎክር መች ያሸንፈኛል
ከመከራው ብዛት ጉልበቴ ደከመ
ትካዜ ከቦኛል ተስፋዬ ጨለመ
ነገር ቢሆን ባይሆን አንተን እንዳከብር
አድለኝ በጸጋ ጌታ ያንተን ክብር
ከሀገር ወጥቼ በዱር መሰደዴ
በባዕዳን ሀገር እርቄ መሄዴ
ለበጎ ነውና መቼ ይከፋኛል
ፈጽሞ እንዳልጠፋ ፍቅርህ ይይዘኛል

295. ስብሐት

ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት
ወሰላም በምድር ስምረቱ ለሰብዕ ሃሌሉያ
ሃሌሉያ /፫/ አሜን ሃሌሉያ

296. ወደ ቤተ እግዚአብሔር

ወደ ቤተ እግዚአብሔር እንሂድ
ባሉኝ ጊዜ እኔን ደስ አለኝ /፪/
የኃጢአት ሸክሜ ቀለለኝ /፪/
እስቲ ላነሳሳው የዳዊትን መዝሙር
አምላኬን ላመስግን በደስታ በፍቅር
በልቤ እያሰብኩኝ ለኔ ያለውን ፍቅር /፪/
የጥፋቱ ማዕበል ጎጆ መጠለያ
የፀድቁ የኖህ የመርከቡ አምሳያ
ቤተክርስቲያን ናት የእኛ መሸሸጊያ /፪/
ኃጢአት እሾህ ሆኖ ቁስሉ ሲወጋጋህ
ሞት ሲንጣጥብህ ሲጠወልግ
ቤተክርስቲያን ሂድ መንገዷም አይጥፋህ /፪/
የቅዱሳን ክብር የሚነገርባት
ድንግል ከነልጇ የምትገኝባት
ይሕች ቅድስት ስፍራ ቤተክርስቲያን ናት /፪/

297. በእንተ ማርያም

በእንተ ማርያም /፪/ ወላዲትከ
ወበእንተ ዮሐንስ ፍቁርከ
እርድአነ እግዚኦ በኃለ መስቀልከ

298. እንዘ የአምር

እንዘ የአምር እምቅድም ሕሊና
ዘይሄሊልበ የአምር /፪/
አርአየ ኃይሎ በላዕሌነ ወፀገወነ
ኧኸ ሠናይቶ እግዚአብሔር

299. ሰዎች እንዘምር

ሰዎች እንዘምር ለአምላካችን
ከሞት ላወጣን ላዳኖችን
እናመስግነው እንደአቅማችን
ምሕረት ለሰጠን በነፍሳችን
አምላክ ተአምሩን ያሳየብህ
ጨኸት ድምፅህን የሰማልህ
በርጠሜዮስ ሆይ አትተወው
አዳኝ ጌታህን ተከተለው
እውርነቴን ያስቀረልኝ
ዓይኖቼ ብርሃን የሰጠኝ
ሁሌም ከእርሱ ጋር እኖራለሁ
አዳኜን ትቼ የት እሄዳለሁ
በርጠሜዎስ ሆይ ታድለሃል
የመዳን ፀጋ ተሰጥቶሃል
እፁብ ድንቅ ነው የአምላክ ሥራ
እውር የሆነው ዓይንህ በራ
ይህን ጌታዬን ምን ልበለው
ለውለታውስ ምን ልክፈለው
ስሙን ላወድስ ላመስግነው
አምላክ ክፍያው ይህ ብቻ ነው
አስራ ሁለት ዓመት ደም ሲፈስሽ
ሰዎች ሲርቁሽ ሲንቁሽ
ማን ፈወሰሽ አንቺ ሴት
ያበቃሽ ማነው ለድኅነት
እምነትሽ አድኖሻል አለኝ
ኃይል ወጣ ከእርሱ የሚያጽናናኝ
የጌታን ልብሱን ብዳስሰው
ደሜ ቀጥ አለ ላወድሰው
በቤተሳይዳ በአልጋ ስትኖር
በመጠመቂያ በወንዙ ዳር
ድውይ ስትሆን በሽተኛ
እንዴት ተፈወስክ አውጋን ለኛ
አልጋ ታቅፌ ስንገላታ
መዳን ትሻለህ አለኝ ጌታ
አምላኬ እርሱ ፈወሰኝ
አልጋህ ይዘህ ሂድ አለኝ

300. ዘይክል ኩሎ

ዘይክል ኩሎ ወአልቦ ዘይሰህኖ ለእግዚአብሔር
አምላከ ነዳያን ረዳኤ ምንዱባን
ናዛዜ ህዙናን ወተስፋ ቅቡጻን
ንህነ ህቤከ /፪/ ተማሕጸነ
የድሆች መጠጊያ ተስፋ ላጡት ተስፋ
ሁሉንም የሚችል ደራሽ ለተገፋ
ለኛም ድረስልን በኃጢአት ሳንጠፋ
ናዛዜ ሕዙናን.....
ከገነት ሲሰደድ አዳም ተሳስቶ
ባለቀሰ ጊዜ ልጅነቱን አጥቶ
ትድናለህ ብለህ ያዳንከው በመስቀል
የቅዱሳን አምላክ አቤቱ ቸል አትበል
ወተስፋ ቅቡዓን.....
ሕዝበ እስራኤልን ፈርኦን ሲገዛቸው
ጭንቅና መከራ እያፀናባቸው
በነራሔል ለቅሶ ሙሴን ላክህላቸው
ረዳኤ ምንዱባን.....
እኛም ወገኖችህ ወዳንተ እንጮኻለን
ከጭንቅ ከመከራ እንድትታደገን
ጌታ አንተ ነህና ናዛዜ ህዙናን
ናዛዜ ህዙናን.....

301. ከወገኔ ጋራ

ከወገኔ ጋራ እዘምራለሁ
በደስታ በሐሴት ስሙን እጠራለሁ
ምግብና መጠጤ አምላኬ ነውና
ዘውትር አቀርባለሁ ለጌታ ምስጋና
ሕዝቡ ተሰብስቦ በቤተ ክርስቲያን

ሲዘመር ደስ ይላል በአንድነት ሆነን
በረከት የሞላው ዝማሬው ይገርማል
ከእጣኑ ጋራ ወደላይ ይወጣል
ቀሳውስቱ ሌሊት ማኅሌት ሲቀርቡ
ከመላዕክቱ ጋር ወረብ ሲወርቡ
ብርሃንን ለብሰን በደስታ ስንዘምር
ትዝታው ልዩ ነው ሕሊና ሲሰውር
ራዕይ ነውና ኑና ተመልከቱ
ሰዎች ሲዘምሩ እንደ መላዕክቱ
የጽጌው ማኅሌት የትንሳኤው ደስታ
ልዩ ዝማሬ ነው እንዳይመስለን ተርታ

302. ድንቅ ነው

ድንቅ ነው ልዩ ነው ልዑል የኛ ጌታ
ምስጋና ይድረሰው ከጧት እስከ ማታ
የማይመረመር በሰው ልጅ ህሊና
ረቂቀ ባሕርይ ገናና ነውና
ያለ የነበረ ከዘመናት በፊት
ለዘለዓለም ኗሪ ፈጣሬ ዓለማት
በፍጥረታት ሁሉ የሚመሰገነው
ኃያሉ ጌታችን በእውነት ግሩም ነው
በፍፁም ልዩ ነው የእርሱ ጌትነቱ
አልፋና ኦሜጋ ጽኑ ነው መንግስቱ
በመላዕክት ዓለም በሰማይ ከተማ
ለክብሩ ሲዘመር ማህሌት ሲሰማ
ያለምንም እረፍት በቀንና ሌሊት
ንፁህን መላእክት የሚያመሰግኑት
አዳምን ለማዳን ፍፁም በመውደዱ
የማይሞተው አምላክ ሞተ በፈቃዱ
ምስጢሩ ረቂቅ ነው ለሰዎች አእምሮ
ፍቅሩ ያስደንቃል ስናየው በአንክሮ

303. ዘሰማየ ገብረ

ዘሰማየ ገብረ ሰማየ ገብረ ወምድረ ሣረረ /፪/

አልቦ ዘይመስሎ ለአምላክነ /፬/

ሰማይን የዘረጋ መሬትን ያጸና /፪/

ኃያል ጌታ ሕያው አምላክ ያለ እርሱ ማን አለና /፪/

304. ንሴብሆ

ንሴብሆ /፪/ ለአምላክ እዝራ
ንሴብሆ ለአምላክ እዝራ
ለምስጋና ቀሰቀስከኝ በእኩለ ሌሊት
በተመስጦ ስለፍቅርህ ልጀምር ማህሌት
ንሴብሆ ለአምላክ እዝራ
ስመለከት ወደሰማይ በጨረቃ ብርሃን
ግርማ ለብሶ አስገረመኝ የአምላኬ ዙፋን
ንሴብሆ ለአምላክ እዝራ
ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን በመንፈስ
እንዘምር
እልል እንበል በምስጋና ፀጋውን እንጀምር
ንሴብሆ ለአምላክ እዝራ
አእዋፉ በማለዳ መዝሙር ሲጀምሩ
በቋንቋቸው ያንተን ክብር በምስጢር ሲያወሩ
ንሴብሆ ለአምላክ እዝራ
ከበሮ ሆይ ጸናጽል ሆይ ለምስጋና ተነስ
በማለዳ ለአምላካችን ምስጋናን እናድርስ /፪/
ንሴብሆ ለአምላክ እዝራ

305. ቸርነት ምህረትህ

ቸርነት ምህረትህ ቢነገር ቢነገር
ማን ይደርስበታል ጌታ ያንተን ፍቅር
የምትጠብቀን አትተኛምና
ሰልፉ ያንተ ሆኖ ወጣን ከፈተና
ግብፅ ተሸበረች ተፈታ ጅማቷ
ዝም ያለው ሲናገር የታገሰው ጌታ
በደም የሰራነው ፒራሚዱን ትተን
ወጣን ከባርነት እግዚአብሔርን ይዘን
በቃዴስ ጠገብን ረካን በሲና
ታላቁን በረሀ ሸፈነው ደመና
ከፊታችን ባለው ለበሰን ግርማ
እግዚአብሔር ታላቅ ነው ምድር ሁሉ ትስማ
በያዕቆብ መርገም አስማት መች ይሠራል
የበለአም እብደት በአህያው ታግዷል
ሲጠብቀን ውሎ ያድራል ሲጠብቀን
ከእቅፉ በታች ነን ማነው የሚነጥቀን
ኤናቃውን ሁሉ ውጡ ከርስታችን
ከቀስታችሁ በላይ ታላቅ ነው ጌታችን
በቤቱ እንድንኖር ሰጥቶናል በተድላ
እንበዛለን ገና ከእንግዲህ በኋላ

306. ሞት ነው ርሃብ

ሞት ነው ርሃብ ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየን /፪/
ኃይሉ በእኛ ላይ አድሮ እንበረታለን
ፀጋው በእኛ ላይ አድሮ እንበረታለን
ከአንተ ርቀው ሸሽተው እየሄዱ
ጠፋባቸው የፅድቅ መንገዱ
በሥጋዊ ጥበብ ሲፈልጉህ
በመታለል ስንቶች አንተን አጡ
በተዋሕዶ የከበርከው ጌታ
በመድኃኔዓለም ሁንልን መከታ
ስንደክም ምኞት ሲፈትነን
ኃይልን ሰጥተህ በእጆችህ ደግፈን
የዓለም ሰይፍ በእኛ ላይ ተስሏል
ሥጋችንን ሊቆርጠው አድብቷል

ኃይልን ስጠን እንድናሸንፈው
ፀጋህ ለእኛ የእምነት ጋሻችን ነው
ሐዋርያት ፀጋህ በዝቶላቸው
ስለፍቅርህ ፈሰሰ ደማቸው
ዛሬም ለእኛ ፀጋህን አብዛልን
እንዳንደክም ፈተና ሲገጥመን
ጋሻ ሆነህ እንድትመክትልን
ቸር አምላክ ሆይ ወዳንተ እንጮሀለን
ቢገጥመንም ችግር ወይ መከራ
አትለየን ጌታ ከእኛ ጋራ

307. ተመስገን

ተመስገን /ፎ/ ጌታዬ ተመስገን ጌታዬ
ባይሳካኝ ባይሞላ ጓዳዬ
ባንተ ተሸፍኗል ጉድፍ ገመናዬ
ኑሮዬ ቢሆንም እጅጉን መራራ
ሕይወት ለኔ ከብዳ ብትሆንም ግራ
ሁሉን ነገር አንተ ለበጎ አድርገሀል
አምላክ ለስጦታህ ምን ይከፈልሀል
ያሰብኩት ባይሞላ ባይሳካልኝም
ተመስገን እላለሁ አልጎደለብኝም
አላፍርም ጠርቼህ አምናለሁ ጌታዬ
ሁሉ ባንተ ሆኗል ይድረስ ምስጋናዬ
ደመናት ባይታይ ንፋስም ባይነፍስ
ኤልሻዳይ እግዚአብሔር ስሙ ይወደስ
የጓዳዬን ምስጢር የሚያውቀው እርሱ ነው
በጎደለኝ ሁሉ የሚሞላው አለው

308. እናመሰግን

እናመሰግን አምላካችንን

እናመሰግን ፈጣሪያችንን

ለዚህ ያደረሰንን

ጨለማውን ገፎ ብርሃንን ለሰጠን

ምስጋና ለእርሱ ይሁን ለኃያሉ ንጉሣችን

ዘመናትን በዘመናት ያፈራርቃል

ስለሁሉም ሁሉን ያውቃል

ሳንለምነው የወደድነውን ይሰጠናል

ከፈቃዱም ይሰማናል

ውዳሴውን አዘጋጁ ያለዕረፍት

በአዲስ ቅኔ ተቀኙለት

በአዲስ መዝሙር ዘምሩለት

እንደ ወዳጁ እንደ ዳዊት

ዝናማናትን ይሰጠናል በጊዜያቱ

ፍጥረቱንም ይመግባል በጊዜያቱ

ፍጥረቱንም ይመግባል በየዕለቱ

ጎልፈት የለው በመንግሥቱ

ውዳሴውን.....

ስሙ ታላቅ ኃያል ንጉሥ

የሚሉለት ቅዱስ /ፎ/ መላእክቱ በሰማያት

ምስጋናውን ያቀርባሉ ያለዕረፍት

የተቤዠህ ፍጥረትህን

ክብር ምስጋና ለአንተ ይሁን

ውዳሴውን....

309. ያከብርዋ

ያከብርዋ ለሰንበት መላዕክት
በሰማያት ጻድቃን በውስተ ገነት
ወኩሉ ፍጥረት አሳት ወአናብርት
እለውስተ ደይን ያረፉባቲ
እስመ ባቲ አእረፈ እምኩሉ ግብሩ
ያከብሯታል ሰንበትን መላዕክት
በሰማያት ጻድቃንም በገነት
ፍጥረታት በሙሉ አሳዎች እና እንበሪዎች
በመቃብር ያሉ ያከብሯታል
አምላክ በእርሷ እንዳረፈ ከስራ ሁሉ

310. እልል በሉ

እልል በሉ በአንድነት ዘምሩ አመስግኑት
ለክብሩም ዘምሩለት
እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም በሉት
በኃጢአት ባርነት ስንኖር ተገዝተን
ከቤቱ ስንርቅ ትዕዛዙን አፍርሰን
አይቶ ዝም ላለን ጠላቶች ሳለን
ውለታው ግሩም ነው ክብር ለእርሱ ይሁን
/፪/
ራሱን አዋርዶ እኛን አከበረን
ሥጋውና ደሙን ብሉ ጠጡ አለን
መልካም እረኛ ነው የሚያሳጣን የለም
ምስጋና ይድረሰው ለመድኃኔዓለም /፪/
ሕይወቱን የሠዋ እንደ አምላክ ማን አለ
ለሰው ልጆች ብሎ በመስቀል የዋለ
ፍቅሩም አይለካ አያልቅም ቢወራ
ከሰማያት ወርዶ ሆነ ከእኛ ጋራ /፪/
ሥራውን እናድንቅ እንዲህ ለወደደን
ከማያልቀው ፍቅሩ በረከት ላደለን
ለማይነገረው ለአምላክ ስጦታ

ውዳሴን እናቅርብ እንዘምር በእልልታ /፪/

311. ሰዎች ደስ ይበለን

ሰዎች ደስ ይበለን በአምላካችን
ከኃጢያት ባርነት ነጻ ያወጣን
ተነሱ እናመስግን ውለታው ብዙ ነው
ምን ይከፈለዋል ተመስገን ብቻ ነው
በኃጢአት በሽታ ወድቄ ሳለሁኝ
መድኃኒት ክርስቶስ ከውድቀቴ አነሳኝ
ስጦታው ብዙ ነው ለኔ የሰጠኸኝ
ተመስገን ብቻ ነው አምላክ ላንተ ያለኝ
እንደ በርጠሜዎስ እውር የነበርኩኝ
ዛሬ ግን በአምላኬ ድኅነት አገኘሁኝ
ሕጉ ለመንገዴ ብርሃን ሆኖኛል
የእርሱ ስለሆንኩኝ ሰላሙን ሰጥቶኛል
በድንቅ አጠራርህ በፍቅር የጠራኸኝ
ከአጋንንት እስራት ነፃ ያወጣኸኝ
አልፋና ኦሜጋ ዘላለም የምትኖር
ኤልሻዳይ የሆንከው አማኑኤል ተመስገን
የዕዳ ደብዳቤዬን ጌታ የቀደደው
የማዳኑን ስራ በዓይኔ አይቻለሁ
ቸርነቱ አያልቅም ድንቅ የሆነ ጌታ
ስሙን እናወድስ እንዘምር በእልልታ

312. ረድቶኛልና እግዚአብሔር ይመስገን

በወጀብ በዐውሎ ውስጥ በመከራዬ ቀን /፪/

ረድቶኛልና እግዚአብሔር ይመስገን

አድኖኛልና እግዚአብሔር

313. የወደደኝ ጌታ

የወደደኝ ጌታ ምን አድርጌለት ነዉ
ብዘምርለትም ያንስበታል ይኸዉ
ከወድቀቴ አንስተህ ድካሜን ያገዝከኝ
ሰባራውን ድልድይ ገጥመህ ያሻገርከኝ
በኢያሪኮ መንገድ ስለምን ቁጭ ብዬ
ብርሃን እጅግ ናፍቆኝ ከሰው ተገልዬ
የብርሃን ጌታ ወደእኔ መጣና
አይኔን አበራልኝ በእጁ ዳሰሰና
ለብዙ ዘመናት አልጋ ላይ ተኝቼ
የሚረዳኝ አጣሁ ጠሉኝ ዘመዶቼ
የኔ ጌታ አምላኬ ወደኔ መጣና
አልጋህን ተሸከም አለኝ ፈወሰና
አስራ ሁለት አመት ደም እየፈሰሰኝ
ምራቅ እየተፉ ሁሉም ሲያንቋሸሹኝ
የጌታዬን ልብሱን ጫፉን ብዳስሰው
ኃይል ከእርሱ ወጣ ደሜን ቀጥ አረገው
ሰካራም ዘማዊ ወንበዴ ነበርኩኝ
የአመፀኞች መሪ ደምን ያፈሰስኩኝ
ዛሬ ግን ታሪኬን ጌታ ቀይሮታል
ለኃያሉ እግዚአብሔር ምስጋና ይገባል

314. አይሰለቸኝም

አይሰለቸኝም ከቶ ውዳሴ መዝሙር ቅኔ
ብዙ ነው ያረገልኝ እግዚአብሔር በዘመኔ
ቸርነትና ፍቅሩን ያላራቀ ከባሪያው
በለመለመው ስፍራ በጎቹን የሚያሰማራው
ታላቅ ነው የኛ ንጉሥ ታላቅ ነው የኛ ጌታ
መጽሐፉን የዘረጋ ማሕተሙን የፈታ
አንገቱን ፍፁም ደፍቶ ቀና እንድል አድርጎኛል
እየቃተተ ሞቶ በሕይወት አቁሞኛል
አልችልም የእርሱን ፍቅር መዘርዘርና ማውራት
ውለታውን ለመግለፅ የለኝም ብርቱ ቃላት
ያንተ ክንድ የማይንደው ተራራ ጋራ የለም
ወጥቻለሁ ከጥልቁ ታላቅ ነህ ዘለዓለም
የተከፈተ ደጃፍ ሰጥተኸኛል በፊቴ
ተመስገን ክበርልኝ ንገሥልኝ አባቴ
ለይተህ የጠራኸኝ ያበዛህልኝ ፀጋ
ትዝታዬ ነህ ጌታ ሲመሸና ሲነጋ
ወዳጅና ዘመዴ ብዬ ስጠራህ ልኑር
ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ለወጠኝ ያንተ ፍቅር

315. ኑ በእግዚአብሔር

ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን /፪/
ለታላቁ ክብር ለዚህ ያበቃን
ከሞት ወደ ሕይወት ላሸጋገረን
ኑ በእግዚአብሔር ኑ በድንግል ደስ ይበለን
የሰማዩን መንግስት ርስቱን የሰጠን
ከጨለማ አውጥቶ ብርሃን ላሳየን
ለዚህ ድንቅ ውለታ ምስጋና ያንሰዋል
በእርሱ ደስ ይበለን ክብር ይገባዋል
ከአለት ላይ ውሃ ፈልቆ ጠጥተናል
ሰማያዊ መና አምላክ መግቦናል
ፍቅርህ የበዛ ነው ምን ልክፈልህ ጌታ
ስምህን ላመስግነው ከጧት እስከ ማታ
በቃዴስ በረሃ ምንም በሌለበት
በኤርትራ ባሕር ወጀብ በበዛበት
ለእርሱ መንገድ አለው ከቶ ምን ተስኖት
ልባችሁ አይፍራ በፍፁም እመኑት
በባርነት ሳለን በድቅድቅ ዓለም
ብርሃንን አገኘን በድንግል ማርያም
ያጣነውን ሰላም ዛሬ አገኘን
እጅግ ደስ በለን በእመቤታችን

የሃና የኢያቄም የእምነታቸው ፍሬ
በእግዚአብሔር ፈቃድ ተወለደች ዛሬ
የኢያቄም ስዕለቱ የሃና እምነት
ለምኚልን ለኛ ኪዳነ ምህረት

316. ለኔስ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ

ለኔስ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሻለኛል /፪/
መታመኛዬ እርሱ ነውና
ይገባዋል ክብርና ምስጋና
ሕጉን እያሰብን እንቅረብ ወደርሱ
ይምረናልና መሐሪ ነው እርሱ
በልባችን ይንገሥ ይግባ ከቤታችን
የሕይወታችን ዋልታ እርሱ ነው ተስፋችን /፪/
ከቶ አላገኝም እርሱን የሚመስል
ነፍሴን የሚያከብራት የሚሰጠኝ ኃይል
በመከራ ሰዓት ከክፉ የሚያድነኝ
ከየት አገኛለሁ መጠጊያ የሚሆነኝ /፪/
በለመለመ መስክ መሸሸጊያዬ ነው
በሰላም ወጥቼ በሰላም ገባለሁ
ተስፋዬ እርሱ ነው ይመራኛልና
ዘወትር አቀርባለሁ ክብርና ምስጋና
ዘወትር አቀርባለሁ ለአምላኬ ምስጋና

317. በፍቅር ተስቦ

በፍቅር ተስቦ ወረደ ለእኛ ሲል
የፍቅሩን ፍፃሜ ገለጸው በመስቀል
ለኛ ያላረገው ከቶ ምን አለና
አፋችን ዝም አይበል እናቅርብ ምስጋና
ደስ ይበለን ሰያማትን ቀዶ
›› ታላቁ አባታችን
›› የዘመናት ንጉሥ
›› ኢየሱስ ጌታችን
›› የኤፍራታው ህፃን
›› በዳዊት ከተማ
›› ተወልዶ ማደሩ
›› ምስራች ተሰማ
እንዳተ ያለ በኃጢአት ውስጥ ወድቀን
›› ስንኖር ተጎሳቁለን
›› አምላክ የኔ ጌታ
›› ከሞት ውስጥ አዳንከን
›› ዝናውንም አውሩ
›› ለአህዛብ ሁሉ
›› እንደ እግዚአብሔር ያለ
›› ማንም የለም በሉ
ደስ ይበለን ወረደ ወደምድር
›› ሰላሙን ሊሰጠን
›› ሰላም ለእናንተ ይሁን
›› ብሎ ሊሰብክልን
›› በመስቀል ተሰቅሎ
›› እኛን የተቤዠን
›› ከሲኦል እስራት
›› በፍቅሩ የፈታን
ሃሌሉያ ምስጋና በሰማይ
›› ምስጋና በምድር
›› ሁሉን ቻይ ለሆነው
›› ለቸሩ እግዚአብሔር
›› ሃሌሉያ ለእርሱ
›› ለነፍሳችን ጌታ
›› ዝማሬን እናቅርብ
›› ከጧት እስከማታ

318. ስሙ በክብር

ስሙ በክብር ከፍ ከፍ ብሏልና /፪/
ለታላቅ ስሙ ለቅዱስ ስሙ ይድረሰው ምስጋና /፪/
ሕዝቡን እየመራ ያሻገረ
ባሕረ ኤርትራን ከፈለ
ጠላቶችም ውሃ ከደናቸው
ሕዝብህም በደስታ እልል አለ
ለታላቅ ስሙ ለቅዱስ ስሙ ይድረሰው
ምስጋና /፪/
ፈረሰኛውና ፈረሶቹ
አልቻሉም ባሕሩን ለመሻገር
እርሱ ቆሟልና ከፊታቸው
ድንቅን የሚሰራ እግዚአብሔር
ለታላቅ ስሙ ለቅዱስ ስሙ ይድረሰው ምስጋና /፪/
ጉልበቴ ነህ ኃይሌ ዝማሬዬ
ብለው ተቀኙለት እነሙሴ
ከበሮውን ያዙት እነ ማርያም
ውዳሴ ሊያቀርቡ ለሥላሴ
ለታላቅ ስሙ ለቅዱስ ስሙ ይድረሰው
ምስጋና /፪/
ተዋጊ ነው አሉት ድል አድራጊ
እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚራራ
ቀላያትን ከድኖ የሚያሰጥም
ልጆቹን በቃዴስ የሚመራ
ለታላቅ ስሙ ለቅዱስ ስሙ ይድረሰው ምስጋና /፪/

319. ገና እንዘምራለን

ገና እንዘምራለን /፬/
እንደ መላዕክቱ ብርሃንን ለብሰን
ገና እንዘምራለን
ወላዲተ አምላክን ከፊት አስቀድመን
በዳዊት በገና መሰንቆ ታጅበን
በሥላሴ ክብር ገና እንዘምራለን
ገና እንዘምራለን
በምሥጋና ስርዓት ከሠለጠኑት ጋር

ልብን የሚያስደስት መዝሙር እየዘመርን
ያልተሰማ ዜማ ያልታየ ምስጋና
ይፈልቃል አይቀርም ከእኛ ልቦና
ገና እንዘምራለን
በትዕቢትም ሳይሆን በታላቅ ትህትና
በልዩ ተመስጦ በፍቅር ልቦና
ሥራችን ይሆናል ለአምላክ ምስጋና
ገና እንዘምራለን
ዳዊት በተመስጦ እርቃኑን ቢሆንም
ሜልኮል በዝማሬው ብትስቅበትም
አምላክ ከወደደ እንዲያመሰግነው
በደስታ እንዳይዘምር ከልካዩ ሰው ማነው
ገና እንዘምራለን

320. ማን እንደርሱ

ማን እንደ እርሱ እንደ እግዚአብሔር
ቸርነቱ ብዙ በሰማይ በምድር
ሞገድና ነፋስ የሚታዘዙለት
አብርሀት ቀላያት የመሰከሩለት
ህቱም መቃብርን ሳይከፍት የተነሳ
ነፍሳትን አዳነ ከሲኦል አበሳ
ፈዋሴ ድውያን አርነቱ ብዙ
የፀጋ ልብሳቸው ጽድቅን ለታረዙ
የተዋረዱትን ከፍ ከፍ የሚያደርግ
ለባልቴቷ ዳኛ ፈራጅ ለደሀ አደግ
የጠፋውን አዳም ሊፈልግ የመጣ
ከባርነት ዓለም ከሲኦል ያወጣ
ብርሃን ዘበአማን ጨለማን ያራቀ
ሰውን ከራሱ ጋር ሞቶ ያስታረቀ
በመከራ ሳሉ ሕዝቦቹን ያሰበ
ሥጋውና ደሙን ቆርሶ የመገበ
ከባቴ አበሳ ምሕረቱ የበዛ
ጌታችን እርሱ ነው የነፍሳችን ቤዛ

321. የማይደፈር

<u>የማይደፈር ግሩም ነው</u>
<u>በእኛ ዘንድ ግን ትሁት ነው</u> /፪/
<u>ስለኛ ሲል ተዋረደ</u>
<u>አማናዊው በግ ታረደ</u> /፪/
በትህትና ገባ ወደ መንደራችን
አደረ ከእኛ ጋር ፍቅር ነው ጌታችን
አየነው ዳሰስነው ከሱ ጋራ በላን
ተሞላን በረከት የሐዲሱን ኪዳን
ባዶ አደረገ እራሱን ስለኛ
ሳይተኛ ጠበቀን ታማኙ እረኛ
ደቀቀ ተመታ የቤልሆር ጉልበት
የመለኮት እሳት ፊቱ ቢነድበት
እኛ ግን ጨበጥነው ያንን ግሩም እሳት
ሰውነታችንን በክብር ስላያት
ከገናናው ክብር ጽኑ ድምፁን ሰማን
ክፉዎች ወደቁ እኛን ግን አጽናናን
በጠባቡ ደረት እኛንው መሰለ
ሞታችንን ወስዶ ጌታ ተሰቀለ
አጣንለት ቋንቋ ለመግለፅ ማዳኑን
ገባን ከርስታችን ይዘን ማሕተሙን

322. በዘባነ ኪሩብ

በዘባነ ኪሩብ ለሚቀመጠው
በእሳት ድንጋዮች ቅጥሩን ላጠረው
ዘምሩ ለእግዚአብሔር ለጌታ ዘምሩ
የተከበረ ነው በሰማይ በምድሩ /፪/
ኢሳይያስ ሲያየው እጅግ አፈረ
የተፈራ ነው የተከበረ
የሰማይ ደጆች ተንቀጠቀጡ
ለቅዱስ ስሙ ክብርን ሲሰጡ
ያልተቀደሰ ለምጽ ያነነደደው
እንዴት ይችላል ሊመሰግነው
በል ፍቀድልን ፍቅር ነህና
ልግባ መቅደስህ ላቅርብ ምስጋና
ዙፋንህ ታየኝ ትምክህቴ ሆይ
ስትመሰገን በሰማይ ላይ
ሲያመሰግንህ የተደሰተ
ባይተዋር አልሁን አልውጣ ካንተ
ቅኔ ሞላበት ያንን ሰገነት
ልቀላቀለው ተመኘሁ በእውነት
ልዘምርህል ባይገባኝም
ዝም የሚል ልሳን አልሰጠኸንም

323. ስላደረክልን

ስላደረክልን ስለውለታህ
ስለ ፍፁም ፍቅርህ ስለ ስጦታህ
የቅዱሳን አምላክ እናመሰግንህ /፫/
ተራራው ሸለቆው ላንተ ልሳን አለው
ያመሰግኑሀል ትህትናህ ብዙ ነው
ነፍሳት ያከብሩሀል በሰማይ ጉባኤ
እኔም ላመስግንህ እንደችሎታዬ
ካህናት ተንስኡ ቁሙ ለማህሌት
ክብሩን ተናገሩ በቀንና በሌት
ልባችን ይመሰጥ ይውጣ ወደሰማይ
በመንፈስ ዘምሩ ለአምላክ አዶናይ
በከበረ ደሙ መቅደሱን የሠራ
የማጠይፋ መቅረዝ በውስጡ ያበራ
ከቶ ለታደገን ከኃጢያታችን
ይመስገን እግዚአብሔር ቸር አምላካችን
ከበሮውን አንሱ እንደ ሙሴ እህት
በቅኔው ማህሌት እንዘምርለት
ጸናጽሉም ይጨሐ ለከበረ ስሙ
እረኛ ነውና ንጉሥ ለዓለሙ

324. ወደ ማደሪያው

ወደ ማደሪያው ገብቼ ልስገድ ለእግዚአብሔር
ምስጋናንም ላቅርብ ስለ ስሙ ክብር
አድርጎልኛልና አመሰግናለሁ
በአፀደ መቅደሱም እሰግድለታለሁ
በፊቱ ለመቆም ማልጄ እነሳለሁ /፪/
በመከራዬ ቀን ሆኖኛል መከታ
ቤቱ ተገኝቼ በፍፁም ደስታ
የከንፈሬን ፍሬ ልሰዋ በእልልታ /፪/
አስር አውታር ባለው በበገና
በመላዕክቱ ፊት ለማቅረብ ምስጋና
የአፌንም ነገር ሰምተኸናልና /፪/
ለስሙ ልንበርከክ ለርሱ እንደሚገባ
ስዕለቴን ልፈጽም ላቅርብለት መብዓ
ወደ አደባባዩ በምስጋና ልግባ /፪/
አሸበሽባለሁ ድምፄን አሰምቼ
በቤተ መቅደሱ ሌሊት ተገኝቼ
እንደ ካህናቱ እጆቼን ዘርግቼ /፪/

325. ዝም አትበሉ

ዝም አትበሉ እግዚአብሔር አመስግኑ /፪/
ቅዱስ /፫/ ሥሉስ ቅዱስ በሉ
መላዕክትን ሁኑ ምስጋናን ጀምሩ
ቅዱስ ቅዱስ በሉ
የሙሴ እህት ማርያም ከበሮውን አንሺው
በምስጋና መዝሙር እስራኤልን ጥሪው
አምላክን እናግንን እንዘምር በእልልታ
ከኛጋር ይሆናል <u>የሠራዊት ጌታ</u> /፪/
ፍጥረታትም ጩኹ ሰማያት ዘምሩ
ስለቅድስናው ውዳሴን ጀምሩ
ዳዊት ሆይ ተነሳ ስለ ጽዮን ዘምር
ከበሮ ይመታ <u>በገናው ይደርደር</u> /፪/
ወገኖች እንዘምር ለእግዚአብሔር ክብር
ውለታው ብዙ ነው ለኛ ያለው ፍቅር
ማዳኑን ያያችሁ ዘምሩ በእልልታ
ለጌታ ለእግዚአብሔር <u>ለሠራዊት ጌታ</u> /፪/
ባሕሩን አቋርጦ ወንዝ ያሻገራቸው
ተራራውን ንዶ ያቀለለላቸው
በአውሎ ነፋስ መሐል መንገድ አለው ጌታ
ለንጉሥ ክርስቶስ <u>እንዘምር በእልልታ</u> /፪/

326. በበጎ ፈቃዱ

በበጎ ፈቃዱ ሁሉ በእርሱ ሆነ /፪/
ነገር ሁሉ በእርሱ ተከናወነ /፪/
ሰማይና ምድር ክብሩን ተናገሩ
ፈጥሯቸዋልና እንዲገለጥ ክብሩ
በፈጠረው ፍጥረት የሚታወቅ እርሱ
እግዚአብሔር ይመስገን ስሙን አወድሱ
አልሆነም ለእርሱ ፍፁም አንዳች ነገር
ብንመረምረው በሰማይ በምድር
ፈቃዱ ነውና መልካምና በጎ
ፈጥሮ አሳይቶናል ሁሉን ውብ አድርጎ
ክረምትና በጋ ሌሊትና ቀን
ሁሉን አሳይቶ ጌታ አስተማረን
ያደረገው ሁሉ እንከን የሌለው
ለዚህ ቅዱስ አምላክ ምሳሌም የለው
ያዘነውን ያውቃል ደስም ያለውን
ሁሉ በእርሱ ፈቃድ ስለሚከወን
ችግርና ደስታ ለበጎ ነውና
ይሕን ላስተማረን ይድረሰው ምስጋና

327. የሕይወት እንጀራ

ኑ የሕይወት እንጀራ እንብላ የሕይወት እንጀራ /፪/

ለዘለዓለም በቤቱ እንኖራለን

ድውያነ ሥጋ ጸጋው የራቃችሁ

በሥጋም በነፍስም ጽድቅ የተራባችሁ

ለመዳኑ ሕይወት አምላክ ሲጠራችሁ

በፍርሐት ቅረቡ ወደ ፈጣሪያችሁ

ሥጋውን ፍሪዳ አድርጎ ሰጥቶናል

ደሙን መጠጥ አድርጎ በፍቅር አድሎናል

ከዚህ ሰፊ ማዕድ ቅረቡ ይለናል

ከቅዱሳን ጎብረት ይቀላቅለናል

ኑ ወደኔ ይላል የዓለሙ ሁሉ ቤዛ

ጊዜአችን አይለፍ በዋዛ ፈዛዛ

ሥጋውን ካልበላን ንስሐ ገብተን

ደሙንም ካልጠጣን ከኃጢአት ርቀን

በመጨረሻው ቀን እዳ አለብን

328. ምስጋናዬን

ምስጋናዬን ለአምላኬ አቀርባለሁ
በማደሪያው ገብቼ እሰግድለታለሁ
ኤልሻዳይ ነው ጌታ ሁሉን ቻይ
<u>ይፈፀማል አምናለሁ የልቤ ጉዳይ</u> /፪/

ዘንባባዬን ይዤ እንደ ህፃናቱ
ሆሳዕና ልበለው ሰግጄ በፊቱ
ምንም ባዶ ብሆን እውቀት ቢጎለኝ
ለስሙ ልዘምር ከልካይም የለኝ
የሕይወት ትርጉሜ አንተ ነህ ደስታዬ
ስምህን ማገልገል ክብሬ ነው ስራዬ
ለታመነው ጌታ ምስክር የሆኑ
ከብረው ተመለሱ ለበረከት ሆኑ /፪/
አምላኬ በፊትህ ቃል አለብን እኔ
ቋንቋዬ መዝሙር ነው ያንተ እንደመሆኔ
በአሚናዳብ ደጃፍ በቅድመ ታቦቱ
ያየክብርህ ዑደት ጠራኝ ማህሌቱ
መነሻዬ አንተ ነህ ጉልበቴና ክብሬ
መድረሻዬም አንተ መደምደሚያ ቅጥሬ
በጽዮን ተራራ ስትገለጥ ያኔ
ነጩን ልብስ አልብሰህ አስነሳኝ ለቅኔ /፪/

329. አማን በአማን

አማን በአማን /፬/ አማኑኤል ተመስገን
ለዚህ ፍቅርህ ምን ልበልህ
ድብቁን ኃጢአት አንተ ብትገልጠው
ይቅር ብለኸኝ ባትሸፋፍነው
እንደ ሰው በቀል ቢሆርህ ጌታ
የኔ ኃጢአትስ የለውም ቦታ
በየደቂቃው ኃጢአት ስሰራ
ስሰርቅ ስበድል አንተን ሳልፈራ
አንተ ግን ፊትህ ምንም ቢቀየም
በቁጣህ በትር አልገረፍከኝም
ምህረትን ልከህ አድነኝ ዛሬ
ታክቶኛልና በኃጢአት መኖሬ
ዓለም በኃጢአት እየሳበችኝ
በፍቅር በደስታ መኖር አቃተኝ
የኃጢአት ኑሮ ጣፋጭ ቢመስልም
ውጤቱ መሮ ፍፁም አይጥምም
እንደ በደሌ ስላልከፈልከኝ
ተመስገን እንጂ ሌላ ምን አለኝ

330. ደስ ይበለን

ደስ ይበለን ደስ ይበለን
አምላክ አለ መሀላችን
ምን ይከፈል ለዚህ ሥራህ
ገናና ነው አምላክ ክብርህ
ምሕረቱን አይተናልና
አድርሶናል አምላክ በጤና
ይሕችን እድሜ የጨመረልን
ለንሰሐ ጊዜ የሰጠን
ኃጢአትህን ይታገስሀል
በቸርነት አምላክ ያይሀል
ደስታ ነው በሰማያት
በአንድ ኃጥእ የጽድቅ ሕይወት
እልል በሉ የጎበኛችሁ
በምሕረቱ አምላክ ያያችሁ
በችግር ቀን ያሰበን ሁሉ
አመስግኑ ዝምም አትበሉ
ድንግል ማርያም ትፀልያለች
ኃጥኡን ሰው ማረው እለች
በድንግል ክብር እንኖራለን
በቸርነት አምላክ እያየን

331. ባርከን ባርከን

ባርከን ባርከን ልጆችህን ባርከን
በቅዱስ መንፈስህ አንድ ሐሳብ አድርገን /፪/
ባርኪን ባርኪን ልጆችሽን ባርኪን
ድንግል ሆይ በምልጃሽ አንድ ሀሳብ
አድርጊን
ድንግል ሆይ በምልጃሽ ከልጅሽ አስታርቂን
ጥሪህን ስንሰማ ወዳንተ እንድንመጣ
በሕግህ ልንኖር ከቤትህ ሳንወጣ
በሕይወት ስንደክም እንዳንጠፋ በዓለም
እርዳን ፈጣሪያችን ቸሩ መድኃኔዓለም
ከተፈረደብን ባርነት ሕይወት
ከመጣብን መርገም በመብል ምክንያት
ከሲያል እስራት እኛ የዳንብሽ
ድንግል ሆይ ምን ጊዜም አይለየን ምልጃሽ
አንድነት ስናጣ ፍቅር ስትመነምን
በምግባር ስንደክም ሲጎድል እምነታችን
በሥጋችን ፈቃድ ወድቀን እንዳንጠፋ
በምሕረትህ ጎብኘን አንተ ሁነን ተስፋ
ርህርህተ ሕሊና ቅድስት እናታችን
አሳሳቢ ሁል ጊዜ ስለ ኃጢአታችን
ሊያድነን ነውና ክርስቶስ መሞቱ
አስምሪን እመአምላክ ድንግል ወላዲቱ

332. ሃሌሉያ

ሃሌሉያ በሰማያት ላለው
ዓለማትን ፈጥሮ ለሚገዛው
እዘምራለሁ እቀኝለታለሁ
ጌትነቱን ክብሩን አደንቃለሁ
ገናና ነው ክብርን የተሞላ
ድንቅ የሚያደርግ የለም ከእርሱ ሌላ
ጉልበት ሁሉ ለስሙ ይሰግዳል
ከአማልክት እርሱን ማን ይመስላል
በልብሱ ዘርፍ መቅደሱ ተሞልቶ
ስለ ክብሩ በገናው ተቃኝቶ
ምስጋናችን በእጣኑ ጢስ ሲያርግ
ይመስጣል ያ የሰማዩ ሰርግ
ሲቀኝለት ዳዊት በማጎሌት
ቅዱስ ሲሉ ሱራፌል በጎብረት

ከዙፋኑ ምሕረት ይታወጃል
በምድራችን ሰላም ፍቅር ይሰፍናል
መሠወሪያው የእሳት ነበልባል ነው
ሠረገላው ነፋስ ደመና ነው
የእግዚአብሔር ስም የፀና ግንብ ነው
ለሚፈሩት ኃይልና ብርታት ነው

333. ባለውለታዬ

ባለውለታዬ ባለውለታዬ
ከአመድ ያነሳኸን ከትቢያ ተጥዬ
ተመስገን ጌታዬ
በሩን ቢዘጋብኝ ስምኦን ጨክኖ
ዝቅ አድርጎ ቢያየኝ ከአይሁድ ጋር ሆኖ
እንድቀርብ ወደሱ አዘዘ ጌታዬ
እግሩን አጥበዋለሁ ወድቄ በእንባዬ /፪/
የቀራጭ አለቃ ቢሆንም ስራዬ
እንድወርድ ከዛፉ አዘዘ ጌታዬ
ማዕረጌን መሸከም እስኪያቅተኝ ድረስ
ቤቴ ተባረከ በኢየሱስ ክርስቶስ /፪/
ድንጋይ የጨበጡ ፈራጆች ከበውኝ
ነውሬን ዘርዝረው ጌታ ፊት አቆሙኝ
ፈረድችባቸው ኃጢአትም በእነርሱ
በሰላም ሂጅ/ድ ብሎ ምሮኛል ንጉሡ /፪/
የማምነውን አምላክ አውቀዋለሁ እኔ
በሰራልኝ ሥራ በዕድሜ በዘመኔ
ፍቅሩን ተሸክሟል የልቤ ትከሻ
ልለየው አልቸልም እስከመጨረሻ /፪/

334. እግዚአብሔር ኃያል ነው

እግዚአብሔር ኃያል ነው የሚሳነው የለም
በዙፋኑ ጸንቶ ይኖራል ዘለዓለም
ማዕበሉን ከፍሎ ሕዝቡን ያሻግራል
ለሰው የሚሳነው ለርሱ ግን ይቻላል
ማዳንና ጥበብ ኃይል በእጁ ሆኖ
ለሰው የማይቻል ለርሱ ቀሊል ሆኖ
ፈጥኖ ይጎበኛል የምስኪኑን ጓዳ
ፈፅሞ አይዘገይም ጌታ ሲሰናዳ
አንዱን እየሻረ አንዱን እየሾመ
የተዋረደውን ክብር እየሸለመ
ከኋላ ያለውን ከፊት አሳልፎ
በጎ ቀን ያመጣል ጨለማውን ገፎ
እንደ ቋጥኝ ቢከብድ የሕይወት ፈተና
ሰውን የሚያፀና አምላክ አለንና
ደስ ያሰኛል እርሱ መከራን አጥፍቶ
ታግሶ የቆመ ማን አፈረ ከቶ
የሚያስፈራ ጊዜ ቢመጣ ክፉ ቀን
እናልፋለን እኛስ እግዚአብሔርን ይዘን
ወራት ከብዶባችሁ ያጎነበሳችሁ
ታሪክ ሆኖ ያልፋል እግዚአብሔር ሲያያችሁ

335. ዘምር ዘምር አለኝ

ዘምር ዘምር አለኝ ልቤ ተነሳሳ /፪/
የአምላኬን ቸርነት እንዴት ብዬ ልርሳ
ያደረገልኝን እንዴት ብዬ ልርሳ
የሚቃጠለው ስብ በፊትህ ምንድነው
ሰማይና ምድር ሁሉም ገንዘብህ ነው
ያለኝን ሰብስቤ ላኑረው በፊትህ
ዋጋ አይሆንም ጌታ ስለቸርነትህ
ይበዛም ይሰፋል እግዚአብሔር ምስጋና
አይቆምም በዘመን ማዕበል ነውና
እንኳን ድንጋይ ቀርቶ ጋራው ቢናድብኝ
የከንፈሬን ፍሬ ማንም አይወስድብኝ
የጳውሎስ የሲላስ መከራው ቢፀና
አልተውም ቅኔውን የአምላኬን ምስጋና
ሊያስጥለኝ አይችልም እስር ሰንሰለቴ
አለብኝ ውለታ የሰማይ አባቴ
የተደረገለት ብዙ የተቀበለ
ይኖራል በፍቅሩ እየተቃጠለ
ክብሬን ሁሉ ትቼ ልዘምርልህ
ይህ ነው ችሎታዬ ላንተ የምሰጥህ

336. ወዶናልና

ወዶናልና ዳግም አይጠላንም
አይቶናልና መቼም አይረሳንም
ወረት የሌለው ታማኝ ቅዱስ ጌታ
ከኛ ጋራ ነው ሁሌ ጠዋት ማታ
ከድቅድቁ ዓለም ከጨለማው ስፍራ
ወደሚደነቅ ብርሃን እየጠራ
ሕዝቦቹ ሳንሆን ሕዝቦቹ አረገን
እስራኤል ዘነፍስ ርስት አገኘን
ጥበበቦችን ለማሳፈር ብሎ
ሥጋን ለበሰ ሁላችንን መስሎ
በእግዚአብሔር ልጅ ሞት ሕይወት አገኘን
ነፃነት ሰጠን እልል እልል እንበል
ብራብ ምግቤ ነው ብጠማ መጠጤ
ብታረዝ ልብሴ ብቸገር ምርኩዜ
ኃይሌ ብርታቴ መጽናኛዬ እርሱ ነው
የጠላቶቼን ክንድ የሰባበረው
ጠላት ቢከበን ቀስቱን ሰይፉን ስሎ
ሊያጠፋን ቢጥር ዲያብሎስን መስሎ
ዳዊትን ረድቶ ጎልያድን የጣለ
የእስራኤል አምላክ መሐላችን አለ

337. ዝናውን ሰምቼ

ዝናውን ሰምቼ ፈለግሁት

በሾላ ላይ ሆኜ አየሁት
ካንተ ጋር ነን አለኝ መድኃኒቴ
ዛሬስ መዳን ሆነልኝ ለቤቴ
የረከሰው ቤቴን ጌታዬ ሳይንቀው
ጨለማውን ገፎ ብርሃን አለበሰው
ለገናናው ስሙ ለርሱ ተንበርክኬ
ዛሬስ ተለወጠ ጎስቋላው ታሪኬ
ካለኝ እኩሌታ ለደሀ እሰጣለሁ
የበደልኩትን ሰው እጥፍ እክሳለሁ
ያንተ ካደረከኝ ያንተ ነኝ ብያለሁ
ንገስብኝ አምላክ እገዛልሃለሁ
እንደምን ወደደኝ ምን አግኝቶ ከእኔ
ሕይወቴ ያደፈ ነው የገባሁ ኩነኔ
እሱ ግን ጎበኘኝ በማዳን አዋጁ
ስሙን አተመብኝ አደረገኝ ልጁ
የአብርሃም አምላክ የእስራኤል መና
የጠፋን ሊፈልግ ዳግም መጥቷልና
እኔንም ጎበኘኝ በማዳኑ ጥሪ
የውለታው ከፋይ ነፍሴ ሆይ ዘምሪ

338. በመጨረሻው

በመጨረሻው አንነሳለን ከሙታን
ጌታ ሲመጣ በአየር ሆነን እያየን
ብርሃን ነው ለሚኖሩ ይህ ክብር
የሚናፈቅ ነው በልቦናቸው የሚያድር
የስንዴ ቅንጣት ትንሳኤ ካላት በምድር
ተስፋ አለን እኛም በሰማይ ሀገር ልንኖር
ፀሐይ ስትጨልም ከዋክብትም ሲረግፉ
ምድርና መላዋ ለዘለዓለም ሲያልፉ
በሰማይ ኃይላት ንውጽውጽታ ሲሰማ
ጌታ ይመጣል በመለኮቱ ግርማ
እልፍ አእላፋት መላእክቱ ሲታዩ
ብርሃን ሲሞላ ምድርና ሰማዩ
የምድር ዳርቻ በንፋስ ኃይል ሲመታ
ከጭንቅ አድነን አማኑኤል የኛ ጌታ
ለሚታመኑ በሃይማኖት ለጸኑ
ይታያል በግልጽ የጌታችን ማዳኑ
በምድር እያሉ ኃጢአትን ለሚሰሩ
ያስደነግጣል ያስፈራቸዋል ክብሩ
ጌታ በዚያን ቀን እንዳንጣል በሲኦል
በቅዱስ ስምህ ይዘናል ተማጽነናል
በበደላችን እንዳትከፍለን አደራ
እንደ መርገም ነው ጌታ ሆይ የኛ ሥራ

339. ተነሡ እንዘምር

ተነሡ እንዘምር /፫/ ለአምላክ ባንድ ቃል

ሁላችንም እንጂ ወንድ ሴት አንበል

ተነሡ እንዘምር ለአምላክ ባንድ ቃል

የአምላክ ምስጋና ምን ያሳፍረናል

እንኳንስ እርሱና ሰው ይመሰገናል

ለሚያወርድልን ዝናመ ምሕረትን

ደግሞም ለሚሰጠን እክለ በረከትን

ሁሉንም በጊዜው ለሚሠጠን ጌታ

መዘመር አለብን ሁላችን በእልልታ

340. ሀበነ እግዚኦ

ሀበነ እግዚኦ ዓዕይንተ አእምሮ ወትረ
ኪያከ ይርአያ /፪/
ወአእዛንኒሃ ቃለ ዘባህቲትከ ይስምዓ /፪/

341. የዘመናት ጌታ

የዕለት የዓመት የዘመናት ጌታ
ለዚህ ላደረስከኝ ዘመኔን ሳትገታ
አቀርብልሃለሁ የክብር ሰላምታ /፪/
ኑ እናመስግን ከልባችን የሰማዩን አባታችንን
ለዚህ ዕለት ለዚህ ዓመት ላደረሰን ሁላችንን
የሰው ልጆች እድሜ ጥንቱንም ሲጀመር
ምን ቢወጣ ቢወርድ ቢበዛ ቢደመር
አንድ ቀን አይሞላም እንደ አንተ አቆጣጠር /፪/
ስለዚህ አምላክ ሆይ ንዑድ ነው ክቡር ነው
ወደ አንተ እንዲመለስ ቀን የሰጠኸው ሰው
ደካማ ነውና ሰው እድሜ ከራበው /፪/
እጅግ አደንቃለሁ የአምላክን ጥበብ
ምድርን በአበባ ሰማዩን በኮከብ
እንዳሸበረቀ አስተውዬ ሳስብ /፪/
ከንቱ ካሳለፍኩት ጊዜዬን በዋዛ
ምን ያደርግልኛል ዘመኔ ቢበዛ
ደግሞም በጠቅላላው ዓለምን ብገዛ
ወርኃ ክረምት አልፎ መስከረም ሲጠባ

ምድር በልምላሜ ስታጌጥ በአበባ
እናምናለን ለአንተ ምስጋና አንዲገባ /፪/

342. እስመ ለዓለም ምህረቱ

እስመ ለዓለም ምሕረቱ /፪/
አያልቅም ብዙ ነው የአምላክ ቸርነቱ
አመስግኑት ጌታን ሁላችሁ በአንድነት
መሐሪ ነውና ለሰው ልጆች ሕይወት
የማይሞተው ሞቶ የተቀበረው /፪/
ከገሃነም እሳት እኛን ሊያድን ነው /፪/
በፈጠረው ፍጥረት እጅግ ተሰቃይቶ
ነፍሳትን አወጣ ከሲኦል ለይቶ /፪/

343. ተናገሩ

ተናገሩ ድንቅ ሥራውንም መስክሩ /፪/

ተአምሩን ለዓለም ንገሩ /፪/

ድንቅ ሥራውን መስክሩ

344. ልዑል እግዚአብሔር

ልዑል እግዚአብሔር /፪/ ምስጋና ይገባሃል /፪/

ለዚህች ዕለት ለዚች ሰዓት በሰላም በጤና አደረስከን

345. ከክርስቶስ ፍቅር

ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየኝ ማነው

መከራ ችግር ስቃይ ወይስ መራቆት ነው /፪/

አንፈራም አንሰጋም አንጠራጠርም

እግዚአብሔር ከኛ ጋራ ይኖራል ለዘለዓለም /፪/

በትጋት ተራምደን እንግባ በጠዋት

በደሙ መሥርቶ ከሠራልን ቤት /፪/

ከቶ የት ይገኛል እንዲህ ያለ ቤት

የውኃ ግዳግዳ የደም መሠረት /፪/

ይኸው እዚህ አለ የአማኑኤል ቤት /፪/

346. አንትሙ

ኦ አንትሙ ሕዝበ ክርስቲያን

በከመ ተጋባዕክሙ በዛቲ ዕለት

ከማሁ ያስተጋብዕክሙ በደብረ ጽዮን ቅድስት

ወበኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም /፪/ አግዓዚት

ትርጉም፡- እናንት የክርስቲያን ወገኖች ሆይ በዚህች ዕለት እንደተሰበሰባችሁ ቅድስት በምትሆን በደብረ ጽዮን ነጻ በምታወጣ በኢየሩሳሌም ይሰብስባችሁ።

347. ሃሌ ሉያ

ሃሌ ሉያ ለእርሱ እንዘምር በእልልታ

ክብር ይገባዋል የሠራዊት ጌታ /፬/

ጽናጽል ከበሮ በገናም ይደርደር

ነፃ ላደረገን ከባርነት ቀንበር /፬/

ለፍቅር ለሰላም ለምሕረት አባት

ይጎሰም ነጋሪት ይነፋ መለከት /፬/

ሁሉ በእጁ ሳለ ድሃ ለሆነልን

የነገሥታት ንጉሥ ጌታችን ይመስገን /፬/

ለገዛልን ርስት በደሙ ለዋጀን

በመስቀል ተሰቅሎ በሞቱ ላዳነን /፬/

ስለኛ ደህንነት ሐፍረትን ለናቀው

ለአማልክት አምላክ ምስጋና ይድረሰው /፬/

እኛ ክርስቲያኖች ሁላችንም ዛሬ

ለዓለም መድኃኒት እናቀርብ ዝማሬ /፬/

ሃሌ ሉያ ለእርሱ እንዘምር በእልልታ

ክብር ይገባዋል ለሠራዊት ጌታ /፬/

ፀናፅል ከበሮ በገናም ይደርደር

ነፃ ላደረገን ክባርነት ቀንበር /፬/

348. ለአምላካችን አንዘምር

ለአምላካችን አንዘምር ለጌታችን እንዘምር /፪/

ብዙነው ውለታው የእግዚአብሔር /፪/

ወደእኛ ለመጣው ከሰማያት ወርዶ

በበረት ለተኛው ከድንግል ተወልዶ

ለሰው ልጆች ፍቅር ሰው ለሆነው ወዶ /፪/

እኛ ለተሰደድን ለተሰደደልን

ተጠምቆና አጥምቆ አርአያ ለሆነን

በበደልነው ሁሉ እርሱ ለካሰልን /፪/

በመስቀል ተሰቅሎ ፍቅሩን ለገለፀው

ዓለምን ለማዳን ደሙን ላፈሰሰው

ለቸሩ ክርስቶስ ምስጋና ይድረሰው /፪/

ለሐዘን ለደስታ ስለደረሰልን

በኑሮአችን ሁሉ ስለቀደመልን

በበጎ ስጦታው ፍቅሩን ላበዛልን /፪/

ስለቸርነቱ ብዙ አድርጎልናል

ታዲያ ለዚህ ሁሉ ምን ይከፈለዋል

ሰዎች ዝም አንበል ማመስገን ይገባል /፪/

349. ኩሉ ከንቱ

ኩሉ ከንቱ ከንቱ ንብረቱ እስመ ኩሉ ኃላፊ ውእቱ /፪/

መድኃኔዓለም /፪/ አድኅነነ /፪/ እሞተ ከንቱ /፪/

ትርጉም፡- ሁሉ ከንቱ ንብረቱ ሁሉ ከንቱ ነው። መድኃኔዓለም ከከንቱ ሞት አድነን።

350. ሁላችን እንጸልይ

ሁላችን እንጸልይ የሃይማኖ ጸሎት /፪/

እንድናውቅ ምስጢሩ /፪/ የተዋህዶ እምነት

የአንድነት ሦስትነት ምስጢሩ ከገባን /፪/

ከቶ ምንም አይኖር /፪/ የሚያደናግረን

የአምላክ ሰው መሆን ምስጢረ ሥጋዌ /፪/

ያስረዳናል በእውነት /፪/ የአንድነት ሕላዌ

የአንድነት ሦስትነት ምስጢሩ ይረቃል /፪/

በሃይማኖት ትምህርት /፪/ ጕልቶ ይታወቃል

ሁላችን እንፀልይ....

351. ኃይሉን ያለብሰኛል

ኃይሉን ያለብሰኛል ቅዱሱ ጌታዬ

የዓይኖቼ ተስፋ ታማኝ ጠባቂዬ

በሰላም ወጥቼ በሰላም እገባለሁ

እግዚአብሔር ሳለልኝ ምንስ እሆናለሁ /፪/

በእርሱ ደስ ይለኛል ፍቅሩን ቀምሻለሁ

በመከራዬ ቀን በእርሱ ድኛለሁ

የዘለዓለም ደስታ በእርሱ ማመኔ ነው

ዓለሙም ንብረቱም ሁሉም ኃላፊ ነው /፪/

ዘመን የማይሽረው ቀን የማይለውጠው

የአብርሃም አምላክ እግዚአብሔር ኃይል ነው

ፍቃዱን ለማድረግ አምላክ ይመራኛል

ሕጉም ለመንገዴ ብርሃን ሆኖኛል /፪/

ጎብኝቶኛል አምላክ ድንቅ አድርጎልኛል

በመስቀል ስቃዩ በደሙ ገዝቶኛል

በእርሱ ደስ ይበለን እንቅረብ ከቤቱ

አያልቅም ብዙ ነው የአምላክ በረከቱ /፪/

352. ዘይክል ኩሎ

ዘይክል ኩሎ ወአልቦ ዘይሰአኖ ለእግዚአብሔር

አምላክ ነዳያን ረዳኤ ምንዱባን

ንሕነ ሀቤከ /፪/ ተማኅፀነ

353. ወዘምሩ ለስሙ

ወዘምሩ ለስሙ /፪/ ሀቡ አኰቴተ ለስብሐቲሁ /፪/

በልቆ ለእግዚአብሔር ግሩም ግብርከ /፪/

ለስሙም ዘምሩ /፪/ ምሥጋናን አቅርቡ ለጌትነቱ /፪/

እግዚአብሔርን /፪/ ሥራህ ድንቅ ነው በሉት /፪/

354. ሁላችን እናቅርብ

ሁላችን እናቅርብ ለአምላክ ምስጋና

እሱን ለማመስገን ተፈጥረናልና /፪/

ዓለምን ላስገኘ በረቂቅ ምሥጢሩ

ለእግዚአብሔር በደስታ ዘምሩ /፪/

በአምላካዊ ጥበብ ሁሉን የፈጠረው

ክብሩ እንዲታወቅ እንዲመሰገን ነው /፪/

ፍጥረታት በሙሉ እንደስጦታቸው

ያመስግኑታል ውለታውን አውቀው /፪/

የበረከት አምላክ እንዲባርከን

እንዘምር ሁላችን በመንፈስ ሁነን /፪/

ለኃያሉ አምላክ ለሠራዊት ጌታ

በገናው ይደርደር ከበሮው ይመታ /፪/

ከጥፋት ለዋጀን በከበረው ደሙ

የዝማሬን መስዋዕት እናቅርብ ለስሙ /፪/

355. መንግሥቱ ዘለዓለም

መንግሥቱ ዘለዓለም /፪/

ወምኩናኑኒ ለትውልደ ትውልድ /፪/

መንግሥቱ ዘለዓለማዊ ነው /፪/

አገዛዙም ለልጅ ልጅ ነው /፪/

356. ለአምላክ ተቀኙ

ዘምሩለት /፬/ እስኪ ለአምላክ ተቀኙለት /፪/

ስለክብሩ ቃኙ ሁልጊዜ አወድሱት

ለፈጠረን አምላክ ስቡህ እንበልለት

ዓለምን ፈጥሮልን እኛን እንዲደላን

ምን እንከፍለዋለን እንበል ተመስገን

ምድርን በአበባ ያስጌጠልን ለእኛ

ብርሃን እንዳናጣ ፀሐይን ዳግመኛ

ውሃ እንዳንጠማ ቀላያትን ፈጥሮ

አድሎናልና እንዘምር በአንክሮ

እስኪ ዘምሩለት እንደመላእክት

እንደ አርባዕቱ እንስሳ ቀንና ሌሊት

ክብርና ምስጋና ይገባዋል ለእርሱ

እንዘምር በእልልታ ገብተን ከመቅደሱ

357. ከሕግ እንዳንወጣ

መጽሐፍ ቅዱስን ሁሉም ያነበዋል

ምዕራፍና ቁጥሩን ሁሉም ይጠቅሰዋል

በዚህ ብቻ አይበቃም ተርጓሚ ያሻዋል

እንደ ፈቃዳችን ብንተረጉመው /፪/

በውጥን የሚያስቀር ስሕተቱ ብዙ ነው /፪/

ከቶ በሰው ፈቃድ ትንቢት እንዳልመጣ

ይመክረናል መጽሐፍ ከሕግ እንዳንወጣ

እንጠይቅ መምህራን ያሉት በደረጃ /፪/

እናንብብ መፃሕፍት ይሁኑን ማስረጃ /፪/

358. አትልፊ በከንቱ

አትልፊ በከንቱ አትድከሚ ዓለም /፪/

ቆርጫለሁ እኔ ከጌታ አልለይም /፪/

እኔ አልገበዝም አልደለልም

ልቤ አያወቀ አምላኬን አልክድም

ዓለምን ለመምሰል እምነት አልለውጥም

በክንቱ ማባበል ከመንገዱ አልወጣም

ሥጋዊ ፍላጐት አያታልለኝም

ዓለማዊ እውቀት አያስታብየኝም

እነዚህ በአንድነት ይጠፋሉ ሁሉም

የእግዚአብሔር ጽድቅ ግን ይኖራል ለዘለዓለም።

ሰውን ለማስደሰት ትዕዛዙን አልጥስም

በከንቱ ማባበል ከመንገዱ አልወጣም

ለዲያብሎስ እጄን በፍፁም አልሰጥም

ጌታ እግዚአብሔርን አላሳዝነውም

ከቅዱስ እግዚአብሔር እኔ አልለይም

በምድርም በሰማይ ያለእርሱ አልኖርም

መመኪያዬ እርሱ ነው ባዝንም ብደስትም

ሕይወቴ ጌታ ነው ያለእርሱ አልኖርም።

359. መንክር እግዚአብሔር

መንክር እግዚአብሔር በላዕለ ቅዱሳኒሁ /፪/

አምላከ እስራኤል ውእቱ ይሁብ ኃይለ ወጽንዓ
ለሕዝቡ ኄኘ /፪/

ትርጉም፡- እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ላይ ድንቅ ነው።
(አድሮባቸው ድንቅን ይሠራል።) የእስራኤል አምላክ
እርሱ ለሕዝቡ ኃይልን እና ብርታትን ይሰጣል።

360. ይትባረክ እግዚአብሔር

እግዚአብሔር ዐቢይ /፪/ ወዐቢይ ኃይሉ

ወአልቦ ጕልቁ /፬/ ጕልቁ ለጠበቢሁ

ትርጉም፡- እግዚአብሔር ታላቅ ነው። ኃይሉም
ታላቅ ጽኑ ለጥበቡም ስፍር ቁጥር የለውም።

361. ወሥኑስ

ወሥኑስ ለዘይቤ /፪/ ያዕቆብ/ /፪/

ይእቲ ሥጋ /፪/ እማርያም እንተ ነሥኣ መድኅን /፪/

ትርጉም፡- የያዕቆብ ደም ግባት (ውበት) ያላት መጽዓ
ክርስቶስ ከማርያም የነሣት (የለበሳት) ሥጋ ናት።
ምሥጢረ ሥጋዌን ይተረጉማል።

362. ዘመንበሩ ዓቢይ

ዘመንበሩ ዓቢይ መንበሩ ውእቱ መንበሩ ዘኪሩቤል /
/፪/

ያቀድሞ አዕምሮ /፪/ ሕሊና ሰብእ /፪/

ትርጉም፡- ከፍ ባለ ዙፋኑ በኪሩቤል ላይ የሚቀመጥ
እርሱ የሰውን ሕሊና (ሀሳብ) አስቀድሞ ያውቃል።

363. ወመኑ መሐሪ

ወመኑ መሐሪ ዘከማከ /፪/

ወኩሉ ይሴፎ ኪያከ /፬/

ትርጉም ፡ ሁሉም አንተን ተስፋ ያደርጋልና።
እንዳተ ይቅር ባይ ማንነዉ።

364. ምሥጋና ጀመረ

ምሥጋና ጀመረ ብሎ ሃሌሉያ

ማኅሌታይ ያሬድ ዘኢትዮጲያ

ምሥጋና ጀመረ ብሎ ሃሌሉያ ብሎ

ይበል /፪/ ይበል ሃሌ ሉያ
ጥዑመ ልሳን ያሬድ ዘኢትዮጲያ
ብሉይን ከሐዲስ ሐዲስን ከብሉይ

አስተባብሮ ቃኘዉ ያሬድ ማኅሌታይ

ምሥጢር ተገልጾለት ከምድር እስከ ሰማይ

በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ምሥጢር እያስማማ
ምሥጋና ጀመረ በጽዮን ከተማ
ለቅድስት ሥላሴ በሦስት ዓይነት ዜማ
በወርቅ ፅናፅል በብር ከበሮ

ዜማዉ ሲንቆረቆር በሰዉ ልጆች ጆሮ

የያሬድ ዝማሬ ያድሳል አእምሮ

ተዋሕዶ አቅርቢ ለአምላክ ምሥጋና
በዕዝራ መሰንቆ በዳዊት በገና
ዜማዉን ከያሬድ ተምረሻልና

365. እግዚአብሔር ልዩ ነዉ

እግዚአብሔር ልዩ ነዉ ኃያል አምላካችን ልዩ ነዉ/፫/

ሞትን ድል የነሳዉ ልዩ ነዉ /፪/

ከክርና ሞገስ ሞልቶ የተረፈዉ ልዩ ነዉ
ብርሃንን እንደ ልብስ የተጎናፀፈዉ ልዩ ነዉ
በትዕዛዝ ብቻ ዓለምን ያቆመዉ ልዩ ነዉ
እኛን የተቤዠ በእዉነት ልዩ ነዉ /፪/
በበረከት ክንዱ አጥብቆ የያዘን ልዩ ነዉ

እራሱን የሰዋዉ የዓለም ብርሃን ልዩ ነዉ

አካሉን መድኃኒት አድርጎ የሰጠን ልዩ ነዉ

የፈዉሳችን ፀሐይ የፃድቃን ጮራ ነዉ

ኃጢያታችን ጨለማ ቢያደርገዉ ኖሮአችንን
ባንተ ተጎናፅፈናል የማዳንን ብርሃን
አምላክ ሆይ ተመስገን

ስላደረክልን ሁሉ ስለማሩም ስራህ
የራስህን እንስጥህ ተመስገን እንበልህ

366. ዘምሩ ለአምላካችን ዘምሩ

ዘምሩ ለአምላካችን ዘምሩ /፪/

ዘምሩ ለንጉሣችን ዘምሩ /፬/
ቸርነቱ በእኛ ላይ ስለበዛ /፪/
ይክበር ይመስገን መድኃኔዓለም የዓለም ቤዛ /፬/

367. ዋይ ዜማ

ዋይ ዜማ ዘሰማእኩ በሰማይ እመላእክት
ቅዱሳን እንዘይብሉ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ
እግዚአብሔር መልዓ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲ

368. ስምአኒ

ስምአኒ እግዚኦ ጸሎትየ
ወይብጽዓ ቅድሜከ ገአርየ
ወኢትሚጥ ገጽከ እምኔየ
በእለተ ምንዳቤየ አጽምእ እዝነከ ኀቤየ
አመ እለተ እጼውአከ ፍጡነ ስምአኒ
ትርጉም፡- አቤቱ ስማኝ ጸሎቴን ጩኸቴም ወደአንተ ትድረስ ፊትህን ከእኔ ዘንድ አትመልስብኝ በመከራዬ ቀን ስማኝ ጆሮህንም ወደእኔ በጠራሁህም እለትም በፍጥነት ስማኝ

369. ይትባረክ እግዚአብሔር

ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ /፪/
የአባቶቻችን አምላክ ይባረክ /፬/

370. በልዑል መጠጊያ

በልዑል መጠጊያ የሚኖር በልዑል መጠጊያ /፪/ ይከለላል ከክፉ /፪/
አንደበቱን ከኃጢአት ከልክሎ አምላኩን
ካሰበ ካልተመጻደቀ በሥራው ራሱን ካልካበ
ይከለላል ከክፉ /፪/
ጨርቄን ማቄን ሳይል ራሱን ለአምላኩ
ከሰጠ በዓለም ምደራዊ ሀብት ተታሎ
አምላኩን ካልሸጠ ይከለላል ከክፉ /፪/
እስከመጨረሻው ለመኖር በእምነቱ ከጸና
ካላፈገፈገ ከአምላኩ ሲገጥመው ፈተና
ይከለላል ከክፉ /፪/

371. አቀድም አእኩቶቶ

አቀድም አእኩቶቶ ለእግዚአብሔር /፪/

በእንተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ /፪/

በእንተ ስደታ ለድንግል ማርያም

372. ርሃበ ወጽምኣ

ርሃበ ወጽምኣ አዘክሪ ድንግል ርሃበ ወጽምአ /፪/

ምንዳቤ ጎዘን ዘአክሪ ድንግል /፪/

ትርጉም፦ ርሃቡንና ጥሙን ችግሩንና ሐዘኑን

እመቤታችን አሳስቢልን

373. እስከ ማዕዜኑ

እስከ ማዕዜኑ እግዝዕትየ ዉስተ ምድረ ነኪር ትሄልዊ /፪/

ገሊላ እትዊ /፬/ ሀገረኪ ገሊላ እትዊነ /፪/

ትርጉም፦ እስከመቼ ድረስ እመቤቴ ሆይ

በባዕድ ሃገር ትኖሪያለሽ ወደ ሃገርሽ /፬/ ወደ ገሊላ ግቢ።

374. ተፈጸመ

ተፈጸመ ማህሌተ ጽጌ ስሙር /፪/

ንግሥተ ሰማይ /፫/ ወምድር /፬/

ትርጉም፦ የሰማይ የምድር ንግሥት የሆንሽ የእመቤታችን የጽጌ መዝሙር ተፈጸመ።

375. ከማኁ ሐዘን

ከማኁ ሐዘን ወተስዶ ሶበ በኩለኄ ረከቦ /፪/

ርእዮ ለይብኪ አይነ ልብ ዘቦ /፭/

ትርጉም፦ እንደ እርሷ ሐዘን መከራ ቢያገኘዉ ኖሮ ልብ ያለዉ ሰዉ ከንዘኑ ባልተቆጠበ ነበር።

376. የም ጸለሉ

የም ጸለሉ መላእክት ላዕለ ማርያም ወላዕለ

ወልዳ ክርስቶስ በደብረ ቁስቋም /፪/

እንዘይብሉ ስብሐት /፪/ በአርያም ስብሐት በአርያም /፪/

ትርጉም፦ እነሆ መላእክት ማርያም ከልጇ ጋር በቁስቋም ተራራ ላይ ከለሏት በእግዚአብሔር በሰማይ ምሥጋና እዉነትም በምድር ይሁን

377. መአዛሆሙ ለቅዱሳን

መአዛሆሙ ለቅዱሳን ከመጽጌ ደጎላት ዘዉስተ ቆላት /፪/ ጸጎዩ ቀንሞስ ሞስለ ናርዶስ /፬/

378. ንዒ ርግቢዬ

ንዒ ርግቢዬ ወንዒ ሠናይትየ /፪/

ምስለ ሚካኤል /፬/ ወገብርኤል /፬/

ትርጉም፦ መልካሟ ርግብ እመቤቴ ሆይ ከሚካኤልና ከገብርኤል ጋር ነይ።

379. አክሊለ ጽጌ

አክሊለ ጽጌ ማርያም ቀጸላ

መንግስቱ ለጊዮርጊስ /፪/

ክበበ ጌራ ወርቅ /፪/ አክሊለ ጽጌ /፪/

ትርጉም፦ ማርያም በጊዮርጊስ ንግሥ /ክብሩ/ ጊዜ የአበባ ዘዉዱ ናት የክብ የንግሥና አክሊል ናት የአበባ ዘዉድ እሷ ክብነት ያለዉ የወርቁ ስቁር ናት።

380. እምነ እምነ ንኢ

እምነ እምነ ንኢ /፬/

በሰላም /፪/ ንኢ ማርያም /፪/

እናታችን ነይ ነይ /፬/ በሰላም /፪/ ነይ ማርያም /፪/

381. አሠርገዋ

አሠርገዋ ለምድር አሠርገዋ ለጽጌ /፪/

እስመ ዉእቱ ክብሮሙ ለቅዱሳን መድኃኔዓለም /፪/

ትርጉም፦ ምድርን በአበባ አስጊጣት መድኃኔዓለም የቅዱሳን ክብራቸዉ ነዉ።

382. ማርያም ጎየኪ

ማርያም ጎየኪ እም ገጸ ሄሮድስ /፪/

ለአርእዩ /፬/ ተዓምረ ግፍኪ /፪/

ትርጉም፦ ማርያም ሸሸች ከሄሮድስ ፊት /፪/
ለማሳየት /፬/ የግፍ ተዓምርሽን /፪/

383. እስመ ዉእቱ

እስመ ዉእቱ ክብሮሙ ለቅዱሳን መድኃኔዓለም /፪/
አሰርገዋ ለምድር አሰርገዋ ለጽጌሃ /፪/

ትርጉም፦ ምድርን በአበባ አስጌጣት መድኃኔዓለም
ለቅዱሳን ክብራቸዉ ነዉ።

384. እንዘ ተሐቅፊዮ

እንዘ ተሐቅፊዮ ለሕፃንኪ ድንግል /፪/

ምስለ ሚካኤል /፬/ ፍሡሕ ወገብርኤል /፫/

ትርጉም፦ ድንግል ሆይ ልጅሽን ታቅፈሽ ከሚካኤልና
ከገብርኤል ጋር ነይ።

385. ምንም ሳትበድል

ምንም ሳትበድል ኃጢያት ሳይኖርባት

አንድያ ልጇን ሄሮድስ ሊገድልባት

ሀገር እንደሌለዉ ከሀገር ሲያሳድዳት ምን በድላ
ይሆን ምን ኃጢያት ኖሮባት

የአዳም መዳኛ ድንግል ማርያም አንድ ልጇን ይዛ
ዞረች በዓለም /፪/

ሄሮድስ ምቀኛ የዲያቢሎስ ወዳጅ
ሊገድለዉ አስቦ የድንግልን ልጅ
መቼ ለእርሷ አሰበ ጨከነባት እንጂ
ስትሆን ለፍጥረት የዓለም አማላጅ

የሲና በረሐ እግሯን እየፈጀዉ

አንጀቷ ተርቦ ዉኃ ጥም ሲፈጀዉ

መቼ ለእርሷ አዘነች የእርሷን መንገላታት

ሐሳቧ ለእርሱ ነዉ እንዳይገድሉባት

አቤት መከራሽ አቤት ስደትሽ
እኔ ልካፈለዉ ወራዳዉ ልጅሽ
መሰደድ ያለብኝ እኔ ነበርኩኝ
የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የተላለፍኩኝ

386. ዉድስት አንቲ

ዉድስት አንቲ በአፈ ነብያት /፪/

ወስብሐት /፭/ በሐዋርያት /፪/

ትርጉም፦ በነቢያት አፍ የተመሰገንሽ

በሐዋርያትም የተመሰገንሽ ነሽ

387. ንግሥተ ሰማያት

ንግሥተ ሰማያት ወምድር ማርያም ድንግል /፪/

ተፈፀመ /፬/ ማኅሌተ ጽጌ /፪/

ትርጉም፦ የሰማይ የምድር ንግሥት የሆንሽ

እመቤታችን ሆይ የአንቺ ማኅሌት ጽጌ ተፈጸመ።

388. ክበበ ጌራ ወርቅ

ክበበ /፪/ ጌራ ወርቅ

አክሊለ ጽጌ ማርያም /፬/

ትርጉም፦ በወርቅ አክሊል የተሸለመች እመቤታችን

የጊዮርጊስ የሰማዕትነቱ አክሊል አበባ ናት።

389. ከመጽጌ ሮማን

ከመጽጌ ሮማን ከመጽጌ /፪/

አበባዬ /፪/ ወላዲተ አምላክ ሲሣይ /፪/

ትርጉም፦ እንደ ሮማን አበባ ያማረች የአምላክ እናት
ማርያም ሲሳይ ናት።

390. ብክዩ ኀዙናን

ብክዩ ኀዙናን ሃልየክሙ ስደታ ለማርያም /፪/

ማርያም ተአይን ባህቲታ ዉስተ አድባረ ግብፅ ከመ
አፍ /፪/

ትርጉም፡- አልቅሱ ምዕመናን አስባችሁ የማርያምን
ስደቷን /፪/ ማርያም ስትዞር ብቻዋን በግብፅ በርሃ
እንደ ወፍ /፪/

391. አክሊለጽጌ ማርያም

አክሊለ ጽጌ ማርያም ቀፀላ መንግስቱ ለጊዮርጊስ
ክበበ ጌራወርቅ /፪/ አክሊለ ጽጌ /፪/

392. አዘክሪ ድንግል

አዘክሪ ድንግል አዘክሪ

ለልጅሽ አሳስቢ አዘክሪ

ለኃጥአን አኮ ለፃድቃን /፪/

ካንቺ መወለዱን	አዘክሪ
በቤተልሔም	››
በጨርቅ መጠቅለሉን	››
መኝታዉ ግርግም	››
ለኃጥአን አኮ ለፃድቃን	››

በዚያ በብርድ ወራት	አዘክሪ
የገበረለትን	››
የአድግና የላም	››
እስትንፋሳቸዉን	››
ለኃጥአን አኮ ለፃድቃን	››

በግብፅ በርሃ	አዘክሪ
መሠደድሽን	››
የአሸዋዉን ግለት	››
ርሃቡንና ጥሙን	››
ለኃጥአን አኮ ለፃድቃን	››

በመቃብሩ ዘንድ	አዘክሪ
ባነባሽዉ እንባ	››
አሳስቢ ድንግል ሆይ	››
ገነት እንድንገባ	››
ለኃጥአን አኮ ለፃድቃን	››

393. ድንግል መከራሽን

ድንግል መከራሽን ጥቂት ላስታዉሰዉ

በሄሮድስ ዘመን ፍጥረት ያለቀሰዉ

አንቺ የአምላክ እናት ደግሞም እመቤት

እንደ ችግረኛ ተነሳሽ ስደት

ኸረ ለመሆኑ እንዴት አለቀልሽ
ስትንከራተቺ በረሃዉን አቋርጠሽ
ይገድሉታል ብለሽ ለልጅሽ አስበሽ
በሔሮድስ ዘመን መከራሽን አየሽ /፪/

አዛኝቷ ማርያም በጠራሁሽ ጊዜ

እንድትደርሺልኝ በመከራ ጊዜ

መከራን ያየ ሰዉ መቼም አይጨክንም

አትጨክኚብኝ አደራሽን ማርያም /፪/

የአማኑኤል እናት አንቺ መከረኛ
እድሜሽን ጨርሰሽዉ ሆነሽ ሐዘንተኛ
መከራን ያየ ሰዉ መቼም አይጨክንም
አትጨክኚብኝ አደራሽን ማርያም /፪/

394. ሰቆቃወ ድንግል

ሰቆቃወ ድንግል /፬/

ርዕዩ ለይብኪ አዳነ ልብ ዘቦ /፬/

ትርጉም፡- ልብ ዓይን ያለዉ ሰዉ የድንግልን ለቅሶ
አይቶ ቢያለቅስ አግባብ ነዉ።

395. ንኢ ርግብየ

ንኢ ርግብየ ወንኢ ሰናይትየ
ምስለ ሚካኤል /፬/ ፍሱሕ ወገብርኤል

396. ወደ ምሥራቅ እዩ

ወደ ምሥራቅ እዩ ወደ ፀሐይ መዉጫ

ድንግልን ክበቧት እንበል ሃሌ ሉያ

ለአምላክ እናት ለአዛኝት /፬/

እልል እንበል እንዘምርላት /፪/

ወገኖች ተነሱ እናታችን መጣች
ስሟን ስንጠራ መቼ ትቀራለች
የተከዘን ልታጽናና ነይ ስንላት ትመጣለችና
/፪/
የጽጌዉ ማኅሌት በጸሎት ሲጀመር
ማርያም ትመጣለች በደመና አየር
ንዒ ስንል በሰዓታት ልትባርከን ትመጣለች
በእዉነት /፪/

ፍልሰታ ሲጀመር ቃልኪዳን ገብታለች

የሌሊት ዉዳሴን ንዒን ትሰማለች

ሕፃናትን በበረከት ልትጎበኝ

ትመጣለች በእዉነት /፪/

በፍፁም ቸርነት እንዲምረን ጌታ
በአማላጅነትሽ ሁኚልን መከታ

እናታችን አለኝታችን እንድናለን
ድንግል አንቺን ይዘን /፪/

397. ምስለ ሚካኤል

ምስለ ሚካኤል ወገብርኤል ንኢ ሠናትየ ማርያም /፪/ ንኢ /፮/ እመ አምላክ ንኢ ማርያም /፪/

398. አፈ ንብ

አፈ ንብ ማቱሳላ ወልደ ሔኖክ እመአፈ ልምላሜ

ቡሩክ አፈ መላእክት /፪/

ቀስመ ጽጌ ጽጌ /፪/

ጽጌኪ እመ አምላክ /፪/

ትርጉም፡- የአምላክ እናት እመቤችን ሆይ

የንብ አፍ የሔኖክ ልጅ የሚሆን ማቱሳላ ከተባረከ (ከተቀደሰ) ልምላሜ መልአክ አፍ ልጅሽ አበባን ቀሰመ

399. ኦ ድንግል

ኦ ድንግል አዘክሪ ርሃበ ወጽምዓ /፪/

ርሃበ ወጽምዓ /፪/ ወሐዘን ምንዳቤ ወሐዘን /፪/

ትርጉም፡- ድንግል ሆይ አሳስቢ ርሃቡን ጥሙን /፪/ ርሃቡን ጥማቱን /፪/ በበረሃ የደረሰብሽን /፪/

400. ለምኚ ድንግል

ለምኚ ድንግል ለምኚ /፪/

ለኃጥአን /፫/ አይደለም ለጻድቃን /፪/

ለምኚ ታላቅ ስጦታዬ
›› አዛኝ ሩኅሩኅ ነሽ
›› የጌታዬ እናት
›› ጸጋን የተሞላሽ
›› የአምላክ ማደሪያ
›› ለምነሽ አስምሪ
›› አማናዊት ጽዮን
›› ከእኔ አትለይኝ

ለምኚ ሐዘንሽ ሐዘኔ
›› ለእኔ ይሁን ድንግል
›› የተንከራተትሽዉ
›› በሀገረ እስራኤል
›› ትእግስትሽን ሳየዉ
›› ልቤ ይመሰጣል
›› የሐዘን እንባ ጎርፍ
›› ዓይኔን ይሞላዋል

ለምኚ በቀራኒዮ አምባ
›› በዚያ በፍቅር ቦታ
›› ከእግረ መስቀሉ ስር
›› ከክርስቶስ ጌታ
›› ለእኛ ተሰጥተሻል
›› እናት እንድትሆኝን
›› ልጆችሽ ነንና
›› ምልጃሽ አይለየን

ለምኚ አንደበቴን ጌታ
›› በምሥጋና ሙላዉ
›› ደስ ይበልሽ ብዬ
›› እኔም ላመስግናት
›› አንደበቴን ጌታ
›› በምሥጋና ሙላዉ
›› ደስ ይበልሽ ብዬ
›› እኔም ላመሥግናት

401. መዓዛ አፈዋት

መዓዛ አፈዋት ማርያም /፪/ ጽጌ መንግሥት ቡርክት /፪/
ጽጌ ጽጌ ዘሰሎሞን ወዳዊት አብርሐ ወአጽብሐ /፪/

402. ክበበ ጌራ ወርቅ

ክበበ ጌራ ወርቅ ጽሩይ እም እንቁ ባሕርይ /፪/
ዘየሀቱ /፭/ እም እንቁ ባሕርይ /፪/
ትርጉም፡- ከእንቁ በሚያበራ አክሊል
የተሸለመች እመቤታችን የጊዮርጊስ አክሊል

403. ንዒ ርግብየ

ንዒ ርግብየ ወንኢ ሠናይትየ /፪/
ትናዘዘኒ /፪/ ሐዘነ ልብየ /፪/
ትርጉም፡- ከልቤ ሐዘን ታረጋጊኝ ዘንድ መልካምዋ ርግብ ሆይ ነይ።

404. ምዕረ በዘባንኪ

ምዕረ በዘባንኪ ወምዕረ በገቦኪ /፪/
በአዚለ ሕፃን /፬/ ደከምኪ ማርያም ብዙኃ /፪/
ትርጉም፡- አንድ ጊዜ በጀርባሽ አንድ ጊዜ በጎንሽ /፪/ ሕፃንን በማዘል /፬/ ደከምሽ ማርያም በብዙ /፪/

405. ትመስል እምኪ

ትመስል እምኪ ማርያም ዕለተ ሣልስተ
ወርሀብእተ ትመስል እምኪ /፪/ ዘወለደት
ጽጌ /፫/ ወፀሐየ ዓለም

406. ሠናይትየ

ሠናይትየ /፪/ ርግብ /፪/

ንኢ ማርያም /፬/ ሠናይትየ ንኢ ማርያም

ትርጉም፦ መልካም ርግብ ማርያም ነይ

407. ንኢ ማርያም

ንኢ ማርያም /፫/ /፪/

በሰላም /፫/ ንኢ ማርያም /፪/

ነይ ማርያም /፫/ /፪/

በሰላም ነይ ማርያም

408. እሴብህ ፀጋኪ

እሴብህ ፀጋኪ ኦ እግዝእትየ ማርያም

እጽ ልምልምት ወፍሬ ጥዕምት /፫/

ሐረገ ወይን /፫/ አንቲ ማርያም

አጸደ ወይን /፫/ አንቲ ማርያም

ትመስሊ ፊደለ ወትወልዳ ወንጌል ወታገመወሪ
መስቀል ትመስሊ ፊደለ ወትወልዳ ፀሐየ ወታገምሪ

መዝሙር በእንተ ልደቱ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ

409. ዮም ተወልደ

ዮም ተወልደ መድኃኔ ዓለም

ዮም ተወልደ ከሣቴ ብርሃን

ትርጉም፡- የዓለም መድኃኒት ዛሬ ተወለደ ብርሃንን

የሚገልጥ /የብርሃን ጌታ/ ዛሬ ተወለደ

410. የምሥራች ደስ ይበለን

የምሥራች ደስ ይበለን /፪/
የዓለም መድኃኒት ተወለደልን ምስራች ደስ ይበለን
ኢየሱስ የዓለም ቤዛ /፪/
የዓለም ቤዛ /፪/ ለኛ ተወለደልን
ንጉስ ሔሮድስ ይህን ሲሰማ
ፈልጋችሁ አምጡት በቀን በጨለማ /፪/
ሰብዓ ሰገል እንደታዘዙት
በኮከብ ተመርተው ሕፃኑን አገኙት /፪/
ሰገዱለት ከመሬት ወድቀው
ወርቅና እጣኑን በረከቱን ሰጥተው

411. ሰማይ ተከፈተ

በአምላካችን አንጻር እንጸልያለን
በእግዚአብሔር ቅዱሳን በግርማ ተከበን
ሰማይ ተከፈተ ደስይበለን
ማኅሌት ተሰማ ‹‹
ዛሬ ተከበናል ‹‹
በመለኮት ግርማ ‹‹ /፪/
ከሰማይ ተሰማ የመላዕክት መዝሙር
የሰላም የደስታ የእውነት የፍቅር
ደመና ከበበን ድንግል ተደሰተች
የሕዝቡን መመለስ ትመለከታለች
ታላቅ ደስታ ነው በሰማይ ሠራዊት
ሰይጣን ድል ተነስቶ እና ስንባረክ
ሰዎች ዕልል በሉ ውስጣችን ይታደስ
አምላክ ከእኛ ጋር ነው በልባችን ሊነግሥ
ሰዎች ዕልል በሉ ውስጣችን ይታደስ
አምላክ ከእኛ ጋር ነው በልባችን ሊነግሥ

412. ተነሱ እንዘምር

ተነሱ እንዘምር እልል እንበል /፪/

በመልአኩ በገብርኤል ቃል /፪/
ተወልዶልናል ተጠምቆልናል /፪/
እሰይ እሰይ የዓለም ቤዛ አማኑኤል /፪/

413. በጎል ሰከበ

በጎል ሰከበ በአጽርቅት ተጠብለለ
ቤዛ ኩሉ ዓለም /፪/ ዮም ተወልደ /፪/

414. ይትፌሥሓ አድባረ ጽዮን

ይትፌሥሓ አድባረ ጽዮን ወይትሐሠያ አዋልደ
ኢትዮጵያ /፪/
እስመ ተወልደ ብሑተ ልደት መድኃኔዓለም
በኢየሩሳሌም መድኃኔዓለም /፪/
ትርጉም፡- የጽዮን ተራሮች ይደሰታሉ፤ የኢትዮጵያም
ልጆች ሐሤትን ያደርጋሉ ፤ በልደቱ ብቸኛ የሆነ
መድኃኔዓለም በኢየሩሳሌም ተወልዷልና፡

415. በከመ ሰማዕነ

በከመ ሰማዕነ ከማሁ ርኢነ
በሀገረ እግዚአ ኃያላን በሀገረ አምላክነ
አዳምን ሊያደነው ቃል እንደገባለት
በመስቀል ተሰቅሎ ቤዛ ሊሆንለት
እንደተናገረ ከሰማይ ወረደ
በሰው አካል ታየ በጎል ተወለደ
ነቢያቱ እንዳዩ በትንቢት መነፅር
የያዕቆብን ኮከብ የእሴይን ስር በትር
እኛ ግን በአካል ተገልፆ አየነው
በግዕዘ ህፃናት በጎል አገኘነው
ከሕዝቅኤል ምስራቅ ፀሐይ እንዲወጣ
ወገኑን ሊታደግ መድኅን እንዲመጣ
ነቢያቱ እንዳሉ እኛም እንደሰማን
በአምላችን ሀገር የሆነውን አየን

416. ክርስቶስ ተወልደ /ተወልደነ/

ክርስቶስ ተወልደ እሰይ
ክርስቶስ ተጠምቀ በማይ
ወለደነ ዳግመ እማይ /፪/ ዳግመ /፪/ ወለደነ ዳግመ
እማይ
ትርጉም፡- ክርስቶስ ተወለደ፣ ክርስቶስ ተጠመቀ
ዳግም ከውሃ ወለደን

417. በጎለ እንስሳ

በጎለ እንስሳ /፪/
በጎለ እንስሳ ተወለደ አማኑኤል /፪/
ትርጉም፡- በእንስሳት በረት ተወለደ
አማኑኤል

418. ክርስቶስ ተወልደ /አስተርእዮቱ/

ክርስቶስ ተወልደ ወተጠምቀ /፪/
አስተርእዮቱ አማን አስተርእዮቱ /፪/
ትርጉም፡- ክርስቶስ ተወለደ ተጠመቀ መገለጡም
እውነት ነው።

419. ሰማይና መሬት

ሰማይና መሬት የማይወስኑት
ሥጋና መሬት የማይወስኑት /፪/
መለኮት ከትስብእት ይለያል ለሚሉ /፪/
ቃል ሥጋ ሆነ ሲል ያስረዳል ወንጌሉ /፪/
ቀድሞ በነቢያት ሁሉን ያናገረ /፪/
ከሰማያት ወርዶ ከድንግል አደረ /፪/
ሰማይና ምድር የማይወስኑት
ሥጋን ተዋሕዶ ታየ በልደት /፪/
በጌታችን ልደት ሞት ከጠፋልን /፪/
በእልልታ እንግለፀው መደሰታችንን /፪/
ጌታችን ሲወለድ ለዓለሙ ሁሉ /፪/

እንኳን የሰው ልጆች እንስሳት ዘለሉ /፪/

በኮከብ ተመርተው ሰብአሰገል ሄዱ /፪/

ሰማይና መሬት የማይወስኑት /፪/

ስጋን ተዋሕዶ ታየ በልደት /፪/

420. አምላክ ሰው ለመሆን

አምላክ ሰው ለመሆን ስለአፈቀረ /፪/

በነቢያት /፪/ ትንቢት አናገረ

በአዋጅ ተነግሮ ትንቢቱ ሲፈፀም /፪/

አምላክ ተወለደ /፪/ ከድንግል ማርያም

ከድንግል ማርያም በለበሰው ሥጋ /፪/

እኛን ወገኖቹን /፪/ አለበሰን ጸጋ

ነቢያት በትንቢት ጻድቃን በውዳሴ /፪/

ይነጋገራሉ /፪/ ከድንግለ ሙሴ

ንጽህናዋን አይቶ ነውር እንደሌለባት /፪/

መልአኩ ገብርኤል /፪/ ትፀንሻለሽ አላት

ድንግለ ሙሴ (የሙሴ ድንግል) እመቤታችን ናት።

421. ገብርኤል አወፈየኒ

ገብርኤል አወፈየኒ ህፃነ ማርያም ድንግል /፪/

ወበቤተልሔም /፪/ ተወልደ አማኑኤል /፪/

ትርጉም፡- ገብርኤል ሆይ የድንግል ማርያምን ልጅ የአማኑኤልን በቤተልሔም መወለድ አብሥረኝ።

422. አንፈርዓው ሰብአ ሰገል

አንፈርዓው ሰብአ ሰገል /፪/

ረኪቦሙ ሕጻነ ዘተወልደ ለነ /፪/

ትርጉም፡- የተወለደልንን ሕጻን/ክርስቶስን/አግኝተው ሰብአ ሰገል ዘለሉ /ሰገዱ/።

423. ዘነቢያት ሰበክም

ዘነቢያት ሰበክም /፪/

ወአስተርዓየ ገሀደ /፪/

ትርጉም፡- ነቢያት የሰበኩት በገሀድ /በግልጥ/ ታየ።

424. አንፈርዓው

አንፈርዓው ሰብአ ሰገል /፪/

አምኃሆሙ አምፅኡ መድምመ

ትርጉም፡- ሰብአ ሰገል ዘለሉ /ሰገዱ/። የሚያስደንቅ እጅ መንሻንም አመጡ።

425. የጥበብ ሀገሯ ወዴት ነው

የጥበብ ሀገሯ ወዴት ነው

ማደሪያዋስ ወዴት ነው /፪/

ቦታ ጐዳናዋ ከወዴት ተቃኘ

ዝናና ወሬዋ ከወዴት ተገኘ

ፈልጐ የገዛት ማነው በቀይ ወርቅ

ባሕሩን ተሻግሮ ስሟን በማወቅ

ማነው ያወረዳት ከደመና በላይ

ድምጿንስ የሰማ ከላይ ከሰማይ

እርሷን የሚጠሉ ናቸውና ከንቱ

አይቀርላቸውም ጎላ የሞትሞቱ

ሁሉን የሚያውቅ እርሱ እርሱ ያውቅላታል

426. አብሠራ ወይቤላ

አብሠራ ወይቤላ ለማርያም ገብርኤል አብሠራ መልአክ /፪/

አልቦ ማኅለቅት ለሰላሙ ዲበ መንበረ ዳዊት መንግሥቱ ትፀንዕ /፪/

ትርጉም፡- መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ለእመቤታችን አበሠራት ካንቺ የሚወለደው ለሰላሙ ፍፃሜ የለውም አላት መንግስቱ በዳዊት መንበር ላይ ትፀናለች

427. ከእመቤታችን ተወልዶ

ከእመቤታችን ተወልዶ ሥጋን የለበሰው /፪/
እኛን ሊያድነን ነው /፪/ ከሞት እኛን ሊያድነን ነው
በዮሐንስ እጅ ተጠምቆ ድኅነትን ያመጣው /፪/
በቀራንዮ ተሰቅሎ ደሙን ያፈሰሰው /፪/
በሦስተኛው ቀን ተነስቶ ሞትን ድል ያረገው /፪/

428. ይቤሎሙ ኢየሱስ

ይቤሎሙ ኢየሱስ ለአይሁድ እመኑ ብየ
ወእመኑ በአቡየ አብርሃም /፪/ በመስቀልየ
ትርጉም፡- ኢየሱስ አይሁድን ዛሬስ
በመስቀሌ ለወገኖቼ አበራለዉና በእኔ እመኑ
በአባቴም እመኑ አላቸዉ።

429. የጥበብ ሰዎች መጡ

ሰማይና መሬት የማይወስኑት
ተወስኖ አየነው በጠባብ ደረት
ዘጠና ዘጠኙን መላዕክትን ትቶ
አገኘነው ዛሬ በበረት ተኝቶ
የጥበብ ሰዎች መጡ /፪/ ሰምተውት በዜና
እያበራላቸው ኮከብ እንደ ፋና
ድንግል እመቤቴ ሰላምታ ይድረስሽ
ለአምላክ ወገኖች መመኪያቸው የሆንሽ
ከአንቺ ተወለደ የዓለም መድኅን
ኩነኔን አጥፍቶ ጽድቅን ሊያወርስን
ጌታችን ሲወለድ በቤተልሔም
ኃዘን ተደምስሶ ሰፈነ ሰላም
እንጨቶች አፈሩ ፍሬ በረከት
ወንዞች ሁሉ ሆኑ ማርና ወተት
ሰብአ ሰገል መጡ ሊሰግዱ በሙሉ
የእስራኤል ንጉሥ ወዴት ነው እያሉ
እጅ መንሻውን ሰጡ እንደየስርዓቱ
እጣኑን ለክህነት ወርቁን ለመንግስቱ

430. መጽአ ከመ ይቤዙ ዓለመ

መጽአ ከመ ይቤዙ ዓለመ /፪/

የሀበነ ሰላመ ጋዳ ያበውኡ ቁርባነ /፪/

ትርጉም፡- ዓለምን ያድን ዘንድ መጣ። ሰላምንም
ይሰጠን ዘንድ። እጅ መንሻን እንደ ቁርባን ያስገባሉ።

431. ሣር ቅጠሉ ሰርዶው

ሳር ቅጠሉ ሰርዶው ሰንበሌጥ ቀጠማው
በዚያች ቀን በዚያች ወር ለምለም ነበረው
በእልልታ ዘመሩ በደስታ ተውጠው
ጌታ መወለዱን የምስራች ሰምተው
እልል በይ ቤተልሔም /፪/ ሃሌ ሃሌሉያ
የፍቅር የሰላም ነሽና ገበያ /፪/
ያ ትሑት እረኛ የትሕትና አባት
ብርሃንን ለበሰ በእኩለ ሌሊት
ጥሪ ተደርጎለት በሰማይ መላዕክት
ለመመልከት በቃ የጌታውን ልደት
እረኝነት ሥራ ተንቆ እንዲቀር
ብሎ ሰው በልማድ ደንግጎ ነበር
የብዙ ሰው ሕይወት መሆኑን እረኛ
ክርስቶስ ሲወለድ ተረዳነው እኛ

432. ተወልደ ኢየሱስ

ተወልደ ኢየሱስ በቤተልሔም /፪/ ዘይሁዳ
በቤተልሔም
አዋልደ ጢሮስ አሚሓ ይሰግዳ /፪/ በቤተልሔም

433. በኮከብ መፅኡ

በኮከብ መፅኡ /፪/ ሠብዓ ሰገል
ለአማኑኤል /፬/ ይሥግዱ ሰብዓ ሰገል

434. ወአንቲኒ

ወአንቲኒ ቤተልሔም ምድረ ኤፍራታ
እምኔኪ ወጽአ ንጉሠ ይሁዳ
አዋልደ ጢሮስ አሜሐ ይሰግዳ
ኩሎሙ ነገስት /፪/

435. መጽአ ከመይቤዙ

መጽአ ከመይቤዙ ዓለም /፪/
የሀበነ ሰላመጋዳ ያበውው ቁርባን /፪/
ትርጉም፡- ዓለም ለማዳን መጣ አንድነቱንም
ይሰጠን ዘንድ እጅ መንሻም ያቀርቡ ዘንድ

436. አማኑኤል

አማኑኤል /፪/ ከእኛ ጋር ሆነ እግዚአብሔር
ዳግም ሊወልደን ከማይሞት ዘር
ዙሪያው አበራ ቤተልሔም
ጌታ ሲወለድ መድኃኔዓለም
ብርሃን ይለብሳል ጥልቁ ጨለማ
የምናመልከው ድምጹን ሲያሰማ

ያን የሞት ዘመን የጥፋት ጊዜ
አሳልፈነው በሐዘን ትካዜ
አሁን ታድሰን በልጁ ደም
ደስታ ከቦናል ፍቅር ሰላም
ሕጉን ተላልፈን ከደጅ ስንወጣ
ስለወደደን ሊያድነን መጣ
ስጋ ደማችን ከእርሱ ተጣብቋል
ከኛ ጋራ ነው ማን ይችለናል
እሩቅ አይደለም ቅርብ ነው ጌታ
የሚጠብቀን በቀን በማታ
ሞገስ ሆኖልን ከፍ ብለናል
እናምነዋለን ይዋጋልናል

437. ዘድንግል መናሥግተ

ዘድንግል መናሥግተ ኢያርጎም /፪/

ኢያርጎም ዘኪሩቤል ኢርዕዮ ኧኸ /፬/

ትርጉም፡- የእመቤታችንን የድንግልናዋን ማኅተም
አልለወጠም (አልፈታም) ኪሩቤልም አላየውም
አልመረመረውም፡፡

438. አሐዱስ

አሐዱስ ሶበ እምግርያም ተወልደ /፪/

ኮነነ ዘመደ /፪/ ኮነነ ዘመደ /፪/

በአምላክ ሕሊና የታሰበች
ከዓለም በፊት የታወቀች
በእርሷ ለማደር ቃል ተላከ
በነቢያትም ተሰበከ
ከፍጥረቱ አስበልጦ

ከሴቶቹ ሁሉ እርሷን መርጦ

ዙፋኑን ትቶ መጣ ወረደ

ሥጋዋን ለብሶ ተዋሐደ

በተዋሕዶ አከበረን
ከእኛ ተወልዶ ዘመድ ሆነን
በማህፀኗ ለማደሩ
የገጠመ ነዉ ያ ምሥጢሩ

439. ወወለደት

ወወለደት ወልደ ዘበኩራ /፬/
መንጦላዕት ደመና ሰወረ /፬/
ትርጉም፡- የበኩር ልጇን ወለደች
የደመና መጋረጃ ጋረዳት

440. እምሰማያት

እምሰማያት ወረደ ወእምማርያም ተወልደ
/፪/ ከመይኩን ቤዛ /፪/ ለኩሉ ዓለም /፪/
ለብሰ ሥጋ ማርያም /፪/
ትርጉም፡- ከሰማያት ወረደ ከድንግል
ማርያም ተወለደ /፪/
እንዲሆነን ቤዛ /፪/ ለዓለሙ ሁሉ /፪/
ለበሰ የማርያምን ሥጋ /፪/
ቤዛ ለዓለም ሁሉ
ለበሰ የማርያምን ሥጋ

441. ዮም ሰማያዊ

ዮም ሰማያዊ በጎል ሰከበ
ለዘተወልደ እምቅድስት ድንግል /፪/
ርእይዎ ኖሎት /፪/ አእኩትዎ መላእክት /፪/
ትርጉም፡- እነሆ ዛሬ ሰማያዊ ንጉስ
በበረት ተኛ ከቅድስት ድንግል
ማርያም የተወለደውን ሰማያዊ
ንጉስ እረኞች አዩት
መላእክትም አመሰገኑት

442. ንኡ ናንሶሱ

በብርሃኑ ንኡ ናንሶሱ
በብርሃኑ ንኡ ናንሶሱ
ትርጉም፡- በብርሃኑ እንመላለስ

443. በበረት የተኛው

በበረት የተኛው ቅዱሱ ሕፃን
ልብስም አለበሰ ነበረ ዕርቃኑን
የምታለብሰው ልብስ ባታገኝ እናቱ
ትንፋሽ አለበሱት ከበው እንስሳቱ
እሰይ የምሥራች ሃሌ ሃሌ ሉያ
ጌታ ተወለደ ሊሆነን አርዓያ

444. ደስ ይበለን

የምስራች ደስ ይበለን /፪/
የዓለም መድኃኒት ተወለደልን /፪/
የምስራች ደስ ይበለን

አዳም ሆይ ደስ ይበለህ
የዓለም መድኃኒት ተወለደልህ
ሔዋን ሆይ ደስ ይበልሽ
የዓለም መድኃኒት ተወለደልሽ

ሰብአ ሰገል እንደታዘዙት /፪/
በኮከብ ተመርተው ህፃኑን አገኙት

ሰግዱለት ከመሬት ወድቀው
ወርቅ እጣኑን ከርቤ በረከቱን ሰጥተው
ንጉሥ ሄሮድስ ይህንን ሲሰማ
ፈልጋችሁ አምጡት በቀን በጨለማ

445. አንቺ አንቺ

አንቺ አንቺ ቤተልሔም የይሁዳ መሬት
ባንቺ ተወለደ የዓለም መድኃኒት /፪/

አዳም ክብር ሲሻ ቤተልሔም
ለሁሉም ሰላም ቤተልሔም
ጌታ ተወለደ ቤተልሔም
ከድንግል ማርያም ቤተልሔም

እስራኤል ሕዝቤን ቤተልሔም
የሚጠብቃቸው ቤተልሔም
ካንቺ ይወጣል ብሎ ቤተልሔም
እንደ ነገራቸው ቤተልሔም

እጅ መንሻ አቀረቡ ቤተልሔም
የምስራቅ ነገስታት ቤተልሔም
ህፃኑን ከእናቱ ቤተልሔም
ተኝቶ አገኙት ቤተልሔም

ቅዱሳን መላእክት ቤተልሔም
ያሸበሸቡለት ቤተልሔም
ስብሀት ለእግዚአብሔር ቤተልሔም
ብለው ዘመሩለት ቤተልሔም

446. እስመ እምዘርዓ ዳዊት

እስመ እምዘርዓ ዳዊት ዘመጽአ /፪/
በቤተልሔም ዘይሁዳ በቤተልሔም እንዘይ /፪/

447. ሶበ ሰማዕንነ

ሶበ አማዕነ ዜናከ መጽአነ ጎቤከ /፪/ መጽአነ /፬/

አንቺ ቤተልሔም የዳዊት ከተማ

ምስራች ቃሉ በአንቺ ቤት ተሰማ

ወልድም ተሰጠን ሕፃን ተወለደ

አስጨናቂው ዘመን በእርሱ ተወገደ

ሰውና መላእክት በአንድ ላይ ዘመሩ
የእግዚአብሄር ክብር ለዓለም መስከሩ
ምስጋና በሰማይ ለእግዚአብሔር ይሁን
ሰላም ለሰው ልጆች በምድር ላይ ይስፈን

እናትና ልጅ ፀሐይ ሳይነካቸው

የእግዚአብሔር መላእክት ከፊታቸው ወድቀው

በከብቶች በረት አምላክ ተወለደ

የነገሥታት ንጉስ ሞትን አስወገደ

ድንቅ መካር ኃያል የሰላም አለቃ
ጌታ ሆይ በስምህ ግዛቱ አበቃ
ሰላምን የሚሰጥ አልፋን ኦሜጋ
የእስራኤል ንጉስ ተገልጸአል በሥጋ

448. ተልኮ መጥቶ

ተልኮ መጥቶ /፪/ ገብርኤል /፪/
እንዲህ ብሎ አላት ለድንግል /፬/
የማሕፀንሽ ፍሬ /፪/ ኢየሱስ /፪/
የተባረከ ነው ቅዱስ /፬/

449. በክንፉ ጋረዷት

በክንፉ ጋረዷት /፫/

ለድንግል ደስ ይበልሽ አላት /፪/ ኸኸ /፪/

ከጌታ ተልኮ ድንግልን ለማብሰር
ክንፉን እያማታ ምስራች ሲናገር
ድምጽን እያሰማ እስከ ሊባኖስ
በፍጥነት ወረደ መልእክት ለማድረስ

ሀሩን ከወርቅ ጋር አስማምታ ስትፈትል

ከፊቷ በመስገድ እስዲህ አላት ለድንግል

ደስታ ይገባሻል ከሰው ተለይተሽ

አምላክን ለመውለድ ስለተመረጥሽ

ድንግልም መልሳ አለችው ለገብርኤል

ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል

መሬትም ያለዘር ማፍራት እንደማትችል

እንዴትስ አምኜ የአንተን ቃል ልቀበል

መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት ለድንግል

መንፈስ ቅዱስም በአንቺ ላይ ይመጣል

የልዑል ኃይልም ይጸልልሻል

የእግዚአብሔር አብ ልጅ ከአንቺ ይመጣል

ለእግዚአብሔር አይሳነውም

ቃሌን ተቀበይ ጽኚ በምስጋና

450. ኢየሩሳሌም

ኢየሩሳሌም /፫/ በሆን ጌታ ሲወለድ ባየን
እንደ ዮሴፍ ወይ እንደ ሰሎሜ በሆን /፪/
እንድ እረኞች ወይ ሰብአ ሰገልን በሆን /፪/

451. ዮም ፍሥሐ

ዮም ፍሥሐ ኮነ በእንተ ልደቱ ለክርስቶስ /፪/
እም ቅድስት ድንግል /፪/ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ /፪/

452. ወነዋ ተወልደ

ወነዋ ተወልደ መድኃኔዓለም /፪/
ፍሥሐ ለኩሉ ዘየአምን /፪/
ወነዋ ተጠምወ መድኃኔዓለም /፪/
ፍስሥ ለኩሉ ዘየአምን /፪/
ትርጉም፡- ዛሬ ተወለደ የዓለም መድኀኒት /፪/ ደስታ ነውና ለሚያምኑት /፪/
ዛሬ ተጠመቀ የዓለም መድኀኒት /፪/
ደስታ ነውና ለሚያምኑት /፪/

453. ለዘተወልደ

ለዘተወልደ እምቅድስት ድንግል ምንተ ንብሎ ናስተማስሎ ለመድኃኒነ /፪/
አርዌ ገዳምኑ አንበሳ <u>ወሚመ</u> /፪/ ከራድዮን /፪/

454. በቤተልሔም ተወልደ

በቤተልሔም ተወልደ አማኑኤል /፪/
እም ዘርዓ ዳዊት /፫/ ተወልደ አማኑኤል /፪/

455. ይቤላ መልአክ

ይቤላ መልአክ ለማርያም /፪/
ትወልዲ ወልደ ንጉሥ በቤተልሔም
ይቤላ መልአክ ከጌታ ተልኮ
ይቤላ መልአክ ቅዱስ ገብርኤል
ይቤላ መልአክ ሰላምታ አቅርቦላት
ይቤላ መልአክ ለማርያም ድንግል
ይቤላ መልአክ ትወልጃለሽ አላት
ይቤላ መልአክ ቀዳሚውን ቃል
ይቤላ መልአክ ማኅደረ መለኮት
ይቤላ መልአክ ማርያም ቅድስት
ይቤላ መልአክ የሕዝብ ሁሉ እናት
ይቤላ መልአክ እጎተ መላእክት
ይቤላ መልአክ እሙ ለብርሃን
ይቤላ መልአክ ደብተራ ፍጽምት
ይቤላ መልአክ ወገበዋቲሃኒ
ይቤላ መልአክ ሐመልማለ ወርቅ
ይቤላ መልአክ ትበርሂ እምፀሐይ
ይቤላ መልአክ ኖኅተ ምሥራቅ
ይቤላ መልአክ ሰላም ለኪ ድንግል
ይቤላ መልአክ በአልባሰ ወርቅ
ይቤላ መልአክ ወላዲተ አምላክ

ይቤላ መልአክ ማርያም ንጽሕት
ይቤላ መልአክ ወትሌአሊ እምእድባር
ይቤላ መልአክ ስብሕት ወቡርክት
ይቤላ መልአክ ኦ ምልእተ ጸጋ
ይቤላ መልአክ እግዚአብሔር ምስሌኪ
ይቤላ መልአክ ቡርክት አንቲ እምአንስት
ይቤላ መልአክ ድንግል በኀሊናኪ

456. ሃሌ ሃሌ ሉያ

ሃሌ ሃሌ ሉያ /፪/

በሰማይ በምድር ምሕረት ሆኗልና

ሃሌ ሃሌ ሉያ አሜን ሃሌ ሉያ

መላእክት ዘመሩ አመሰገኑት

እየተደነቁ በአምላክ ቸርነት /፪/

ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት አሉ

እረኞችም አብረው እሱን አከበሩ /፪/

ዓለምን ለመፍጠር ከተጠበበት

ይበልጣል ከሁሉም እኛን ያዳነበት /፪/

ከዳግማዊት ሔዋን ከእመቤታችን

በረቂቅ ጥበቡ ተወልዶ አዳነን /፪/

ሁላችሁም ሂዱ ከቤተልሔም
ታገኙታላችሁ በከብቶች ግርግም
ኢየሱስ ክርስቶስ ወሀቤ ሰላም
ሞታችንን ወስዶ ሕይወትን ሰጠን /፪/
ወልደ እግዚአብሔር መጣ ከላይ ከሰማይ

ፍቅር አወረደው ከመንበሩ ላይ /፪/

አልተጸየፈውም መሆን ከግርግም

ትጎትናው ደነቀኝ የመድኃኔዓለም /፪/

457. ወነዋ ተወልደ

ወነዋ ተወልደ መድኃኔዓለም /፪/
ፍሥሐ ለኩሉ ዘየአምን /፬/
ትርጉም፡- ዛሬ ተወለደ የዓለም መድኃኒት
/፪/ ደስታ ነውና ለሚያምኑት /፬/

458. ውእቱ ኢየሱስ

ውእቱ ኢየሱስ /፫/ እምቅድስት ድንግል /፪/
በእንተ ልደቱ ለክርስቶስ ዮም ፍሥሐ ኮነ
በእንተ ልደቱ ለክርስቶስ

459. ለክብረ ቅዱሳን

ለክብረ ቅዱሳን ወለቤዛ ብዙኃን
ተወለደ ተጠመቀ እም ድንግል
በጎል ሰበከ ቤዛ ኩሉ ዓለም

460. እርሱ ባይወለድ

እሰይ /፪/ ተወለደ

እሰይ /፪/ ተጠመቀ

ከሰማየ ሰማያት ወረደ

ከድንግል ማሪያም ተወለደ

እርሱ ባይወለድ እሰይ እሰይ
ቸር አባታችን እሰይ እሰይ
እርሱ ባይወለድ እሰይ እሰይ
መድኃኒታችን እሰይ እሰይ
መች ትገኝ ነበረ እሰይ እሰይ
ገነት ምድራችን እሰይ እሰይ
እንደጠል ወረደ እሰይ እሰይ
ከሰማይ ወደእኛ እሰይ እሰይ
ወገኖቹን ሊያድን እሰይ እሰይ
ከኃጢአት ቁራኛ እሰይ እሰይ
ብርሃን ወጣላቸው አሰይ እሰይ
ለእምነት ወገኖቹ እሰይ እሰይ
በጨለማ ጉዞ እሰይ እሰይ
እንዲያ ሲሰላቹ እሰይ እሰይ
እግዚአብሔር አብ ላከ እሰይ እሰይ
አንድያ ልጁን እሰይ እሰይ
እርሱ ወድዷልና እሰይ እሰይ
እንዲሁ ዓለሙን እሰይ እሰይ

461. አብሠራ ገብርኤል

አብሠራ ገብርኤል ሊቀመላእክት /፪/
ኧኸ ወይቤላ /፭/ ትወልዲ ወልድ/ /፪/

462. ማርያም

ማርያም /፫/ ደስ ይበልሽ በገብርኤል ሰላምታ /፪/

ባንቺ ስላደረ የዓለም ሁሉ ጌታ /፪/

የአምላክ ቸርነቱ ፈቃዱ ሲሆን
ጨለማው ተገፎ ሲወጣ ብርሃን
ድንግል ተቀምጣ በቤተ መቅደስ

ሐር ወርቅ አስማምታ ስትፈትል ንግሥት

ገብርኤል /፪/ ዜናዊ ሐዲስ
የአምላክን መወለድ ሥጋ በመልበስ
ገብርኤል ሲያበስራት ድንግል ስትሰማ

በእርስዋ ላይ አደረ የመለኮት ግርማ

እውነተኛ መልአክ መሆኑን ስላየች
ይሁንልኝ ብላ ቃሉን ተቀበለች

463. ከነቢያት ሀገር

ከነቢያት ሀገር ኢየሩሳሌም
ከቅድስት አውራጃ በቤተልሔም
በጎል ተወለደ /፪/ መድኃኔዓለም /፪/
ለእኛ ቤዛ ሊሆን በበደልነው ፈንታ

ዛሬ ተወለደ ይገባል እልልታ /፪/

የነግሥታት ንጉሥ የነዳያን ሕይወት
ተጠቅልሎ ተኛ በጎለ እንስሳ
ትጎትናን ሊያስተምር በሕፃንነት
በከብቶች ማደሪያ ተኛ በበረት
ግኡዛን የሆኑ የማይናገሩ
እስትንፋሳቸውን እንስሳት ገበሩ

464. ተወለደ

ተወለደ አምላክ ተወለደ /፪/

አንዲት ብላቴና የአሥራ አምስት ዓመት ልጅ
ጌታን ወለደችው በመላእክት አዋጅ
በጎቱም ድንግልና ተወለደ ጌታ
ዓለምን የሚድን የሰዎች አለኝታ
ይህን ዓለም በቃሉ ከተፈጠረበት

ይበልጣል ልደቱ አምላክ ሰው የሆነበት

እንደምን ይገርማል ይሄ ተዋሕዶ

አየነው አምላክን ከድንግል ተወልዶ

ፍጹም ድንግልና ክብርን የተመላሽ
እንደምን አምላክን በማሕፀን ያዝሽ
ዓለምን በቃሉ የፈጠረ ጌታ
ወለደችው ድንግል የሔዋን አለኝታ
አንቺ ብላቴና እናታችን ማርያም

በምድር ተፈልጎ እንደአንቺ አልተገኘም

በሐሰብ በግብር ንጹሕ ስለሆነች

ለአምላክ ማደሪያ ድንግል ተመረጠች

መዝሙር በእንተ ጥምቀቱ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ

465. ሆረ ኢየሱስ

ሆረ ኢየሱስ /፪/
እም ገሊላ /፫/ ሐበ ዮሐንስ

466. በመንፈስ የሐውር

በመንፈስ የሐውር እምኃይል ውስተ ኃይል
/፪/ ካህን ካህን ወነብይ /፪/ ዮሐንስ
መጥምቅ /፪/
ትርጉም፡- ካህንና ነቢይ የሆነ ዮሐንስ
መጥምቅ ከኃይል ወደ ኃይል
በመንፈስ ይሸጋገራል

467. መኑ እንደሰት

ኑኑ እንደሰት /፪/
ጌታ ተጠመቀ /፬/ ተጠመቀ በማየ
ዮርዳኖስ /፪/

468. አጥምቆ በማይ

አጥመቆ በማይ /፪/

ዮሐንስ /፫/ አጥመቆ በማይ

ትርጉም፡- ዮሐንስ መድኃኒታችንን በውሃ አጠመቀው

469. ዮሐንስኒ ይቤ

ዮሐንስ /፪/ ይቤ ዘአጥምቆ በዮርዳኖስ /፪/

ርኢክሞ ወስእንኩ ጠይቆቱ ስእንኩ /፪/

ትርጉም፡- በዮርዳኖስ ጌታን ያጠመቀው ዮሃንስ

ጌታዬን አየሁት መርምሬ ልደርስበት አልቻልኩም

470. ይእዜኒ ለሰላም

ይእዜኒ ለሰላም ንትለዋ ለሰላም /፪/

ተጠምቀ ነዋ መድኃኔዓለም መድኃኒነ መድኃኔዓለም
/፪/

471. ዮሐንስ ሐደ ዮርዳኖስ

ዮሐንስ /፪/ ሐደ ዮርዳኖስ

የበደለዉን ሕዝብ ጠርቶ ለንስሐ

ያስተምር ጀመረ ገብቶ ከበርሐ

አባጣ ጎርባጣ ጠማማ ኮረብታ

ይስተካከል አለ ሁሉም በየቦታ

በዮርዳኖስ ማዶ በሔኖን ከተማ
የንስሐ ጥሪ በሩቁ ተሰማ
ግመል ጸጉር ለብሶ ወገቡን ታጠቀ
ዮሐንስ ተመርጦ ጌታን አጠመቀ
ባሕር ተጨነቀች ሸሸችም በፍርሃት

እሳተ መለኮት እንዳያቃጥላት

መንፈስ ቅዱስ መጣ ሊሆነዉ ምስክር

ከአብ መወለዱን ልጅነቱን ሊያከብር

472. ወቅድሳት

ወቅድሳት መንፈስ
ወሀበነ ማየ መንጽኤ ዚአነ
ትርጉም፡- መንፈስ ቅዱስ በመቅደስ
ለኃጢአታችን ማንጫ ውኃን ሰጠን

473. መድኃኒነ ተጠመቀ

መድኃኒነ ተወለደ ነዋ
መድኃኒነ ተጠመቀ ነዋ
ይእዜኒ ለሰላም ንትልዋ /፪/

ትርጉም፡- መድኃኒታችን እነሆ ተወለደ
መድኃኒታችን ተጠመቀ አሁንም እነሆ
ሰላምን እንከተላት

474. ሶበ መጽአ

ሶበ መጽአ ቃል እምሰማይ ለተናብቦ /፪/
ከበቦ /፬/ ሰማይ ባሕር ነድ በማይ ከበቦ /፬/
ትርጉም፡- ቃል ከሰማይ ለመናገር በመጣ
ጊዜ እሳት የዮርዳኖስን ባህር ከበበው
ውኃውም የሚሄድበት ቦታ ከበበው
ውኃውም የሚሄድበት ቦታ ጠበበው

475. ወጽአ ወገብአ

ወጽአ ወገብአ በሰላም /፪/ ወገብአ በሰላም
/፪/
ትርጉም፡- በሰላም ወጥቶ በሰላም ገባ

476. ፈለገ ዮርዳኖስ

ፈለገ ዮርዳኖስ የእምነታችን ጣእሙ
ለክርስቲያን ታሪክ አንቺ ነሽ መቅድሙ
ቅድስት /፫/ ዮርዳኖስ ሆይ የጌታ ሀገሩ
አብ ወልድ መንፈስቅዱስ በአንቺ ላይ
አደሩ

477. ኢየሱስ ሆረ

ኢየሱስ ሆረ አገረ እሴይ
ዮሐንስ አጥመቆ በማይ /፪/
ወለደነ እመንፈስ ወማየ

478. እንዘ ሕጻን

እንዘ ሕፃን ሊቀ በዮርዳኖስ ተጠምቀ
ኧኸ በዮርዳኖስ /፬/ ተጠምቀ በዮሐንስ

479. ልዑል እግዚአብሔር

ልዑል እግዚአብሔር /፪/ ምስጋና ይገባሃል /፪/
ለጥምቀት በዓል /፪/ በሰላም በጤና አደረስከን /፪/

480. በጎል በጎል

በጎል በጎል ሰብዓ ሰገል በጎል ሰብዓ ሰገል
በጎል ሰብዓ ሰገል ሰገዱለት /፪/
ድንግል ማርያም ንጽህት ቅድስት /፪/
የጌታዬ እናት ምስጋና ይገባሻል
ከሴቶች ሁሉ ባንቺ አድሮብሻል /፪/

ፀሐይ /፪/ ፀሐይ ሠረቀ /፪/
ፀሐይ ሠረቀ ክርስቶስ ተጠምቀ
በጎል በጎል አማኑኤል /፪/
እግዚአብሔር ፍቅሩን ሲገልጽልን
አንድያ ልጁን ለኛ ሰጠን
ስጋን ነስቶ ከእናታችን /፪/
ኃጢአታችንን ሊያስወግድልን
ክርስቶስ ጌታ ተወለደልን
እልል /፪/ ደስ ይበለን /፪/
መድኅን ተወልዶ ነፃ ወጣን
ዮሐንስ አጥምቆ ድል አገኘን
አንቺ ዮርዳኖስ ምንኛ ታደልሽ /፪/
የእግዚአብሔር መንፈስ ከላይ ወርዶብሽ
የዓለም መድኃኒት ተጠመቀብሽ

481. ዮሐንስኒ

ዮሐንስኒ ያጠምቅ /፪/
በጌኖን /፬/ በማዕዶተ ዮርዳኖስ
ዮሃንስ ሲያስተምር ያጠምቅ
በጫካ በሜዳ ››
ግመል ፀጉር ለብሶ ››
ሆኖ ምድረ በዳ ››
ወንዞችና ባሕሮች ያጠምቅ
ብዙዎች እያሉ ››
እንደምን ታደለች ››
ዮርዳኖስ ከሁሉ ››
አምላኩን የሚወድ ያጠምቅ
ብዙ ሰው እያለ ››
ጌታውን ለማጥመቅ ››
ዮሐንስ ታደለ ››
ከሐጢአት ተለዩ ያጠምቅ
በውሃ ተጠመቁ ››
መንግስተ ሰማያት ››
እንዳለች እወቁ ››

482. በወንጌሉ ያመናችሁ

በወንጌሉ ያመናችሁ /፪/
እንኳን ለብርሃነ ጥምቀቱ አደረሳችሁ /፬/

483. አንሶሰወ

አንሶሰወ /፪/ ወአስተርአየ
ወረደ ወልድ /፬/ ወልድ ውስተ ምጥማቃት

484. ሃሌ ሉያ

ሃሌ /፪/ ሃሌሉያ ሃሌ ሃሌ ሌያ ሃሌሉያ
ኧኸ ተጠምቀ ሰማያዊ በእደ መሬታዊ /፪/

አምላክ ሆይ ሕዝቦችህ ዳኑ በልደትህ
አምላክ ሆይ ሕዝቦችህ ዳኑ በጥምቀትህ

485. እግዚኦ መርሐ

እግዚኦ መርሐ ዮርዳኖስ አጽብሐ
ወበ እየ ዮሐንስ ወበ እየ ፍፁመ ተፈስሐ
ጌታውን መራና ዮርዳኖስ አደረሰው
በዚህም ዮሐንስ በዚህም ፈፅሞ ደስ አለው

486. በእደ ዮሐንስ

በእደ ዮሐንስ ተጠምቀ ኢየሱስ ናዝራዊ
ሰማያዊ /፫/ ኢየሱስ ናዝራዊ

487. የዓለምን በደል

የዓለምን በደል የሰውን ግፍ አይቶ
ዘጠና ዘጠኙን መላእክትን ትቶ
ፅድቅን ለመመስረት በደልን አጥፍቶ
የሰላሙ መሪ የሰላሙ ዳኛ
አምላክ ተወለደ ተጠመቀ ለኛ /፪/
የሰማዮች ሰማይ የማይችለው ንጉሥ
ተወልዶ ሲጠመቅ እኛን ለመቀደስ
ተራሮች ደንግጠው ዘለሉ እንደ ፈረስ
ባሕር ተጨነቀች ጠበባት መሬቱ
ዮርዳኖስም ሸሸ አልቆመም ከፊቱ
እንደተናገረው ዳዊት በትንቢቱ
ልጁ በዮርዳኖስ ጽድቅን ሲመሰርት
መጣ በደመና ሰማያዊው አባት
እየመሰከረ የልጁን ጌትነት
እንደምናነበው በወንጌል ተፅፎ
መንፈስ ቅዱስ ታየ በራሱ ላይ አርፎ
በርግብ ምሳሌ ክንፉን አሰይፎ
ባሕር ስትጨነቅ ተራራው ሲዘልል
ሰማዩ ሲከፈት ደመና ሲናገር
ዓለም በዛሬው ቀን አየች ልዩ ምስጢር

488. አማን በአማን

አማን በአማን /፪/
ኧኸ መንክረ ስብሐተ ጥምቀቱ /፪/
እውነት በእውነት /፪/
ድንቅ ነው የጌታ ጥምቀት

489. ግነዩ ለእግዚአብሔር

ግነዩ ለእግዚአብሔር እስመ ሐር
እስመ ለዓለም ምህረቱ እስመ ለዓለም /፪/
እናመስግንሽ የአምላክ እናት በዝማሬ
የዓለም ቤዛ ነውና ማህፀንሽ ፍሬ /፪/
ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ካንቺ ተወልዶ
መለኮት ወረደ ዮርዳኖስ እኛን ለመቀደስ /፪/
በድንግልና የወለድሽው ያንቺ ፅንስ
የድኩማኖች ብርታት ነው የሕሙማን
ፈውስ
በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ እዳችን ፋቀ
በቸርነቱ አወቀን ከበደል አራቀን
ስምሽን የጠራ ዝክርሽንም ያዘከረ
በመንግስተ ሰማይ ይኖራል እንደተከበረ
ብርሃነ መለኮት ያደረብሽ አዳራሽ
ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ድንግል አንቺ ነሽ
እመቤታችን እናታችን ማርያም
የተማፀነሽ ይኖራል እስከ ዘለዓለም /፪/
ድንግልናሽም ሳይለወጥ ወልድን የወለድሽ
የጌታችን እናት ማርያም ድንግል አንቺ ነሽ

490. ጥምቀተ ባሕር

ጥምቀተ ባሕር ዮርዳኖስ ነያ /፪/ ሃሌ ሉያ /፬/
ጌታችን ሲጠመቅ ባሕር ምን አለች
አልችለውም ብላ ወደፊት ሸሸች
ብርሃነ መለኮት በወንዙ ሲሞላ
ዮርዳኖስም ሸሸች ቀረች ወደኋላ
ማን ነበር የመጣው ደመናውን ጭኖ
መንፈስ ቅዱስ ታየ በርግብ አምሳል ሆኖ
ለልጁ ምልክት ሊሰጥ ፈለገና
ቃሉን ተናገረ ሆኖ በደመና
ጌታችን ሲጠመቅ በሠላሳ ዓመት
ባሕር ኮበለለች ግዑዟ ፍጥረት
ሰማይ ተከፈተ ሆነልን ፀአዳ
ከሩቅ መጥቷልና አብ ታላቅ እንግዳ
እልል በይ ዮርዳኖስ የጽድቅ መገኛ
የሕይወት መሠላል ድኅነታችን ለኛ
ቀላያት አብርህት ብዙዎች እያሉ
እንደምን ተመረጥሽ ዮርዳኖስ ከሁሉ

491. በሠላሳ ክረምት

በሠላሳ ክረምት በዮርዳኖስ ተጠምቀ
በዮርዳኖስ /፪/ ዮርዳኖስ /፪/
ተጠምቀ በዮሐንስ

492. ኧኸ ሐዲኅ ተስዓ

ኧኸ ሐዲኅ ተስዓ ኧኸ ወተስዓተ ነገድ
ቆመ ማዕከለ ባሕር

493. ሐዲጎ ተሰዓ

ሐዲጎ ተሰዓ ወተስዓተ ነገደ ነገደ
ኧኸ ማዕከለ ባሕር /፬/ ቆመ ማዕከለ ባሕር

494. ዮሐንስኒ ሐሎ

ዮሐንስኒ ሐሎ ያጠምቅ
በሔኖን በቅሩበ ሳሌም

495. ወረደ ወልድ

ወረደ ወልድ /፫/
እምሰማያት ውስተ ምጥማቃት /፪/

496. በፍሥሐ

በፍሥሐ /፪/ ወበሰላም
ወረደ ወልድ /፬/ ወልድ ውስተ ምጥማቃት

497. መፅአ ቃል

መፅአ ቃል እም ደመና ዘይብል /፪/
ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር /፪/
መጣ ቃል ከደመና እንዲህ የሚል /፪/
የምወደው የማፈቅረው ልጄ ይህ ነው /፪/

498. በፍስሐ ወበሰላም እምሰማያት

በፍስሐ ወበሰላም /፪/

ወረደ ወልድ /፪/ ውስተ ምጥማቃት /፪/

ትርጉም፡- በደስታና በሰላም እግዚአብሔር ወልድ

ወደ መጠመቂያ ወረደ

499. ነድ ለማየ ባሕር

ነድ ለማየ ባሕር ከበቦ /፪/

ማየ ባሕር ጎበ የሐውር ፀበቦ /፬/

ትርጉም፡- እሳት የባሕሩን ውሃ ከበበው ባሕሩም

የሚሄድበት ጨነቀው።

500. ቅዱስ

ቅዱስ /፫/ አልፋ ሕያው አምላካችን ክብሩ ይስፉ /፪/
እስይ ተጠመቀልን እኛ እንዳጠፉ

501. ቤዛ ኩሉ

ቤዛ ኩሉ ዓለም ዮም ተጠምቀ /፪/
ቤዛ ኩሉ ዓለም ዮም ተጠምቀ /፪/

502. በዛሬው ጥምቀቱ

በዛሬው ጥምቀቱ እሰይ እሰይ

ተነግሮ አዋጅ እሰይ እሰይ

ነጻነት አገኘን እሰይ እሰይ

በእግዚአብሔር አብ ልጅ እሰይ እሰይ
እሰይ እሰይ ተጠመቀ /፪/

ከሰማየ ሰማይ ወረደ /፪/
በቅዱስ ዮሐንስ ተጠመቀ
አብም መስከረ እሰይ እሰይ

ቃሉን አላበየም እሰይ እሰይ

የምወደው ልጄ እሰይ እሰይ

ይሄ ነው እያለ እሰይ እሰይ

ጌታ በዮሐንስ እሰይ እሰይ
ሊጠመቅ ሲል ገና እሰይ እሰይ
ወደ ኋላ ሸሸ እሰይ እሰይ
ዮርዳኖስ ፈራና እሰይ እሰይ
ዘለሉ ተራሮች እሰይ እሰይ

እንደ ጊደር ሁሉ እሰይ እሰይ

እፁብ ነው ድንቅ ነው እሰይ እሰይ

ምን ይገርም እያሉ እሰይ እሰይ

ውኃን ወይን አረገ እሰይ እሰይ
በተጠራበት ቤት እሰይ እሰይ
የብርሃናት ጌታ እሰይ እሰይ
የዓለም መድኃኒት እሰይ እሰይ

503. ኢየሱስ ክርስቶስ

ኢየሱስ ክርስቶስ ይወደናል ይጠብቀናል /፪/
በጥምቀቱ ልጅነት ሰጥቶናል /፬/

504. ዮሐንስ አጥምቆ

ዮሐንስ አጥምቆ ለኢየሱስ /፪/
በፈለገ ዮርዳኖስ በፈለገ ፈለገ ዮርዳኖስ /፪/

505. ጥምቀትከ ይኩነነ ቤዛ

ጥምቀትከ ይኩነነ ቤዛ /፪/
ይኩነነ ቤዛ /፬/ ጥምቀትከ ይኩነነ ቤዛ /፪/

መዝሙር በእንተ ቅዱስ ኡራኤል

506. ዓይኑ ዘርግብ

ዓይኑ ዘርግብ ዓይኑ /፪/

ሐመልማለ ወርቅ /፪/

ልብሱ ዘመብረቅ /፪/

ነፍስና ሥጋዬ በምግብ ተጣልተዉ
መላኩ ኡራኤል ቆሞ አስታረቃቸዉ
ለሰዎች ድኅነት ፅድቅን የሚሰብክዉ
ነዉና ኡራኤል የሰላም መላእክት
እጅና እግሬ ታስሮ ሽባ የነበርኩኝ

ይሄዉ ተጠምቄ በጠበሉ ዳንኩኝ

ስለቴ ሰምሮልኝ ሁሉን አጊንቻለዉ

ለአምላክ ኡራኤል እመሰክራለዉ

አልፈልግም ሐኪም ምን ያደርጋልኛል
አምላክ ኡራኤል ፈጥኖ ያድነኛል
ሕሙማን ለምኑ ስንፋና አይያዛችሁ
ኑና ተጠመቁ ፀበሉ አለላችሁ
ያመናችሁ ሰዎች ኑና ተጠመቁ

አማላጅነቱን በግልፅ አሳዉቁ

አምላክ ኡራኤል አንተ ችላ አትበለኝ

መጥቻለዉ እና በችሎታህ እርዳኝ

507. ኡራኤል አማልደን

ኡራኤል አማልደን ከአምላክችን

እንዳንጠፍ እንዳንሞት በነፍሳችን /፪/

508. መላከ ሰላም

መላከ ሰላም /፫/

ኡራኤል /፪/ መላከ ሰላም

509. ሐመልማለ ወርቅ

ሐመልማለ ወርቅ /፫/

ኡራኤል /፫/ ሐመልማለ ወርቅ

510. ከመ ትባርከነ

ከመ ትባርከነ በመስቀልከ ዘወርቅ /፪/
ተዋነይ በጽድቅ /፬/ ዑራኤል ሐመልማለ ወርቅ

511. መልዓከ ሰላምነ

መልአከ ሰላምነ ሊቀ መላዕክት ኡራኤል /፪/
ሰአል ወጸልይ በእንቲአነ
አእርግ ጸሎተነ ቅድመ መንበሩ ለመድኃኔዓለም
ፀበልህ የሚፈውስ የዋህ መልዓክ /፪/
የምህረት ዝናምህን ፍጥረት ሁሉ ያደነቀው
ጸጋህ ልብስ ሆኖ እንዲያስጌጠን
በረድኤት በፍቅርህ እባክህን አትለየን
መራሔ ብርሃን ኡራኤል ሆይ አትለይን
በምልጃ ብርሃንህ በረድኤትህ ጥላ ስር ነን
ፈጣን ንስር ነው ለምህረት
ሰውን ለማዳን /፪/ የማይዘገይ

512. ኡራኤል ወሩፋኤል

ኡራኤል ወሩፋኤል /፪/
አስተምህሩ ለነ በስሂን
ወበ ትህርና ህበ ውዕቱ ነበልባል

513. ቀዋምያን ለነፍሳት

ቀዋምያን ለነፍሳት እሙንቱ ሊቃናት
ዑራኤል ወሩፋኤል
ይትፌነዉ ለሳህል /፪/ እም ህበ ልዑል
ለነፍሳት የቆሙ እነዚህ መላዕክት
ዑራኤልና ሩፋኤል
ከልዑል ዘንድ ለይቅርታ /፪/ ይላካሉ
ከልዑል

መዝሙር በእንተ ጾም

514. አምላካችን ጾመልን

አምላካችን ጾመልን አርባውን ቀን /፪/

ምሣሌውን ሰጠን ምሳሌውን /፪/

515. ዘጾመ ወጸለየ

ዘጾመ ወጸለየ ወሠዓለ /፪/

እሙነ ይነሥእ ዕሴቶ /፬/

የጾመ የፀለየ የለመነ /፪/

እውነት ነው ዋጋውን ይቀበላል /፬/

516. ንጹም ጾመ

ንጹም ጾመ ወናፍቅርቢጸነ /፪/

ወንትፋቀር /፬/ ንትፋቀር በበይናቲነ /፪/

ትርጉም፡- ጾምን እንጹም ወንድሞቻችንን እንውደድ እርስ በእርሳችን እንዋደድ

517. ማርያም በስምሽ

ማርያም በስምሽ ይዘናል ቀኖና /፪/

ትንሣኤሽን ልጅሽ ያሳየናልና /፪/

ፆም ማለት እንግዲህ ይኸው ነው ሥርዓቱ /፪/

ሐዋርያት ፆመው ለእኛ አበረከቱ /፪/

ነፍስና ሥጋችን በመብል ተጣልተው /፪/

ሽማግሌ ሆኖ ፆም አስታረቃቸው /፪/

አብረው እያደሩ አብረው እየዋሉ /፪/

አያምርም አይመስልም በመብል ሲጣሉ /፪/

ነፍስም ከሥጋዋ መለየቷን አውቃ /፪/

የዓለም ተድላዋን ደስታዋንም ንቃ /፪/

በፆም በሱባኤ ትኖራለች ታጥቃ /፪/

ነፍስም ለሥጋዋ ትመክረው ጀመረች /፪/

በብዙ ምሳሌ እያመሳሰ ለች /፪/

ሥጋዬ ሞኝ ነህ መብልን አትውደደው /፪/

ከአዳም አንሥቶ ከመጀመሪያው ሰው /፪/

ለመብል መገዛት ሲጠቅም መች አየኸው /፪/

518. ሙሴኒ ጾመ

ሙሴኒ ጾመ /፪/ በደብረ ሲና

እግዚእነ ጾመ አርአያሁ ከመ የሀበነ፡፡

ትርጉም፡- ሙሴ በደብረ ሲና (በሲና ተራራ) ጾመ፡፡

ጌታችንም ምሳሌውን (አርአያውን) ሊሰጠን ጾመ፡፡

519. እንጹም እጸልይ

እንጹም እጸልይ /፪/ ሁላችን /፪/

ድኅነት እንድናገኝ ከመድኃኒታችን /፪/ እንጹም ሁላችን

የሰው ልጅ እንዳትሆን የመንፈሱ ድኃ

ሰጥቶሃልና ዕድሜን ለንስሐ

አርባ ሌሊትና አርባ ቀን የጾመው

ኃጢአት ኖሮት ሳይሆን የሰው ልጅ ለአንተ ነው

መብላት ለሥጋ እንጂ ለነፍስ አይጠቅምም

እንዳለ መጽሐፍ ሰው በእንጀራ አይኖርም

ስትጾም ስትጸልይ ለሰዎች ተመች

ፊትህን አታክፋ እንደግብዞች

መከራና ችግር ቢደራረብብህ

ሰይጣንን ድልንሳው በጾም በጸሎት

ገዳመ ቆሮንጦስ የክርስቲያን አርማ

ዝናሽ ተነገረ በዓለም ተሰማ

520. ፍቅርና ሰላምን

ፍቅርና ሰላምን ታፈራለች ጾም /፪/

ፍፃሜ የሌለለዉ እስከ ዘላለም /፪/

የጾምን ፍሬ ሁላችን አዉቀን /፪/

በፀሎት እንትጋ ፍሬዉ አይለፈን /፪/

አምላክ ተፈተነ በክፍ ጠላት /፪/

ጾምን ሊመሰርት ስለኛ ሕይወት /፪/

አምላክ ተሸከመ ሕመማችንን /፪/

የሕይወትን ዉኃ ከጎኑ ሰጠን /፪/

ሕዝቦችህን ጠብቅ ክፉ ፈተና /፪/

ቅዱስ አምላካችን ኃይላችን ነህና /፪/

521. ክርስቶስ በስምህ

ክርስቶስ በስምህ ይዘናል ቀኖና

ስቅለት ትንሳኤህን እናያለንና

ጾም ማለት እንግዲህ ይኸዉ ነዉ ሥርዓቱ

ሐዋርያት ጾመዉ ለእኛ አበረከቱ

ነፍስና ስጋችን በመብል ተጣልተዉ

ሽማግሌ ሆኖ ጾም አስታረቃቸዉ

አብረዉ እያደሩ አብረዉ እየዋሉ

አያምርም አይመስልም በመብል ሲጣሉ

ነፍስም ከስጋዋ መለየቷን አውቃ

የዓለም ተድላዋን ደስታዋን ንቃ

በጾም በሱባኤ ትኖራለች ታጥቃ

ነፍስም ለሥጋዋ ትመክረዉ ጀመረች

በብዙ ምሳሌ እያመሳሰለች

ሥጋዬ ሞኝ ነህ መብልን አትዉደድ

ከአዳም ጀምሮ ከመጀመሪያዉ ሰዉ

መብል ሲጎዳ እንጂ ሲጠቅም መቼ አየኸዉ /፪/

522. አልተወኝም

አልተወኝም ጌታ ለካስ ይወደኛል
ዛሬም ስበድለው ልጄ ነህ/ነሽ ይለኛል /፪/
በበደል ጉራንጉር በኃጢአት ጫካ
ብጠፋበት እንኳን አልተወኝም ለካ
ዛሬም ልጄ ብሎ ዳግም ይጠራኛል
ለካስ አልጠላኝም ጌታ ይወደኛል /፪/
ለሥልጣን ለክብሬ ብዬ ስክደው
ለገንዘብ አድልቼ እኔ ስረሳው
ለኔ ያለው ፍቅር አልቀነሰብኝም
ዛሬም ይወደኛል ጌታ አልጠላኝም /፪/
ታዲያ ለዚህ ፍቅሩ ለሌለው ወሰን
ከጭንጫው መቃብር ላወጣኝ እኔን
በሕይወቴ ሁሉ ፍፁም ለመራኝ
ክብርና ምሥጋና አቀርባለሁኝ /፪/

523. አቤቱ በመንግስትህ

በመንግስትህ አስበኝ /፪/

በበደሌ ብዛት /፪/ አይተህ አትጣለኝ /፪/

ሳስበዉ በደሌ ብዙ ነዉ
በጨለማ ነፍሴን በላት ወድማ /፪/
ሆዴ ባባ አፈሳለዉ እንባ /፪/
እርቃኔን ቀረሁኝ ተገፈፈ ልብሴ
መድረሻ ጠፋብኝ ተጨነቀች ነፍሴ
የብርሃን ጸዳሌ ከዓይኔ ተገፈፈ
ከፊትህ ለመቆም ጉልበቴ ታጠፈ
አልቻልኩም ደግፈኝ እንድቆም /፪/
ለገነት የበቃዉ ያቀማኛ ሽፍታ
እኔንም ደግፈኝ አዉጣኝ የዛን ለታ /፪/

524. አባታችን ሆይ

አባታችን ሆይ የሁላችን ጌታ /፪/

ቅዱስ መንፈስህን ስጠን በተርታ /፪/

ወዳንተ መልስ የሰዉን ልቡና /፪/
ባላወቀዉ መንገድ እርሱ ሄዷልና /፪/
እዝነ ልቦናችንን ወደ አንተ አዘንብለን /፪/
ይቅርታ ልንጠይቅ ከፊትህ የቆምነዉ /፪/
መሐሪ መሆንህን ስለምናዉቅ ነዉ /፪/
አይተህ እንዳላየ ታልፈዋለህ ሁሉም /፪/
መዓቱም ምሕረቱም ሁሉም ያንተ ሲሆን /፪/
ሥልጣንህ ረቂቅ ነዉ አይመረመርም /፪/

ዘመንና ወራት ሊሽሩት አይችሉም /፪/
የፍቅር ባለቤት ቸሩ አምላካችን /፪/
ዕድሜ ለንስሐ ስጠን ለሁላችን /፪/
እንማልድሀለን በለቅሶ በሐዘን /፪/
የይቅርታህ ብዛት ከእኛ ጋር እንዲሆን /፪/
የሰማይ መላእክት የምድር ሰራዊት /፪/
ያመሰግኑሀል በቀንና በሌት /፪/

525. በኢየሩሳሌም

በኢየሩሳሌም በበጎች በር በቤተሳይዳ እኖር ነበር

ማን ያድነኛል እያልኩኝ አልጋህን ይዘህ ሂድ አለኝ

›› ›› እምነትህ አዳነህ አለኝ

›› ›› አምላኬ መጥቶ ፈወሰኝ

በአልጋ ላይ ከዋልኩ ሰንብቻለዉ
ሰዉነቴ አልቆ መንምኖለዉ
ዉኃዉን ሳያማታ ቅዳሜ
ቀድመዉ የዳኑ እኔ ቆሜ
አይዞህ የሚለኝ የሚያጽናናኝ
ደጋፊም የለኝ ብቸኛ ነኝ
ሠላሳ ስምንት ዓመት እያሉ

ተሳለቁብኝ መጻጉ እያሉ

እዘንልኝና አድነኝ

ሙሉ ጤነኛ አድርገኝ

ልትድን ትወዳለህ ሲለኝ
እዉነትም እዉነት አልመሰለኝ
አም እወዳለዉ ስለዉ ጌታ
ፈወሰኝ አምላክ የእኔ አለኝታ
ስማኝ አምላኬ እጮሃለዉ

ኃጢያቴ በዝቶ አለቅሳለዉ

በመብል ጠፍቶ ልጅነቴ

ባሪያህ አድርገኝ ዉድ አባቴ

እንደ እኔ ታማሚ የሆናችሁ
አምናችሁ ጌታ ያድናችሁ
እንደኔ ድዉይ የሆናችሁ
የጌታ እናት ታማልዳችሁ

526. የዳዊት ሐዘኑ

የዳዊት ሐዘኑ የጴጥሮስ ንስሐ /፪/
እኛን ያነጻናል እንደ ንጹሕ ዉኃ /፪/

ይቅር ባይ ነህና የሰዉን በደል
የእኔን አበሳዬን አሁን ይቅር በል
የዳዊት ሐዘን የጴጥሮስ ለቅሶ /፪/

የተቀበለ አምላክ ተበድሎ ክሶ

ዛሬም ይቅር በል የሕዝቡን አበሳ /፪/
አንተ የከፈልክልን የእኛ ሁሉ አበሳ
በደለኛዉ እኔ የአንተን ሕግ ጥሼ /፪/

ንጹህ ስጋዬን በጭቃ ለዉሼ

በንስሐ ዉኃ አጥቤና አድሼ /፪/
አሁን ይቅር በለኝ መጣሁ ተመልሼ

527. ልቤ አቤት በል

ልቤ አቤት በል እንጂ አምላክህ ሲጣራ

በሐዘን በልቅሶ ትካዜህን አዉራ

በደሌን አዉቄ ይቅርታ ልጠይቅ

ሁሉን ቻይ ነህና ፍጥረትህን የማትንቅ

አለቅሳለዉ ዘወትር አነባለዉ
አዉቃለዉ አምላኬን ብዙ በድያለዉ
ልቅሶና ጮኸቴን ተቀበለኝ
ጎስቋላ ሆኛለዉ ኃጢያት ያደከመኝ /፪/

መንገድ ተሳልፌ ፈጣሪን አስቀየምኩ

በሚጠፋ ንብረት አምላኬን ለወጥኩህ

አሁን ግን አምኜ ብዙ እንደ በደልኩህ

በረከሰ አንደበት ይቅርታን ለመንኩህ

የኃጢያት ጉዞ እኔን ሰልችቶኛል
ኃጢያቴ በዝቶብኝ መቆም ተስኖኛል
ነሽና በፊቱ ክብር ሞገስ ያለሽ
ድንግል ልመናዬን አድርሺ ከልጅሽ

528. አቤት አቤት ኃጢያቴ

አቤት አቤት ኃጢያቴ ብዛቱ /፪/

መስፈሪያም የለዉም እርሱ ሊተወኝ በቸርነቱ

ከእኔ ኃጢያት ይልቅ ይበዛል ምህረትህ
አደራ እንድትምረኝ ጌታ በቸርነትህ /፪/
እስከ አንገቴ ደርሶ የኃጢአቴ ብዛት
ሊዉጠኝ ነዉና አዉጣኝ የእኔ አባት /፪/

ለእግሬ መቆሚያ ከሌለዉ ባሕር
ድረስልኝ ጌታዬ ወድቄ እንዳልቀር /፪/
ወደ አንተ ስጣራ በጩኸት ደክሜ
ተስፋ ሊያስቆርጠኝ የኃጢያት ሸክሜ /፪/
ወደ ኃላ ልቤ እንዳይመልሰኝ
መልካም እረኛዬ አንተ ጠብቀኝ /፪/
የሰራሁት ሁሉ ካንተ አይሰወርም
ይቅር ትለኛለህ አልጠራጠርም /፪/
መመለሴን እንጂ መሞቴን አትወድም
በዚህ እጽናናለሁ ከፍቅርህ አልርቅም /፪/
አንተን ስበድልህ ይቅር እንዳልከኝ
የሚበድሉኝን ይቅር በልልኝ /፪/
ይቅርታ ማድረግ እኔን ቢከብደኝ
አንተ አይቸግርህም ይቅርታ ስጠኝ /፪/

529. አደባባይ ቆሜ

አደባባይ ቆሜ ስምህን ከመስበክ

መጀመሪያ ልቤ ከፊትህ ይንበርከክ

ከአገልግሎት በፊት አንተን ልወቅህ

መሥዋእት ከማቅረብ ልታዘዝልህ /፪/

አሐዱ አብ ብዬ ስምህን ብቀድስ

ለድሆች ብሰጥ ቤትህ ብገሰግስ

በመላእክት ልሳን ብዘምር በእልልታ

ምን እጠቅምሀለዉ ካልፈራሁህ ጌታ /፪/
ተራራ እስካፈልስ እምነት ቢኖረኝ

ሥራ ከሌለበት ምንም አይጠቅመኝም

ልቤን ስትመረምር ከሆንኩኝ ቀላል

ክርስቲያን መባሉ ምን ይጠቅመኛል /፪/

ጨዉ አልጫ ቢሆን በምን ይጣፍጣል
ከዉጭ ተጥሎ በእግር ይረጋገጣል
አንተን ለሚከተል እንዳልሆን እንቅፋት
አምልኮቴ ይሁን በፍቅር በፍርሃት /፪/

የእዉቀት ሰዉ መሆን አይጠቅመኝ

እኔስ መስቀልህ ነዉ ፍቅርህ ያሸነፈኝ

ከእምነቴ የተነሳ መታዘዝ ይሁነኝ

ስምህን መፍራት ነዉ በእምነት የሚያኖረኝ /፪/

530. ወደ ሕይወት መንገድ

ወደ ሕይወት መንገድ ይመራኛል ጌታ /፪/

በጨለማ ህይወት እንዳልንገላታ /፪/

ፈጣሪ ብቻ ነዉ ሕይወቴና ክብሬ /፪/

በእርሱ ደስ ይለኛል ሳቀርብ ዝማሬ /፪/

ጉልበት ሁሉ ለአንተ በፍርሃት ይሰግዳል /፪/

ምህረትን አድለን ፈጣሪ ቸል አትበል /፪/

ለኃያሉ ጌታ በአንተ ይረካል /፪/

በምህረትህ ማረን አቤቱ ፈጣሪ /፪/

ሰላምን አድላት ለኢትዮጲያ /፪/

እጆቿን ዘርግታ ስትል ሃሌ ሉያ /፪/

531. ነነዌን ሊያቃጥል

ነነዌን ሊያቃጥል የወረደዉ እሳት /፪/

ተመልሶ አረገ /፪/ በጸምና ጸሎት /፪/

ስለሆነ ከልብ የሐዘናቸዉ ምንጩ

ነበር እንደ ራሔል /፪/ ዕንባ እየረጨ

ለነነዌ ሰዎች ደስታን ያበሰረ

ጋሻና ጦራቸዉ /፪/ ጸምና ጸሎት ነበር

እንኳን የሰዉ ልጆች እንስሳት ሳይቀሩ

በዮናስ ሰብከት /፪/ ጸም ጸሎት ተማሩ

እስራኤል ሰለቸዉ

እስራኤል ሰለቸዉ የሰማዩ መና /፪/

ዓለም አምሮት ሄደ ጸጋዉን ተወና /፪/

የእግዚአብሔር ስጦታ ጎብስቱ ሰልችቶት /፪/

ዓለም አምሮት ሄደ ከተወዉ ባርነት /፪/

የፈርያን ጅራፍ አልታየዉ አለ
የእህል አምሮቱን ዉርደቱንን ከለለ /፪/
ግብጽ ልሂድ ብሎ አመጸ በእግዚአብሔር
መድረሱ አልገባዉም ከከነዓን ሀገር /፪/
የኪዳኑ ታቦት የሙሴ ገጽታ

ዓለም ስላማረዉ አደረገዉ ተርታ /፪/

የአምላክን ክህነት የአሮን ሥርዓት

በዓለም ለወጠዉ ትልቁን አምኃ /፪/

የጎብረቱን ጉዞ በፍቅር የሄደዉ
የማጎሌት ደስታ እስራኤል ታከተዉ /፪/
የእግዚአብሔር ድንኳን ደመና ያጀባት
የኪዳኑ አርማ በበረሃ ተዋት /፪/
ዛሬም ይህ ትዉልድ እስራኤልን ሆኗል
ቤተክርስቲያኑን አምላኩን እረስቷል /፪/

ግብጽና ባቢሎን አጓጉተዉ ወስደዉት

ወርቁን ከእጁ ጣለ መዳብ አስጎምጅቶት /፪/

ለተዘጋጀዉ ቤት ወራሾች እኛዉ ነን /፪/

መቼም ከማያልቀዉ በረከት ያደልከን

ዘላለማዊ ሕይወት ለሰጠኸኝ

ምሥጋናችን ይድርስህ ጸጋህ አይለየን

እኛ በድለን ትዕዛዝህን ጥሰን

አንተ መስቀል ላይ ደምህ ፈሰሰልን

ፍቅርህን ስናስብ እጅግ ይደንቀናል

ለዚህ ሁሉ ዉለታህ ምን እንከፍላለን

532. አዝናለዉ አለቅሳለዉ

አዝናለዉ አለቅሳለዉ

ስለ በደሌ ሁልጊዜ አለቅሳለዉ

አዝናለዉ አለቅሳለዉ

ስለጥፋቴ ሁልጊዜ አለቅሳለዉ

ነገር ግን መሐሪ ነህና እንደምታድነኝ አምናለሁ /፪/

ሥጋዬ ለራሱ እያታለለኝ /፪/
ሁሉን በመፈለግ ወሰደና ለጥፋት ሰጠኝ
ከመሬት ተገኝታ እመሬት ልትገባ /፪/
ከንቱ አስቀረችኝ ያሳሳች ሥጋ ሰገብጋባ /፪/
ትቻት ልመጣ ነዉ አፈር ሥጋዬን
ትቻት ልመጣ ነዉ መሬት ሥጋዬን
እንድትቀበላት አምላኬ ሆይ አደራ ነፍሴን /፪/

533. ሞቼ ስለማልቀር

ሞቼ ስለማልቀር ትንሣኤ ስላለኝ

በተስፋ ቤታችን ስለምንገናኝ

ወዳጅ ዘመዶቼ አታልቅሱ በቃኝ /፪/

አቀናለሁና ገና አዲስ ኑሮ

አምላክን አስቡት ይብቃችሁ እሮሮ /፪/

ይልቅ ጸልዩላት ለነፍሴ እረፍት

ዓለም አታላይ ናት ዘላቂ አይደለችም

ለሥጋ ነዉ እንጂ ለነፍስ አትመችም /፪/

ግን ከሥጋ ጋር ስንኖር ትዕዛዙን ከጠበቅን

534. የጥበብ ሃገሯ

የጥበብ ሃገሯ ወዴት ነዉ

ማደሪያዋስ ወዴት ነዉ /፪/

በዉኑ ጎዳናዋ ከወዴት ተቃኘ
ዝናዋ ወሬዋ ከወዴት ተገኘ
ፈልጎ የገዛት ማነዉ በቀይ ወርቅ
ባሕሩን ተሻግሮ ስሟን በማወቅ
ማነዉ ያዋረዳት ከደመና በላይ

ድምጿንስ የሰማ ከላይ ከሰማይ

እርሷን የሚጠሉ ናቸዉና ከንቱ

አይቀርላቸዉም ኃላ የሞት ሞቱ /፪/

ሁሉን የሚያዉቅ እርሱ ያዉቃታል

የእዉነት ጎዳናዋ ያስተምርላታል

በክርስቶስ ፈቃድ ምድር ላይ ታየች

እነሆ ቤት ሰራች ሰባ አምድ አቆመች /፪/

ጥበብ ግን እርሱ ነዉ መድኃኒታችን

በሥጋ ተገልጦ እኛን አዳነን

በደሙ ፈዉሶ ተወዳጀን

ለእርሱ የመረጠን ይክበር ይመስገን /፪/

535. ዋ ለነፍሴ

ዋ ለነፍሴ ምንም ስንቅ አልያዝኩኝ /፪/

አዬ ለኔስ ወዮልኝ ዋ ለነፍሴ

ምንም ስንቅ አልያዝኩም

ነፍሴን እየጎዳዉ ሳስብ ስለሥጋ
ዓለም ስትስበኝ እንዳላገኝ ዋጋ
መንፈስህን ስጠኝ ከበደል አንጻኝ
ቃልህን እሰማለሁ ማስተዋል የለኝም

ፍጹም ሆኖ መቆም ጌታ ሆይ አቃተኝ

ታዲያ እንደፈቃድህ እንዴት ብዬ ልገኝ

ድካሜን ታዉቃለህ አምላክ ሆይ አበርታኝ

አለቅሳለዉ ጌታ ከእግርህ ስር ወድቄ

ሕይወቴ ተዛብቶ በኃጢያት ማቅቄ

ዘመኔን ጨረስኩኝ መልካምን ሳልሰራ

ቸርነትህ ይርዳኝ ልኑር ካንተ ጋራ

ፈተናዉ ከበደኝ ለነፍሴ ፈራሁኝ

ደስታ ከእኔ አርቆ ቢበዛ ሐዘኔ

አትተወኝ አንተ ሁንልኝ ከኃኔ

536. ለዉለታህማ

ለዉለታህማ ጌታ ምን እንከፍልሃለን /፪/

ለማይነገር ስጦታህ ተመስገን እንልሃለን /፪/

ማቃችንን ቀይረህ አዲስ ላለበስከን
ቁስላችንን አጥበህ ዘይት ለቀባኸን
ጠላት ሲያዋርደን አንተ ላከበርከን
ለዚህ ሁሉ ዉለታህ ምን እንከፍልሃለን
እኛ በበደልን ትዕዛዝህን ጥሰን

አንተ በመስቀል ላይ ደምህን ፈሰሰልን

ፍቅርህን ስናስብ እጅግ ይደንቀናል

ለዚህ ሁሉ ዉለታህ ምን ይከፈልሃል

የእኛ ፍቅር ስቦህ ከሰማይ ወርደህ
ደካማ ሥጋችንን ተዋደህ አክብረን
እግራችንን አጥበህ ፍቅርን ላስተማርከን
ዉለታህ ክበዶናል ምን እንከፍላሃለን /፪/
ባሮች እንዳልነበርን ልጆች አደረከን

መቼም ከማያልቀዉ በረከት አደልከን

ዘላለማዊ ሕይወት ለሰጠኸን

ምሥጋናችን ይድረስህ ጸጋህ አይለየን

537. እርዳኝ ዝም አትበል

እርዳኝ ዝም አትበል የሰራዊት ጌታ

ተስፋ እንደሌለዉ ሰዉ ልቤ አያመንታ

አንተን ለማገልገል የነበረኝ ብርታት

ዛሬስ ተስኖኛል አቅቶኛል መትጋት

ጨንቆኝ እጣራለዉ ጸጋ አጥታ ሕይወቴ
እባክህ አርመኝ እርዳኝ መድኃኒቴ
ልቤ ድንጋይ ሆኖ ቃልህ አልሰበረዉ
የእጅህን ስራ ጌታዬ አስተካክለዉ

የክርስትና ኑሮ ሥርዓቱን አፍርሼ

አለቅሳለዉ ጌታ በሐጢያት ተከስሼ

ሰላምና ፍቅር ነበር ክርስትና

እኔ ግን ተናወፅኩ አልጸናሁምና

ስራዬንና ቃሌ አልገናኝ አሉኝ
በጠማማዉ ልቤ አንተን አሳዘንኩኝ
ጽኑ መሰረት ነህ የሕይወት አለት
እየተናወፅኩኝ አቃተኝ መትጋት

በእረፍት ዉኃ ዘንድ በለመለመ ሳር

በጎችህን ሁሉ በፍቅር የምታኖር

በሕይወቴ እንዲታይ የቸርነትህ ክብር

ከደጅህ ተጥዬ ለስምህ ልዘምር

538. የሰማዩ አባት

የሰማዩ አባት ደግ ነህ መልካም እረኛ ነህ

ለሁሉም ጊዜ አለህ በጊዜዉ ሁሉን ታደርጋለህ /፪/

ማን ያበድርሃል እግዚአብሔር ለአንተ ብድራትን

ሁሉን ታደርጋለህ በኃይልህ ችሎታህ

አንችልም እግዚአብሔር እኛ በአንተ ፊት

ከታናሽነቴ ጀምረህ እኔን ያስተማርከኝ

የቃልህን ወተት በቤትህ ለኔ የመገብከኝ

ላንተ የምከፍልህ እግዚአብሔር አንዳችም የለኝ

ለማልቀስ ጊዜ አለዉ አምላኬ ደርሶ ለመሳቅ

ከራሳችን ጸጉር አንዲቷን ጥቂቱን ሳናዉቅ

የእኛስ ተግባር ሆኗል ለሁሉም ደርሶ መጨነቅ /፪/

539. አቤቱ ልንበርከክ

አቤቱ ልንበርከክ ልማር

ሕግን አስተምረኝ ወድቄ እንዳልቀር /፪/

አቤቱ ለመማር ስፈልግ ደጅህን ስጠና
ተመለስ ይለኛል የሥጋ ፈተና
አቤቱ በልቤ እርሻ ላይ የዘራኸዉን ቃል
ዲያቢሎስ ወፍ ሆኖ ከልቤ ይለቅማል

አቤቱ ይህንንም ያንን ሁሉን ነገር ስመኝ

ከቤትህ እንዳልርቅ ቃልህ ይመልሰኝ

አቤቱ አባት ላንድ ልጁ እንደሚራራለት

በቁጣህ አትቅሰፈኝ በደሌን በማየት

አቤቱ ዉለታህ ምን ያህል ጌታ ያንተ ፍቅር
ምን ይከፈልሀል ሲያጠፋ ለሚምር
አቤቱ ቁስሌን አጥበህልኝ ማቄን ለቀየርከዉ
ተዓምህን እኔ ዘርዝሬ አልዘልቀዉም

አቤቱ ኃያል ነህ ገናና አማካሪም የለህ

ፍርድህ ሚዛናዊ የእዉነት አባት ነህ

አቤቱ የተዋረደዉን አንተ ታከብራለህ

መልክና ቁመና መች ትመዝናለህ

540. ላይቀር መሞት

ላይቀር መሞት አፈር መልበስ መግባት ከመቃብር

መስሎኝ ቋሚ ይህ ሥጋዬ ለእርሱ ብቻ ስጥር

ዘመን መቁጠር ዕለት ወራት ክረምት በጋ

ለሊትና ቀን ሲፈራረቅ ሲጨልም ሲነጋ

በማየቴ ሆነ መደሰቴ /፪/

ኸረ ወዲያ ወዲያልኝ ዋይ ብለሽ ለነፍሴ

አድርጎኛል የኃጢያት ምንጭ ደካማዉ መንፈሴ

መሐሪ አምላክ ለጋስ ጌታ ቸሩ ፈጣሪዬ

አንተ እኮ ነህ ለዘለዓለም ለእኔ መመኪያዬ

ይቅር በለኝ ምህረትህ አይራቀኝ /፪/

541. በእያሪኮ መንገድ

በእያሪኮ መንገድ ጌታ አንተ ስታልፍ

ግፊያ ሆኖ ስደናቀፍ

የዳዊት ልጅ ማረኝ ብዬ ተማፀንኩኝ

ዓይኔንም ፈወስከኝ ዛሬ ማየት ቻልኩኝ /፪/

አንተን እንዳላይ ቁመቴ አጠረብኝ
ከፊት እየሮጥኩ ከዛፍ ላይ ወጣሁኝ
ጌታ ሆይ ጠራኸኝ ዘኪዮስ ሆይ አልከኝ
ቤቴ እንድትገባ ፈቃድህ ሆነልኝ /፪/

ሐሴትም ሆነልኝ በጣምም ደስ አለኝ

አንተን በእንግድነት በቤቴ ተቀበልኩኝ

ኃጢያቴን ሁሉ በአንተ ፊት ጥያለዉ

ሐብቴን አካፍል ዘንድ እንዲገባ አዉቃለዉ /፪/

ክፋትን ገንዘብ መሰብሰቤን ትቼ
አንተን ልከተልህ ሁሉን እረስቼ
ኑሮዬንም ባርከዉ የሕይወት ዘመኔን
መርጫለዉ አንተን በቤትህ መኖሬን /፪/

542. ማረን አባታችን

ማረን አባታችን ማረን

ማረን እግዚአብሔር

ከዘመኑ መቅሰፍት

ከልለህ አዉጣን ሰዉረህ

እግዚአብሔር ሆይ ይበዛ ምህረትህ

ህፃናት ሲያለቅሱ እናት አባት አጥተዉ
ተስፋቸዉ ሲጨልም አዛዉንት ሚሪ አጥተዉ
አትጨክን አምላክ ቁጣህን መልሰዉ
የዘመኑን ንዳድ እሳቱን አብርደዉ
ያለዕድሜዉ ሲቀጠፍ ወጣቱ እንደ አበባ

ወላጅ አንጀቱ ሲያር ሲታጠብ በእንባ

እዘንልን አምላክ ምህረትህን አብዛ

መድኃኒት አንተ ነህ ለሕይወታችን ቤዛ

እንኳን የታመመዉ የቆመዉ ሲሰጋ
የሥጋዊ ጥበብ መላም አጥቷል ዋጋ
ከሰዉ ወገን የለም አንዳች ቅንጣት ተስፋ
ምህረትህ ይብዛልን በሞት እንዳንጠፋ

ሕግህ ከለላ ነዉ ከጥፋት መዳኛ

አንድ ለአንድ እንፅና እንዳናዝን እኛ

ሌላ መላም የለ ቃልህ ያድነነል

ከዘመኑ ስጋት ነፃ ያወጣናል

543. በስራዬ የት ይሆን

በስራዬ የት ይሆን መግቢያዬ /፪/

ጨነቀኝ ጠበበኝ ነፍሴ ወዲያልኝ /፪/

ተሸክሜ የኃጢያት ክምር /፪/
ይመሻል ይነጋል በከንቱ ስዞር /፪/
ገሰገሰ ቀኑ ጨለመብኝ /፪/
በድያለዉ ወዳንተ እጮህዉ /፪/
ይቅር በለኝ እማጸንሃለዉ
ችላ አትበለኝ ከፊትህ ቆሜያለዉ /፪/
አለፈብኝ በከንቱ ጊዜዬ /፪/

እየጓጓዉ ለዚህች ለሥጋዬ /፪/

በንሥሐ ሳላጥበዉ እድፌን /፪/

ልትደርስ ነዉ ያቺ የፈተና ቀን /፪/

544. ልመናዬን ስማኝ

ልመናዬን ስማኝ ቃሌን አድምጠኝ /፪/

እዉነተኛ አምላክ ሰላምህን ስጠኝ /፪/

ክርስቲያኖች ሁሉ ትዕዛዙን አክብሩ
ምሥጋናን አቅርቡ ስገዱ ዘምሩ
የጌታን አመጣጥ ለዓለም ንገሩ
ደቀ መዛሙርቱ ወንጌል አስተምሩ
በመልካም የሚሄድ ጽድቅን የሚሰራ

የፈጣሪዉን ስም በከንቱ የማይጠራ

ይጎበኛል በምድር ከሰማዩ ስፍራ

በቀኝ ይቀመጣል ከቅዱሳን ጋራ

ስለጠላቶቼ በጽድቅ ምራኝ
በጦር ቃል ከበቡኝ ተሳለቁብኝ
መሐሪ ይቅር ባይ መጠጊያ ሁነኝ
አንተ በቸርነትህ ይቅርታን ስጠኝ

545. ሁላችን እንጸልይ

የሐይማኖት ጸሎት /፪/

እንድናዉቅ ምሥጢሩን /፪/ የተዋህዶን እምነት

በአንድነት ሦስትነት ምሥጢሩ ከገባን

ከቶ ምንም አይኖር /፪/ የሚያደናግረን

የአምላክ ሰዉ መሆን ምሥጢረ ሥጋዌ

ያስረዳናል በእዉነት /፪/ በአንድነት ህላዌ

በአንድነት ሦስትነት ምሥጢሩ ይረቃል /፪/

በሐይማኖት ጸሎት በሐይማኖት ትምህርት ጎልቶ ይታወቃል

546. ሰዉ ለሰዉ

ሰዉ ለሰዉ /፪/ ቢፋቀር ምነዉ /፪/

ለሰዉ ይመስለዋል ብዙ የሚቆይ
ግን በድንገት ያልፋል ሁሉንም /፪/ ሳያይ
ሐብትን ያከማቻል ቀኑን ሳይዉቀዉ
በድንገት ይጠራል /፪/ አይከተለዉም
የሰዉ ልጅ በተራ መጠራቱ ላይቀር

ምነዉ አንዱ ለአንዱ መቃብር /፪/ ባይቆፍር

አይጠቅምም መጨነቅ እንዲያዉ ለዉበት

ይረግፋል ይጠፋል ሁሉም /፪/ ከመሬት

ዋ ቁንጅና ከንቱ ማማርም ብላሽ
አፈር ትቢያ ሲሆን ሲጨልም /፪/ ሲመሽ
ድኃ ባለጸጋ አንድ ነዉ መንገዱ
በጨርቅ ተገንዞ በሳጥን /፪/ መሄዱ
ሰዉ ዙሪያዉን ቢያጥር መዝጊያዉን ቢሰራ

በሕንፃ ላይ ሕንፃ ቢያስመስል ተራራ

አይቀርም መሄዱ ሁሉም /፪/ በየተራ

547. ኑ እንቅብ

ኑ እንቅብ መጠራት ሳይመጣ /፪/

ሥጋዉን እንብላ /፪/ ደሙንም እንጠጣ

የቀራንዮ በግ የአምላክ ሥጋዉ
ተሰዉቶልናል እንመገበዉ
እድፋን ኃጢያታችንን በንሥሐ አንፅተን
እንቀበለዉ አምነን በልጅነታችን
መቅረብ ወደ ጌታ በእዉነት የሚገባዉ

በስተርጅና አይደለም በወጣትነት ነዉ

ጨረቃና ፀሐይ ደም የለበሱት

ክዋክብት በሰማይ የተነጠፉት

ይሄዉ ተፈተተ እሳተ መለኮት /፪/

ቅድስት እናታችን ቤተክርስቲያን
ትመግበናለች ሥጋና ደሙን
የአማኑኤል ሥጋ ይሄዉ ተዘጋጀ
ለግብጣ ተጠራን አዋጁ ታወጀ
መጥቁ ተወለደ እንቅረብ በእልልታ

በኃላ አይረባም ዋይታና ጫጫታ

ይህንን እድል ፈጥነን እንጠቀምበት

ዓለምን አልያዝንም ብዙ ልንቆይበት

አሁኑኑ ቅረቡ ታዉጇል አዋጁ
የይለፍ ደብዳቤ ስንቅን አዘጋጁ
ይህ ዓለም ጠፊ ነዉ በሐብት አትመኩ
ብሏል አምላካችን ተስፋችሁን እንኩ

548. እግዚአብሔር መልካም ነው

እግዚአብሔር መልካም ነው
በመከራ ቀንም መሸሸጊያ ነው /፪/
ከገነት ሲሰደድ አዳም አባታችን
ሞት ነግሶብን ሳለ በእኛ በሁላችን
ቃል እንደገባለት ተወልዶ ሊያድነው
በመከራው ጊዜ መሸሸጊያ ሆነው /፪/
አብርሃም ከካራን ከእናት ከአባቱ ቤት
ከንአን ሲገባ ሲሰደድ በእምነት
ከተሰጠው ተስፋ አንዳች ሳይጎድልበት
እንደ ምድር አሸዋ ዘሩን አበዛለት /፪/
በሃዘን በችግር በመከራ ጊዜ
ጭንቄን የሚያርቅ ነው የነፍሴን ትካዜ
የቀደመው እባብ ሰላሜን ሲነሳኝ
እግዚአብሔር መልካም ነው ሐዘኔን
አስረሳኝ
ክርስቶስ ኢየሱስ ሐዘኔን አስረሳኝ

549. ማርያም ኃዘነ ልቡና

ማርያም ኃዘነ ልቡና ታቀልል /፪/

ኃዘነ ልቦና /፬/ ታቀልል /፪/

ማርያም የልብን ኃዘን ታቀላለች /፪/

የልብን ኃዘን /፬/ ታቀላለች

550. ነፍሴ ሆይ

ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን በቅን አገልግይ

የተቀበለዉ በቀራኒዮ

ያ ሁሉ መከራ በመስቀል ላይ

ለአንቺ ሲል ነዉና ነፍሴ ሆይ

ተዘጋጅተሽ ኑሪ ሁል ጊዜ
በነገ በዛሬ እንዳትታለይ /፪/ ነፍሴ ሆይ
በንሥሐ ጥምቀት ታጠቢና

ክቡር ደሙን ጠጪ ሥጋዉንም ብይ /፪/ ነፍሴ ሆይ

ዘላለም በደስታ እንድትኖሪ
ከዘላለም ቤትሽ መንግስተ ሰማይ /፪/ ነፍሴ ሆይ

551. ወዳንተ እሰግዳለዉ

ወዳንተ እሰጋዳለዉ ሳለዉ በሕይወቴ

ላንተም እገዛለዉ እስከለተ ሞቴ

አንተ ነህና መድኃኒቴ የዘለዓለም ቤቴ /፪/

ሳይመሽብን ቀኑ ሳይጨልም ድንገት
በፅድቅ ጎዳና ልጓዝ ወደ ፊት
ምራኝ መንገዱን አሳየኝ እንዳልሳሳት
የነፍስ የሥጋዬ የሕይወቴ ቤዛ

አትበለኝ ችላ በደሌ ቢበዛ

አንተን አምኜ እኖራለዉ ወዴት እሔዳለሁ /፪/

552. አንድ ጊዜ

አንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ሆኛለዉ /፪/

በፍቅሩ ተስቤ በደሙ ድኛለዉ

ዓለም ተይኝ ንቂ ትቼሻለዉ

ጥበበኛዉ ሰይጣን በመጣዉ ቢመጣ
ዳግም ተመልሼ ከእቅፍህ ላልወጣ
በመስቀሉ ግርጌ አርፌ እኖራለዉ
ዓለም ተይኝ የእግዚአብሔር ሆኛለዉ

ቢያሙኝ ቢያጥላሉኝ ቢሳለቁብኝ

ዉርደትን ተንኮልን ቢሸርቡብኝ

ለእኔ እንደዉ ደስታ ነዉ ሐዘንም የለኝ

ሰይጣን እፈር የክርስቶስ ነኝ

ጓደኞቼ ጠሉኝ ተለዉጬባቸዉ
የጥንቱን ፀባዬን ስለነፈኳቸዉ
ብቻዬን የሆንኩኝ ቢመስለኝም ለእኔ
ጌታ እንደሆነ አለልኝ ከጎኔ

553. መቼ ነዉ ጌታ

መቼ ነዉ ጌታ አረ መቼ ነዉ

መቼ ነዉ ጌታዬ እንደቃልህ የሚሆን ጉዞዬ /፪/

አልተማርኩም አልል አስተምረኸኛል /፪/
ቃልህን እንደ ወተት አጠጥተኸኛል /፪/
የታለ አኗኗሬ አንተን የሚመስለዉ /፪/

በልማድ ህይወት ነዉ የምመላለሰዉ /፪/

ይህ አንደበቴማ በቃልህ ሰልጥኗል /፪/
ልቦናዬ ካንተ ከፊትህ ኮብልሏል /፪/
አንተን እንደማዉቅህ አብዝቼ ባወራም /፪/

የተዘራዉ ሁሉ ፍሬ አላፈራም /፪/

እዘንልኝ እና መንገዴን አቅናልኝ /፪/
የአመፃ ስራዬን በደሌን ተዉልኝ /፪/

554. እስከ መቼ ነዉ

እስከ መቼ ነዉ የማልለወጠዉ

ባልተሰበረ ልብ የምመላለሰዉ

በሰጠኸኝ ፀጋ ድካሜ ተከድኖ
ዓለም ይከበኛል አልቆና አግኖ
ይህን ከንቱ ወጥመድ ጣለዉ ከኃላዬ
ትንሽ መሆኔን ይወቅ ሕሊናዬ /፪/

ፀሐይ ስትቀላ ክዋክብት ሲረግፉ

ለገናናዉ ክብርህ ወድቀዉ ሲሸነፉ

ለሁለት ሲከፈል ድንጋያማዉ አለት

የኔ ልብ መቼ ይሆን የሚሸነፍለት /፪/

ቃልህን ስሰማ ልቤን ይነካኛል
ጽድቅን አስባለዉ ሐዘን ይሰማኛል
ወዲያዉ ተመልሼ ሁሉን እረሳለዉ
ለዚህ ዓለም ስብከት ልቤን እከፍታለዉ /፪/

555. እያለፈ ነዉ ዘመኔ

እያለፈ ነዉ ዘመኔ ትዕዛዜን ሳልፈፅም ወየዉ ለኔ /፪/

በጠራኝ ጊዜ ምን እላለዉ ና ብሎ ወደ እኔ /፪/

የጠራኝ ጊዜ ምን እላለዉ ነይ ብሎ ወደ እኔ /፪/

በወጣትነቴ ሳልሰራ እያየዉ አለፈኝ ብዙ አዝመራ /፪/

ከእንግዲህ በመስራት ጌታ ሆይ ልኑር ካንተ ጋራ /፪/

የማስብበት በየእለቱ ንፅህ ልብን ስጠኝ አቤቱ /፪/

ከትዕዛዝህ ዉጪ በመሆን እንዳልቀር በከንቱ /፪/

እንደየስራዉ ለመስጠት በግርማ መንግስቱ ሲመጣ /፪/

ማን ይሆን የሚቆም ከፊቱ ፈተናን የወጣ /፪/

እንዳይስታችሁ ተጠንቀቁ እየተማራችሁ ከቃሉ /፪/

ይመጣሉና በእሱ ስም አምላክ ነን የሚሉ /፪/

ትዕግስትን በመያዝ ሁላችሁ እስከመጨረሻዉ ጠንክሩ /፪/

ያን ጊዜ ይሆናል በእርሱ ዘንድ የማዳን ተግባሩ /፪/

556. ድንግል ሆይ ስላንቺ

ድንግል ሆይ ስላንቺ ነውና መሐሪ

አማልጂኝ ከአንዱ ልጅሽ ከፈጣሪ

ስሙን እንዳልጠራ አንደበትም የለኝ

ፊቱንም እንዳላይ ሥራዬ አሳፈረኝ

ታውቆኛል ጥፋቴ ብዙ እንደበደልኩኝ

ትዕዛዙን እንደሻርኩ ሕጉን እንደጣስኩኝ

አንተ ክቡር መልአክ ልደቱን አብሳሪ

አማልደኝ ከጌታዬ ከፈጣሪ

በፊቱ እንዳላፍር የተጠራሁ ለታ

እለምነዋለሁ ከአሁኑ ይቅርታ

ጻድቃን ስማዕታት እናንተ ሁላችሁ

አማልዱን ከአምላኬ ከአምላካችሁ

557. አታዉኪኝ ነፍሴ

አታዉኪኝ ነፍሴ አታስጨንቂኝ /፪/

በዓለም መድኃኒት በእግዚአብሔር ታመኚ /፪/

ዋልያ እንደሚናፍቅ ወደ ዉኃ ምንጮች /፪/
ጌታዬን ለማየት ነፍሴ ናፈቀች /፪/
የሕይወትን ዉኃ እያስታወሰች /፪/

ወደ ህያዉ አምላክ ነፍሴ ተጠማች /፪/

መቼ ተነስቼ መቼ እደርሳለዉ /፪/
የጌታዬ ፊቱን መቼ አየዋለዉ /፪/
የአምላኬን ዉኃ እያስታወሰች /፪/

የሕይወትን ዉኃ እያስታወሰች /፪/

ወደ ህያዉ አምላክ ነፍሴ ተጠማች /፪/

558. ነብዩ ዳንኤል

(የአብርሃም አምላክ በሚለዉ ዜማ)

ነብዩ ዳንኤል በጾም ስላመነ /፪/

ከአንበሶች ጉድጓድ ሕይወቱን አዳነ /፪/

ኤልያስ የወጣዉ በእሳት ሰረገላ /፪/

በፆም በፀሎት ነዉ አይደለም በሌላ /፪/

የነፍስንም ቁስል ጾም ታድናለች /፪/

የሥጋን ፍላጎት እያዳከመች /፪/

እስቲ ልብ እናድርግ እናስተዉ ደግሞ /፪/

ጌታ ለሐዋርያት ያላቸዉን ቀድሞ /፪/

ይህ እርኩስ መንፈስ ሊወጣ የሚችል /፪/

በጾም በፀሎት ነዉ እንደ ወንጌሉ ቃል /፪/

559. የነፍሳችን ቤዛ

(አማን በአማን በሚለዉ ዜማ)

የነፋሳችን ቤዛ የቅዱሳን ሐብት /፪/

ፀጋን የሚያሰጠን ፃም ነዉ መድኃኒት /፪/

የእስራኤል ልጆች በሙሴ ሲመሩ /፪/

በጾም በፀሎት ነዉ ባሕር የተሸገሩ /፪/

የቅዱሳን አባቶች ጾም ነዉ ጋሻቸዉ /፪/

ወደ ሕይወት መንገድ የሚመራቸዉ /፪/

ክፍላችን እንዲሆን ከቅዱሳን ጋራ /፪/

ፍቅር ቤታችንን በፀሎት እንስራ /፪/

ልባችንም ይሁን የፀሎት ጎዳና /፪/

የእግዚአብሔር መንግስት እንድንወርስ በጤና /፪/

560. የእመቤታችን አማላጅነቷን

የእመቤታችን አማላጅነቷን ክብሯን

የቀነሰ ያዋረደ

እዳ አለብን /፪/ ከፈጣሪያችን /፪/

የተሰጣት ሙሉ ሥልጣን
ክብር ያገኘች በቃልኪዳን
ስሟን የጠራ እንደሚድን
በመፅሐፍ ሲነገር
እዳ አለብን /፪/ ከፈጣያችን /፪/

ቤዛዊተ ኩሉ የተባለች

በነ ቅዱስ ኤፍም የተመሰገነች

በነ አባ ጊዮርጊስ ምሥጋናን ያገኘች

በመናፍቃን ዘንድ ምንዉ ተዘነጋች

እዳ አለብን /፪/ ከፈጣያችን /፪/

ከሴቶቹ ሁሉ ልዩ ናት እያልን
በሁለቱም ወገን በፍፁም ድንግል
የብርሃን እናቴ ማርያም ስትባል
በደካሞች ዘንድ ምነዉ ተዘነጋች
እዳ አለብን /፪/ ከፈጣያችን /፪/

ቃና ዘገሊላ ከልጇ ጋር ሳለች

ከሰርጉ ቤት ገብታ ድንግል አማልዳለች

እንኳንስ እምአምላክ ቤዛዊተ ኩሉ

ፃድቃን ሰማዕታት በእዉነት ያማልዳሉ

እዳ አለብን /፪/ ከፈጣያችን /፪/

561. ኃጢያቴ በዛ

ኃጢያቴ በዛ እመቤቴ

ምህረት ላኪልኝ ለሕይወቴ /፪/

ከሲኦል አዉጪኝ አዛኚት
የፃድቃን እናት እመቤት
ሰላማዊት ናት ሀገረ እግዚአብሔር

በአንቺ ነዉ መወጣት ከኃጢያት ቀንበር /፪/

የሚሰግዱልሽ ፃድቃን ሰማዕታት
የሚላኩልሽ ቅዱሳን መላእክት
ከእነሱ ጋር ነይ እመቤቴ
እንዲታረቀኝ ለማያዊ አባቴ /፪/

አስታርቂኝ እኔን ከልጅሽ
እማልዳለዉ ከፊትሽ
ስምሽን ጠርቶ ያፈረ ማነዉ
የአዳም ተስፋ ስራሽ ድንቅ ነዉ /፪/

የፍቅር እናት እመቤታችን
አስታርቂን እኛን ከጌታችን
ዘወትር ነይልን እናቴ ማርያም
ላንቺ ቅርብ ነዉ መድኃኒዓለም

562. ነፍሴ ሆይ

ነፍሴ ሆይ /፪/ እግዚአብሔርን በቅን አገልግይ /፪/

ምሥጋናዉንም ሁሉ አትርሺ

እግዚአብሔን በቅን አገልግይ

በምህረቱና በቸርነቱ የሚጠብቅሽ የሚከልልሽ

ምኞትሽን በበረከቱ የሚያጠግባት

ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔን በቅን አገልግይ

ኃጢያትሽን ሁሉ ይቅር የሚልሽ ደዌሽንም ሁሉ የሚፈዉስ

ሕይወትሽን ከጥፋት የሚያድናት

ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን በቅን አገልግይ

ምሥጋናዉንም ሁሉ አትርሺ

እግዚአብሔርን በቅን አገልግይ

ሕይወትሽን ከጥፍት የሚያድናት

ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን በቅን አገልግይ

563. እንደተቆጣኝ አልቀረም

እንደተቆጣኝ አልቀረም በርህራሄዉ ማረኝ

ቁጣዉን መልሶ ለነፍሴ ለልቤ መፅናኛ ስጠኝ

ምን ልክፈለዉ ለአምላክ ለወደደኝ

ልስገድለት ላመስግነዉ ኃይል ስጠኝ /፪/

ዳገት ቁልቁለት በዛብኝ ለፅድቅ ወዳንተ ስጓዝ
ጠላት ተጠምጥሞ ካንገቴ ጎንጎኔን ነደፈኝ በመርዝ
መፍትሄዉ ጠፋብኝ ሰቃይ በዛብኝ
አምላኬ ሆይ በጥበብህ አላቀኝ

ብቸኛ ነኝ ጭንቅ የያዘኝ የጠበበኝ

የዓለም ንፋስ ማዕበሉ ያንገላታኝ

መላም የለኝ እኔ ተክዣ ቆሜያለዉ

ኃይሌ ጉልበቴ መድኃኒቴ በለኝ አለሁ /፪/

ቆሜ ሳየዉ ፊት ኃላዬን ቀኝ ግራዬን
እረዳት የለኝ ምርኩዝ የለኝ ነኝ ብቻዬን
የዉስጥ የዉጪዉን ዘርዘሬ ብነግረዉ
እንደ ነፍሴ የምቆጥረዉ የማዋየዉ /፪/

አይተህ ይህን መጨነቄን መገፋቴን

ላክልኝ ለእኔ ድንግልን እመቤቴን

ቅዱሳን ሰማዕታት ፃድቃን መላእክትን

ፍጥረትህ ነኝ እንዳልጠፋ አትጨክን /፪/

የነበርክ ያለክ ለዘለዓለም የምትኖር
ከስራዬ ባሳዝንህ ዘወትር
ያለእረዳት አፅናኝ ብቻዬን ያልተዉከኝ
ተስፋ አልቆርጥም ላመስግንህ ፍቀድልኝ /፪/

564. ስለኔ የሞተዉ

ቤዛ የሆነልኝ ስለኔ የሞተዉ

በፍቅሩ ማረከኝ ጠራኝ በይቅርታዉ

ሰዎች ሲጠየፉኝ ሲወግሩኝ ሲያስቡ

እሱ ተቀበለኝ በሚራራ ልቡ

ቀረብኩኝ ወደ እርሱ ሸክሜን ተሸክሜ
ጭነቴ ተራግፎ እንዲቀየር ስሜ
ከእግሩ ስር ተደፋዉ አምኜ በደሌን
በእንባዬ አጠብኩት ንፁህ ቅዱሱን
ኃጢያተኛ ሳለዉ እርሱ ግን ወደደኝ

ሰዉ ቢፈርድብኝ አምላኬ ነፃ አወጣኝ

እንደ ሰዉ ፍርድማ ተወግሬ ነበር

እርሱ ግን ታደገኝ አነፃኝ በፍቅር

ሽቱዉን ቀባሁት ሰጠሁት መባዬን
እርሱም ተቀበለኝ ለወጠዉ ታሪኬን
የኃጢያት ኑሮ ጨለማ ሕይወቴን
ብርሃን ሆነልኝ ቃሉን በመስማቴ
እንደ ሰዉ አይደለም ጥፋቴን አይወድም

ይምረኛል እንጂ በሰዉ ላይ አይፈርድም

እኔን ከፍ ያደረከኝ ከወዳቂነቴ

ምሥጋና ይድረስህ የሰማዩ አባቴ

565. የጌታዬ እናት ፀለየች

የጌታዬ እናት ፀለየች

ማርያምም እንዲህ እያለች /፪/

ነፍሴ ጌታዬን ታከብረዋለች
መንፈሴም በአምላኬ ሐሴት ታደርጋለች
<u>የእኔን የባሪያይቱን ትህትና</u>
<u>የእስራኤል አምላክ ተመልክቷልና</u> /፪/

ትዉልድ ሁሉ ብፅህት ይሉኛል

እርሱ ታላቅ ስራን አድርጉልኛል

<u>ስሙም ቅዱስ ነዉ ምህረቱም</u>

<u>ለትዉልደ ትዉልድ ዘለዓለም</u> /፪/

ኃይል አድርጓል ጌታ በክንድ
ትዕቢኞች ተዋረዱ
<u>ገዢዎች ከዙፋን ስለተጣሉ</u>
<u>ትሁታን ዳግሞ ከፍ ከፍ አሉ</u> /፪/

ባለጠጎች ሲጠሙ ሲራቡ

ድሆች በምህረትህ ጥቂት ጠገቡ

<u>ለአባቶቻችን እንደማለ</u>

<u>ምህረቱን አስቦ እኛን ተቀበለ</u> /፪/

566. እግዚአብሔር አለኝታችን

እግዚአብሔር አለኝታችን ግሩም ነዉ

እግዚአብሔር ግሩም ነዉ ኃያል ነዉ

ለጠላት ክንዱ ብርቱ ኃያል ነዉ

ሕዝቡን ሲመግብ እጁ ሰፊ ነዉ
የማያልቅበት ቸር እረኛ ነዉ
ሰማይና ምድርን የፈጠረ

ክዋክብትን በሕዋ ያኖረ

በቃሉ ብቻ ምድርን ያፀና

ማን ያክለዋል እሱን በዝና

በሞት ጥላ ዉስጥ አምላክ ታደገን
በሐዘን ጊዜ ጌታ ጎበኘን
ፍቅሩ ኃያል ነዉ ሩህሩህ ጌታ
ምን ወሰን አለዉ ለአንተ ዉለታ

567. ከዳዊት አብራክ

ከዳዊት አብራክ ዘር ባያስቀርልን ኑሮ

አዳም በሲያል በቀረ በዉርደት አንገቱን ቀብሮ

ዝምታ በወረረን በወደቅን ማቅ ለብሰን

ቸርነቱ በዝቶ ግን እመቤታችንን ሰጠን

ፀሐይ ክርስቶስ ወጣ ከቤተልሔም ሀገር
የእንጆራ ቤት ነች እና የእኛ የፍቅር ባሕር
ተበልቶ አይጠገብም የማጎፀንሽ ፍሬ
ሕይወት ሆኖን በላነዉ የማጎፀንሽን ፍሬ
ግርማዋ የሚያስፈራ የሙሴ ቤተመቅደስ
ተገኙብሽ በሰላም ሰዉና ሥሉስ ቅዱስ
የወርቅ መንበር ነሽና ደመና የከበበሽ
የሥላሴ ሙሽራ <u>ዕፁብ</u> /፪/ ድንቅ ነሽ

568. ስሜ ተለዉጦ

ስሜ ተለዉጦ ዘማዊ ብባልም

ራራልኝ ጌታ ነዉሬን አልቆጠረም

ፈሪሳዊያኑ አካልበዉ ቢወስዱኝ

ኢየሱስ ግን በፍቅር ፊት አየኝ በርህራሄ አየኝ

የተደበደበዉ አካሌን ስላየ
ስለእኔ መዋረድ አምላክ ተሰቃየ
አወጣኝ ከድንጋይ ከቀያፋ በትር
ለእኔ ያደገዉን <u>ኸረ እንዴት ልዘርዝር</u> /፬/

ከዘማዊት ሴት ጋር አወራ ተብሎ

መስቀል አደረገ ስሜን ተቀብሎ

ቀራጭና ዘማዊ ያድናል ይባላል

ትከሻዉ ሰፊ ነዉ እኛን ተሸክሚል /፬/

በኃጢአት ስወድቅ በሕይወት ዘመኔ
ቸርነቱ በዝቷል በረከቱ ለእኔ
መሐሪ መሆኑን ጌታ ሲገልፅላት
በልዩ ቸርነት ዘማዊቷን ጠራት /፬/

ነዉር ያለባችሁ ተሰብሰቡ በእርሱ

ከዉርደት ያድናል መሐሪ ነዉ እርሱ

ለበሽተኞች ነዉ የመጣሁት ብሏል

ነፍስና ቁስልህን ደዌህን ያድናል /፬/

569. ማን ነዉ እርሱ

ማን ነዉ እርሱ ማን ነዉ እርሱ /፪/

ምድርን የሰራ በኃያል ቃሉ ማን ነዉ እርሱ
ሕይወት የሰጠ ለፍጥረት ሁሉ ››
የባሕርን ሞገድ የሚገስጸዉ ››
የኃይላት ጌታ ጌታችን ማን ነዉ ››

ከጥልቀት በታች ከምጥቀት በላይ ማን ነዉ እርሱ
ማነዉ ጌታችን ሁሉንም የሚያይ ››
ማን ነዉ እርሱ ማን ነዉ እርሱ ››
ከፈሳሾች ዉስጥ ወንዙን የሚያፈስ ማን ነዉ እርሱ

ምድርን ልምላሜ ፍጹም የሚያለብስ ››
ጥቃቅን ነፍሳትን የሚመግበዉ ››
የሚመሰገን ጌታችን ማን ነዉ ››

የሰማይ መብረቅ የሚያንጎዳጉድ ማን ነዉ እርሱ
በፍትህ በእዉነት ለጽድቅ የሚፈርድ ››
አምሳያ ለእርሱ የሌለዉ ጌታ ››
እግዚአብሔር ስሙ የሁሉ አለኝታ ››

ስብራትህን የሚጠግነዉ ማን ነዉ እርሱ
ትንሽነትህን የማይጸየፍ ››
አድሎን የማያዉቅ ለሰዎች ፊት ››
ለሁሉ የሚሰጥ የጽድቅ ሕይወት ››

እዉነትና ምህረት የከበቡት ማን ነዉ እርሱ
ለሕዝብ የሚሰጥ ልዩ ሕይወትን ››
የሚፈሩትን የሚያከብራቸዉ ››
የአማልክት አምላክ ስሙ ቅዱስ ነዉ ››

570. ስምኽ ማርያም

የተወደደ ስምኽ ማርያም
እንዳንቺ ንፁሕ በዓለም የለም
አሳስቢልን እንዲምረን መድኃኒዓለም

በንፅሕናሽ በመመረጥሽ
ድንግል በእዉነት እፁብ ደንቅ ነሽ
አሳስቢልን እንዲምረን መድኃኒዓለም

ፍጥረታት አንቺ ይማፀኑሻል

ከሲያል ዓለም አዉጪን ይሉሻል

አሳስቢልን እንዲምረን መድኃኒዓለም

አስራትሽን ኢትዮጲያን
ጠቢቅልን ድንግል ሕዝቧን
አሳስቢልን እንዲምረን

571. ተስፋ አለኝ

ተስፋ አለኝ በአምላኬ

ተስፋ አለኝ በእግዚአብሔር

ምናምንቴ ሆኜ በዚህች ምድር ብኖር

ተስፋ አለኝ በእግዚአብሔር

ጥበብ የተሞሉ ታላላቅ ኃይለኞች
ሥልጣን የጨበጡ የምድር ብርቱዎች
ስላልተመረጡ በሐብታቸዉ ብዛት
ተስፋ አለኝ ለፅድቁ ለሰማያዊዉ ቤት /፪/

የአምላክ ዓይን ልዩ ነዉ አያዳላም ለሰዉ

ፍቅሩ ለፍጥረቱ ምንጊዜም እኩል ነዉ

ፀሐይን ለፍጥረት ያወጣል በእኩል

ፃድቅና ኃጥእ ክፉ ሰዉ ሳይል /፪/

በኃጢያት ብወድቅም ሕይወቴ ቢጎድፍ
በንሥሐ ዳንኩኝ እኔ ሳልቀሰፍ
አምላክ ቸርነቱ ምሕረቱ አድኖኝ
አዲሲቷን ምድር እናፍቃለሁኝ /፪/

ያለፈዉ በደሌ ተደምስሷልና

ወደፊት ለፍቅሩ ለፅድቅ ሥራ ልቅና

በዓለም ከሚኖሩ ባለተስፋ ሁነዉ ሰላም ያገኛሉ

ክርስቶስን መርጠዉ /፪/

572. አልፈርድም እኔ

አልፈርድም እኔ በማንም በደል በማንም ኃጢያት

በፈረድኩበት እንዳልመዘን ጌታ ሲመጣ በኃይለ ሥልጣን

በቸርነቱ አምላክ ባይተወን በደሌን ሁሉ

ዉስጤ ቢፈተሽ በተሰጠኝ ሕግ በቅዱስ ቃሉ
በምን ምግባሬ በሰዉ ፈርዳለሁ ዓይኔን አቅንቼ
በደል በዝቶ ለራሴ ሳላዉቅ በኃጢያት ሞቼ

ይልቅ የአንዱን ሽክም ሌላዉ አዝሎ መጓዝ ይሻላል
መፍረድ ከመጣ አንድም ሰዉ አይድን ሁሉም በድሏል
ወንድም ወንድሙን እየከሰሰ ለፍርድ አቁሞ
አሕዛብ ያያል በንትርኩ እጅግ ተገርሞ

ክርስቲያን ሆኖ ከወንድሙ ጋር እየተጣላ
ዓለም ዳኛችን በፀብ ፍርድ ቤት ታረቁ ብላ
ክርስቲያን ሆነን በአሕዛብ መሃል እየተካሰስን
አምላክ አዘነ የመስቀልን ዓርማ ትተን

መቼ ከሰሰ የከሰሱትን የገረፉትን
አይተናል እንጂ ለጠላቶቹ ምህረት ሲለምን
ለፅድቅ ሥራ ለእዉነት ብለን መጥተናል እንጂ
ማን ነዉ የሾመን በወንድሞች ላይ አርጎ ፈራጅ

መቼ ከሰሰ የከሰሱትን የገረፉትን
አይናል እንጂ ለጠላቶቹ ምህረት ሲለምን
በፅድቅ ሥራ ለእዉነት ብለን መጥተናል እንጂ
ማነዉ የሾመን በወንድሞች ላይ አድርጎ ፈራጅ

573. አምላካችን ቅዱስ ነህ

አምላካችን ቅዱስ ነህ

ፈጣሪያችን ቡሩክ ነህ

የዘለዓለም አምላክ ነህ /፪/

የአዳም ልጅ ከትቢያ /፪/ ወደ ነበረበት
ለምለም ከአፈር እንዲሆን ከመሬት
በተናገርከዉ ቃል ባዘዝከዉ መሠረት
እንደ ጎርፍ መጥተህ ትወስዳለህ ድንገት
ከሕልም የረዘመ /፪/ ሕይወት የለንም

ማለዳ እንደሚበቅል እንደ ጠዋት አረም

ጠዉልጎ እንደሚቀር እንደ ጠዋት አረም

ሕይወትህ ናትና እንደ ጠዋት ጤዛ
ረግፎ የሚቀር ዉበትና ለዛ
እባክህ የሰዉ ልጅ ኃጢያት አታብዛ
ዕድሜያችን ሰባ ዓመት ቢበዛ ሰማንያ

በመከራ ያልቃል እርሱም በዓለም ዙሪያ

እኛም እናልፋለን በጭራሽ ሳንሰራ

በራስ ተሸክመን የኃጢያት አዝመራ

የመከራ ዓመታት አሳልፈናል
ፍርድህን በመፍራት ተሸብረናል

እባክህ ጌታ ሆይ በቸርነትህ ሥራ
ለአገልጋዮችህ አምላክ ሆይ ራራ

574. አምላኬ ሆይ

አምላኬ ሆይ ያን ጊዜ እንድትራራ

አምላክ ሆይ አደራ ስለእኛ እንድራራ

ወደ አፈርነት ፈጥነህ ሳትመለስ
የሰዉ ልጅ ተዘጋጅ ንሥሐ ታጥበህ
ነዉና ዕድሜያችን እንደ አደይ አበባ
ነገ ሳይሆን ዛሬ ንስሐ እንግባ

ሰዉ በአፉ ቢያምን በልቦናዉ ክዶ

ምንም ጥቅም የለዉ ያለ ተዋህዶ

ፈራሹ ሥጋዬ ለማትፈርሰዉ ነፍሴ

እባክህን ተገዛ ለቅድስት ሥላሴ

ምንም ብበድል ቢበዛ ኃጢአቴ
አቤቱ አትቅሰፈኝ በወጣትነቴ
ለፍርድ ስትመጣ በእለተ ምጽዓት
ምን እመልስ ይሆን አምላክ አንተ ፊት

575. አንጻኝ

አንጻኝ እጠበኝ ከኃጢያቴ /፪/

አንተ ነህና መድኃኒቴ

አንተ ነህና ረዳቴ አንጻኝ እጠበኝ ከኃጢያቴ /፪/

ላንተ ይገዛ ሰዉነቴ
ይቅር ከእንግዲህ መዋተቴ
ፊትህን መልስ ራራልኝ
ልኑር ካንተ ጋራ እዘንልኝ /፪/

እንዳልመለስ ወደኃላ

የኃጢያትን ፍሬ እንዳልበላ

ጠብቀኝ እንጂ በኃይልህ

እንዳልወድቅብህ ልጅህ

ኃጢያቴን አጥበህ አሳርፈኝ
አምላኬ አንተ ነህ ሌላም የለኝ
እኔነቴን ሳስብ አሳዘነኝ
ልኑር ከአንተ ጋር እዘንልኝ

576. ተይ ተመከሪ

ተይ ተመከሪ ነፍሴ ሆይ ተይ ተመከሪ /2/

በዓለም መድኃኒት ነፍሴ ሆይ

በእግዚአብሔር ታመኚ

ለሥጋ መገዛት ነፍሴ ሆይ
ምንዉ ቢቀርብሽ ››
ዉርደት ነዉ ፍጻሜዉ ››
ዉርደት ነዉ ፍጻሜዉ ››
የሚያከናንብሽ ››
መልካም የሆነዉን ››
ጻድቁን ተከተይ ››
ክርስቶስን መስለሽ ››
ቸርነትን ሥሪ /፪/

ሞትን ማን ይመርጣል ነፍሴ ሆይ

ሕይወትን በመጥላት ››

ከእንግዲህ መራቅ ነዉ ››

ከስርቆት ከዝሙት ››

ጸጋ እንዲበዛልሽ ››

የቃሉ በረከት ››

ከቤቱ አትጥፊ ››

ፍቅር ከሞላበት /፪/

ለአንቺ ነበር ጌታ ነፍሴ ሆይ
ደሙን ያፈሰሰዉ ››
ተሰቅሎ ሞቶ ነዉ ››
ፍቅሩን የተገለፀዉ ››
በፍቅሩ ላሰበኝ ››
ዘወትር ጠዋት ማታ /፪/

ብወድቅ ምርኩዝ ድጋፍ ነፍሴ ሆይ

ጋሻ ይሆነኛል ››

በፍቅሩ ያየኛል ››

ማን እንደ እርሱ አለ ››

የሕይወቴ ቤዛ /፪/

577. ነይ ነይ

ነይ ነይ እመቤቴ ነይ ነይ

ነይ ነይ ድንግል ማርያም ነይ ነይ

ነይ ነይ የእኛ አማላጅ ነይ ነይ

ነይ ነይ የእኛ ተስፍ ነይልኝ

ከአንቺ በስተቀር ማንም የለኝ

ድንግል ማርያም ሆይ ድረሽልኝ /፪/

በዚያች በጠባብ በር ነይ ነይ
ማንስ ይወስደኛል ››
ይህ ደካማ ሥጋ ››
ሰፊዉን ይለኛል ››
በሰፊዉም ሄጂ ››
አሁን ወድቄያለዉ ››

እመ አምላክ ከዚህ አዉጪኝ ነይ ነይ

ተማፅኜሻለሁ ››

ምሪኝ ተከተይኝ ››

አላዉቅም መንገዱን ››

ወደ ሕይወት ጎዳና ››

የሚያሻግረዉን ››

ኃጢያትና በደል ነይ ነይ
በላዬ ላይ ሰፍሮ ››
ጽድቅን እንዳልሰራ ››
ይዞኛል ቀስፎ ››
ዓለማዊ ነገር ››
የጠቀመኝ መስሎኝ ››
በዲያቢሎስ ታንቄ ቀረሁ ››
ከዲያቢሎስ ገመድ ››
ኸረ አንቺዉ አዉጪኝ ››
አዛኚት ነሽና ››
አትጨክኚበት ››

የዳዊት መሰንቆ ነይ ነይ

የኤልያስ መና ››

እናቴ ልበልሽ ››

አዛኚት ነሽና ››

አንቺንም ተማፅኖ ››

ያጣ የለምና ››

አንቺዉ አርቂልኝ ››

ያን ሰይጣን መሰሪ ››

ከእኔ ሳትለይ ››

ከእኛዉ ጋር ኑሪ ››

578. ስምሽ ጣዕም አለዉ

ስምሽ ጣዕም አለዉ ኪዳነ-ምህረት /፪/

በላኤ ሰብም ይህን አሰበ

ከጥርኝ ዉኃ አንጠባጠበ

ልቤ በልጅሽ ላይ ሲያምፅ
በጭካኔ
ይህን ዓለም አይቶ ሲንከራተት እኔ
በልቤ ፅላት ተሳይቢኝ
ጣዕምሽ ከዓለም እንዲለየኝ /፪/
ጠላት ሲፈትነኝ ሊጥለኝ በስጋ
በክፉ ምኞቴ ነፍሴ ስትወጋ
እንዳባቶቼ ልጥራሽ እኔ
ማን አለኝና በዚህ ዓለም
በስምሽ ተማፅኖ ነፍሳት ተምረዋል

ከቅዱሳን ዓለም ምጎረት አጊንተዋል

ወደብ ነሽ አንቺ ማረፊያ ቦታ

እየወደድኩሽ ልኑር በደስታ

579. እመቤቴ ስልሽ

እመቤቴ ስልሽ ፊትሽ ተንበርክኬ /፪/

አማልጂኝ ከልጅሽ ከቸሩ አምላኬ

ሳልቅስ ስተክዝ ስወድቅ ከደጅሽ /፪/
አይዞህ አለዉ በይኝ ድንግል ስለምንሽ

ሲጨንቀኝ ሲጠበኝ ሲርድ ሰዉነቴ

ባዶነት ሲሰማኝ ጠፍቶኝ እኔነቴ

ድረሺልኝ ድንግል መፅናኛ እናቴ

የዓለም ስደተኛ ሆኜ ቀርቻለዉ

የዓለም መጻተኛ ሆኜ ቀርቻለዉ

ድንግል በስደትሽ አማልጂኝ እላለዉ

ዓለም ዘርግቶ ጥላዉን በእኔ ላይ
እቻልኩም እና ይሄን ሁሉ ስቃይ
ሰላማዊት እናት ድንግል ሆይ
ሰላምን ህይወትን ከሚሰጠዉ አምላክ
ፍቅርን ቸርነትን ከሚያድለዉ አምላክ

ባንቺ አማላጅነት ሕይወቴ ትባረክ

580. መልእክተ ወንጌልን

መልእክተ ወንጌልን በደሙ የጻፈ

ስቃይን ታግሶ ችሎ ያሳለፈ

በርሃብ በግርፋት በግዞት አብዝቶ

በገድል በትሩፋት ጠላትን ድል ነስቶ

ንዋየ ጎሩይ ነዉ ለዓለም ያበራ
ሐዋርያዉ ጳዉሎስ ለፅድቅ የተጠራህ
እንቅልፍን እያጣህ ቀን ከሌት ሳይታክት

የኃላዉን ትቶ ተጓዘ ወደፊት

በድካም ተጠምዶ በገድል እያረሰ

ከደማስቆ እስከ ሮም ቃልን አዳረሰ

እዉነትን መናገር ከቶ ያላፈረ
ህዝብን ከአህዛብ በአንድ ያስተባበረ
አምላክ እንዳይናቅ ከልቡ የተጋ
ጸንቶ የተጓዘ ለምትበልጠዉ ፀጋ
በሮም አደባባይ ሰማዕት የሆነ

የተዋህዶ አርበኛ ለአምላክ የታመነ

በጣዕመ ስብከቱ ዓለሙን አጣፍጦ

አክሊል ተቀዳጀ ሳይታክት እሮጦ

581. በአምሳሉ ፈጥሮናልና

በአምሳሉ ፈጥሮናልና እናመሰግነዉ

በአርያዉ ፈጥሮናልና ሁሉ በእጁ ነዉ

ከእኛ የሚፈለገዉ ማመን
ከእኛ የሚጠበቀዉ መታመን
አፍም ይፁም ከማዉራ ይከልከል
ጆሮም ይፁም ከመስማት ይከልከል
ዓይን ይከልከል ከማየት ይቆጠብ
ልሳን ይፁም ከመናገር በአርምሞ

እጅ እግር ይፁም ከመዳፈር በተደመመዉ

መምጫዉ ደርሷል ቀርቧል ቀኑ
ቀርቧል ቀኑ እንመላለስ በብርሃኑ

582. ጊዜዬ እስኪደርስ

ጊዜዬ እስኪደርስ ወዳንተ መምጫዬ

ለንስሐ አብቃኝ አቤቱ ጌታዬ አቤቱ ጌታዬ

ብርሃኔ መድኃኒቴ ተስፋህ ይመልሰኝ
ጥፋቴን ደምስሰህ ይቅርታ አድርግልኝ
ተስፋዬ እረዳቴ አንተ አትጣለኝ
አምላኬ አታጥፋኝ ከሲኦል አድንኝ
መሐሪ ይቅር ባይ ምህረትህ ይጎብኘኝ

ከሐጢያት ፍላፃ ፀጋህ ይታደገኝ

አዳኜ መድኃኒቴ ሰላምን ላክልኝ

የድኅነት ደጆችህን በፍቅር ክፈትልኝ

አቤቱ ምኅረትህ በእኔ ላይ ይሁን
ተጨነኩ ጌታዬ ስጠኝ ሰላምን
ከክፉ እንድሸሽ አድነኝ እኔን
በጎ እንድሰራ ምራኝ መንገዱን
ሕይወት ሞት ድኅነት መኖራቸዉን ባምንም

ሐጢያት ዉድቀት ጥፋት አያዘናጋኝም

ስርየት እንደማገኝ ተስፋ ቢኖረኝም

ትምክሕቴ አንተ ነህ በሌላ አልመካም

የበደሌ ብዛት የሚያስከፋህ ቢሆን

በሥጋህ በደመምህ እጠብ ኃጢያቴን

ወዳንተ እመጣለዉ አደራ ነፍሴን

በሰማያዊ ቤት አኑር ሕይወቴን

583. ጌታ ያለዉ

ጌታ ያለዉ ሁሉም አለዉ

የዘላዓለም ሕይወት ባለቤት ነዉ

እመኑ በጌታ ይህ ብቻ ይበቃል

የቀረዉን እርሱ በፍቅር ይሰጣል

ሰላም ላጡ ሰላም ፍቅር ላጡ ፍቅርን
ለታረዙ ልብስን ለተራቡ እንጀራ
ለተጠሙ ዉኃን ለታመሙት ፈዉስን
ተስፋ ላጡ ተስፋን ለደካሞች ኃይልን

584. ከእምነት አደባባይ

ከእምነት አደባባይ አሻግሬ አይቼሽ

እስካነጋግርሽ በዉኔ አጊንቼሽ

አነጋግሪኝ ማርያም ጆሮዬ እንዲነቃ

ኃጥያቴን እጠቢዉ አድርጊዉ ጥሩ እቃ

ኦ ድንግል ሆይ እጅግ ግሩም ነሽ
የልቤ እንዲደርስ እንዴት ልበልሽ
ኪሩቤል ሱራፌል አዕላፍ መላእክት

ክብርት ናት አሉ የጌታ እናት

መላእክ የሚያዕናናሽ በቀኝም በግራ

የሲና ሐመልማል የታቦር ተራራ

የልጅሽ ትህትና የአንቺ ደግነት
የክርስቲያን ምርኩዝ የሆንሽ እመቤት
እንዴት ላመስግንሽ የልቤ እንዲደርስ
የትኅትና እናት የፍቅር ዉቅያኖስ
መዓዛሽ ያማረ ግሩም ፅጌረዳ

እኔ አንቺን አምኜ ፍፁም አልጎዳ

ትኅትና ልጫማ ፍቅርን ልልበስ

በአንቺ አማላጅነት በመንፈስ ቅዱስ

አረ እንዴት ቢሆን ነዉ የሚስተካከለዉ
አይንሽን ባይኖቼ እመቤቴ የማየዉ
አንቺን የማይበት ምንም ዓይን የለኝ
እንቅልፍ ሲወስደኝ በህልሜ ጥሪኝ
ኃይልና ብርታቴ አንቺ ሁኚኝ

ከጠላት ስዋጋ ጋሻ ሆንሽልኝ

ማልቀስ አስተምሪኝ መሳቅ ይብቃኝ

የሲኦል እሳቱ እንዳያቃጥለኝ

ላስብሽ በአርምሞ ወደ ላይ መጥቄ /፪/
የምድሩን ሳሳድድ እዳልቀር ወድቄ /፪/

585. የአብ ቃል አክብሮሽ

የአብ ቃል አክብሮሽ እናት ያደረገሽ

እግዚአብሔር በቃሉ ፍም ያከበረሽ

የምንመካብሽ መሰላል አንቺ ነሽ /፪/

ቅድስና ላንቺ ፅድቅም ላንቺ ሆኖ
ዓለምን የፈጠረ ባንቺ ተወስኖ
የገነት ፍሬ ነሽ ሕይወትን ያፈራሽ
አንቺን ለመረጠ አንቺን ላነፃሽ
ምሥጋና ይድረሰዉ ለቸሩ አምላክሽ /፪/

አዳም የኖረብሽ የኤዶም ገነት ነሽ

የኤፌሶን ወንዝ ወርቅ የሚያፈልቅብሽ

የጊዮን ማዕበል ኢትዮጲያን የከበብሽ

ዮርዳኖስን ሆንሽ አህዛብን ፈወስሽ

በልጁ ቃልነት አብም አከበረሽ /፪/

መአዛሽን ወዶ ወልድ ዋህድ ዋጀሽ
አብም በሰማያት በሕሊናዉ ፃፈሽ
መንፈስ ቅዱስ መጥቶ አንቺ አከበረሽ
እመካብሻለዉ እመቤቴ ስልሽ /፪/
ወልድ በወደደዉ ካንቺ መወለዱን

ንፅህት ሆኖ አጊንቶሽ ቅዱስ ሥጋሽን

ለቃሉ ማደሪያዉ ፅላትና ታቦት

በብሩህ ደመና ተመስለሽለት

ከስጋሽ ተከፍሎ ከደምሽም ደም ወስዶ

ከነፍስሽም ነፍስ ፍፁም ተዋህዶ /፬/

586. ማነዉ የሚያድነኝ

ለዚህ ለኃጢያት ህግ ከተሰጠ

ከህይወት መርገምን ከመረጠ

ለሞት ከተሰጠ ከንቱ ኑሮ

ማነዉ የሚያድነኝ ሞትን ሰብሮ

ሥጋ በሥጋ ሕግ ይስባል
መንፈስ በመንፈስ ሕግ ይዳኛል
ለየትኛዉ ጌታ ተገዝቼ
ጌታዩን እመርጣለዉ አንዱን ትቼ

ኃጢያት እሰራና ይጨንቀኛል
አምላኬ ሲለየኝ ይሰማኛል
ጌታ ሲለየኝ ይሰማኛል
አምላኬ ሲለየኝ ይሰማኛል

በኃጢያት በመኖር በዚህ ዓለም
የአምላክን ትዕዛዝ በማጣመም
በስርቆት በዝሙት በስካር
በዲያቢሎስ ፈቃድ ስኖር

የኃላ የኃላ ዉድቀት ነዉ

አምላክ በክንዶቹ ያልያዘዉ

የጨለማዉ ጉዞ ምን ይጥማል

ዓይን እያሳወረ ያዋርዳል

መላእክት በሰማይ ያለቅሳሉ
የእግዚአብሔር ቅዱሳን ያነባሉ
በኃጥያት ተማርከን ስንወሰድ
ሰይጣን ድል አጊንቶ ስንዋረድ

587. ቅያሜዉ ይቀርና

ቅያሜዉ ይቀርና አምላክ ሆይ ታረቀን

አንተ ስለራስን ሞት ነዉ የከበበን

እስከመቼ ድረስ ሕዝብህ ተጎሳቁሎ
በረከሰዉ መንፈስ ለእርኩሰት ተጥሎ
ምድር እያለቀሰች ደም እየሸተታት
እባክህ አምላኬ ኢትዮጲያን ታረቃት
እባክህ አምላኬ ሐገሬን ታረቃት

የዘመኑ ጣኦት ገንዘብ እያሳተን
ይህ ደካማ ሥጋ አምላክን አስተወን
ግብዝነት ሞልቶት ፈራሹ አካል
በነፍስ በሽታ ሕዝባችን ታሟል /፪/

ክንፋችን ተመቶ መብረር አቅቶናል
በመንፈስ በሽታ ሕዝባችን ታዉኳል
ምግባር የጎደለን ተራ ሰዉ ሆነናል
እባክህን አምላካችን በፍጥነት ታረቀን /፪/

ፀጋዉ ተለየን በአድነት የመላን
እርቅ የተነፈግን ሰላም የጎደለን
ሆነን ስለቀረን እግዚአብሔር ታረቀን
ፅድቅህን አድለን ፅድቅን ለተመኘን

588. የእኛ ጌታ

የእኛ ጌታ የእኛ መድኅን

በቸርንትህ ታደገን እኛ እንደሆንን ኃይል የለንም /፪/

ጠዋት ለምልማ ታማ ጠፋች
የሰዉ ጎሊና እያባባች
ዓለም ምኗ ነዉ የጣፈጠን
እያሳሳቀች የወሰደችን

ዛሬ አለች ቢሏት ትጠፋለች
ለተንኮሏ ዓለም ማነች
እሾክ በቅሎባት እሾህ ሆና
በመተላለፍ ሰዉ ሊያልቅ ነዋ

ከእኛ ጋር ያለዉ ኃይል ነዉ
በሥጋዊ ዓይን ባናየዉ
የጦሩ ብዛት መች ያድናል
የዓለም ጥንስስ ተዋህዷል

እንደ ሰዉ ጥበብ ጥበበኛ
እንደ ሰዉ ወደር ወደረኛ
እንደ ዓለም ጉልበት ጉልበተኛ
በዓለም ፊት ሲታይ ህመምተኛ

589. ለእኔስ ልዩ ነች

ለእኔስ ልዩ ነች ድንግል ማርያም

ለእኔስ ልዩ ነች እመብርሃን

<u>ፈልጌ</u> /፬/ ላንቺ ምሥጋና አላገኘሁም /፪/

ልቤ ሲያበቅል የኃጢያት አረም
ዉስጤ ሲሸፍት አልተወቺኝም
ከቤተመቅደስ እጇን ዘርግታ
ትጠራኛለች የእኔ መከታ

የሆዴ ሐዘን የልቤን ምሥጢር
እነግርሻለዉ አንድም ሳይቀር
የምትሸሸጊ የሕዝብን ኃጢያት
ለእኔስ ልዩ ነሽ ድንግል አዛኒት

ጣዕሙ ልዩ ነዉ ካንቺ ጋር መኖር
ድንግልን ይዜ መቼም አላፍር
ወደ ፅድቅ ሕይወት ትወስደኛለች
ድንግል ማርያም ለእኔ እናቴ እኮ ነች

በሐዘን ስሰበር ማንን እጠራለዉ

ዉስጤ ሲደማ ለማን እነግራለዉ

ከኃጢያት እድፍ ንፁህ መሆኛዬ

አንቺ ነሽ ለእኔ የእኔስ መፅናኛዬ

የኃጢያት ቁስል ያላንቺ አይጠግም
ልጅሽ ሳይፈቅድ በሕይወት አልኖርም
ከልጅሽ ሌላ መድኅን የለኝም
ከፀሎት በቀር ፍፁም አልድንም

590. እግዚአብሔር ሆይ እወድኃለሁኝ

እግዚአብሔር ሆይ እወድኃለዉ

ስለስምህ እቃጠለላለዉ

ፍቅርህ እኔን ይመስጠኛል

እንደ እግዚአብሔር ከየት ይገኛል

ዓለም ሁሉ በጠላኝ ጊዜ
ስንገላታ ይዞኝ ትካዜ
አንተ ከጎኔ አልተለየህም
እግዚአብሔር ሆይ ወደር የለህም

ሳኦል እኔን ሲያሳድደኝ
ጎሊያድም ሲዝትብኝ
ግርማ ሆነህ ከፌቴ የቆምክ
እግዚአብሔር ሆይ ስምህ ይባረክ /፪/

ሞቷል ብለዉ ቀብረዉኝ ሰዎች
ሚስኪን ሆኜ ሳይኖረኝ አንዳች
ከመቃብር ቆፍሮ አወጣኝ
አይዞህ ብሎኝ አምላኬ አፅናናኝ

አሳብህን በእግዚአብሔር ላይ ጣል
ለዘላለም ያበራልሀል
ታማኝ አባትህ እርሱ ነዉና
ሰላም በረከት የእርሱ ነዉና

591. የመስቀሉ ፍቅር

የመስቀሉ ፍቅር /ነገር/ ሲገባን /፬/

እመቤታችን እናያታለን

የመስቀሉ ፍቅር የገባቸዉ /፬/

እመቤታችን አለች ከጎናቸዉ

አባ ሕርያቆስ አባታችን
የመስቀሉ ፍቅር ሲገባዉ
ልቤ አፈለቀ አለ መልካም ነገር
ከእመቤታችን ጋር ሲነጋገር
ከድንግል ማርያም ጋር ሲነጋግር

ነይ ነይ እምዬ ማርያም
ነይ ነይ ቤዛዊት ዓለም
<u>አንድ ወልዳ ስሙን አበዛችዉ</u> /፪/
አንዱ ሀገር ስትሄድ መድኃኒዓለም አለችዉ
<u>አንድ ወልዳ ስሙን አበዛችዉ</u> /፪/
አንዱ ሃገር ስትሄድ ኢየሱስ አለችዉ
<u>አንድ ወልዳ ስሙን አበዛችዉ</u> /፪/
አንዱ ሃገር ስትሄድ ክርስቶስ አለችዉ
<u>አንድ ወልዳ ስሙን አበዛችዉ</u> /፪/

ለመናኒዉ ፀሎት ልዩ እጣን
የዋሻዉ ሻማ ነሽ እመብርሃን
መዓዛሽ ሸተተኝ ከግሸን /ከዒዮን/

ትናፍቂኛለሽ ምን ልሁን
ትርቢኛለሽ ምን ልሁን

ዳዊት በመዝሙሩ ያነሳሻል

የያእቆብ ድንኳን ነሽ ይልሻል

የእግዚአብሔር ሃገር የሚሉሽ

እመቤቴ ማርያም አንቺ ነሽ /፪/

ቤተልሔም ስሔድ አይሻለዉ
ቀራንዮም ስሄድ አይሻለዉ
ፍፁም አትለይም ከልጅሽ
የአንቺስ ልዩ ነዉ ፍቅርሽ /፪/
ነይ ነይ እምዬ ማርያም /፪/

592. ኑ ተመልከቱልኝ

ኑ ተመልከቱልኝ የአምላክን ቸርነት

አንደበት የለኝም ስራዉን ለማዉራት

ሰላምና ፍቅሩ በልቤ ተሞልቷል

በምን ቋንቋ ላዉራ ቃላቶች ያጥሩኛል /፪/

ሰማይ ጉም ቢመስል ቀላያት ቢናጉ
የጥፋት አጋንንት እጅጉን ቢተጉ
እኔን የሚጠብቅ ኃይሉን አይሰዉረርም
እረኛዬ ከእኔ ዘወትር አይርቅም

ፍርሃት ከእኔ ላይ ጨለማም ትወገድ
በጌታዬ ትምክህት እንደ ልቤ ልሂድ
የሞት አበጋዞች ተስፋችሁ ጨልሟል
እግዚአብሄር ሊያድነኝ አጠገቤ ቆሟል

ቅዱሳን በሙሉ ለእኔ ዘብ ቆመዋል
ወደ እርሱ ሕብረት ሊስቡኝ ጓጉተዋል
ዘወትር በመዓልት ድንግል ትመጣለች
በብርሃን እጆቿ ትባርከናለች

593. ኪዳነ-ምህረት

ኪዳነምህረት እናቴ አማልጂኝ እኔን ከልጅሽ

የፍቅር /የሰላም/ እናት ነሽና /፪/

የተገለጠዉ ብርሃን በምስራቅ የተወለደዉ
በፍቅር ሰንሰለት አስሮ ዓለም ሁሉ አዳነዉ
/፪/

በርሃዉን ባሰብኩኝ ጊዜ የግብፅን የአሸዋ ግለት

አንቺ ትንሽ ብላቴና አረ እንዴት ቻልሽዉ በእዉነት
/፪/

ዝም ብዬ ይደንቀኛል የአምላክን ስራ
ሳስበዉ
ምክንያት አንቺን አድርጉ ይህንን ዓለም
አዳነዉ /፪/

594. ከካራን ዉጡ

ከካራን ዉጡ ከነዓን ግቡ

ወደ ፅድቅ ሕይወት ዛሬ ቅረቡ

ካራን ጣኦት ነዉ የሚመለከዉ

የአሕዛብ ሀገር የሞት መንደር ነዉ /፪/

እንዳባታችን እንደ አብርሃም
ወገኖች ዉጡ ከካራን ዓለም
የግፍ እንጀራ ይብቃችሁ እና
ከካራን ዉጡ በአምላክ ጎዳና

የጣኦት ምስል የሚሸጥበት
ዓለም በዝሙት የሚነድበት
ከሰዶም መንደር ከካራን ዉጡ
የኃጢያት ሰንሰል ዛሬ ቁረጡ

የኃጢያት ዓለም ዛሬ ይብቃና
የፍቅር ሕይወት እንልበስና
ከካራን መንደር በፍጥነት ወጥተን
ከነዓን ገብተን ማደር አለብን

ማርና ወተት የሚፈልቅበት
ሰዎች በፍቅር የሚኖሩበት
ከሰማያዊት ኢየሩሳሌም
ዛሬ ብንገባ እናገኛለን የአምላክን ሰላም

595. የአርያም ንግስት

የሰማይ የምድር የአርያም ንግስት

አንቺ ነሽ እመቤቴ የአምላክ እናት

ኧኸ ድንግል አማልጂን ኧኸ ቅድስት ተራጂን

ለሔዋን ተስፋዋ ለአዳም ዘር ሕይወት
ለድኅነቱ ምክንያት አንቺ ነሽ በእዉነት
የኦሪት መፅናኛ ለአዲስ ኪዳን በር
የወንጌል መሰረት የአምላክ ማኅደር
የአብርሃም እርሻ የምሥጢር ዋሻዉ

እናትና ድንግል ሁለቱንም ሆንሽዉ

የኤፍሬም ዉዳሴ የያሬድ ዉብ ዜማ

የማትጠልቂ ፀሐይ የሕይወት ሻማ

596. ለንስሐ ሞት አብቃኝ

ለንስሐ ሞት አብቃኝ /፪/

በሂሶጵ እርጨኝ እጠበኝ

እንደ በረዶ አንፃኝ /፪/

አመፃዬ በዛ ኃጢያትም ጨመርኩኝ
ልቤ ደነደነ ክፋትን ፈፀምኩኝ
እንደ ፈርኦን ልቤ እንዳይፀናብኝ
አድነኝ እንደ ኖኅ አምላክ እራራልኝ
አድነኝ /፫/ ስለ ድንግል ብለህ አድነኝ
አድነኝ /፪/ ስለፃድቃን ብለህ አድነኝ
ኃጢያቴም በረታ ሰለጠነብኝ

ከቃልህ አስወጣኝ ሕግህን ጣስኩኝ

እንደ ነነዌ ሕዝብ ንስሐን ስጠኝ

ምህረትህን ልከህ ልቤን ስበርልኝ

አድነኝ /፫/ እንደ ቸርነትህ አድነኝ

አድነኝ /፪/ እንደ ምህረትህ አድነኝ

ያደፈዉ ገላዬን አንተዉ አጥራልኝ
ከሰዶም ጎሞራ እንዳይብስብኝ
መንገድና ሕይወት አንት ነህ ምራኝ
የቅዱስ ጴጥሮስን ንስሐ ስጠኝ
አድነኝ /፫/ እንደ ቸርነትህ አድነኝ
አድነኝ /፫/ ስለእናትህ ብለህ አድነኝ
አድነኝ /፪/ ስለፃድቃን ብለህ አድነኝ

597. የቅዱሳን አምላክ

አብርሃምን ከካራን የጠራኸዉ ጌታ

ሙሴ በሲና የሆንከዉ መከታዉ

ልጠፋ ነዉና በሥጋ ፍላጎት

የይስሐቅ ጌታ ህይወቴን ታደጋት /፪/

የኤርትራን ባሕር በኃይል የከፈትከዉ
በሲና በርሃ ሕዝብህን የመገብክ
ኖኅን ከጥፋ ዉኃ የዳነብህ አምላክ
ሎጥን እንዳዳንከዉ ፍፁም ምኅረትህን ላክ
/፪/

የተነበዩልህ ነቢያት በሙሉ

አምላክ ሰዉ ሆኗል ይወለዳል ሲሉ

ከአሳ አንበሪ ሆድ ዮናስን ያወጣህ

ዓለም ልትዉጠኝ ነዉ አይለየኝ ፀጋህ /፪/

ሥጋን ተዋህደህ በወሰንከዉ ሰዓት
የሞትክልኝ አምላክ ያዳንከኝ ከሞት ሞት
እንደ ወንጌልህ ሕግ የምኖር አድርገኝ
በመጨረሻዉ ቀን በቀኝህ አድርገኝ /፪/

አልቻልኩምና ልፈፅም ሕግህን

የሐዋርያት አፅናኝ ስጠኝ ብርታትህን

ምግባረ ጎዶሎ ሆኖለዉና

የቅዱሳን አምላክ እርዳኝ እንድፀና /፪/

598. ድንግል ሆይ

ወላዲተ አምላክ የሁሉ እመቤት

ለምኚልን ለኛ ከልጅሽ ምህረት

ባንቺ አማላጅት በሱ ቸርነት

እንዲያወጣን ነፃ ከፍርድ ቅጣት

ድንግል ሆይ ለምኚልን /፪/

በበደል ተዳክሞ ፍቃደ ነፍሳችን
በምድራዊ ምኞት ናዉዞ ልቦናችን
ፍቅርና ትህትና ጠፍቶ ከፊታችን
ለሞት እንዳይሰጠን ይህ ክፍ ስራችን

የሚስኪኖች ተስፋ የደካሞች ኃይል

ጠዉልገናልና ጥላ ሁኚኝ ድንግል

እምነት ጨምሪልን ልቦናችን ይፅና

እማምላክ አብሪልን የመዳንን ፋና

ፍፁም እንዳናዝን እንዳናፍር ኂላ
ተነጥቀን እንዳንቀር ከዘላለም ተድላ
በፍቅርሽ መልሽን ከሲኦል ጎዳና
ድንግል መመኪያችን ተስፋችን ነሽና

599. ከአገልግሎት በፊት

አደባባይ ቆሜ ስምህን ከመስበክ
መጀመሪያ ልቤ ከፊትህ ይንበርከክ

ከአገልግሎት በፊት አንተን ልወቅህ
መስዋዕት ከማቅረብ ልታዘዝልህ
አሐዱ አብ ብዬ ስምህን ብቀድስ
ለድሆችም ብሰጥ ቤትህ ብገሰግስ
በመላዕክት ልሳን ብዘምር በእልልታ
ብዘምር በእልልታ ከበሮ ብመታ
ምን እጠቅምሀለሁ ካልፈራሁህ ጌታ
ተራራ እስካፈልስ እምነት ቢኖረኝ
ፍርሃት ከሌለበት ምንም አይጠቅመኝ
ልቤን ስትመረምር ከሆንኩኝ ቀላል
ክርስቲያን መባሉ ምን ይጠቅመኛል
ጨው አልጫ ቢሆን በምን ይጣፍጣል
ከውጪ ተጥሎ በእግር ይረገጣል
አንተን ለሚከተል እንዳልሆን እንቅፋት
አምልኮቴ ይሁን በፍቅር በፍርሃት
የእውቀት ሰው መሆን ምንም አልጠቀመኝ
እኔስ መስቀልህ ነው ፍቅርህ ነው ያሸነፈኝ
ከእምነት ተነሳ መታዘዝ የሆነኝ
ስምህን መፍራት ነው በእምነት የሚያኖረኝ

600. ዛሬ ተይዣለዉ

ዛሬ ተይዣለሁ በፍቅሩ ስጦታ

ዉለታህ ማርኮኛል የሠራዊት ጌታ

ከአመድ ያነሣኸኝ ከትቢያ ተጥዬ

ዉለታህ ከበደኝ <u>ማረከኝ ጌታዬ</u> /፪/

ያልሰጠኸኝ ነገር በዚህ ምድር የለም
ፍቅርህ ወሰን የለዉ ድንቅ ነዉ ዘላለም
እኔነቴን ሳስብ ምንድን ነኝ እላለዉ
ፍቅርህን ሳስተዉል <u>ሁልጊዜ አለቅሳለዉ</u> /፪/

ለብቻዬ ሆኜ አምላኬን ሳስበዉ

ከጎሊና በላይ ዉለታህ ብዙ ነዉ

የተጣለዉን ሰዉ ማንሰሳት ያዉቅበታል

ምስኪኑን ሲያፅናና ከሁሉ ይበልጣል /፪/

ሰዉ ነህ ተብያለዉ አንተ ሰዉ ስላልከኝ
ማን ያስታዉሰኛል አንተ ባታከብረኝ
አትጣለኝ አንተ ሁሉም ያከብሩኛል
ኃጢያቴን ባትቆጥር ለእኔ ይበቃኛል

601. አማኑኤል ሆይ

አማኑኤል ሆይ መድኃኒቴ ሆይ
አትተወኝ አንተ ሞትን እንዳላይ /፪/
የግብፅ ከተማ ደምቃ ስትታየኝ
ተሰሎንቄ አድጋ ለዓይኔ ስትስበኝ
ኤልሻዳይ ኢየሱስ ልቤን መልስልኝ /፪/
መታመን በሰው ላይ ምንም አይጠቅምም
መከታነት በሰው ለእኔ አይሆንም
አትተወኝ አንተ አምላክ ዘለዓለም /፪/
የሚያጽናናኝ የለም እኔ እንዲህ ስጠፋ
ሕልምም ሆኖብኛል የሰው ሁሉ ተስፋ
ቃልህን የማታጥፈው አንተ ከእኔ አትጥፋ /፪/

602. አባታችን ሆይ

አባታችን ሆይ ሁላችን ጌታ /፪/
ቅዱስ መንፈስህ አይራቀን ጧት ማታ
ወዳንተ መልሰው የሰውን ልቦና /፪/
ባላወቀው መንገድ እሱ ሄዷልና
እዝነ ልቡናህን ወደኛ አዘንብል /፪/
ይቅርታን ልንጠይቅ ከፊትህ ቆመናል /፪/
ይቅርታን ልንጠይቅ ከፊትህ የቆምነው /፪/
መሐሪ መሆንህን ስለምናውቅ ነው /፪/
አይተህ እንዳላየ ታልፈዋለህ ሁሉን /፪/
መዓቱም ምህረቱም ሁሉም ያንተ ሲሆን /፪/
ሥልጣንህ ረቂቅ ነው አይመረመርም /፪/
ዘመንና ወራት ሊሽሩት አይችሉም /፪/
የፍቅር ባለቤት ቸሩ አምላካችን /፪/
ዕድሜ ለንስሐ ስጠን ለሁላችን /፪/
እንማልድሀለን በለቅሶ በሀዘን /፪/
የይቅርታህ ብዛት ከእኛ ጋር እንዲሆን /፪/
የሰማይ መላዕክት የምድር ሠራዊት /፪/

603. እግዚአብሔርን ጥራው

እግዚአብሔርን ጥራው በመከራ ጊዜ
ያድንህልና ከሐዘን ከትካዜ
ጋሻና ጦሬ ብለህ ምርኩዜ
አመሰግንህ ዘንድ እነሳለሁ በእኩለ ሌሊት
እንዳመሰገነህ ነቢዩ ዳዊት
በንጹህ ልቡና እንደ መላዕክት
በቅድስናው ሥፍራ ለእግዚአብሔር ስገዱ
እርስ በእርሳችሁም ተዋደዱ
ጸብና ክርክር እንዲወገዱ
እምነትን ከስራ አስተባብረህ ከልብ
በወጣትነትህ ፈጣሪህን አስብ
ሥራህም በሰው ፊት ይብራ
እንደ ፀሐይ ይብራ እንደ ኮከብ
በቤተክርስቲያን ፀሎት በድንግል ኪዳን
አቤቱ ጠብቃት ኢትዮጵያን
ለሕዝቧም ስጣቸው ፍቅር አንድነትን
እለምንሃለሁ አምላኬ ሆይ አንዲት ነገር
ከቤትህ ገብቼ በደስታ እንድኖር
ከባለሟሎችህ ከአብርሃም ከይስሀቅ

ከያዕቆብ ጋር

604. የሰው ልጅ በኃይልህ

የሰው ልጅ በኃይልህ ፈጽሞ አትመካ /፪/
አንድ አምላክ አለና በኃይሉ ኃይል የሚለካ /፪/
ኃይል እንደ ሶምሶን ከአምላክ ሲሰጥ እንጂ /፪/
በጉልበት መመካት ለማንም አይበጅ /፪/
ሰናክሬም ቢነሳ በሕዝቅያስ ላይ /፪/
የደረሰበትን አልሰማህም ወይ /፪/
ጎልያድ በኃይሉ ዳዊትን ቢንቀው /፪/
አዋረደው እንጂ ኃይሉ ምን ጠቀመው /፪/
እንደ ዳታንና እንደ አቤሮን አይሆንም በግድ /፪/
ተመርጦ ነው እንጂ ለክብር በአምላክ ፈቃድ /፪/
ክህነትን ለአሮን ሕግንም ለሙሴ /፪/
ከሰው ሁሉ መርጠው ሰጧቸው ሥላሴ /፪/

605. በመከራ ጽና

በመከራ ጽና በፈተናም ጽና
ለጊዜው ነው እንጂ ሁሉም ያልፋልና /፪/
ኢዮብ ተጨነቀ በጣም ተማረረ
በመከራው ብዛት ትዕግስትን ተማረ
ልጅ የሌለው ሆነ አጣ ንብረቱን
በመከራው ጸና አልካደም አምላኩን
መፈተን መልካም ነው ያነጥራል እንደ ወርቅ
በመጨረሻው ቀን በክብር እንድንደምቅ
አንዱን ስትሻገር ሌላው ቢተካብህ
በሕይወትህ ዘመን ፈተና ቢያጠቃህ
ከአምላክህ ተስማማ ራስህን አዋርድ
በቃሉ ተመራ እንደ ፈቃዱም ሂድ
ዋጋ ከአምላክህ ዘንድ በሰማይ አለና
በርታ ክርስቲያን ሆይ በመከራ ጽና

606. በደልህን አምነህ

በደልህን አምነህ ንሠሐ ግባና
ወደ አምላክህ አልቅስ ተጸጸትና
አመስግነው ጌታን አፍቅረው ከልብህ
በጉብዝናህ ወራት በእርሱ ደስ ይበልህ
ስትቸገር አይቶ ንቆ የማይተውህ
አምላክህን ውደድ እርሱ ነው አለኝታህ /፪/
የኃጢአት ኑሮን አቁምና ዛሬ
ለማፍራት ተነሳ የንስሐን ፍሬ
የእግዚአብሔርን ድምጽ አትናቅ ጥሪውን
ተመለስ ይልሀል አስተውል መንገዱን
የጉብዝናህ ወራት ያበቃል ያከትማል
ድካም መሸነፍም መውደቅም ይመጣል
ተስፋህ ይጨልማል ንብረትህም ያልቃል
ወጣትነትህስ መች ሁሌ ያኖራል
የወደቅህ ለታ ማንም አያይህም
ሁሉም ሲኖርህ ነው ካንተ ጋር አይቆምም
እስከመቼ ድረስ እንዲህ ትኖራህ
መለከት ሲነፋ ወዴት ትገባለህ
ለካህኑ ነግረህ የሰራኸውን ኃጢአት
ቀኖና ተቀበል እንድታገኝ ስርየት
ቤትህን አዘጋጅ ክርስቶስ ይመጣል
ማድጋህን ክፈት እርሱ ይሞላዋል
ተመለስ ወደሱ በደሙ ገዝቶሀል
እሱም አይቀየም ሊቀበልህ ወዷል
አመስግነው ጌታን……..

607. አምላካችን ተመስገን

አምላካችን ተመስገን /፪/
ለዛሬ/ለዚህ/ ቀን ያደረስከን /፪/
በኃጢአት ስንማቅቅ በምሕረትህ ጠራኸን
በዓለም ስንባዝን ነበር በይቅርታህ መራኸን
አምላክ ሆይ ተመስገን
ትዕግስትህ ብዙ ነው አያልቅም ርህራሔህ
የምንከፍልህ ምን ይሆን ብዙ ነው ውለታህ
አምላክ ሆይ ተመስገን
ከቶ የማትፈልግ ከሰው ልጆች ወሮታ
ቸር ፈጣሪ ነህና ሥራህ ድንቅ ነው ጌታ
አምላክ ሆይ ተመስገን
ይቅር ባይ አምላካችን ሆይ አንተን
እናመልካለን
ከመአትህ ታግሰህ ሁሉንም ይቅር አልከን
አምላክ ሆይ ተመስገን
ኃጢአታችን ጨለማ ቢያደርገው ኑሮአችንን
ባንተ ተጎናጽፈናል የመዳንን ብርሃን
አምላክ ሆይ ተመስገን
ስላደረክልን ሁሉ ስለግሩም ስራህ
የራስህን እንስጥህ ተመስገን እንበልህ
አምላክ ሆይ ተመስገን

608. ድንግል መከራሽን

ድንግል መከራሽን ጥቂት ላስታውሰው
በሄሮድስ ዘመን ፍጥረት ያለቀሰው
አንቺ የአምላክ እናት ደግሞም እመቤት
እንደ ችግረኛ ተነሳሽ ስደት
ኾረ ለመሆኑ እንዴት አለቀልሽ
ስትንከራተቺ በረሀውን ቆርሰሽ
ይገድሉታል ብለሽ ለልጅሽ አስበሽ
በሔሮድስ ዘመን መከራሽን አየሽ /፪/
አዛኝቷ ማርያም በጠራሁሽ ጊዜ
እንድትደርሽልኝ በመከራ ጊዜ
መከራን ያየ ሰው መቼም አይጨክንም
አትጨክኚብኝ አደራሽን ማርያም አደራሽን /፪/
ማርያም አቤት የዛን ጊዜ ያየሽው መከራ
ያለቀስሽው ለቅሶ ጭራሽ አይወራ

የአማኑኤል እናት አንቺ መከረኛ
እድሜሽን ጨረስሽው ሆነሽ ሐዘንተኛ

609. አድኚኝ እናቴ

አድኚኝ እናቴ ከስጋ ፈተና
ሥጋዬ ከኃጢአት ከቶ አልራቀምና
ሸክሜ የከበደኝ ብቸኛ ሆኛለሁ
አትለዩኝ ድንግል አደራ እልሻለሁ /፪/
የአማኑኤል እናት የተዋሕዶ አክሊል
አትጥፊ ከመሀል እንድትሆኚን ኃይል
ምንም ቢበዛብሽ የእኛ ጉስቁልና
ከእኛ ጋራ ከሆንሽ አለን ቅድስና /፪/
ተስፋዬ ነሽና እመካብሻለሁ
ግራ ቀኜም አልል ምርኮኛሽ ሆኛለሁ
ስቅበዘበዝ አይቶ ተስፋ የሰጠኝ
እግዚአብሔር ይመስገን ካንቺ ያስጠጋኝ /፪/
በሥጋ ደክሜ በነፍስ እንዳልጠፋ
እማጸንሻለሁ ድንግል የእኔ ተስፋ
የመንግስቱ ወራሽ እንድሆን አድርጊኝ
መልካም ስራን መስራት እኔን አስተምሪኝ
/፪/
አንቺ የሌለሽበት ጉባኤው ባዶ ነው
በቁም የደረቀ ሕይወት የተለየው
በመሀከል ገብተሽ ሙዱው ጎዶሎውን
ሠርጉ ተደግሷል ጎብኚልን ጓዳውን /፪/

610. እኔስ በምግባሬ

እኔስ በምግባሬ ደካማ ሆኛለሁ /፪/
እዘኚልኝ ድንግል እለምንሻለሁ /፪/
ያንን የእሳት ባሕር እንዳላይ አደራ
ድረሺልኝ ድንግል ስምሽን ስጠራ /፪/
የዳዊት መሰንቆ የኤልያስ መና
የናሆም መድኃኒት ነይ በደመና /፪/
አንቺ ነሽ ጉልበቴ በደከመኝ ጊዜ
የልቤ መጽናኛ ረዳት ምርኩዜ /፪/
አፈሳለሁ እንባ በጣም ተጨንቄ
እማፀንሻለዉ በደሌን አዉቄ /፪/

611. ምሳሌሽ ግሩም ነው

ምሳሌሽ ግሩም ነው የማይነገር ምሥጢር
የሙሴ ጽላት ነሽ የአሮን በትር
ማርያም ምልዕተ ክብር ሰላም ለኪ
ቅዳሴሽ ሕይወት ነው አማናዊቷ ደመና
እሳቱ ያልፈጀሽ ሐመልማለ ሲና
ርሕርሕት ወለተ ሃና ሰላም ለኪ
በሥጋሽ ድንግል ነሽ በሕሊናሽም ድንግል
የሕዝቅኤል በር የጻድቃን አክሊል
ቅድስት ማሕደረ ቃል ሰላም ለኪ
የጌድዮን ጸምር የቀራንዮ ስጦታ
የነቢያት ትንቢት የአበው ደስታ
ድንግል ምድረ ኤፍራታ ሰላም ለኪ
ስለ እኛ ለምኚ እንድንሰራ ትሩፋት
ጸጋን ተመላሽ ኪዳነ ምሕረት
ማርያም የጌታ እናት ሰላም ለኪ
ትንቢትሽ እውነት ነው የተነገረው ቃሉ
ያመሰግኑሻል ይኸው ትውልድ ሁሉ
ቅድስት ብጽዕት እያሉ ሰላም ለኪ
ሞገስሽ እፁብ ነው የሚያስደንቅ ነው ክብርሽ
ከሰው የተገኘሽ እፀ ሕይወት ነሽ
አድኖናል ጥዑም ፍሬሽ ሰላም ለኪ

612. ዓለምን ዞሬ

ዓለምን ዞሬ አየሁት ሁሉን በተራ ቀመስኩት /፪/
ፈጽሞ የለም /፪/ ሰላም እንደ ልጅሽ ቤት /፪/
ሀብት ንብረቴን ጨረስኩና
ጉልበቴ ሁሉ ደከመና /፪/
ጎስቋላ ሆንኩኝ /፪/ ደካማ የሌለው ጤና
ስቃ አሳስቃ ተቀብላ መልኳን አስውባ ተኳኩላ /፪/
ዛሬ ጣለቺኝ /፪/ ይቺ ዓለም አትረባም ብላ /፪/
የትናንትና ወዳጆቼ ዛሬ ሲሆኑ ጠላቶቼ /፪/
ባክኜ ቀረሁ /፪/ በዓለም ላይ ተንከራትቼ /፪/
የአባቴ ቤት ሲናፍቀኝ ፍቅሩ ምሕረቱ ትዝ ሲለኝ /፪/
ሁሉንም ትቼ /፪/ ድንግል ሆይ ዛሬ መጣሁኝ /፪/
ልጅም እንድባል ባይገባኝ
ባሪያው እሆን ዘንድ ቢፈቅድልኝ /፪/
ጎስቋላው ልጁ ደካማው ልጁ
ድንግል ሆይ ዛሬ መጣሁኝ /፪/
እናቴ አንቺን ንቄ ትቼ የአባቴን ቤት ረስቼ /፪/
ተሰቃየሁን ተንከራተትኩኝ ልደሰት
በዓለም ገብቼ /፪/
አባቴ ሲያየኝ ተደስቶ ጎረቤቶቹን ሁሉ ጠርቶ
ሠርጉን ደገሰ /፪/ የበደልኩትን ረስቶ
እስካሁን ድረስ በድያለሁ
ዓለም ደህና ሁኝ አብቅቻለሁ /፪/
ወደ አባቴ ቤት /፪/ ዳግመኛ ተመልሻለሁ /፪/

613. ስለ ድንግል ብሎ

ስለ ድንግል ብሎ ኢትዮጵያን ይጎብኛት
ድሮስ ከአምላክ በቀር ይች አገር ማን አላት
በሠራዊት ብዛት መች ትጠበቃለች
በቅዱሳን ጸሎት እሳት ካልታጠረች
ዓለም ሽምቆባት አሕዛብ ይስቃል
በልጆችሽ እንባ አውሬው ይቀልዳል
ታሳቅ ሕዝብ መሆኑን ማን በነገራቸው
ከዘመናት በፊት አምላክ የጎበኘው /፪/
እውነተኛ እንባ ፈለቀ ከምድር

በፍጡራን ዋይታ ፍጹም ብትማረር
እንባና ደማችን ተደባልቆ ፈስሷል
አምላክ ቅጣት ይብቃን አሁን ይቅር በለን
ቅዱሳንን መንቀፍ ወገኔ ተውና
ይልቅ ስለ እነርሱ የጽድቅ ጎዳና
በረድኤታቸው በክብራቸው ጥላ
እንከተላቸው ከፍቅራቸው ኀላ

614. አምላክ ሆይ ጠብቀኝ

አምላክ ሆይ ጠብቀኝ

ጌታ ሆይ ጠብቀኝ ከጥፋት አድነኝ

የተቀደሰውን ካለሥፍራው ጥዬ
ፈጽሜ ሳልጠፋ በምግባር ጎስቁዬ
በሥጋዬ ድካም ነፍሴ ሳትዝልብኝ
ወደ እኔ ተመልከት ክንድህን ዘርጋልኝ

መንገዳገድ በዝቶ እንዳልቀር ወድቄ

ከሕያው ማዕድህ እንዳልሄድ ርቄ

አምላኬ እረኛዬ ድምጽጎን አሰማኝ

ቦታዬን ሳላውቀው ተኩላ እንዳይበላኝ

በንስሐ ውሃ ሕይወቴን አንፅቼ
ሰላሜ እንዲመለስ ቃልህን ሰምቼ
አንድ አድርጌ ይዤ ምግባር ከሃይማኖት
አልጫው ሕይወቴ ይሁን ጣፋጭ ሕይወት

615. ልመናዬን ስማኝ

ልመናዬን ስማኝ ቃሌንም አድምጥ

እውነተኛው አምላክ ሰላምህን ስጥ

ክርስቲያኖች ሁሉ ትእዛዙን አክብሩ

ምስጋናን አቅርቡ ስገዱ ዘምሩ

የጌታን አመጣጥ ለዓለም ንገሩ

ደቀ መዛሙርቱ ወንጌል አስተምሩ

በመልካም የሚሄድ ጽድቅን የሚሠራ

የፈጣሪውን ስም በከንቱ የማይጠራ

ይጎበኛል በምድር በሰማዩም ሥፍራ

በቀኝ ይቀመጣል ከቅዱሳን ጋር

ስለ ጠላቶቼ በጽድቅህ ምራኝ

በጥል ቃል ከበቡኝ ተሰለፉብኝ

መሐሪ ይቅር ባይ መጠጊያ ሁነኝ

አንተ በቸርነት ይቅርታን ስጠኝ

616. ሰምዓኒ እግዚኦ ጸሎትየ

ሰምዓኒ እግዚኦ ጸሎትየ

ወይብጻሕ ቅድሜከ ገዓርየ /፪/

ወኢትሚ ገጸከ እምኔየ

በዕለተ ምንዳቤየ አጽምዕ አዝነከ ኃቤየ

አመ ዕለተ እጼውዓከ ፍጡነ ስምዓኒ

አቤቱ ስማኝ ጸሎቴን

ጩኸቴም ይድረስ ከፊትህ ዘንድ /፪/

አትመልስ ፊትህን ከእኔ ዘንድ

በመከራዬ ቀን አድምጥ ጆሮህን ወደ እኔ /፪/

በጠራሁህ ዕለትም በፍጥነት ስማኝ

617. እንሂድ እንገስግስ

እንሂድ እንገስግስ ወደ አባታችን

ጠርቶናልና ርስቱን ሊያወርሰን

የዘለዓለም ሕይወት እንዳይቀርብን

ሀብታችን ቤታችን ይህ አይደለምና

እንጓዝ ወደ እርሱ በቀናው ጎዳና

ዓለምን ድል ነሥተን ወደ እሱ እንድንሄድ

ፈጥነን እንለፈው ጠባቡን መንገድ

መንገድ ላይ ሳለን በመገስገስ ላይ

ከጠላት ሥር ወድቀን ከአንተ እንዳንለይ

አቤቱ ጌታ ሆይ ኃይልህን ስጠን

ድል ነስቶ እንዳይገዛን ፀራችን ሰይጣን

በወጥመድ ተይዘን መሄጃው ጠፍቶብን

ወድቀን እንዳንቀር እርዳን አምላካችን

ቤታችን ተዘግቶ መግቢያ አጥተን እንዳንቀር

እንለምንሃለን እንድትለን ይቅር

618. ታዛዥህ ልሁን

ለቃልህ የምገዛ ትሁት ሠው እንድሆን

ለቀሪው ሕይወቴ ምራኝ መንገድህን

ዓለምና ውበቷ ማርከው እንዳይገዙኝ

ጉልበቴም እንዳይደክም ኃይልህን አጎናፅፈኝ

ሳትጎሰቁል ነፍሴ ሳትዝልብኝ

ሥጋዬን ጎስመህ መንፈሴን አቅናልኝ

የዓይኔ ብርሃን ፈዞ ማየት ተስኖኛል

የዓለም ጨለማ ፊቴን ከልሎኛ

በመስቀልህ ብርሃን ከጨለማ አውጣኝ

ገጸ ምሕረትህን ፈጥነህ ግልጥልኝ

ፍቅርህን አውቄ ለእኔ ያለህን

ፍቃድህን ልፈፅም ታዛዥህ ልሁን

ሁሉ ባይሰምርልኝ አንደእኔ ምኞት

ለበጎ ነዉ ልበል ለእኔ ደኅንነት

ጥፋቴን የማትወድ ይቅር ትለኛለህ

ወዳንተ እስክመለስ ትታገሰኛለህ

መሐሪ ነህና አዶናይ አባቴ

ከበደሌ አንፃኝ ደግሞም ከኃጢያቴ

619. አትራቀን

አትራቀን እንዳንቀር ወድቀን

አባታችን ሆይ መሐሪ ይቅር ባይ

አዉጣን ከስቃይ

ደካሞች ነንና

የፅድቁም ጎዳና ጠፍቶብናልና አትራቀን ...

ኃጢያታችን በዝቶ

በደላችንም በርክቶ

ቢያስከፋህም ከቶ

ስራችንን አይተህ

በደላችችንን አስበህ

በእኛ ተቆተህ አትራቀን.....

ይቅር ባይ ነህና

የኃጥኡን ሞቱን አትፈልግም እና

አትተወን እኛን

በሲኦልም ጥልቅ ዉስጥ አትበቀለን አትራቀን...

የአብርሃም የይስሐቅ

ጽድቃቸዉን አስበህ

ማረን እባክህን

መንጋዎችህ እኛን

እንዳንቀር ጠፍተን

በፅድቅህ ጎብኘን አትራቀን ...

620. ደካማ ነኝ እኔ

አቤቱ ፈጣሪ የኃጥአን ተስፋ

እንዳልወድቅ ደግፈኝ በዓለም እንዳልጠፋ

በምህረትህ ብዛት ደምስስ በደሌን

ደካማ ነኝ እኔ መንዝ የተሳነኝ

ጠላት በዙሪያዬ ከቦ የሚያስጨንቀኝ

በህግህ ለመኖር እኔ አልቻልኩም እና

ፈታኜን ጣልልኝ ኃይል የአንተ ነዉና

አንተን ማሳዘኔ በደሌም ቢበዛ

ባታገኝም ከኔ የፅድቅ መአዛ

በምህረትህ ብዛት አንተ ይቅር በለኝ

ስራዬን አትየዉ እኔ ደካማ ነኝ

ዘወትር አለቅሳለዉ ድካሜን አዉቄ

መኖሬ ሲሰማኝ ከቃልህ ርቄ

በመንገድህ ምራኝ ፊትህን እንዳይ

ስለ እናትህ ብለህ ከእኔ አትለይ

621. እመቤቴ ማርያም

እመቤቴ ማርያም እለምንሻለሁ

በለቅሶ በዋይታ ፊትሽ ወድቄአለሁ

እመቤቴ ስሚኝ እለምንሻለሁ /፪/

ኃዘኔን ጭንቀቴን ለማን እነግራለሁ

ችግሬን ጉዳቴን ለማን አዋያለሁ

እመቤቴ ስሚኝ ተማፅኜሻለሁ /፪/

ኃዘኑም በዛብኝ ፈተናው ከበደኝ

እንደምን ልቻለው እኔ ደካማ ነኝ

የአማኑኤል እናት ፈጥነሽ ድረሺልኝ /፪/

በጣም ተንገዳገድኩ ልወድቅ ነው እኔ

እመአምላክ ደግፊኝ ቁሚልኝ ከጐኔ

ምንም አጋር የለኝ ከአንቺ በቀር ለኔ /፪/

622. በደላችንን ይቅር በለን

ይቅር በሉ ይቅር እንድትባሉ

የሚለዉን ቃልኪዳንህን አስታዉሰህ ወደ ፈተና አታግባን

ከክፉ ነገር አድነን ከክፉ ስህተት

የአንተ ናትና መንግስትም ኃይልም ክብርም ለዘለዓለም አሜን

623. እግዚአብሔር ሆይ እርዳኝ

እግዚአብሔር ሆይ እርዳኝ ቸርነት አድርገህ

እድሜ ለንስሐ እንደ ሕዝቅያስ ሰጥተህ

ጠማማውን ልቤን በቃልህ አቃንተህ

አላውቀውም ብሎ ሲጠየቅ ያመፀው

ዶሮ እስኪጮህ ድረስ ሦስት ጊዜ የካደው

የጅረት ወንዝ ነው የሰጠኸው እንባ

ጴጥሮስ ተፀፅቶ ንስሐ እንዲገባ

ጽዋው እንዳይደርሰኝ የይሁዳ እድል

ልጅህ ሆኖ ውሎ ማታ መከብለል

ጴጥሮስ እድለኛ አልቅሶ ተማረ

በትዕቢቱ ይሁዳ እንደወጣ ቀረ

ዘመኗን በሙሉ በዝሙት አቃጥላ

ለንስሐ ጠራት ጌታ በገሊላ

ታድሳ ተነሳች በእንባዋ ብዛት

በእግሩ ሥር ተደፍታ ማርያም

እንተ እፍረት

624. ሃሌ ሉያ ሕያዉ ሆነህ የምትኖር

ሃሌ ሉያ ህያዉ ሆነህ የምትኖር

ሞትን ያሸነፍክ በሥልጣንህ

ክርስቶስ የእኛ ጌታ ለዳዊት በእዉነት የማልህ

አቤቱ ወዴት ነዉ ምህረትህ

የተራበች ነፍስ ትጠባበቃለችና ከተስፋህ

ለስምህ ምሥጋናን በማቅረብ

እዉነትነትህንም በማሰብ

የሰዉን ፊት አይተህ የማታደላ

መማለጃ የማትበላ እዉነተኛ ንጉሥ አንተ ነህና ክርስቶስ

625. ወደ ቤተ እግዚአብሔር

ወደ ቤተ እግዚአብሔር እንሒድ ሲሉኝ /፪/

እንደ ዳዊት እንደ ንጉሥ ተደሰትኩኝ /፪/

መላእክት በሰማይ የሚያመሰግኑህ /፪/

አምላካችን ፍቃድህ ይሁን እንዘምርልህ /፪/

ሞትን አሸንፎ ለተነሳዉ ጌታ /፪/

ዘምሩለት ተቀኙነት በጠዋት በማታ /፪/

በመስቀል ላይ ሳለ ሲወጋ ጎኑ /፪/

ዉኃና ደም አንድ ላይ ሆኖ ፈሰሰልን /፪/

በዉኃ ተጠምቀን ደሙን ጠጥተን

መንግስቱን እንድንወርስ ስላደረገን

ስሙ ይክበር ከፍ ከፍ ይበል የጌታችን

ስሙ ይክበር ከፍ ከፍ ይበል የአምላካችን

626. አቤቱ ማረን

አቤቱ ማረን ይቅር በለን /፪/

ያለአንተ መድኃኒት የለን /፪/

ሥጋዬን ብሉና ደሜን ጠጥታችሁ

ዘላለማዊ ሕይወት ይኑራችሁ

አቤቱ ----------

ብሎ ነበር እርሱ የሚሰማዉ ጠፋ

ሁሉም በየድርሻዉ ምኞቱን ሲያስፋፋ

አቤቱ ---------

በሕይወት ለመኖር ትዕዛዙን ጠብቀን

ምኞት ሳናበዛ እናስብ ስሙን

አቤቱ --------

በሥጋዉ ቀድሶ ቢያድነን በደሙ

ምን ዉለታ ሰራን ለአምላክ በስሙ

አቤቱ --------

ይህን ቅዱስ ሥጋ ይህን ክቡር ደም

እንዴት ልጆች ብቻ በልተዉት ይፈጸም

አቤቱ -------

ብዙ ሰዉ ለግብጥ ተጠርቶ ነበር

ጊዜን በማሳለፍ ከዚያዉ ከደጅ ቀረ

አቤቱ -------

ሌሎች በጥበብ ለመዳን ሲደክሙ

ሕይወት የተገኘዉ በሥጋ ወደሙ

አቤቱ -------

627. እስመ ለዓለም ምሕረቱ

እስመ ለዓለም ምሕረቱ /፪/

አያልቅም ብዙ ነዉ የአምላክ ቸርነቱ /፪/

አመስግኑት ጌታን ሁላችሁ በአንድነት /፪/

መሐሪ ነዉና ለሰዉ ልጆች ሕይወት /፪/

እስመ ለዓለም ምሕረቱ /፪/

የማይሞተዉ ሞቶ የተቀበረዉ /፪/

ከገሀነም እሳት እኛን ሊያድን ነዉ /፪/

እስመ ለዓለም -------

ከማርያም የነሳዉ ያ ቅዱስ ሥጋዉ /፪/

ቀራንዮ ሲዉል የሚያሳዝን ነዉ /፪/

እስመ ለዓለም ------

በፈጠረዉ ፍጥረት እጅግ ተሰቃይቶ /፪/

ነፍሳትን አወጣ ከሲያል ጎትቶ /፪/

እስመ ለዓለም -------

628. ሰላም ሰላም ማርያም ድንግል

ሰላም ሰላም /፪/ ማርያም ድንግል

ልመናሽ ለሚያምኑት ድኅነት ያሰጣል /፪/

ደቀ መዛሙርቱ በሐሳብ ሲዋኙ

ይኸዉ በቅርብ ቀን ምልክት አገኙ

ሰላም ሰላም -----

ለእኛ ለልጆችሽ ኃጢያት ላደከመን

ከልጅሽ ይቅርታን ድንግል ለምኝልን

ሰላም ሰላም -----

በሐና በኢያቄም እመቤታችን

በዚህች ቀን ባርኪልን ስብሰባችንን

ሰላም ሰላም ---------

629. በዓለም ጥላ ማረፍ

በዓለም ጥላ ማረፍ አይምሰልህ ጤና

ዓለም ከንቱ ጥላ ትሄዳለችና

ዓለም ጥላ ስትሄድ ፀሐይ ስትበረታ

ደግሞ ወድቆ ቀረ የሰዉ ልጅ አዉታታ

ተነሱ እንከተል እኛም ከሔዱት

አፈር ከሸተተን ከያዘን በሽታ

ብንቆርብ አንቀርም ይሄን ጊዜ እንበርታ

መቁረብ በሕይወት ነዉ ንሥሓ መግባት

ይህ ሁሉ አይገኝም ከገቡ መሬት

ሰዎች ተጠንቀቁ እወቁ ሁላችሁ

ዓለም አታላይ ነች እንዳታስቀራችሁ

630. መመኪያዬ አንተ ነህ

መመኪያዬ አንተ ነህ የነፍሴ መዳኛ

ተመልከት ወደእኔ አትስጠኝ ለዳኛ

ሕይወቴን ለአንተ /፪/ ብያለዉ

አምላክ የእኔ ጌታ የት አገኝሀለዉ።

ከበደሌም አንፃኝ ደግሞም ከኃጢያት

በመንፈስ ይታደስ መላ ሰዉነቴ

ሕይወቴን ላንተ ------

አቀበቱ ልቤ በጭንጫ ላይ ትዕቢት

አሸብርቆ ነበር የማይፈርስ መስሎት

ሕይወቴ ለአንተ ------

የጸም ንጉሥ መምጣት ስለተነገረ

መደልደል አለበት እየተሰበረ

ሕይወቴን ለአንተ -------

ሶስናን ያዳንካት ከሐሰት ምስክር

እኔንም አድነኝ ካልታሰበ ነገር

ሕይወቴን ለአንተ --------

631. አምላክ ሆይ ወደ እኛ

አምላክ ሆይ ወደ እኛ ባትመጣ ለብሰህ የማርያምን ሥጋ

ባክኖ የነበር የአዳም ዘር ዉጤቱ ነበር የሚያሰጋ

በዚያ ዓመት በዚያች ወር በዚያች ቀን ድኅነት ለሰዉ ልጅ ስትሰጥ

ምን የበዛ ነበር ትህትና ትዕግስትህ የማይለወጥ

የእሾህ አክሊል ደፍተዉ በእራስህ ጎንህን ሲወጉ በጦር

አንተ ግን ለእርነሱ የአባትህ ምሕረትን ትለምን ነበር

ግን መቼ አወቁ እርነሱ በኃጢያት ደንድኖ ልባቸዉ

መድኃኒታቸዉን ገረፉ ሰቀሉህ አንተም ሞትክላቸዉ

ዳግም ስትመጣ ለፍርድ ከዓለም ፍጻሜ በኃላ

አረ እንዴት እድለኞች ናቸዉ በፊትህ የሚያገኙት ተድላ

በዚያች በደብረዘይት ቦታደስታና ለቅሶ ሲፈልቅ

ከቶ ከየት ይሆን እጣዬ ያን ጊዜ የእኔ አወዳደቅ

የፀፀት እሮሮ በፊትህ እንዲያቃጥለኝ እኔን

እርዳን ፈጣሪዬ ካሁኑ አድሰዉ የዛገዉ ልቤን

632. አባታችን ሆይ

አባታችን ሆይ የምትኖር በሰማይ

መንግስትህ ትምጣልን ክብርህን እንድናይ /፪/

ፈቃድህ በሰማይ ሕይወት እንደሆነ

እንዲሁም በምድር ሰላምን ስጠን /፪/

ስጠን ለዛሬ የእለት ምግባችንን

በደላችንንም ይቅር እንድትለን /፪/

ጌታ ሆይ አታግባን ከክፉ ፈተና

አንተ ካልረዳሽን ኃይል የለንምና /፪/

ኃይልና ምስጋና መንግስትም የአንተው ናት

አሜን ለዘለአለም ይሁንልን እረፍት /፪/

633. ዴማስ ሆይ ተመለስ

የይሁዳ ጉዞ አያዋጣምና

ዴማስ ወደ ሕይወት እባክህ ቶሎ ና /፪/

ከወንጌል ገበታ መመገብ ጀምረህ

ወንድሜ ተመለስ ወዴት ትሄዳለህ

ይጠራሃልና መስቀሉን ተመልከት

የወንጌል ቡቃያ እውነተ ሕይወት /፪/

ብዙ ክርስቲያኖች መንገዱን ጀምረው

የዓለም አሸንክታብ ድምቀት ሲጠራቸው

ፈተና ሲመጣ ወንጌሉን ወርዉረዉ

ሞትን ይመርጣሉ ሕይወትን ሰርዘዉ /፪/

የመስቀሉ ሕይወት ከልብህ ሳይጠፋ

በእግዘአብሔር ጉባኤ መስክረህ በይፋ

ልጄ የተባልከዉ በጥምቀት ቀለበት

እንዴት ትሄዳለህ ተነድተህ ወደ ሞት /፪/

የክብር አክሊል ተዘጋጅቶልሃል
አምላክ ለሽልማት ዴማስ ሆይ ይልሃል
ወዴት ትሄዳለህ እባክህ ተመለስ

መዝሙር በእንተ ደብረ ዘይት

634. እያለፈ ነዉ ዘመኔ

እያለፈ ነዉ ዘመኔ ትዕዛዜን ሳልፈፅም ወየዉ ለኔ /፪/

በጠራኝ ጊዜ ምን እላለዉ ና ብሎ ወደ እኔ /፪/

ጠራኝ ጊዜ ምን እላለዉ ነይ ብሎ ወደ እኔ /፪/

በወጣትነቴ ሳልሰራ እያየዉ አለፈኝ ብዙ አዝመራ /፪/

ከእንግዲህ በመስራት ጌታ ሆይ ልኑር ካንተ ጋራ /፪/

የማስብበት በእየእለቱ ንፅህ ልብን ስጠኝ አቤቱ /፪/

ከትዕዛዝህ ዉጪ በመሆን እንዳልቀር በከንቱ /፪/

እንደየስራዉ ለመስጠት በግርማ መንግስቱ ሲመጣ /፪/

ማን ይሆን የሚቆም ከፊቱ ፈተናን የወጣ /፪/

እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ እየተማራችሁ ከቃሉ /፪/

ይመጣልና በእሱ ስም አምላክ ነን የሚሉ /፪/

ትዕግስትን በመያዝ ሁላችሁ እስከመጨረሻዉ ጠንክሩ /፪/

ያን ጊዜ ይሆናል በእርሱ ዘንድ የማዳን ተግባሩ /፪/

635. አቤት የዚያን ጊዜ

አቤት የዚያን ጊዜ ክርስቶስ ሲመጣ /፪/

ትንሹም ትልቁም /፫/ መድረሻዉን ሲያጣ

ከምስራቅ ከምዕራብ ከሰሜን ከደቡብ /፪/
ነፍሳት ሲላኩ /፫/ መዓትህን ለማዝነብ
ሰማይና ምድር በአንድ ሲዋሀዱ /፪/
የት ይሆን መድረሻዉ /፫/ የት ይሆን መንገዱ

ፃድቃን በቀኝ በኩል ኃጥአን በግራ /፪/

ሲነፋ መለከት /፫/ ሲደለቅ እንዚራ

ምድር ቀዉጢ ስትሆን አፅም ሲሰበሰብ /፪/
ኃፍረት ይይዘዋል /፫/ ሰዉ ለፍርድ ሲቀርብ

ጩኸት ሲበረታ የማይጠቅም ለቅሶ /፪/
እንደ ቁራ ጠቁሮ ጽልመት ተላብሶ
ገነትን ሲያገኙ ፃድቃን በስራቸዉ /፪/
ኃጥአን ወደ ሲኦል /፫/ ተፈረደባቸዉ

636. አምላክ ሆይ ማረን

እውነተኛው ንጉሥ ለፍርድ ሲመጣ
ጻድቁን ሲያከብር ኃጥኡን ሲቀጣ
መለከት ሲነፋ ነጐድጓድ ሲሰማ
ክርስቶስ ሲገለጥ በሚያስደንቅ ግርማ

አምላክ ሆይ ማረን
ማረን አምላክ ይቅር በለን

የነበረው ሁሉ ሲሆን እንዳልነበር
ተነሥተው ሲቆሙ ሙታን ከመቃብር
ፀሐይ ስትጨልም ሰማያትም ሲያልፉ
ምድር ቀውጢ ስትሆን ቀላያት ሲጠፉ

ፍጥረት ሲናድ ዲርስ ግርማ አያስፈራው
የአዳም ዘር በሙሉ ሲቆም ከነሥራው
ማነው የሚገኘው በጐ ምግባር ሠርቶ
ቅዱሳንን መስሎ በሃይማኖት ጸንቶ

በምድራዊ ሕይወት ትሩፋት የሠሩ
ጻድቃን ሲደሰቱ ተግተው ሲዘምሩ
ኃጥአን ሲጠፉቸው የሚሰወሩበት
እኛስ ከየት ይሆን የምንገኝበት

637. አምላክ ሆይ ወደኛ ባትመጣ

አምላክ ሆይ ወደኛ ባትመጣ ለብሰህ
የማርያም ሥጋ /፪/
ባክኖ የነበረው የአዳም ልጅ ውጤቱ ነበር የሚያሰጋ /፪/
በዚያ ዓመት በዚያች ወር በዚያች ቀን ድኅነትን
ለሰው ልጅ ስትሰጥ /፪/
ምን የበዛ ነበር ትኅትናህ ትዕግሥትህ የማይለወጥ/፪/
የሾህ አክሊል ደፍተው በራስህ ጐንህን ሲወጉህ
በጦር /፪/
አንተ ግን ለእነርሱ ከአባትህ ምሕረትን ትለምን ነበር /፪/
ግን መቼ አወቁህ እነርሱ በኃጢአት ደንድኖ ልባቸው /፪/
መድኃኒታቸውን ገረፉህ ሰቀሉህ አንተም
ሞትክላቸው /፪/
ዳግም ስትመጣ ለፍርድ ከዓለም ፍፃሜ በኋላ /፪/
ኧረ እንዴት እድለኞች ናቸው በፊትህ የሚያገኙ
ተድላ /፪/
በዚያች በደብረዘይት ቦታ ደስታና ለቅሶ ሲፈልቅ /፪/
ከቶ ወዴት ይሆን እጣዬ ያንጊዜ የእኔ አወዳደቅ /፪/
የፀፀት እሮሮ በፊትህ እንዳያቃጥለኝ እኔን /፪/
እርዳኝ ፈጣሪዬ ከአሁኑ አድሰው የዛገው ልቤን /፪/

መዝሙር በእንተ ሆሳእና

638. እመአፈ ደቂቅ ወሕፃናት

እመአፈ ደቂቅ ወሕፃናት አስተዳሉከ
ስብሐተ /፪/
በእንተ ጸላኢ /፬/ ከመትንስቶ ለጸላኢ
ወለገፋኢ /፪/
ትርጉም፡-ከሕፃናት አንደበት ምስጋናን
አዘጋጅህ የጠላት
ዲያብሎስ ምክሩን ታፈርስ ዘንድ

639. ሆሳእና በአርያም

ሆሳዕና በአርያም /፪/
ድኅነት ሆነ ለሁላችን ዛሬ በዓለም
አክብሮናል ፈጣሪያችን በኢየሩሳሌም

640. ሆሳእና በአርያም

ሆሳዕና /፪/ በአርያም /፪/
ቅድስት አገር ሆይ ኢየሩሳሌም
ምስጋናሽ ብዙ ነው በመላው ዓለም

በአህያ ላይ ሆኖ ወዳንቺ የመጣው
ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት ነው
ኃይልና ስልጣንም በአንድ ላይ ስላለው
ጠላቶች አፈሩ ሕዝብሽም ደስ አለው
እናውቃለን ባዮች ግብዞች ሲቀሩ
ወጣት ሽማግሌ ህፃናትም ሆነው በአንድ ላይ ዘመሩ
ሰውማ ቢዘምር ምን ያስደንቀናል
ሆሳዕና ሰው ቀርቶ ድንጋይ ያናግራል

641. ሆሳዕና እምርት

ሆሳዕና እምርት እንተ አቡነ ዳዊት /፪/
ቡርክት እንተ ትመጽዕ መንግስት /፪/

642. እናቶች አባቶች

እናቶች አባቶች ህፃናት በሙሉ
ለዓለም መድኃኒት ሆሳዕና በሉ /፪/
ሆሳዕና /፪/ ለወልደ ዳዊት /፪/
በአህያ ጀርባ ላይ አምላክ ቁጭ አለና
አሳየው ለሕዝቡ ታላቁን ትሕትና /፪/
ቤተ መቅደስ ገብቶ የሰላሙ ዳኛ
ይውጣ ብሎ አዘዘ ሌባና ቀማኛ /፪/
የሻጭና ለዋጭ ገበያ ነበርሽ
ዛሬስ ቤተ መቅደስ አምላክ ነፃ አወጣሽ /፪/

643. ደቂቅኒ ይጸርሁ

ደቂቅኒ ይጸርሁ ወሕዝብኒ ኪያሁ ይሴብሕ /፪/
ወይብሉ ሆሣእና በአርያም ብሩክ አንተ
መድኃኔዓለም /፪/

644. በትፍሥሕት ወበሐሴት

በትፍሥሕት ወበሐሴት /፪/
ይሁቦሙ ኃይለ ወሥልጣን /፬/

645. ሰላምሽ ዛሬ ነው

ሰላምሽ ዛሬ ነው ኢየሩሳሌም
ወዳንቺ መጥቷልና አምላክ ዘላለም(2)
ሆሳዕና በአርያም እያሉ ዘመሩ
ህፃናት በኢየሩሳሌም
አንቺ ቤተልሔም የዳዊት ከተማ
የሕዝቦችሽ ብርሃን መጣልሽ በግርማ /፪/
ሆሳዕና እያሉ አመሰገኑት
በኢየሩሳሌም አእሩግ ህፃናት /፪/
ኪሩቤል መንበሩን የሚሸከሙለት
መስቀል ተሸክሞ ሆነን መድኃኒት /፪/
የኢየሱስን ህማም ደናግል አይተው
እያለቀሱለት ሄዱ ተከትለው /፪/

646. ይባእ ንጉሠ ስብሐት

ይባእ ንጉሠ ስብሐት /፪/
ይባእ ንጉሠ ስብሐት /፬/

647. አርዉ ኖኅተ መኪንንት

አርዉ ኖኅተ መኪንንት /፪/
ይባእ እምላከ ምሕረት

648. መኑ ውእቱ

መኑ ውእቱ ዝንቱ ንጉሠ ስብሐት
‹‹ ‹‹ ‹‹ አምላከ ምሕረት
ይባህ ንጉሠ ስብሕት ይባህ አምላከ ምሕረት /፪/
ሆሳዕና በሉ መድኃኒት ነው እርሱ
ለበሽተኞች ፈውስ አድሏል ቀሚሱ
ደጁን ክፈቱለት ቀኑ ነው የጌታ
መኪንንት ተነሱ በሆታ በእልልታ
ለዓለም ምንሰብከው የመዳናችን ቀን
ፍቅሩ እስከመሞት ነው ለኛ እስከመዋረድ
የጥሉ ግድግዳ ፈርሷል እንዳይቆም
ሰውና መላዕክት አብሮ እንዲያዜም
በልባችን መቅደስ ነግሦ የሚኖረው
ለነፍሳችን ዋጋ ካሳ የከፈለው
የድንግል ማርም ልጅ አልፋና ኦሜጋ
ያንጨለማ አጥፍቶ ለኛ ሲል አነጋ
ፍቅር አገብሮት ሞቷል በትህትና
ያመናችሁ ሁሉ ቁሙ በምስጋና
ከምንነግረው በላይ ከተወራለት
ቃላት አይገልጸውም የእርሱን ጌትነት

649. ሆሣእና በአርያም ሆሣእና

ሆሣእና ብለን እናቅርብ ምስጋና

ሆሣእና በሉ ሆሣእና

ለወልደ አምላክ ሆሣእና

ትጎትናን ላሳየን ››

ስሙ ይባረክ ››

ሆሣእና በሉ ››
ለሰማይ ንጉሥ ››
ግርማን ለብሶ መጣ ››
እኛን ሊቀድስ ››
ሆሣእና በሉ ሆሣእና

ለወልደ ዳዊት ››

ነቢያት በትንቢት ››

የተናገሩለት ››

ሐዋርያት በወንጌል ››

የሰበኩለት ››

ሆሣእና በሉ ››
ለአምላክ ምሕረት ››
ተወልዶ ከድንግል ››
እንደ ሕጻናት ››
እረኞች በዋሻ ››
የሰገዱለት ››
የአዳም ልጆች ሁሉ ››
ደግሞም መላእክት ››

መዝሙር በእንተ ስቅለቱ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ

650. በጌቴ ሴማኒ

በጌቴ ሴማኒ በአትክልቱ ቦታ /፪/

ለእኛ ሲል ጌታችን በዓለም ተንገላታ /፪/

አዳምና ሔዋን ባጠፉት ጥፋት /፪/

በእኛ ላይ ደረሰ የዘለዓለም ሞት /፪/

መስቀል ተሸክሞ ሲወጣ ተራራ /፪/

ይገርፉት ነበረ ሁሉም በየተራ /፪/

ተጠማዉ /፫/ ሲላቸዉ /፪/

ቆምጣጤ አመጡለት በሃሞት ቀላቅለዉ /፪/

ድንግል አልቻለችም ዕንባዋን ልትገታ /፪/

እያየች በመስቀል ልጇ ሲንገላታ /፪/

በአምላክነቱ ሳይፈርድባቸዉ /፪/

እንዲ ሲል ጸለየ አባት ሆይ ማራቸዉ /፪/

በረቂቅ ሥልጣኑ ሁሉን የፈጠረ /፪/

በሰዎች ተገርፎ ሞተ ተቀበረ /፪/

651. የአብርሃም አምላክ

የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም ቤዛ /፪/

ወገኖቹን ሁሉ በራሱ ደም ገዛ /፪/

የሐሰት ምስክር አቁመዉ ከሰሱት /፪/

በሞት እንዲቀጣ ሁሉም ፈረዱበት /፪/

ጲላጦስ ገረፈዉ በሰንሰለት አስሮ /፪/

ከሮማዊዉ መንግስት እንዲኖር ተፋቅሮ /፪/

ድንግል አልቻለችም እንባዋን ልትገታ /፪/

እያየች በመስቀል ልጇ ሲንገላታ /፪/

በብርሃን ዙፋን የቆሙት እግሮቹ /፪/

በችንካር ላይ ቆሙ ምንም ሳይሰለቹ /፪/

የብርሃን አክሊል ለሰማዕት ያደለ /፪/

የሾህ አክሊል ደፍቶ ቀራንዮ ዋለ /፪/

652. መስክሪ ቀራንዮ 1

መስክሪ ቀራንዮ መስክሪ ጎልጎታ

›› ›› ›› ሊቶስጥራ

የተቀበለዉን የአምላክ መከራ /፪/

ሊሰቅሉት ሊወስዱት መስቀል አሸክመዉ

ስምዖን ቀሬናዊ ከመንገድ አገኘዉ /፪/

ከድካሙ ብዛት ሳይሰቅሉት እንዳይሞት

ለቀሬናዉ ሰዉ ስምዖን መስቀል አሸከሙት

የአምልክን ትዕግስት በማየት ተደንቆ
ጲላጦስ ጠየቀዉ እንዲፈታዉ አዉቆ /፪/
ጌታም መለሰለት ከላይ ካልተሰጠህ
በእኔ ላይ ልትፈርድ አንዳች ኃይል የለህም /፪/

ስቀለዉ እያሉ ባንድ ላይ ሲጮሁ

ጲላጦስ ጨነቀዉ የሚያደርገዉ ጠፋዉ

ከደሙ ንጽህ ነኝ በማለት ታጠበ

የጌታን ንግግር ቃሉንም አሰበ /፪/

መከራ መስቀልህ ሲነገር ይጨንቃል
ነፍስም ትርዳለች ስጋም ይዳከማል
ድካምህን ሁሉ ከንቱ እንዳላደርገዉ
በንሥሐ እንባ ኃጢያቴን እጠበዉ

653. መስክሪ ቀራኒዮ 2

መስክሪ ቀራኒዮ መስክሪ ጎልጎታ

ካሳ እንደሆነልን እንዳዳነን ጌታ /፪/

በአምላክነቱ ፈጥሮ ዓለማትን

ሥጋን መዋሐዱን ሰዎችን ለማዳን

ክብሩን ዝቅ አድርጎ በታላቅ ትሕትና

ለፍርድ ሲወስዱት ሊቀበል መከራ

መስቀል ተሸክሞ ሲወጣ ተራራ

አይሁድ በየተራ ሲገርፉት ሲያዳፉት

እንዲታገላቸዉ በፍጹም ቸርነት

ምንም ሳያጠፋ በደል ሳይኖርበት

በመስቀል እንዲሞት ቅጣት ተፈርዶበት

ወደኃላ ታስሮ ተገርፎ ተመቶ

ያየዉን መከራ የእሾህ አክሊል ደፍቶ

የሞቱ ሙታንን ከመቃብር ጠርቶ

በራሱ ዉርደት ክብሩን ለሰዉ ልጆች ሰጥቶ

በህይወት እንድንኖር ዳግም እንዳንሞት

ትንሳኤን መስበኩን በከበረች ሰንበት

654. አዘነች

አዘነች /፪/ እናቱም ጨነቃት

እያየችዉ ልጇን በመስቀል ላይ ሰቅለዉት

እዩት ተመልከቱት የአምላክን ስራ

በመስቀል ላይ ሆኖ ለዓለም ሲያበራ

አይሁድ ወንበዴዎች ይዘዉ አሰቃዩት

የእሾህ አክሊል ሰርተዉ በላዩ ደፉበት

የድንግልን ሐዘን እፅዋት አይተዉ

ያለቅሱ ጀመረ ከመሬት ተደፍተዉ

መች እነሱ ብቻ ፀሐይም ጨለመች

የጌታዬን እርቃን እኔ አላይም አለች

የሰማይ ከዋክበት የአምላክን ሞት አይተው

ወየዉ /፪/ አሉ ከመሬት ተደፍተዉ

በይበል ጨረቃ እርር ክስል አለች

ይህንን ስትሰማ መልኳን አጠቆረች

ምድርም አዝና ነበር በጣም ተቸግራ

ሲገርፉት እያየች ጀርባዉን በወይራ

ወየዉ መጨከኑ የሰዉ ልጅ ተፈጥሮ

ጲላጦስ ገረፈዉ በሰንሰለት አስሮ

ማርና ወተትን የሚመግብ ጌታ

አጥቶ ተቸገረ የዉኃ ጠብታ

ያን ሁሉ በትዕግስት ችሎ አሳለፈና

ይመግበን ጀመር ሰማያዊ መና

655. ኪርያላይሶን

ኪርያላይሶን /፫/

በሰማይ በምድር ሥልጣኑ ያለህ ኪርያላሶን

በፍርድ አደባባይ አንተን አቆሙህ

እኛን አድን ብለህ ምራቅ ተፉብህ

በአክሊል እሾህ ላይ በመቃ መቱህ

የተንኮልን ነገር አንዳች በያጡብህ
ይህስ ይሳደባል ብለዉ ከሰሱህ
እሳተ መለኮት ዓለምን የፈጠርክ
ስጋን በመልበስህ በሰይፍ ተመታህ

በእኛ አመፅ ግርፋት የተገረፍክልን ኪርያላይሶን

በሽንገላ እንዳንቀርብ የተሰቀልክልን

ኤሎሄ /፪/ የሲቃ ድምፅ

ዛሬም ይሰማናል ይህ ጥሪ ቃልህ

ስቃይህን አስታዉሰን እናነባለን ኪርያላይሶን
የምህረት እጆችህ እንዲዳብሱን
ስለ እኛ መከራ ስለተቀበልህ
አሁንም ደግፈን እንዳንጠፋብህ
በእጆችህ ቀድሰህ እንዳልሰጠሀቸዉ

እስቲ በእሳት እጅህ ተከላከላቸዉ

አንተ በባህሪህ ሁሉን ቻይ ሆነህ

በመስቀል ቸንክረዉ ቀራንዮ አዋሉህ

656. ጌታ ሆይ

ጌታ ሆይ አይሁድ አማጽያን ሰቀሉህ ሆይ

የዓለም መድኃኒት የዓለም ሲሳይ ሰቀሉህ ወይ /፪/

የአዳም በደል አደረሰህ አንተን ለመሰቀል

የሐዋን ስህተት አበቃህ ለሞት ቸሩ አባት /፪/

ንጹህ ክርስቶስ ሆነህ ወንጀለኛ

ብለህ ስለእኛ መስቀል አሸክመዉ

አስረዉ ገረፉህ እያዳፉህ /፪/

እጅና እግርህን በብረት ተመታህ የዓለም ጌታ

የእሾህ አክሊል ደፍተህ ጎንህን ተወጋህ አልፋና ኦሜጋ

ግብዞች እንደራሳቸዉ መስሏቸዉ
ምራቅ እየተፉ በፊትህ ቀለዱ
አንተን ሊጎዱህ /፪/
በመስቀል ላይ ተጠማዉ ስትል ታላቅ በደል

ሐሞትና ከርቤ ሰጡህ ቀላቅለዉ ጠጣ ብለዉ /፪/

ይቅር ባይ ግልፅ በደላችንን ሁሉ ሳታይ

አንተ ይቅር በለን በእኛ ሳትከፋ እንዳንጠፋ

657. በዕፀ መስቀል ላይ

በዕጸ መስቀል ላይ በእዛ አደባባይ /፪/

አምላክ ሆይ ጌታ ሆይ ተንገላታህ ወይ

መከራ አየህ ሆይ

መስቀል አስይዘዉ ኪርያላሶን
ወደ ጎልጎታ ››
ሲገርፉ ሲያዳፉ ››
ስትንገላታ ››
ያንን አቀበት ኪርያላሶን
ያንን ዳገት ››
ጀርባህ ተገርፎ ››
ስትቃትት ››

አንተን እያዩ ኪርያላይሶን
ሴቶች ሲያለቅሱ ››
እናቶች ቀርበዉ ››
ላብህን ዳበሱ ››
መስቀል አስይዘዉ ኪርያላሶን
እንዲያ ሲያዳፉህ ››
የቀሬናዉ ሰዉ ››
ስምዖን አገዘዉ ››

658. ለእኛ ብሎ ተንገላታ

ለእኛ ብሎ ተንገላታ የሁላችን ጌታ

አዳም ቅጠል በልቶ ባመጣዉ በሽታ

አምላክ ዋለ ቀራንዮ ለብሶ ከለሜዳ
አዳም ሕግ አፍርሶ በጎተተዉ ዕዳ /፪/
ለመስቀል ተሰለፈ እየተገረፈ
በዕፅ ሊፈዉሰዉ በዕፅ ላይ አረፈ /፪/
ምንም በደል ሳይኖርበት የዓለም መድኃኒት
ፍዳን ተቀበለ ለሰዉ ልጆች ድኅነት /፪/
በመሬት ላይ ተንገላታ ሩኅሩኅ ጌታ
አዳም ቅጠል በልቶ ባመጣዉ በሽታ /፪/

659. ኦ የማይሞተዉ ሞተ

ኦ የማይሞተዉ ሞተ /፪/

ሄደ ቀራንዮ እየተጎተተ

ወድቆ እየተነሳ እንዲያ እየቃተተ

ሞትን ይሽረዉ ዘንድ የማይሞት ሞተ /፪/

እጅና እግሩን ታስሮ ሄደ አደባባይ
እየተገረፈ ታግሶ ስቃይ
አለቀሰች ቆማ ድንግል ማርያም
ተሰቅሎባት ልጇ መድኃኔዓለም

በአይሁድ አደባባይ ፍርድ ተንጋደደ

ወንበዴ ተለቆ ንጽሕ ሰዉ ታረደ

የማይሞተዉ ሞተ ለሰዉ ፍቅር ብሎ

ዋለ ቀራኒዮ በእንጨት ላይ ተሰቅሎ

ዮሴፍ ኒቆዲሞስ ሥጋዉን ለመኑ
እንዲፈቅዱላቸዉ ሄደዉ መቃብር
ገንዘዉ ቀበሩት በአዲስ መቃብር
ቅዱስ ቅዱስ ኃይል በክብር

660. በትዕግስቱ ብዛት

በትዕግስቱ ብዛት ባይገለጥ ኃይሉ

ስቀለዉ ስቀለዉ አይሁድ ተባባሉ /፪/

የኃያላን አምላክ አልፋና ኦሜጋ
እንደ እኛ ታመመ በለበሰዉ ሥጋ
ህብስት አበርክቶ የሚመግብ ጌታ
ታስሮ ተገረፈ እንደ ክፉ ሽፍታ

እጅና እግሮቹ ታስሮ ብታይ

ድንግል አለቀሰች አለች ዋይ ዋይ

የሚንቀጠቀጡለት መላእክት በፊቱ

እንደምን በችንካር ተወጋ ደረቱ

የንፁሐን አምላክ ወንጀለኛ ተብሎ
ዋለ ቀራንዮ አርቃኑን ተሰቅሎ
በደል ሳናርበት ተሰቀለልን
ሞታችንን ሞቶ ህይወትን ሰጠን

አምላክ ለኛ ብሎ

አምላክ ለኛ ብሎ ቢያፈሰዉ ደሙን

ፀሐይ ከለከለች ደማቅ ብርሃኗን

መስቀል ላይ ዋለ በኢየሩሳሌም
እዩት ተመልከቱት መስቀሉ ማማሩ
ለተመራመረዉ ብዙ ነዉ ምሥጢሩ
ቢገርፉት ቢሰቅሉት ቢያላግጡበት
ምንም አላገኙም በእርሱ ላይ ስህተት

ፈጣሪ መሆኑ ምሥጢሩ ገብቷት
ጌታን አልይዝ አለች ግዑዟ መሬት
ይህ ታላቅ ንጉሥ ሲገለጥ በሰማይ
የናቁት ሁሉ ይሉታል ዋይ ዋይ
ምድርና ሰማይ ከፊቱ ሲሸሹ
የት ልግባ ይላል ትልቁ ትንሹ
ወደላይ ያረገው የከበረው ሥጋ
ዳግመኛ ይመጣል ሁላችን አንዘንጋ

661. ተሰቀልክ ሆይ

ኦ ጌታ ሆይ ተሰቀልክ ወይ /፪/

ምድር አለቀሰች እያለች ዋይ ዋይ

ኦ ጌታ ሆይ ተሰቀልክ ወይ

ኮረብቶች ደንግጠዉ መድረሻ ጠፍቷቸዉ

ክዋክብትም ፈርተዉ ጨለማ ዋጣቸዉ

እጅግ አይደንቅም ወይ ጌታ መሰቀሉ

የጌቶቹ ጌታ ችንካር ላይ መዋሉ

ሰማይና ምድር በተፈጠረበት
ጨለማና ብርሃን ባደረገበት
ችንካር ተከሉበት መትተዉ በብረት /፪/

ድንግል አለቀሰች ዕንባዋ ፈሰሰ

ስደተኛ ልጇመከራ ቀመሰ

ሕማሙን ሳስበዉ አለቅሳለሁኝ

የስቃዩን ነገር አስባለሁኝ

ዕንባዬን ጠራርጎ ርሃቤን ተካፍሎ
ሞተልኝ ጌታ ስለ ሞቴ ብሎ
እኔ ልሙትልህ ሲለኝ ሰማሁት
እንዲህ የወደደኝ ምን አደረኩለት

662. ከሄሮድስ ወደ ጲላጦስ

ከሄሮድስ ወደ ጲላጦስ /፪/

ተንገላታህ ላብህ እስኪፈስ

አመላለሱህ አስረዉ ገረፋህ

ፊትህን ሸፍነዉ በቦትር መቱህ

እንደ ተራ ሰዉ እንደ ቀጣፊ
እጅህን አስረዉ መቱህ በጥፊ

ከመሳፍንቱ ከመኳንንቱ

አደባባይ ዋልክ ደርሶ ትንቢቱ

መስፍኑ ቆሞ ምን ላድርገዉ ቢል
ሁሉም በጩኸት እሉት ይሰቀል

ሁሉም ከሰሱት ሁሉም ጮኹበት

የነገሥታ ንጉሥ ተፈረደበት

663. ዓለምን ለማዳን

ዓለምን ለማዳን የተሰቀለው
ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው
ጌታችን ተሰቅሎ ቢያዩት መላዕክት
በዝማሬ ፈንታ አለቀሱለት
ሚካኤል ዝም አለ ገብርኤል ገረመው
አምላክን እርቃኑን ተሰቅሎስ ስላየው /፪/
ነፍሱን ለወዳጁ የሚሰጥ ቢኖርም
ለጠላቱ የሚሞት በጭራሽ አይኖርም
ጠላቶቹ ስንሆን ለኛ የሞተው
ክርስቶስ ልዩ ነው ወደር የሌለው /፪/
እውርን ቢያበራ የሞተን ቢያነሳ
በመመስገን ፈንታ ሆነበት አበሳ
ሰማያዊው ዳኛ ሊፈረድበት
ተከሶ ቀረበ በጲላጦስ ፊት /፪/
የጸሎተ ሐሙስ ለት እራት የሆነው
አርብ በመስቀል ላይ የተሰቀለው
ፍቅር አስገድዶት ለኛ የሞተው
መልካሙ እረኛችን አማኑኤል/መድኃኔዓለም ነው /፪/

664. በሞት ጥላ ወድቀን

በሞት ጥላ ወድቀን ስንንከራተት /፪/
በረቀቀው ፍቅር ዋጀን ከጥፋት /፪/
በጎልጎታ የታየው ግሩም መድኃኒት
ሃሌ ሃሌ ሉያ ላንተ ለኃያሉ ጌታ /፪/
ስለኛ ተዋረድክ በጎልጎታ
የሞት ሽክም ከብዶን በጣር ስንባዝን /፪/
ወረደ ከሰማይ መጣ ሊያድነን /፪/
ከባርነት ቀንበር ነጻ ሊያወጣን
ምንም ባልበደለ ምንም ባላጠፋው /፪/
ሁሉን ማድረግ ሲችል ደካማ የሆነው /፪/
ሕይወትን ሊያድለን ስለወደደ ነው
እስቲ አስተውሉ የፍቅሩን ብዛት /፪/
ለመስቀል ሞት ታዝዞ እኛን ያዳነበት /፪/
ምንም አቻ የለው የጌታ ቸርነት
ክብርና ምስጋና አቀርባለሁኝ /፪/

665. አልፋና ኦሜጋ

አልፋና ኦሜጋ ፈጣሪ የሆንክ
በከሐዲዎች እጅ ተይዘህ ቀረብክ
ተገፋህ ተደፋህ በጥፊ ተመታህ
እየደበደቡህ ክርስቶስ ሆይ አሉህ
ጽድቅን ስለሰራህ በወንጀል ከሰሱህ
ለአዳም ቤዛ ብለህ ብዙ ተንገላታህ
ቅዱሳን እጆችህ የፊጥኝ ታስረው
እንደበግ ተጎተትህ ልትምራቸው
የትም ቦታ አለህ ሁሉን የምታውቅ
ፊትህን ሸፈኑህ ለመመጻደቅ
በዚያ አደባባይ በጲላጦስ ዘንድ
አሳልፈው ሰጡህ አጋልጠው ለፍርድ
ከሃና ቀያፋ ከካህናቱ ደጅ
ከነሔሮድስ ዘንድ አቀረቡህ በአዋጅ
ግርፋት ሕማሙ አልበቃ ብሎህ
በመስቀል ላይ ልትውል ተፈረደብሕ
ሳዶርና አላዶር ዳናትና አዬራ
ተፈልገው መጡ ለችንካር በተራ

666. እውነት ስለሆነ

እውነት ስለሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ
ዋለ በአደባባይ ሲሰደብ ሲከሰስ
የሐሰት ዳኝነት አምላክን ወቀሰው
ሕይወት ሰጠን እንጂ ጥፋቱ ምንድነው /፪/
ከቃሉ እብለትን ባያገኙበትም
ዝምታውን አይተው አላዘኑለትም
ባላወቁት መጠን ጠሉት ካለበደል
ጥፋቱ ምን ይሆን የሚያደርስ ከመስቀል /፪/
የልቡን ትህትና ፍቅሩን ሳያስተውሉት
ቸሩ ጌታችንን አቻኩለው ሰቀሉት
ሩሕሩሁን ጌታ አቻኩለው ገደሉት
ሞትን አስወግዶ ቢሰጣቸው ሕይወት /፪/
ስለ ቸርነቱ መራራ አሰጎነጩት
ስለርህራሔው የሾህ አክሊል ሰጡት
ሐሞትና ከርቤ ሆምጣጤ ደባልቀው
መራራ አሰጎነጩት ጨክኖ ልባቸው /፪/
ፈውስን ለሰጣቸው ልባቸውን ሞልተው
አሉት ወንበዴ ነው ስቀለው ስቀለው
ከእጁ በረከትን የተሸሙ ሁሉ
ይጮሁ ነበረ ይገደል እያሉ /፪/

667. ድንግል የዚያን ጊዜ

ድንግል የዚያን ጊዜ /፪/ ሐዘንሽ በረታ /፪/
በመስቀል ላይ ሆኖ ልጅሽ ሲንገላታ /፪/
የግፍ ግፍ ደርሶበት የዚያን ጊዜ
ተጠማሁ ሲልሽ
ለውሻ ያጠጣሽ በወርቅ ጫማሽ /፪/
ሴቶች ሲያባርሩት የዚያን ጊዜ
ራርቶ ሆድሽ
ለፍጡር በማዘን ውሃ ያጠጣሽ /፪/
ተጠማሁ እያለ የዚያን ጊዜ
ሲናገር ልጅሽ
ታዲያ እንደምን ቻለ የእናት አንጀትሽ /፪/
እንደዚያ ስታለቅሽ የዚያን ጊዜ
አልችል ሲል ሆድሽ
እነማን ነበሩ ያስተዛዘኑሽ /፪/
ስታለቅሽ በማየት የዚያን ጊዜ
ራርቶ ልጅሽ
ዮሐንስን አጽናኝ እንደ ልጅ ሰጠሽ /፪/

668. ምድረ ቀራንዮ

ምድረ ቀራንዮ ምድረ ጎልጎታ /፪/
መድኃኒት ክርስቶስ ባንቺ ተንገላታ /፪/
መስክረ አንቺ ምድር ግዑዚታ ስፍራ /፪/
መድኃኒት ክርስቶስ ያየብሽ መከራ /፪/
ደሙ እንደውሃ ሲወርድ በመስቀሉ ላይ /፪/
በቀራንዮ ቦታ መከራውን ሲያይ /፪/
ፀሐይ ከለከለች ደማቅ ብርሃኗን /፪/
ለመሸፈን ብላ የአምላኳን እርቃን /፪/
በመስቀል ተሰቅሎ ተጠማሁ እያለ /፪/
የእሾህ አክሊል ደፍቶ ቀራንዮ ዋለ /፪/
እጆቹና እግሮቹን በችንካር ተመትተው /፪/
በመስቀል ተሰቅሎ ፍቅሩን ገለጸው /፪/
ቸሩ መድኃኔዓለም እባክህ ማረን /፪/
ደካሞች ነንና እንዳንቀር ጠፍተን /፪/
በቆረስከው ሥጋ ባፈሰስከው ደም /፪/
አቤቱ ተራዳን እስከዘላለም /፪/

669. ሞተህልና ስለኔ

ሞተህልና ስለኔ ምንም ሳይኖርብህ ጥፋት
ተከሰህ ተወቅሰህ በጲላጦስ ፊት
ኢየሱስ አምላክ ምሕረት ሥብሐት ለክ /፪/
ያንተ መንገላታት ሁል ጊዜ ያሳዝነኛል
ሲወራ
በመስቀል ላይ ሆነህ ያየኸው መከራ
ኢየሱስ የሕይወት እንጀራ ስብሐት ለክ
ከልዑል ቦታ ወርደህ ፈጣሪ ፍጡራን አምላክ
በሰው ፊት ተዋርደህ ስለሰው የሞትክ
በመስቀል ላይ ተጠማሁ እያልክ ስብሐት ለክ
መሐሪ ጌታ ሆይ አሁንም እንደ ቸርነትህ
ብዛት
የእኛን በደል ሁሉ ሳትመለከት
አድነን ከዳግመኛ ሞት ስብሐት ለክ

670. አ ዘጥዕመ

አ ዘጥዕመ ሞተ በሥጋ /፫/
ሲጠማ ለኖረው በሲያል በረሃ
ከጎኑ ሊያጠጣው የሕይወትን ውሃ
በክብር ሊመልሰው በኤዶም ሊያኖረው
በመስቀል ተሰቅሎ ሊያድነው ከፍዳ
ከዙፋኑ ወርዶ ለብሶ ከለሜዳ
በሰው እጅ ተመትቶ በችንካር ተወግቶ
ግዕዛንን ሊሰብክ ወደ ሲኦል ወርዶ
ምውቱን ሊያድነው ራሱን አዋርዶ
ሊቀድስ በደሙ ሊያከብር በስሙ

671. ኧኸ በቀራንዮ

ኧኸ በቀራንዮ ኧኸ በፈሰሰው ደምህ /፪/
ኧኸ በክቡር ስምህ አምላክ ሆይ ማረን እባክህ /፪/

672. እፎ ቀሰፍከ

እፎ ቀሰፍከ ካህናት ይሁዳ ወሌዊ /፪/
መድኃኔ ዓለም /፪/ ሕፃን ወአረጋዊ /፪/
ትርጉም፡- ሕፃኑና አረጋዊውም የይሁዳና የሌዊ
ካህናት መድኃኔዓለም ሆይ እንዴት ገረፉህ

673. የእውነት ብርሃን

ብርሃነ የእውነት ብርሃን ጨለማን ያጠፋ
ሞተ ነፍስን የሻረ ክርስቶስ የዓለም ተስፋ
ስለ ሰው ፍቅር ስለ ሰው ልጅ ክብር
ሥጋን ለብሶ ሰው ሆነ ከአዳም ልጅ ዘር
ምን ዕፀብ ድንቅ ነው ላሰበው
ምን ግሩም ድንቅ ነው የፈጣሪ ሥራው

674. አምላክ ሆይ ልትሆን

አምላክ ሆይ ልትሆን ቤዛ ለሠው ልጅ
መከራን ተቀበልክ በግፈኞች እጅ
የአይሁድ ማኅበር በአንተ ላይ መከሩ
በሞት ሊያስቀጡህ ሁሉም ተባበሩ
በሐሰት ወንጅለው ሸንጎቸው አቆሙህ
በግፍ ዱላ መትተው ምራቅን ተፉብህ
ከገዢው ፊት ቀርበው ሕዝቡን አባበሉ
በርባንን አስፈቱ አንተን ሊያሰቅሉ
አሳልፎ ሰጠህ ጲላጦስ ፈትኖ

ገርፈው እንዲሰቅሉህ ጽድቅህ በደል ሆኖ

በአምስቱ ቅንዋት ቸንክረው በመስቀል

ቀራንዮ አዋሉህ በሽፍቶች መካከል

ውሃ ብትለምን የውሆች ባለቤት

ሀሞትን አጠጡህ የግፋቸው ብዛት

ያንን ሁሉ መከራ በትዕግስት ፈፅመህ

ነፍስህን ከሥጋህ በፈቃድህ ለየህ

የትግስትህን ብዛት መላእክት አደነቁ

ለሰው ልጅ ያለህን ፍቅርህን አወቁ

675. ለቤተክርስቲያን ብለህ

ዘበእንቲአሃ ለቤተክርስቲያን ተጸፋእከ በውስተ ዓውድ

ከመ ትቀድሳ በደምከ ክቡር

ዘበእንቲአሃ ዝግሃታተ መዋቅሕት ፆረ ወተአገሠ ምራቀ

ርኵሰ እንዘ አልቦ ዘአበሰ አምላክ ዲበ ዕፀ መስቀል ተሰቅለ

ለቤተ ክርስቲያን ብለህ ልትቀድሳት በደምህ

በአደባባይ በጥፊ ተመታህ

ንጹሕ ክርስቶስ በአዳም ጥፋት ልትወቀስ

በከንቱ ልትከሰስ አመላለሱህ

ከጲላጦስ ወደ ሄሮድስ

ሁሉን ቻይ ሳለህ ምንም ማድረግ ሳይሳንህ

በአይሁድ እጅ ተገረፍክ

ወዮ ወሰን የሌላት ትዕግሥትህ

ስለ እኛ ብለህ መከራን ተቀበልክ

ምንም በደል ሳይኖርብህ

አምላክ በእንጨት መስቀል ላይ ሰቀሉህ

676. ሙታንን ያድን ዘንድ

ሙታንን ያድን ዘንድ የሞት ሞትን ሽሮ /፪/

ወልደ አምላክ ሄደ ወደ ኂላ ታሥሮ /፪/

ግርማን ለኪሩቤል ያጎናጸፋቸው

ዘውድን ለሱራፌል የሚያቀዳጃቸው

ከለሜዳ ለብሶ ዋለ ከፊታቸው

ቅዱሳን እጆቹ አዳምን የሠሩት

ቅዱሳን እግሮቹ በገነት የዞሩት

ተቸንክረው ዋሉ በጠንካራ ብረት

ምን በበደለ ነው ምን ባደረገ ነው /፪/

ወልድ እንደ ቀማኛ ሲገረፍ የዋለው

አዳም በበደለ የግፍ ግፍ በሠራ

ቸሩ ወልደ አምላክ ዋለ በመከራ

ሁሉንም ታገሰ ሁሉን ቻለ ሆድህ

ትልቁም ትንሹም ሲዘበባትብህ

677. ሰቀሉ ምስሌሁ

ሰቀሉ ምስሌሁ ክልኤተ ፈያተ /፪/ በየማኑ

ወበፀጋሙ /፪/

ወበማዕከሌሙ /፪/ ኢየሱስ /፪/

ወበማዕከሌሙ ኢየሱስ /፪/

ትርጉም፡- ከኢየሱስ ጋራ አንዱን በቀኙ አንዱን

በግራው አድርገው ሁለት ሽፍቶችን ሰቀሉ

678. ዘአልበስም

ዘአልበስም አይሁድ ከለሜዳ ዘለይ /፪/

እኘ ከለሜዳ ዘለይ /፪/ ከለሜዳ /፪/

ትርጉም፡- አይሁድ ጌታችንን ቀይ ግምጃ አለበሱት

679. እፎ ሰቀሉከ

እፎ ሰቀሉከ ካህናት ይሁዳ ወሌዊ /፪/

መድኃኔዓለም ናዝራዊ /፬/

መድኃኔዓለም ናዝራዊ /፪/ መድኃኔዓለም ናዝራዊ

ትርጉም፡- ናዝራዊ መድኃኔዓለም ሆይ

የይሁዳና የሌዊ ካህናት እንዴት ሰቀሉህ

680. ሞተ ስለእኛ

ሞተ ስለእኛ
የነገሥታት ንጉሥ የኃያላን ዳኛ
ሞተ ስለኛ /፪/
ጕለጕታ እስኪደርስ ስቃይ ተቀበለ
ሥጋው ተዳከመ በመከራ ዛለ
በጅራፍ ተገርፎ ደም ነጠበ ገላው
ሞተ ስለኛ /፪/
ሚካኤል ዝም አለ ተገርሞ አስተዋለ
ገብርኤል ሰይፉን ወደ ምድር ጣለ
ከዋክብት ደንግጠው ረገፉ ዛሬ
መላእክት አለቀሱ ቀረና ዝማሬ
ሞተ ስለኛ /፪/
ዑራኤል አምላኩን በመሰቀል ላይ አየ
በብርሃን ጽዋ ደሙን ተቀበለ
ዕንባው አላቆመም ጌታው ሲንገላታ
ተገርሞ አስተዋለ በጥፊ ሲመታ
ሞተ ስለኛ /፪/

መዝሙር በእንተ ትንሳኤሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ

681. ምድር ጸዳች

ምድር ጸዳች ሐሴት አደረገች
ምድር ጸደች ከእድፍም ነጻች
በክርስቶስ ደም በእውነት ታጠበች /፪/
ሴቶች ትንሳዔውን ሲያወሩ በደስታ /፪/
ጮሃ ስትመሰክር ምድር አፉዋን ከፍታ /፪/
የተዘጋው ዓለም ሲገለባበጥ /፪/
ምን ተማከሩ አይሁድ ከፍርድ ለማምለጥ /፪/
አያልቅባቸዉም የእርነሱ ፈሊጥ /፪/
መግነዙ ተገኘ ከመቃብር ወድቆ /፪/
ምልክት እንዲሆን ተወላቸዉ አዉቆ /፪/

እሁድ በማለዳ መቃብሩን ሲያዩ
ሁሉም ተለዉጦ ልቅሶዉ ደስታ ሆነ /፪/
ሁለቱ መላእክት ብርሃን የለበሱ /፪/
ተነስቷል አሏቸዉ ሴቶቹ ሲደርሱ /፪/
ሐዋርያት ሰምተዉ ዜና ትንሳኤዉን
አሏቸዉ በድንገት ሰላም ለእናተ ይሁን /፪/

682. ሞትን ድል አድርጎ

ሞትን ድል አድርጎ ተነሳ ክርስቶስ ተነሳ እሰይ /፪/
እኛንም ከሞት ሊያስነሳ /፪/
ክርስቶስ ከሙታን ተነሳ
ሰላም ሰላም ለሰዉ ልጆች በምድር ሆነ ሰላም
ነፋሳትን ነጻ አወጣ ከጨለማ ጓሮ እሰይ /፪/
የሲኦልን በር ሰብሮ
ኃይሉንም በኃይሉ ሽሮ
ሞት በትንሳኤ ተሻረ የሰዉ ልጅ ከበረ እሰይ /፪/
ጠላት ዲያቢሎስ አፈረ
እጅና እግሩንም ታሰረ
እንዳይኖር ለዘለዓለም ሞት በአዳም ላይ ነግሶ እሰይ /፪/
ክርስቶስ ተነሳ ሞትን ደምስሶ
ግርማ መለኮቱን ለብሶ

683. ኃይለ ጽልመት ተሰደ

ኃይለ ጽልመት ተሰደ /፬/
በሰንበት ኃይለ ጽልመት ተሰደ /፬/
በሰንበት ሕይወት ተሰርዐ /፬/
በሰማያት ተስፋ ሕይወት ተሰርዐ /፬/

684. ተገርፎ ተሰቅሎ

ተገርፎ ተሰቅሎ የሞተው አንበሳ
ተገንዞ በጨርቅ ተቀብሮ እንደራሳ
በሞት እጅ ተይዞ አልቀረም ተነሳ /፪/
አናምናለን ትንሣኤህን

በሥልጣንህ መነሣትህን

አርአያ ነውና እንዲቀር

ሄሮድስ ፈልጎ ተቀብሮ እንዲቀር

በመቃብሩ ዙሪያ ጭፍሮቹንም ቢያሰፍር

ምድር አልቻለችም ትንሣኤን ልታስቀር /፪/

ክርስቶስ ስትነሣ ከህቱም መቃብሩ

ሴቶች ትንሣኤህን ደፍረው ተናገሩ

እንሞታልን ብለው ማንንም ሳይፈሩ /፪/

እንግዲህ አልፈራም ሞትና ኩነኔ

አምላክ ከሞተልኝ ተሰቅሎ ስለእኔ

ተደምስሶአልና የሞት ሥልጣኔ /፪/

685. ዮም ፍስሐ ኮነ /ሃሌ ሉያ/

ዮም ፍስሐ ኮነ በሰንበት ክርስቲያን እስመ ተንሥአ

ክርስቶስ እሙታን ቀደሳ ወአክበራ እምኵሎን መዋዕል

አልዐላ አማን ተንሥአ እምነ ሙታን

ዮም ፍስሐ ኮነ በሰንበት ክርስቲያን እስመ ተንሥአ

ክርስቶስ እሙታን

ቀደሳ ወአክበራ /፪/ እምኵሎን መዋዕለ

ዛሬ ደስታ ሆነ በሰንበት ክርስቲያን ተነሥቷልና ክርስቶስ ከሙታን

ቀደሳት አከበራት /፪/ ከፍም አደረጋት ከሁሉም ዕለታት

ትርጉም፦ ዛሬ በክርስቲያን ሰንበት ደስታ ሆነ ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቷልና ቀደሳት አከበራት ከፍ ከፍ አደረጋት ከሁሉም ዕለታት

686. ትንሳኤከ

ትንሳኤከ ለዕለ አመነ
ብርሃነከ ፈኑ ዲቤነ /፪/
ትንሳኤን ለምናምን ለኛ
ብርሃንን ላክልን ወደኛ /፪/

687. አማን በአማን

አማን በአማን /፪/
ተንስአ እምነ ሙታን /፪/

688. ተነስቷል

ተነስቷል ጌታ ተነስቷል /፪/
ከሙታን መሀል የለም ክርስቶስ ተነስቷል /፪/

በመቃብር ተኛ ተነስቷል
ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት ››
ሞትን አሸንፎ ››
የዓለም መድኃኒት ››
ግርማን ተጎናጽፎ ››
ይኸው ተነሳልን ››

ተነስቷል ሞትን አሸንፎ መውጊያውን ሰባብሮ
ተነስቷል ክርስቶስ ጠላትን መዝብሮ

በሞት ያሸለበው ተነስቷል
ትሑት ባለፀጋ ››
የትንሳኤው በኩር ››
አልፋና ዖሜጋ ››
ግርማን ተጎናጽፎ ››
እሁድ በማለዳ ››

ተነስቷል ማሕተሙም ተፈታ ድጋዩም ደቀቀ
ሲኦልም ተሸረ ዲያብሎስ ወደቀ

ሞትና መውጊያውን ተነስቷል
ከጥልቁ ታጣልልን ››
የልባችን መብራት ››
ይብራ ለአምላካችን ››
ወተንስአ እንበል ››
ሲያል ተሻረልን ››

ተነስቷል የመከራን ቀንበር ከኛ አርቆልናል
የሞት ኃይልን ሰብሮ ጌታችን ተነስቷል

689. ሕያውን ከሙታን

ሕያውን ከሙታን መካከል ለምን ፈለጋችሁ
እንደተናገረው በመቃብር የለም ተነስቷል ጌታችሁ

የለም በመቃብር አትፈልጉት
ዮሐንስ ጴጥሮስ አትሩጡ ላታገኙት
ውጡ መከቃብር ጣሉና በፍታውን
<u>ሂዱ አውጁ ለዓለም ትንሳኤውን</u> /፪/

ሉቃስ ቀለዮጳ ተስፋችሁ ይመለስ
መቃብር ያደረው በትንሳኤ ክብር ሲነግስ
ወደ ኢየሩሳሌም ዳግም ተመለሱ
<u>ሞትን አሸንፏል የተቤዠን ያ ንጉሡ /፪/</u>

<u>መግደላዊት ማርያም አትዘኚ</u>
<u>ሽቱውን ቀብተሽ መሻትሽን ባታገኚ</u>
<u>እንደተናገው ተነስቷል ከሙታን</u>
<u>መግነዝ ፍቱ ሳይል ሞትን ድል አድርጓል</u>
/፪/

690. ወምድረኒ

ወምድረኒ ትገብር ፋሲካ
ተሀሚባ በደመ ክርስቶስ /፪/
ምድር ጸዳች ሐሴት አረገች
በክርስቶስ ደም በእውነት ታጠበች /፪/

691. ክርስቶስ ተንስአ

ክርስቶስ ተንስአ እሙታን
በአቢይ ኃይል ወስልጣን
አሰሮ ለሰይጣን ወአግአዞ ለአዳም
ሰላም /፪/ አምይእዜሰ ይኩን ሰላም
ክርስቶስ ተነሳ ከሙታን
በታላቅ ኃይልና ስልጣን
ሰይጣንን አሰረው አዳምንም ነፃ አወጣው
ሰላም /፪/ ከእንግዲህስ ይሁን ሰላም

692. እዩና እመኑ

እዩና እመኑ ሰዎች
ድንጋዩ ተፈነቃቅሏል
ኢየሱስ በእኩለ ሌሊት በኃይሉ
ሞትን ድል ነስቷል /፪/
እልልታ ለዚህ ይገባል
ግርግርታ ለዚህ ይገባል
የሞት ኃይል ተዋርዷል ዛሬ
ሲኦልም ተመሰቃቅሏል
መላዕክቱ ነጩን ለብሰው
ምሥራቹን አበሰሩ
ተነስቷል ኢየሱስ ብለው
ለዓለም እንዲናገሩ

693. እም እቶነ

እም እቶነ እሳት ዘይነድድ አንገፈነ /፪/
ብርሃናተ ዘይትአጸፈ ተንሥአ ለነ /፬/
ትርጉም፡-ከሚነደው እሳት ከነበልባሉ
አወጣን /፪/
ብርሃናትን ተጎናጽፎ ተነሣልን /፬/

694. ጌታ ተነስቷል እልል በሉ

አምላክ ተነሥቶአል የምስራች በሉ
ሙስና መቃበር በኃይሉ አጥፍቶ
ሁላችን አየነው ክርስቶስ ተነሥቶ
አዳምን ለማዳን ቃል ኪዳን ገባለት
ዘመኑን ጠብቆ ካሣ ሊከፍልለት
ከሰማያት ወርዶ የተሰቀለው
ሞትን በሞት ሽሮ ይኸው አየነው
ደቀመዛሙርቱ እጅጉን ተጨንቀው
በጌታችን መሞት በሐዘን ተሞልተው
በተዘጋ ደጃፍ ተሰብስበው ሳለ
እጆቹን ዘርግቶ ሰላም ለእናንተ አለ
ማርያም መግደላዊት እየገሠገሠች
በሌሊት ተነሥታ ወደ አምላኳ
ሄደች
አይሁድ አንገላተው የሰቀሉት
ጌታን
ተነሥቶ አግኝታ ተመላች በደስታ

695. ብርሃን ወጣ

ብርሃን ወጣ ከመስቀሉ የሚያንፀባርቅ
የአምላክና የሰው ልጆች እውነተኛ እርቅ
ደስ ይበለን በትንሳኤው ብርሃን
እልል እንበል በአንድነት ሆነን
ተነሳልን መድኃኒታችን
ከፊት ለፊት በመሳሉ መስቀሉ ነገር
ለሚወደው ሐዋርያ የወንጌል መምህር
ዮሐንስም ስቅለቱን በማየቱ
አለቀሰ እስከ ዕለተ ሞቱ
ቢያስቅቀው ሞቱ ግርፋቱ
ሞኝነት ነው ለሚጠፉት መሰናከያቸው
በአለም ጥበብ ለሚኖሩት እውነት ተስኗቸው
ለጠቢብ ሰው በመንፈስ ለሚኖረው
የመዳን ቀን እውነተኛ አርማ ነው
ከገሐነም እሳት የሚያድነው
እስከ መሞት ላልተለየው ቅዱስ ሐዋርያ
ለዮሐንስ የወንጌል ሰው የፍቅር ባለሙያ
ምስጋናችን ከምድር ይድረሰው
እንላለን በሰጠን ምሳሌው
ሰዎች ሁሉ እንከተለው

696. ጌታችን ተነስቷል

ጌታችን ተነስቷል የለም በመቃብር
አየነው ተገልጦ በትንሳኤው ክብር
የምስጋና ማዕበል በሰማይ ተነሳ
ሞትን አሸንፎ ክርስቶስ ሲነሳ /፪/
በዝኁ መቃብርሞታችን ሲረታ
ኒቆዲሞስ የለም መግነዝ የሚፈታ
እንደተናገው ተነስቷል በኃይሉ
አዩት በበርሃን የወጉት በሙሉ
እልል /፪/ እንበል እንዘምር ተነሱ
የከበረ ሽቱ ይዘን ለንጉሡ

አለቀ ሌሊቱ ምድር ተደሰተች
እንደ እንቦሳ ጥጃ ለክብሩ ዘለለች
የሲኦልን ስቃይ በደሙ አቅልጠን
ገባን ከርስታችን በትንሳኤው ከበርን
እንፍጠን ሁላችን ወደ መቃብሩ
ከመላዕክቱ ጋር እንዘምር ለክብሩ
በተዘጋው ደጃፍ ገብቶ ተገለጠ
ሐዋርያት ፈሩ ልባቸው ቀለጠ
ምትሀት አይደለም ዳሱት እስራቱን
ቶማሶች እመኑ አይታችሁ ችንካሩን
የኤማሁስ ሰዎች ተስፋ የቆረጣችሁ
ዳግም ተመለሱ ተነስቷል ጌታችሁ

697. የትንሣኤው ብርሃን

የትንሣኤው ብርሃን <u>የሰው ልጅ ሕይወት</u> /፪/

አዳምን መለሰው ከወጣበት ቤት /፪/

እሰይ የምሥራች ደስ ይበላችሁ
ሞትን ድል አድርጎ ተነሳላችሁ } /፪/

ያ በሙሴ ኦሪት <u>የተነገረው</u> /፪/

ሞትን ዛሬ አጥፍቶ የተነሳው ነው /፪/

ማርያም መግደላዊት <u>ምንኛ ታደልሽ</u>

ከሰው ሁሉ በፊት ትንሣኤን አየሽ /፪/

ብርሃን ያሳየዋል <u>የጽድቅንም ፋና</u> /፪/

ለሚገዛለቱ በእውነቱ ጎዳና /፪/

ስምህን ተናገርኩ <u>ሁሉም ተቀበለ</u> /፪/

ከጥፋት ልጅ በቀር ማንም አልታጎለ /፪/

አምላክ ሆይ <u>ባርከህ ቀድሳቸው</u> /፪/

ከጥፋት ልጅ በቀር ሁሉም የአንተው ናቸው /፪/

አንድ ይሁኑ እነርሱም <u>በሰላም በፍቅር</u> /፪/

እኔም አንድ እንደሆንኩ ከቸሩ አባቴ ጋር/፪/

698. ተስፋ ሕይወት ተሠርዓ

በሰማያት ተሰፋ ሕይወት ተሠርዓ /፬/
ኃይለ ጽልመት ተሠደ /፬/
በሰንበት ኃይለ ጽልመት ተሠደ /፪/

699. ሠርአሊነ ሠንበተ ሠንበተ ለእረፍተ ዚአነ

ሠርዓ ለነ ሰንበተ ሰንበተ ለእረፍተ ዚአነ /፪/
ሠርዓ ለነ ሰንበተ ለእረፍተ ዚአነ /፪/
ሠራልን ሰንበትን ለእረፍት /፪/
ሠራልን ሰንበትን ለእረፍት /፪/

700. ፈኑ ዲቤነ ብርሃነከ

ፈኑ ዲቤነ ብርሃነከ /፬/
ትንሣኤ ትንሣኤከ ለእለ አመነ /፪/
ትርጉም፡- ትንሣኤህን ለምናምን ለእኛ ብርሃንን ላክልን

701. መድኃኒተ ኮነ

መድኃኒተ ኮነ /፬/
ለአሕዛብ መድኃኒተ ኮነ /፬/
ትርጉም፡- ክርስቶስ ለእኛ ለኃጥአን መድኃኒታችን ነው።።

702. እሰይ ተነሣ እሰይ እሰይ ተነሣ

እሰይ ተነሣ እሰይ እሰይ ተነሣ /፪/
ተደመሠሠ በአምላክ የዓለም አበሣ
ክብርና ምስጋና እሠይ እሠይ ተነሣ
ይግባው ፈጣሪያችን እሠይ እሠይ
ሞትን አሸንፎ እሠይ እሠይ
አርዓያ የሆነን እሠይ እሠይ
በክርሰ መቃብር ››
ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት ››
ተቀብሮ አልቀረም ››
ተነስቷል በሰንበት ››
ለሐዋርያቱ ››
የምሥራች ያለች ››
ማርያም መግደላዊት ››
ምንኛ ታደለች ››
ዘበኞች ቢያቆሙ ››
አይሁድ ተሞኝተው ››
አልቻሉም ሊያስቀሩት ››
ሞትን ድል አደረገው ››

703. ክርስቶስ ተነሳ

የህያዋን አምላክ ሙታንን ሊያስነሳ
በእኩለ ሌሊት ክርስቶስ ተነሣ /፪/

ankesebirhan16@gmail.com

ሙታን አይደለንም ክርስቶስ ተነሣ
ሕያዋን ነን እኛ ክርስቶስ ተነሣ
በመስቀሉ የዳንን ››
ከኃጢአት ቁራኛ ››
የተዋረደውን ››
ሊያከብር ዳግመኛ ››
ሞትን አሸንፎ ››
ተነሣልን ለእኛ ››

እናንተስ አትፍሩ ክርስቶስ ተነሣ
እነግራችኋለው ››
የተሠቀለውን ››
እንድትሽ አውቃለው ››
ሕያዉን ከሙታን ››
ለምን ፈለጋችሁ ››
እንደተናገረው ››
ተነሥቷል ጌታችሁ ››

ክርስቶስ ሲነሣ ክርስቶስ ተነሣ
በሰንበት ሌሊት ››
አስቀድሞ ታየ ››
ለመግደላዊት ››
እርሷም ትንሣኤውን ››
ለዓለም አበሠረች ››
ጌታዬን አየሁት ››
ተንስቶአል እያለች ››

704. እልል አማኑኤል ተነሣልን

እልል /፪/ አማኑኤል ተነሣልን
ደስ ይበልን ሁላችንን
የሲኦል ደጆች ተከፈቱ እልል
የሰይጣንም ሠራዊቶች አፈሩ እልል
በጨለማው ዓለም ተወጠን ሳለን
ጌታ በትንሣኤው ዛሬ አበራልን
አዝ ------

መቃብራት ሁሉ ተከፈቱ እልል
የታሠሩ ነፍሳት ከግዞት ተፈቱ
እልል
መግደላዊት ማርያም ትንሣኤውን
አይታ
ነገረች ለሐዋርያት በደስታ
ተሞልታ

ሁለቱ መላእክት ብርሃን የለበሱ እልል
ተነሥቷል አሏቸው ሴቶቹ ሲደርሱ እልል

705. ክርስቶስ ተነሣ

ክርስቶስ ተነሣ ከሙታን
በታላቅ ኃይል በታላቅ ስልጣን /፪/
ሰይጣንን አስሮ /፪/
ነፃ አወጣን አዳምን /፪/

706. እንዘምር ሁላችን

እንዘምር ሁላችን ለቸሩ ፈጣሪ /፪/
በትንሣኤው ኃይሉ ሞትን አሣፋሪ /፬/
እሰይ አገኘነው ሕይወታቸንን /፪/
ደስ ይበለን /፪/
ትጉህ የማይተኛ ጊዜውን አክብሮ /፪/
ነፍሳትን አወጣ ከሲኦል በርብሮ /፪/
አዝ -------
ሞት ሆይ ወዴት አለህ ከቶ ማሸነፍህ /፪/
ኃይልክ ተዋረደ አንተም ድል ተመታህ /፪/
አዝ -----
አረገ በስብሐት አገረ በእልልታ /፪/
ሞትን ድል አድርጎ የሠራዊት ጌታ /፪/
አዝ ------

707. ገበረ ሰላመ በመስቀሉ

ገበረ ሰላመ በመስቀሉ /፪/
ትንሣኤሁ አገሀደ ሰላም ገብረ /፬/

708. ሠላም ሠላም

ሠላም ሠላም /፪/
እምይእዜስ ይኩን ሰላም /፬/

709. እናመስግን በዝማሬ በእልልታ

ጠላት ድያብሎስን በሞቱ የረታ
ከእኛ ጋራ ነውና የሠራዊት ጌታ
ጨለማውን ኑሮ የሰደት ሕይወት
በእግዚአብሔር ፍቅር ብርሃን በራበት
ባርነት ቀርቶ ነጻነት ወጣን
ልመናችንን እግዚአብሔር ሰማን
መሠናክሉን ክፉውን ፈተና
አልፈነው ወጣን በአምላክ ጎዳና
አምላክ ከኛ ጋር ስለነበር
ዲያብሎስ አፍሮ ተዋርዶ ቀረ
የሚያስጨንቅ ዛሬ ተፈታ
የሕዝቡን እንባ አበሰ ጌታ
በምሕረቱ ስለጎበኘን
አምላካችን ኑ እናመስግን

710. ፋሲካ

ፋሲካ /፮/
ተዝካረ ትንሳኤሁ ለመድኃኒነ /፬/

711. ተንሥአ ወአንሥአ ኩሎ ሙታን

ተንሥአ ወአንሥአ ኩሎ ሙታን /፪/
ተንሥአ ወፈትሆሙ ለሙቁሐን

712. አቢያ ዜማ ተሰማ

አቢያ ዜማ ተሰማ /፪/
እንዘ የአርግ ወልድ ዲበ መንበሩ
ሚካኤል ወገብርኤል ትንሣኤሁ ዘመኑ /፪/

መዝሙር በእንተ እርገቱ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ

713. ይቤሎሙ ኢየሱስ

ይቤሎሙ ኢየሱስ ለአርዳኢሁ ኢየሱስ ይቤሎሙ /፪/

ሰማይ አዓርግ ኀበ አቡየ ወአቡክሙ /፪/

ትርጉም፡ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ወደ ሰማይ ወደ አባቴ ወደ አባታችሁ አርጋለሁ አላቸዉ።

714. አምላካችን አረገ

አምላካችን አረገ /፪/ ወደ ሠማያት /፪/
የሠማይ መላእክት በደስታ እያጀቡት አረገ
ወደ ሰማያት /፪/

715. አንትሙሰ ንበሩ

አንትሙሰ ንበሩ አገረ ኢየሩሳሌም
እስክትትለብሱ ኃይለ እም አርያም
እናንተ ግን ቆዩ በኢየሩሳሌም አገር
እስከምታገኙ ኃይልን ከሰማይ

716. የማርምያን ሥጋ

የማርምን ሥጋ ለብሶ ጠላትን አጥፍቶ ደምስሶ /፪/
ወደ ቀድሞክብሩ አረገ ወጣ ተመልሶ

717. ሞያ ለሞት

ሞያ ለሞት እግዚኡ ለአዳሠም

ተንሥአ ወልድ በሣልስት ዕለት /፪/

ፈዪሞ ሥርዓተ አርቲያ

ሃይማኖተ ዐርገ ኀበ አቡሁ /፪/

የአዳም ጌታው ወልድ ሞትን

አሸንፎ በሶስተኛው ዕለት ተነሳ

ሃይማኖትን አቅንቶ ሥርዓትን

ፈጽሞ ዐረገ ወደአባቱ /፪/

718. ይቤሎሙ ኢየሱስ

ይቤሎሙ ኢየሱስ ለአርዳኢሁ ኢየሱስ ይቤሎሙ /፪/

ሰማይ አዓርግ ኀበ አቡየ ወአቡክሙ /፪/

ትርጉም፡- ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ወደ ሰማይ ወደ አባቴ ወደ አባታችሁ አርጋለሁ አላቸው።

719. ንግበር በዓለ

ንግበር በዓለ በትፋሥሕተ ዮም /፪/

እስመ ተንሰአ እግዚእነ እሙታን

/፪/

ዐርገ በስብሐት ውስተ ሰማያት

ዘይሴብሕዎ ሊቃነ መላእክት /፪/

ትርጉም፡- ዛሬ በደስታ በዓልን እናድርግ ጌታችን ከሙታን ተነሥቷልና። የመላእክት አለቆች የሚያመሰግኑት እርሱ በቅዳሴ በክብር ወደሰማያት ዐረገ።

720. አረገ በስብሐት

አረገ በስብሐት አረገ በእልልታ
በስብሐት በእልልታ አረገ /፪/ በእልልታ
ሞትን ድል አድርጎ
የሰራዊት ጌታ አረገ አረገ በእልልታ

721. አማን በአማን

አማን በአማን /፬/
መንክር ስብሐተ እርገቱ /፬/

722. አርገ እግዚእነ

አርገ እግዚእነ /፬/
በይባቤ /፬/ ወበቃለ ቀርን /፪/
ጌታቸን አረገ /፬/
በእልልታ /፬/ በመለከት ድምጽ

723. እየባረካቸው ወደ ላይ አቀና

እየባረካቸው ወደ ላይ አቀና /፪/
መድኃኔዓለም /፪/ አረገ በክብር ደመና /፪/

ተሰብስበው ሳሉ ሁሉም በአንድነት
በመካከል ሆኖ ሥግው መለኮት
ባረካቸው ቀደሳቸው አረገ በዓይን
እየታያቸው
/፪/

እንዲልክላቸው አጽናኙን መንፈስ
ከላይ ከአርያም ከአባቱ ሲደርስ
ኃይል ሆናቸው አጸናቸው /፪/
በቃሉ አንድ አደርጋቸው
በአንድነት ሆነው ኢየሩሳሌም
ተስፋ ሲጠብቁ ከላይ ከአርያም
መንፈስ ቅዱስ በእሳት አምሣል /፪/
ወረደ በምሕረት ወሣህል
መላእክት በሰማይ እልል እልል አሉ
እርገቱን አጅበው ምስጉን ነህ እያሉ
የሰማይ ደጅ ተከፈቱ
ዘመሩ ሊቀመላእክቱ /፪/

መዝሙር በእንተ በዓለ ጰራቅሊጦስ

724. ለዛቲ ቤተ

ለዛቲ ቤተ ሐነፃ ወልድ /፪/

ወፈፀማ መንፈስ ቅዱስ /፪/

ይህችን ቤት ወልድ አነፃት /፪/

መንፈስ ቅዱስም ፈፀማት /፪/

725. መንፈስ ቅዱስ ወረደ

መንፈስ ቅዱስ ወረደ ላዕለ ሐዋርያት
ተመሲሎ /፩/ በነደ እሳት

726. ወረደ መንፈስ ቅዱስ

ወረደ መንፈስ ቅዱስ /፪/
ቤተ ቃና ዘወይን /፪/ ዘወይን ዘወይን ቤተቃና ዘወይን

727. ጸጋ ዘአብ

ጸጋ ዘአብ ሒሩት ዘወልድ ሱታፌ ዘመንፈስ ቅዱስ /፪/ ተውህቦሙ /፫/ ለሐዋርያት /፪/

ትርጉም፡ የአብ ጸጋ የወልድ ቸርነት የመንፈስ ቅዱስ አንድነት /በረከት/ ለሐዋርያት ተሰጣቸው።

728. ኃበ አቡሁ አርገ ሠማያት

ኃበ አቡሁ አርገ ሰማያት አርገ ሰማያት /፪/
ጰራቅሊጦስሃ መንፈሰጽድቅ አውረደ /፬/
ትርጉም፡- ወደ አባቱ አረገ መንፈስ ቅዱስንም ላከልን

ስለ እምነት እና ቤተክርስቲያን

729. ተዋሕዶ

ተዋሕዶ /፪/ ሰማዊት
የቀናች እምነት /፪/ ሃሌሉያ
ተዋሕዶ /፪/ መንፈሳዊት
የመንፈስ መብራት /፪/ ሃሌሉያ
ተዋህዶ /፪/ መለኮታዊት
ንጽሕት እምነት /፪/ ሃሌሉያ
ባንቺ ቢያምኑ /፪/ ሰማዕታት
ተፈተኑ በእሳት /፪/ ሃሌሉያ
ባንቺ ቢያምኑ /፪/ ቅዱሳን
ድል ነሱት ሰይጣንን(ኽ) ሃሌሉያ
እንደ ወርቅ /፪/ ተፈትነው
አበራ ገድላቸው /፪/ ሃሌሉያ
ክርስቲያኖች /፪/ አስተውሉ
መዝኑ አስተውሉ /፪/ ሃሌሉያ
ትኑርልን /፪/ እምነታችን
ተዋሕዶ መክበሪያችን /፪/ ሃሌሉያ

730. ተዋህዶ ሃይማኖቴ

ተዋህዶ ሃይማቴ

የጥንት ነሽ የእናትና አባቴ

ማህተቤን አልበጥስም

ትኖራለች ለዘላለም

የግብፅ ከተሞች በደም ገንብተናል
በመግደል ፅድቅ የለም ሞተን ግን ኖረናል
ማጎተብሸን ፍቺ በጥሺዉ ቢሉኝ
እኔስ ከናንገቴ ዉሰዱት አልኩኝ

ጳዉሎስ ተሰየፈ ጴጥሮስ ተሰቀለ

ተዋህዶ እያለ አረ ስንቱ አለፈ

ሌሎችም በእሳት በስቃይ አልፈዋል

ዘመን የማይሽሸዉ ታሪክን ፅፈዋል

ፊተኛ ነንና እንዳንሆን ኃለኛ
ሕዝቤ ተነሳሳ ተነስ አትተኛ
ጅብ ከሄደ ዉሻ እንዳይሆን ጩኸቱ
የተዋህዶ ልጆች አሁን ነዉ ሰዓቱ

አይተን እንዳላየን ስንት አሳልፈናል

የእርሱ ፈቃድ ይሁን ብለን ዝም ብለናል

አሁን ግን ይበቃል ዝምታዉ ይሰበር

ይገለጥ ይታወጅ የተዋህዶ ክብር

731. ዛቲ ይዕቲ

ዛቲ ይዕቲ ደብረ ገሊላ /፪/
መካነ ክብሮሙ ለቅዱሳን
የሰላም የሕይወት የበረከት አገር
ማርና ወተቱን የምታፈስ ምድር
በአማኑኤል ደሙ ተመስርታ ያለች
የሕይወት ውሃ ምንጭ ቤተ ክርስቲያን ነች
ድምጿን እየሰማን አድገን በጉያዋ
ይዞናል ደግፎ የፀናው ኪዳኗ
አሳድጋናለች ቃሉን አጠጥታ
ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ለልጆቿ ሰጥታ
ቅዳሴዋ ጠርቶን እጣኑን አሽትተን
ወድቀናል መቅደሷ ከዓለም ተለይተን
የክርስቲያኖች ቤት ሽረት የሌለባት
እሷን ተጠግተን ጭንቋን ቀን አለፍናት
ርቀን ከቃሏ በደልን ስንሰራ
ለልችታን አታውቅም ልጆቿን ስትጠራ
የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከቶ የማይለያት
የህያዋን ምድር ቤተክርስቲያን ናት
ቤተ ስብሐቱ የምስጋና ደጃፍ
የሰላም ሰገነት የጻድቃን ምዕራፍ
አበው ስለ ክብርሽ መስዋዕት በመሆን
አምሳለ ገነትን ለመውረስ አበቁን

732. የሰዉ ልጆች ሁላችን እንማር

የሰዉ ልጆች ሁላችን እንማር

አስተባብረን ሃይማኖት ከምግባር

የሰዉ ልጆች ሁላችን እንማር

መልካም ስራን በመስራት እንኑር

የሰይጣን ድል መንሻ የክብር መዉረሻ

ሃይማኖት ናትና እዉነተኛ ጋሻ

ለእዉነተኛ ሥራ ሁላችን እንበርታ

ፃድቃን ሰማዕታትን አድርገን መከታ

ፍዳ ዓለምን አልፈን እንድንሄድ ሁላችን

ጸንተን መገኘት ነዉ በሃይማኖታችን

የሰይጣን ድል መንሻ የክብር መዉረሻ
ሃይማኖት ናትና እዉነተኛ ጋሻ
እምነታችን ሁሉ ይሁን በፈጣሪ

ይቅር ባይ ነዉና ሲቻለዉ መሐሪ

733. በደምህ ዋጅተህ

በደምህ ዋጅተህ ያጸናሀትን
ጠብቅልን ቤተክርስቲያንን /፪/
ጽዮንን ክበቧ ቅጥሮቿንም ዙሩ
ሲል ያመሰገናት ዳዊት በመዝሙሩ /፪/
ወልድ ዋሕድ ብሎ ጴጥሮስ ሲመሰክር
መሠረት ነህ ብለህ ሰጥተኸዋልና ክብር /፪/
የቅዱሳን አገር የአምላክ ማደሪያ
ምዕራገ ፀሎት የኃጢአት ማስተስረያ /፪/

734. የቅዱሳን በአት

ልቦና የሚመስጥ መዓዛ ዕጣኗ
ህሊናን ይገዛል ዝማሬ ድጓዋ
የቅዱሳን በዓት የጸሎት ዋሻቸው
ቤተክርስቲን ናት አንባ መጠጊያቸው
የመላዕክት ዜማ የአዕዋፍ ዝማሬ

የሚለቀምባት የትሩፋት ፍሬ
ይዘምሩባታል በአንድነት ተባብረው
የሌዋዊው በትር ጸናጽል ከበሮው
ወራዳዋን ዓለም የናቋት በቅድሚያ
የእምነት አርበኞች ያገኟት በፍልሚያ
የገድላቸው ተዓምር መንቦግቢያ መቅረዝ
የሰማዕታት አክሊል የስራቸው ደመወዝ
መውደቂያዬ ይሁን ከመቃብራቸው
ይፈውሳልና ተረፈ አጽማቸው
ከኃጥአን ድንኳን መውጣቴ ነው ዛሬ
የቅዱሳን በዓት ልትሆነኝ አገሬ

735. ቅድስት ተዋሕዶ

ቅድስት ተዋህዶ ሕጽሕት እምነት
ክርስቶስ በፍቅር የመሠረታት
ሰማዕታት በደም በሞት ያፀኗት
አንዲት ሃይማኖት ናት እንከተላት
የጴጥሮስ መልዕክት የጳውሎስ ስብከት
አንዲት ጥምቀትና አንዲት ሃይማኖት
የነአትናቴዎስ የሰልስቱ ምዕት
ሐይማኖት አንዲት ናት እንመን በእውነት
የነጎርጎርዮስ የአባ ጊዮርጊስ
የዮሐንስ አፈወርቅ የአባ ሕርያቆስ
የነዲዮስቆሮስ የእምነታቸው ፍሬ
ተዋሕዶ እኮ ናት እናክብራት ዛሬ
በጠባቡ መንገድ በእሷ ላይ እንሂድ
ከመንገዱ ወጥተን ሲኦል እንዳንወርድ
በእምነታችን ጸንተን ምግባርን ወርሰን
በሃይማኖት እንቁም በአንድነት ሆነን
ከአባቶቻችን እኛ አንበልጥምና
ክብርን የወረሱት በፍፁም ትሕትና
አንዲት ሃይማኖት ናት የእምነታችን ፋና
በተዋሕዶ እምነት ሁላችን እንጽና

736. ተዋሕዶ

ተዋህዶ መመኪዬ የዘለዓለም ቤቴ /፪/
ባንቺ ተቀደሰ ሕይወቴና ሞቴ /፪/
ሕይወትሽ ጣዕም አለው ሰፊ ነው ታሪክሽ
ሐዋርያት በደም ጽፈው ያቆዩልሽ
እመካብሻለሁ ሌላ ሀብት የለኝም
ራስሽ ክርስቶስ አያሳፍረኝም /፪/
ነቢዩ በትንቢት እንዳስረዳው ቀድሞ
በመንገድላይ ቁሙ እዩ በአርምሞ
የቀደመችውን መንገዷን ጠይቁ
መልካሟ ጎዳና እሷናት እወቁ
ቅዱስ አትናቴዎስ የተሰደደልሽ
አበው በአደባባይ የመሰከሩልሽ
ከሣቴ ብርሃን ያወጀሽ አዋጅ
የማያናውጽሽ የገሀነም ደጅ
ስላንቺ ልመስክር እየዞርኩኝ በዓለም
እውነት ነው ምሶሶሽ አያሳፍረኝም
ማዕደ ሰፊዋ ጥሪሽ አስተጋባ
አማናዊት መርከብ ሁሉ ወዳንቺ ይግባ

737. ተቀደሲ

ተቀደሲ ወንሥኢ ኃይለ ኦ ቤተ እግዚአብሔር /፪/

እስመ ናሁ ንጉሥኪ በጽሐ እግዚአብሔር /፪/

ትርጉም፡ የእግዚአብሔር ቤት ሆይ ክበሪ ከፍም በይ
ኃይልንም ንሺ። የሚያበራልሽ ንጉሥሽ
እግዚአብሔር እነሆ መጥቷልና

738. ቤተክርስቲን አሐቲ

ቤተክርስቲን አሐቲ አንቀፀ
አድኅኖ ይእቲ /፪/ ደብረ ምህረት /፪/

ትጉህ ባቲ /፪/ ሕዝበ ክርስቲያን እንበለ አጽርያ /፪/

ትርጉም ፡ ቤተክርስም አንዲት ናት። የድኅነት በርም
ናት። የምህረት ተራራ ናት። የክርስቲያን ወገኖች
ያለማቋረጥ ትጉባት (አገልግሉባት)

739. ኦ አንትሙ

ሕዝበ ክርስቲያን

በከመ ተጋባዕክሙ በዛቲ ዕለት

ከማሁ ያስተጋብዕክሙ በደብረ ፂዮን ቅድስት

ወበኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም /፪/ አግዓዚት

ትርጉም፡- እናንት የክርስቲያን ወገኖች ሆይ
በዚች ዕለት እንደተሰበሰባችሁ ቅድስት በምትሆን
በደብረ ፂዮን ነፃ በምታወጣ በኢየሩሳሌም
ይሰብሰባችሁ።

740. ኢትዮጲያ ሆይ

እግዚአብሔርን አስመስግኚ /፪/

ከሕዝብሽ ጋር እልል በይ /፫/

እጆችሽን በበረከት ስለመላ /፪/

ስላዳነሽ በጭንቀት ቀን ከሞት ጥላ /፪/

እግዚአብሔር ብርሃንሽ ስለሆነ /፪/

ካስፈሪ ቀን ልጆችሽን ስላዳነ /፪/

ኢትዮጲያ ሆይ እግዚአብሔርን አመስግኚ /፪/

በሽብሸባ እልል በይ /፫/

በሽብሸባ ለአምላክሽ ዘምሪለት /፪/

ስብራትሽን ይጠግናል በምህረት /፪/

ለሕዝብሽ እግዚአብሔር ኃይላቸዉ ነዉ /፪/

በስቃይ የጎበኘ መመኪያቸዉ /፪/

ሕዝብህን ባርክ ለዘለዓለም ጠብቃቸዉ /፪/
በፍቅርህም ከፍ አድርጋቸዉ /፫/
የምስጋና ነጎድጓድ ከአፍሽ ይዉጣ /፪/
ድሮም ቢሆን እግዚአብሔር ነዉ የአንቺ እጣ /፪/

741. ቤተክርስቲያን

ቤተክርስቲያን ባሕረ ጥበባት /፪/
አትመረመርም /፪/ እጅግ ጥልቅ ናት /፪/
በሥጋዊ ጥበብ ለማወቅ ቢቃጣ
የእምነት መነጽሩን ይዞ ስላልመጣ
ሰው ሁሉ በስህተት /፪/ ፈጣሪውን አጣ /፪/
እንመሰክራለን ፈጣሪያችን አለ
እንመሰክራለን አማኑኤል አለ /፪/
እንመነው አንካደው አማኑኤል ቸር ነው /፪/
እንመሰክራለን ድንግል አማላጅ ናት
እንመሰክራለን ማርያም አማላጅ ናት
እንመናት አንካዳት የአምላክ እናት ናት /፪/
ጎበ ጥበባት ጎበ ልሳናት /፬/
ዮሐንስ /፪/ ወንጌለ ስብከት /፪/

የሠርግ ዝማሬዎች

742. ሥላሴ ይባርኳችሁ

ሥላሴ ይባርኳችሁ /፪/
በሥጋ ወደሙ ዛሬ ከበራችሁ
ሥላሴ ይባርኳችሁ
እመ አምላክ ትከተልህ /፪/
ፈተና እንዳይገጥምህ ድንግል ትከተልህ
እመ አምላክ ትከተልህ
ሚካኤል በኑሮአችሁ /፪/
አርምሞ ማስተዋል ትዕግስትን ይስጣችሁ
ሚካኤል በኑሮአችሁ
ገብርኤል ከላይ ወርዶ /፪/
እርሱ ይራዳችሁ በክንፎቹ ጋርዶ
ገብርኤል ከላይ ወርዶ
ዑራኤል በምልጃው /፪/
እውቀትን ጥበብን ይስጥህ በፅዋው
ዑራኤል በምልጃው
ጊዮርጊስ አይለያችሁ /፪/
በፈተና ጊዜ ፅናት ያሳያችሁ
ጊዮርጊስ አይለያችሁ

743. ዘወይን

ዘወይን ዘወይን ቤተ ቃና ዘወይን /፪/

ቤተ ቃና ዘወይን ቤተ ቃና ዘወይን /፪/

በቃናዋ መንደር ሰርግ ተደግሶ
ወይኑ ተሰናድቶ ዳሱ ተቀልሶ
ዶኪማስም ጠራ ደቀመዛሙቱን
ኢየሱስን እና ማርያም እናቱን
ሲበሉ ሲጠጡ እጅግ ደስ አላቸዉ

ያ መናኛ ወይን እየጣፈጣቸዉ

እልልታዉም ደምቋል ሙሽዉም ኮርቷል

ሰርጉ ለእንግዶቹ የበቃ መስሎታል

ወይኑ በመካከል አለቀ ከጋኑ
አፍረዉ ተደበቁ አሳላፊዉ ሁሉ
ማንም ሰዉ ሳይነግራት ይህን ተረድታ
ድንግል ልታማልድ ሄደች ወደ ጌታ
ጋኖቹን ሙሏቸዉ ዉኃዉን ቀድታችሁ

ብሏቸዋል ልጄ ታዘዙት ታምናችሁ

ብላ ስትናገር አሳላፊዎቹ

አምነዉ ጓዳ ገቡ ተሞሉ ጋኖቹ

ማድጋዉ ሲከፈት መልካም ወይን ሆነ
የክርስቶስ ክብር በቤቱ ገነነ
የእማምላክ ፀሎት ታሪኩን ቀየረ
መናኛዉ በሐዲስ ይሄዉ ተቀየረ
ዛሬም ለደከሙ አልጫ ለሆኑ

የነፍሳቸዉ ጣፋጭ አልቆባቸዉ ወይኑ

ድንግል ትቆማለች ስለ እርነሱ ተግታ

እንዲጣፍጡላት ለምና ከጌታ

744. ሙሽሮች አበበ ፍሬአችሁ

ሙሽሮች አበበ ፍሬአችሁ
ሙሽሮች እንኳን ደስ አላችሁ
ለዚህ ቀን ይኸው ደረሳችሁ
በአምላክ ፊት እጅግ ከበራችሁ /፪/
በእግዚአብሔር ቸርነት በመልካም ፈቃዱ
በቅዱስ ቁርባኑ ዛሬ ተዋሐዱ /፪/
በሥርአተ ተክሊል በሥጋ ወደሙ
በመድኃኔዓም ፊት ጋብቻን ፈጸሙ /፪/
በቤተክርስቲያን በፈጣሪያቸው ፊት
ሁለቱም አንድ ሆኑ በዚህች ቅድስት ዕለት /፪/
አንድ የሚያደርጋቸው ተነቦ ወንጌሉ
በካህኑ መስቀል በረከት ታደሉ /፪/
በወንጌል ትዕዛዝ በሐዋርያት ቃል
በእመብርሃን ፊት ጋብቻቸው ጸድቋል /፪/
በአምላክ ስጋና ደም ሁለቱም ታተሙ
የሕብረት ቃልኪዳን በአንድ ላይ አሰሙ /፪/
ጸንቶ የሚያዘልቅ የማይለያቸው
ክቡር ቃል ስላለ በመሐከላቸው /፪/
እስከመጨረሻው አንድ አካል ሆነዋል
የአማኑኤል ስጋ አስተሳስሮአቸዋል /፪/

745. ዳዊት ይሴብህ

ዳዊት ይሴብሕ /፪/ ወይዜምር ዕዝራ
እንዘ ይብሉ ሙሽሪት ሙሽራ /፪/

746. አፈኑ ማቱሳላህ

አፈኑ ማቱሳላህ ወልደ ሔኖክ
እም አፈ ልምላሜ ሙሽራው ቡሩክ
ቀስመ ፅጌ /፫/ ውዳሴኪ ወይዘሪት ሙሽሪት

747. ሕገ ስብዕናሁ

ሕገ ስብዕናሁ ዐቀበ /፪/ በተደንግሎ
ወፈጸመ /፩/ በወንጌል ዘሐሎ

748. ይደሰት ሙሽራው

ይደሰት ሙሽራው በስርዓተ ተክሊል ሲገባ ኧኸ
አሸበረቀ ደመቀ አጌጠ በሰላም አበባ /፪/
በሥጋ ወደሙ ፍጹም እንዳዘዘው በወንጌሉ ኧኸ
በሙሽራው/ሪት ነው ያማረው /፪/ ሥርዓተ ተክሊሉ /፪/

749. ካሕናት ተንስኡ

ካህናት ተንስኡ /፪/ ለተናብቦ
እንዜ ብሉ ንሜብሆ /፪/ እንዘ ይብሉ ንሴብሆ

750. የማኑ

የማኑ ተሀቅፈኑ ወፀጋሙ ታጎተ ርእስየ
ትብሎ መርዓት ትብሎ /፬/ ምርዓት ለመርዓዊሀ

751. በሠርጋችን ዕለት

በሠርጋችን ዕለት እንድትባርከን
ጌታ ጠርተንኃል በእምነት ሆነን
ከእናትህ ጋራ ከእመቤታችን
ከመላዕክት ጋር ና በሠርጋችን
ከሐዋርያት ጋር ና በሠርጋችን
ከወዳጆችህ ጋር ና በሠርጋችን
በገሊላ መንደር እንደተገኘህ
ና በእኛ ድንኳንም ጌታ ስንጠራህ
ስለ እናትህ ብለህ ጌታችን እንዳትቀር
አንተ ነህ ክብራችን የቤታችን ፍቅር
ነይ ከልጅሽ ጋራ እመቤታችን
እንድታሚዱልን የጎደለውን
ንገሪው ለልጅሽ ባዶው እንዲሞላ
በረከት የእርሱ ነው ቤታችንን ይሙላ
በጎደለው ሁሉ እየጨመርሽልን
ቤታችንን ሁሉ ሙዱው እናታችን
ለአገልጋዮቹ ድንግል ንገሪያቸው
ጠርተን እንዳናፍር ጋኖቹን ይሙሏቸው

752. በቃና ዘገሊላ

በቃና ዘገሊላ
ኧኸ ዘገሊላ ክብካብ ኮነ /፪/
ዕዝራኒ ተናገራ
ኧኸ ተናገራ ዳዊት ዘመራ ተናገራ ዘመራ ዳዊት

753. ቃና ዘገሊላ

ቃና ዘገሊላ /፪/ በዚያ በሠርግ ቤት
ተገኝተሻል ድንግል ከልጅሽ ጋራ
ተገኝተሀል ጌታ ከእናትህ ጋራ
እድምተኞች ሞልተው የተጋበዙት
ሲበሉ ሲጠጡ ወይኑ አልቆበት
ድንግል እናታችን ቤዛዊተ ዓለም
ለመከራ ደራሽ እንዳንቺ የለም
አንተ እያለህስ ማፈር የለባቸው
ሁሉ ይቻልሀል ወይኑን ሙላላቸው
ማድጋው ባዶ ነው ብለሽ የተናገርሽ
ጌታን ያሳሰብሽው እመቤታችን ነሽ

የጌታ አምላክነት የተገለፀበት
ምንኛ ታደለ የነ ዶኪማስ ቤት
ዛሬም ይኸው በዚህ በሠርገኞቹ ቤት
በረከት ፈሰሰ በአምላክ ቸርነት
ውሃው ተለውጦ የወይን ጠጅ ሲሆን
በቃና ገሊላ ሁላችን አየን
እግዚአብሔር ከኖረ በመሐከላችን
ሁሌ ይሰጠናል ይሕን መሰል ወይን

754. ይህን ላደረገ

ይህን ላደረገ ሃሌሉያ በሉ
እግዚአብሔር ታማኝ ነው ሁል ጊዜ በቃሉ
ሙሽሪት ሙሽራው እንኳን ደስ አላችሁ
የያዕቆብ አምላክ ሞገስ ሆነላችሁ
ስንቱን ተራራ አልፈነዋል
በሰገነት ላይ አቁሞናል
እስኪ እንዘምር በደስታ
ሁሌ ታማኝ ነው የኛ ጌታ
ከኛ የሆነ ምንም የለም
ተመስገን ጌታ ለዘላለም
ስራህ አበራ በምስጋና
በሙሽሮች ላይ እንደገና
የማይሆን መስሎ የታየን
በእግዚአብሔር ሆኖ ስላየን
እንደ አሳፍ ልጆች ተሰልፈን
ስሙን በቅኔ ለማመስገን
የተባረከ በመዳፉ
ቅኔን ያፈሳል ሁሌ ካፉ
ከመላዕክት ጋር አንድ ሆነናል
የእግዚአብሔር ሥራ መስጦናል
ጋኑ ቢጎድል የወይን ጠጁ
ያስባል ጌታ ለወዳጁ
መናኛው ይውጣ ከቤታችን
አዲስ እንጠጣ ጌታን ይዘን
አቤንኤዜር ነው መዝሙራችን
እየረዳን ነው አምላካችን
ፊታችን በራ በደስታ
ውበት ሆኖናል የኛ ጌታ

755. መርዓዊ ሰማያዊ

መርዓዊ ሰማያዊ ሙሽራው ሰማያዊ
ለእመ ገብረ <u>በዓለ</u> /፪/
ኧኸ /፫/ ይኑሩ በሰላም /፫/ ፀንተው ዘለዓለም
ደናግል ተነሱ ያዙ መብራቱን
ሙሽራው ደረሰ አጉል እንዳንሆን
ወንጌልን ይዘዋል ጎዳናቸው ያምራል
አላማው መልካም ነው እነርሱን እንምሰል
የድካም ዋጋቸው /፪/
ብርሃንን ያበራል ለተከታያቸው
በገሊላ መንደር በሰርግ እንደዋለ
ዛሬም ከእኛ ጋራ አማኑኤል አለ
በሥጋው መስርቶ በደሙ አፅንቶታል
ይህንን ጋብቻ አምላክ ቀድሶታል
ሙሽሪት ሙሽራው ዛሬ አምሮባቸዋል
በቅዱስ ጋብቻ አንድ አካል ሆነዋል
የሙሽራው ሕይወት መልካም እንዲሆን
ካህኑ ይባርኩት ቡሩክ ሰው ይሁን
የሙሽሪት ሕይወት መልካም እንዲሆን
ካህኑ ይባርኳት ቡርክት ትሁን

756. መፅአ መርዓዊ

መፅዓ መርዓዊ ፍሰሐ ለኩሉ ሃሌ ሃሌሉያ
በሰላም ፃኡ ተቀበሉ /፪/
መጣ ሙሽራው ደስታ ለሁሉ ሃሌ ሃሌሉያ
በሠላም ውጡ ተቀበሉ /፪/

757. ደመቀ አበራልን

ደመቀ አበራልን የአማኑኤል ሥራ /፪/
ሙሽሮቹ ሆኑ አብርሃም ወሣራ
በቤተክርስቲያን ጥላ ተከልለው
ተክሊል አደረጉ ሙሽሪት ሙሽራው
ፀጋ መንፈስ ቅዱስ ስለተሰጣቸው
ሙሽሪት ሙሽራው አበራ ገፃቸው
የተራራቀ አካል አንድ ሆነ በተክሊል
እግዚአብሔር ይመስገን እልል እልል እንበል
አጥንትሽ ከአጥንቴ ስጋሽ ከሥጋዬ
አዳም የሰበከው ይኸው ዛሬ ታየ
የተክሊል ብርሃኗ በኛ መሐል በርቶ
ረቂቅ አንድነት ታየ በእርሷ ጎልቶ
ይህን ድንቅ ነገር ለማየት ያበቃን
ምስጢርን የሚገልፅ እግዚአብሔር ይመስገን
ነጭ መጎናፀፊያ በአንድ ተጎናፅፈው
ተክሊል አደረጉ ሙሽሪት ሙሽራው
ሙሽሪት ሙሽራው ለፍቅር ተሸነፉ
የቁርባን መቁረቢያ ነጭ ልብስ አሰፉ

758. ናሁ ናኑ

ናሁ ናሁ ሶበ ሰማዕነ ዜናሁ
መርዓዊነ የዓቢ ግርማሁ
ወመርዓትነ የዓቢ ግርማዋ
አሁን አሁን በእውነት ሰማነው ዜናውን
ሙሽራው ይበልጣል ግርማው
ሙሽራዋ ይበልጣል ግርማዋ

759. ሙሽራዬ

ሙሽራዬ /ፒ/ አበባዬ
ከጎንህ የምትሆን እህት አገኘህ
የኛማ ሙሽራ እንኳን ደስ አለህ
የእግዚአብሔር ፈቃዱ ለዚህ ካበቃችህ
ቤታችሁ ይመረቅ በፍቅር ያፅናችሁ
ወንድም አግኝተሻል የሚያስብልሽ
የኛማ ሙሽራ እንኳን ደስ አለሽ
እግዚአብሔር ይመስገን እኛም ደስ ብሎናል
በቤተክርስቲያን ሠርጋችሁ ውብ ሆኗል
እንደራስህ አርገህ እንድትወዳት
አደራ ሰጠንህ በጌታችን ፊት
እንድታስቢለት አንቺም ለአካልሽ
አደራ ትላለች ወንጌል እናትሽ
በሥጋ ወደሙ ሕይወት አግኝታችሁ
ቤታችሁ ይመረቅ ይባረክ ጓዳችሁ
አምላክ ያለበት ነው ይኼ ጋብቻችሁ
እስከመጨረሻው ኑሩ ደስ ብሏችሁ

760. ትዌድሶ

ትዌድሶ መርዓት ወትብሎ
ኧኸ ወልድ እጐየ ቃልከ አዳም /ፎ/

761. ደስ አላት

ደስ አላት ቤተክርስቲያን በጣም ደስ አላት /ፎ/
ሙሽሪት ሙሽራዉ ልጆችዋ /ፎ/
በተክሊል በቁርባን ተዋሐዱላት

762. መፃ ዘመፅአ

መፃ ዘመፅአ ዘመፅአ እምላዕሉ
መርዓዊ መፅአ /ፎ/ ተቀበሉ
መጣ ሙሽራው መጣ
ሙሽራው መጣ /ፎ/ ተቀበሉ ውጡ ተቀበሉ

763. ያስደስታል

ያስደስታል /ፒ/ የኛ እምነታችን
የኦርቶዶክስ ተዋህዶ የጋብቻ ስርዓታችን
ተፈፀመ /ፒ/ ዛሬ ሠርጋቸው
ምስጋና ይግባው እንላለን /ፎ/ ቸር አምላካችን

764. ወእመ አኮ

ወእመ አኮ ከመ ወሬዛ ኃይል /ፎ/
ኧኸ ትዌድሶ መርዓት እንዘ ትብል /ፎ/

765. ኢያቄም ወሃና

ኢቄም ወሃና
ሙሽሮቹ ያብባሉ ገና /ፎ/

766. ቤተ ክርስቲያን እምነ

ቤተክርስቲያን እምነ /ፎ/ ደስ ይበልሽ
ካባ ለብሰው ወርቅ ለብሰው /ፎ/
ወርቅ ለብሰው መጡ ልጆችሽ

767. ንፅህት ቅድስት

ንፅህት ቅድስት ቡርክት
የአምላክ እናት እመቤት
ልጆችሽ ሙሽሮች ሁለቱም አንድ ሆኑ
ተዋሐዱ ተጣመሩ በቅዱስ ቁርባኑ ኧኸ /ፎ/
ፍፁም መንፈሳዊ ልዩ ፍቅር
አንቺ ያለሽበት መልካም ትዳር
መሰረቱ ዛሬ ልጆችሽ
ቅድስት ሆይ ባርኪያቸው ተገኝተሽ
ድንግል ጎጇቸውን ቀድሰሽ
እውነተኛ ፍቅር መስርተሽ
በመካከላቸው ተገኝተሽ
ሁሉን አሠጫቸው አማልደሽ
ሙሽሮቹም አምነው በምልጃሽ
እናታችን ባርኪን ነይ ሲሉሽ
ፈጥነሽ ድረሺና በሰርጋቸው
ነይ ተመላለሺ መሐላቸው
አንቺን ለሚወዱሽ ለሚያምኑሽ
የሕይወት አጣፋጭ ቅመም ነሽ
ሙሽሮቹም ዛሬ ይጠሩሻል
የጎጆአችን ፋና ነይ ይሉሻል
ቃና ዘገሊላ ተገኝተሽ
መልካሙን ጋብቻ የባረክሽ
ዛሬም ከልጅሽ ጋር በሠርጋቸው
ነይ ተመላለሺ መሐላቸው

768. ደስ አለው ጌታ

ደስ አለው ጌታ በሙሽሮች ደስ አለው ጌታ
በቅዱስ ቁርባን ተወስው ደስ አለው ጌታ
ደስ አላት ድንግል በሙሽሮች ደስ አላት ድንግል

769. አጅቡት በእልልታ

አጅቡት በእልልታ ሲወጣ ሙሽራው
ፍፁም የሚያስደስት የሠርጉ ዕለት ነው
ዘመዶቹ ሁሉ ተቀበሉት ውጡ

የሙሽራው መውጫ አሁን ነው ሰዓቱ
እልል /፪/ እንበል እንዘምር በእልልታ
ይኼን ላደረገ ለሠራዊት ጌታ
ሁሉንም በጊዜው ይፈፅማልና
ይኸው አበቃቸው ለዚህ መልካም ዜና
ሙሽሪት ተደሰች ዝምታው ምንድነው
የዳግም ልደትሽ የሠርግሽ ዕለት ነው
አዳም ጎንሽ ቆሞ ሔዋን ሆይ ሲልሽ
መንፈሳዊ ሐሴት ይሙላ በልብሽ
እህት ወንድሞቿ እናትና አባቷ
ተነሱ ዘምሩ ለልጃችሁ ደስታ
መሔዷ ነውና ወደ ቤቷ ዛሬ
ወደ አዲሰ ጎጆዋ ሽኟት በዝማሬ
ቤተሰቦችሽን ሁሉንም ትተሽ
መሔድሽ ነውና ወደ መኖሪያሽ
ከአማኑኤል ጋራ ባልሽን ይዘሽ
ተነሽ ሙሽራዬ ሆይ ደርሷል ሰዓትሽ
ከድንግልም ጋራ ሚስትህን ይዘህ
ተነስ ወንድሜ ሆይ ደርሷል ሰዓትህ

770. ተፈስሒ

ተፈስሒ ቤተ ክርስቲያን ተፈስሒ ቤተ ሥላሴ
ያሳደግሻቸው ልጆችሽ አብርሃም ሳራን ሲሆኑልሽ
‹‹ ሙሽሮችሽ ‹‹ ‹‹ ‹‹
ትምህርትሽ ገብቷቸው የወንጌሉ ቃል
በኑሮ ሊያበሩ ይኸው መጥተዋል
በክርስቶስ ትምሕርት በቃሉ ተመርተው
ለዓለም መሰከሩ ተራራ ላይ ቆመው
ተፈስሒ
ከእንቅቡ በታች አይደለም መብራቱ
በራ እንጂ ለሁሉም ከነበረከቱ
ጢስ የሌለው ሻማ ደምቀው የከበሩ
ልጆችሽ ሙሽሮች እንደ ጧፍ አበሩ
ተፈስሒ
ሰላም ላንቺ ይሁን ደስ ይበልሽ በጣም
የዘራሽው ማሳ ፍሬውን ሲሸከም
ካባ ደረብሽለት ለውዱ ሙሽራ
አክሊል ደፋሽለት ከምርቃት ጋራ
ተፈስሒ
ቃልሽ ይለውጣል ግሩም ነው ኃያል
አመንዝራዎችን ድንግል ያደርጋል
ተገለጠ ክብርሽ በሙሽሮች ዛሬ
ምስክር ሆኖልሻል የዘራሽው ፍሬ
ተፈስሒ

771. እንደ አብርሃም

እንደ አብርሃም እንደ ሳራ /፪/
ሥላሴ ይኑሩ ከእናንተ ጋራ
ቤታችሁ ይባረክ በረከት ይሙላ
ፈቅደው ይስጧችሁ ሰላምና ተድላ
ቤቱ ሥላሴ ይሁንላችሁ
ዘውትር ይኑሩ መሐከላችሁ
ቤታችሁ ይከፈት ለእንግዳ ሰው
ከፍላችሁ ስጡ ለተራበው
መልካሙን ፍሬ አፍሩ ተግታችሁ
ስመ ሥላሴን እያሰባችሁ
ጌታዬ በይው ውድሽ ነውና
እህቴ በላት ሥጋህ ናትና
ጽድቅ ተሞላ ፍሬ ይስጣችሁ
አብርሃም ሣራን ሁኑ ተግታችሁ

772. ወንድና ሴት አርጎ

ወንድና ሴት አርጎ እንደፈጠራቸው
ኋላም ለኑሮአቸው ጋብቻን ሰጣቸው
አንዱ ከተጋቡ አንድ ሥጋ ናቸው
ከእንግዲህ ወደፊት ይፀናል ፍቅራቸው
ደስ ይበለን ሙሽሪት ሙሽራው /፪/
አንድ አካል ሆነዋል አምላክ አጣምሯቸው
በምንም ምክንት ማንም አይለያቸው
በጣም ይወዳታል ክብርት ሚስቱን
ስለሷ አሳልፎ ይሰራል ነፍሱን
ለአብርሃም ለሣራ እንደሰጠ ትዳር
ለእናንተም ይለግስ የዘለዓለም ፍቅር
አንቺም እንደሣራ እሱም እንደ አብርሃም
ተፋቅራችሁ ኑሩ እስከዘለዓለም
ለዚህ ላበቃችሁ ለቸሩ አምላካችን
ምስጋና ይድረሰው ዛሬ ከሁላችን
በሉ ደና ግቡ ወደ አዲስ ሆጆአችሁ
አምላክ በጥበቡ ፍቅርን ያላብሳችሁ

773. ንሴብሆ

ንሴብሆ /፪/ ለአምላከ ዕዝራ
እሱን ለፈጠረ እሷንም ለሰራ /፪/
ንሴብሆ ለአምላከ እዝራ

774. እሁየ ዘተመነያ

---------- እጉየ /፪/ ዘተመነያ
ኧኸ ዛቲ መርዓት(2) እህተ ነያ /፪/
-------- ያያት /፪/ የተመኛት
ይህቹ ሙሽራ /፪/ ------ ናት

775. ማርያም ጋብቻውን ባርኪ

ማርያም ጋብቻውን ባርኪ /፪/
ጋብቻውን ባርኪ /፬/ ማርያም ጋብቻውን ባርኪ

እንደ ቃና ወይኑን እንደ ቃና /፪/
ማርያም አጣፍጪው ነይና

776. ሁለቱም አንድ ሆኑ

ሁለቱም አንድ ሆኑ ዛሬ /፪/
ኸኸ በእግዚአብሔር በሕያው ቃሉ
ሁለቱም አንድ ሆኑ ዛሬ
ወንድና ሴት አርጎ የፈጠራቸው
በጌላም በቃሉ አንድ ያደረጋቸው
እናትና አባቱን የአዳም ልጅ ይተዋል
ከሚስቱም ጋር በሠላም በአንድ ይተባበራል
ሁለቱም አንድ ሥጋ አብረው ይኖራሉ
ብሎ አስተምሮናል ጌታችን በቃሉ
አንድ ሥጋ ናቸው አይደሉም ሁለት
የባልና የሚስት ሕይወት ወደፊት
እንግዲህ እግዚአብሔር ያጣመራቸውን
በሆነ ባልሆነው ሰው አይለያቸውም
ለወገኖቻችሁ ምሳሌ ሆናችሁ
በክርስትናው ፍቅር በዓለም ያኑራችሁ
ምንጣፋችሁ ብሩህ መኝታችሁ ንጹህ
ስለሆነላችሁ እንኳን ደስ አላችሁ
ዓለም እንዲደነቅ ጠላት እንዲያፍር
በሐዘን በደስታ ይኑራችሁ ፍቅር

777. ድንቅነው በጣም

ድንቅ ነው በጣም ድንቅ ነው ድንቅ ነው በጣም
በሠርጋችሁ እለት ተገኘ መድኃኔአለም
‹‹ ‹‹ ‹‹ ድንግል ማርያም
በቃልህ ተመርተው ለዚህ ቀን በቅተዋል
በፊትህ ጋብቻን ይኸው ፈፅመዋል
በፈሰሰው ደምህ ሕብረት መሥርተዋል
በሥጋም በነፍስም /፪/ ያንተው ነን ብለዋል
ከአዳም አንድ አጥንት ከጎኑ ወስደህ
አጋር እንድትሆነው ሔዋንን ሰጠህ
ሁለቱንም ባርከህ እንደፈጠርካቸው
ዛሬም ለሙሽሮች /፪/ ፅናትን ሥጣቸው
ጌታ ሆይ በሕግህ በቃልህ መሠረት
አንድ ሆነዋልና በዚህ ቅዱስ ዕለት
እሱንም እሷንም ባርከህ ቀድሳቸው
ዘለዓለማዊ ክብር /፪/ ፀጋህን ስጣቸው
የዲያብሎስ ተንኮል እንዳያጠምዳቸው
እስከመጨረሻው ጋሻ ሁንላቸው
ከቅድስቲቷ ቤት ሁለቱም ሳይርቁ
ጽናትን ስጣቸው /፪/ አብረው እንዲዘልቁ

778. ሐመልማል

ሐመልማል /፪/ ሐመልማለ ወርቅ
ልብሱ የኛ ሙሽራ ሐመልማለ ወርቅ
ልብሷ የኛ ሙሽራ ሐመልማለ ወርቅ
በባቢሎን ምድር ያልተፈተለ ነው
በቤተ መቅደሱ ሲለብሱት ያየነው
በክብር ካባው ላይ ፀጋው ተጨምሮ
ሞላቸው ሞገሱ በላያቸው አድሮ
የሙሽራው ጠረን መዓዛው ይሰባል
በቅብዐ ሜሮን በእጣኑ ከብሯል
ያንፀባርቃሉ እንደ አልማ ድንጋይ
በረከትን አፍስሰው ከምሕረት እጁ ላይ
በዚህ ዓለም እንቁ አልከበረም ዘርፉ
በጾም በጸሎት ነው ያማረው መርገፉ
የሰው እጅ አይደለም የተጠበበት
ከላይ የመጣ ነው እድፈት የሌለበት

779. የምሥራች

የምስራች ደስ ይበላችሁ /፪/
አሸብርቆ ዋለ ሙሽሮች ሠርጋችሁ /፪/
ሕይወታችሁ ሠላማዊ ፍፁም ፍቅር /፪/
እንደ ጽጌረዳ እንደ አደይ ፈክቶ የሚኖር
አማኑኤል ያርገው መልካም ትሥሥር
መተሳሰብ መከባበር ይሁን ግብራችሁ /፪/
ሰርጎ እንዳይገባ ዲያብሎስ በትዳራችሁ
በጾም ጸሎት ይታጠር ሙሽሮች ጎጆአችሁ
እግሮቻችሁ ይገስግሱ ወደ እውነት /፪/
አማናዊው ማዕድ ክርስቶስ ወዳለበት
በልባችሁ አኑሩት ታላቁን አባት
ዓኖቻችሁ የጎረቤት አይመልከቱ /፪/
ለወሬ ለሐሜት ጆሮአችሁ አይከፈቱ
በፍቅር በደስታ በጾም ጸሎት በርቱ
ድንግል ማርያም ቅድስት እናት
ለምኚላቸው /፪/
የሚፈልጉትን በሙሉ አንቺ አሠጫቸው
በምድርም በሰማይ ምልጃሽ አይራቃቸው

780. እሰይ እሰይ

እሰይ እሰይ እሰይ /፪/
በተዋሕዶ ምስጢር ስናይ
እሰይ እሰይ በአዳም ተጀምሮ
‹‹ የአንድ አካል ምስጢር
‹‹ በገነት ሲኖሩ
‹‹ በጽድቅ ምድር
አካሌ ናት አላት ሔዋንን በፍቅር
እሰይ እሰይ መካን ሆነው ሳለ
‹‹ ሃና እና ኢያቄም
‹‹ የፀናው አንድነት
‹‹ አልተነጣጠለም
‹‹ በእምነት ቢኖሩ
‹‹ በጾም በጸሎት

ድንግል ተወለደች ልትሆን መድኃኒት
እሰይ እሰይ ዛሬም በሙሽሮች
‹‹ ይህንን አይተናል
‹‹ በቅዱስ ጋብቻ
‹‹ በማይነጣጠል
ምስጢር ተከወነ በሥርዓተ ተክሊል
እሰይ እሰይ የተዋሕዶ ምስጢር
‹‹ እጅግ የጠለቀ
‹‹ ባመኑት ልቦና
‹‹ ፈጽሞ ታወቀ
ዛሬም በሙሽሮች ክብር ተደነቀ

781. የሀብከ ዮብ

የሀብከ ዮብ ዩብከ መድኃኒዓለም /፪/

እድሜ ማቱ ሳላ ወአብርሃም /፪/

ይስጣችሁ ዛሬ ይስጣችሁ መድኃኒዓለም /፪/

እድሜ ማቱሳላን የአብራሀም /፪/

የቅዱስ ጋብቻ ሙሽሮች የተወለናችሁ /፪/
ክርስቶስ ተገኝቷል በመካከላችሁ /፪/
የድንጋዮች ጋን ወይኑን ወይን ሊሞላበት /፪/
ከድንግል ማያርም ጋር ተገኝቷል ከዚህ ቤት /፪/
ደስታዉን አይቶ አምላክ ፍፁም ተደስቷል /፪/
ሊባርካችሁ እጆቹን ዘርግቷል /፪/
በሕይወታችሁም ፍቅር ፍቅር ቅመም ሆኖ /፪/
ትኅትናን ይስጣችሁ እግዚአብሔር በቶሎ /፪/
ሰርጋችሁ እንዲሆን ደስታ ፍቅር የተሞላበት /፪/

በሕይወታችሀ ዉስጥ ክርስቶስ ይግባበት

በሕይወታችሁ ዉስጥ አምላክ ይኑርበት

የበረከት ፍሬ ፀጋዉ እንዲበዛላችሁ /፪/
ዛሬ ተደሰቱ አምላክን ይዛችሁ /፪/
እራስን በመግዛት እዉቀት /፪/ ለመላችሁ /፪/
ዛሬ ተደሰቱ አምላክን ይዛችሁ /፪/
በሥጋ ወደሙ እግዚአብሔር ስለመረጣችሁ /፪/
የመንፈስ ቅዱስም ህፃናቶች ናችሁ

782. እንዘሰውር

እንዘሰውር እምኔነ ይእዜሰ ክሱተ ኮነ /፪/
ተአምረ ወመንክር ገብረ መድኃኒነ በቃና /፪/
ዘገሊላ ከብካበ ኮነ ማየ ረስየ ወይነ
ትርጉም፡-ጌታችን መድኃኒታችን ከእኛ
ተሰውሮ የነበረው አሁን ተገለጠ በቃና ገሊላ
ውኃውን ወይን ጠጅ በማድረግ ተአምራትን
አደረገ

783. ዘበዳዊት

ዘበዳዊት ተነበየ /፪/
በቃና ዘገሊላ /፪/ ከብካብ ኮነ /፬/

784. አንከርዎ

አንከርዎ ለማይ አእኩትዎ ለኢየሱስ /፬/
በእንተ ማይ ዘኮነ ወይን /፬/

785. ተአምረ

ተአምረ ወመንክረ ገብረ መድኃኒነ /፪/
በቃና ዘገሊላ ዘገሊላ ከብካብ ኮነ /፪/

መዝሙር በእንተ ልደታ ለማርያም

786. አልብኪ ነውር

አልብኪ ነውር ወኢምንትኒ በላዕሌኪ /፪/

ፃኢ እምሊባኖስ እኅትየ መርዓት /፬/

የለብሽም ነውር ምንም ነገር በላይሽ ላይ /፪/

ውጪ ከሊባኖስ እህቴ ሙሽራ /፬/

787. አዕይንታ ዘርግብ

አዕይንታ ዘርግብ /፪/ ኢያቄም ወለዳ /፪/

ኢያቄም ወለዳ /፭/ ዘርግብ ኢያቄም ወለዳ ኧኸ /፫/

ትርጉም፡- አይኖቿ የርግብ የመሰሉ /የሆኑ/ ልጅን
ኢያቄም ወለደ፡፡

788. ታትመሻል

ታትመሻል በሰው ልቦና
የደካሞች ምርኩዝ ነሽና
ላመስግንሽ በአዲስ ዝማሬ
እመቤቴ ገናነው ፍቅሬ
የተጽናናንብሽ የድሆች ማረፊያ
ንፋስ ውቂያኖሱን ወጀቡን መቅዘፊያ
ወርሰናል ስምሽን ከወርቁ መዝገብ ላይ
ወለድሽልን ድንግል የሕይወትን ፀሐይ

ጽዮን ብለናል ነሽ መማፀኛችን
ሞትን አናይም ካለሽ እናታችን /፪/
ቀስተደመናዬ ሆነሽ ምልክቴ
አለሁ እስከዛሬ ባንቺው በእመቤቴ
ልጅሽን አምኜ ምን ይጎልብኛል
ያስጨነቁኝ ሁሉ ይታዘዙልኛል
ጽዮን ብለናል ነሽ መማፀኛችን
ሞትን አናይም ካለሽ እናታችን /፪/
ተከቧል ተራራው በብሩህ ደመና
የአብልጅ ክርስቶስ ባንቺ ወርዷልና
ይባቤ ምስጋና አፋችን ይሞላ
መቅደስ አላየሁም ድንግል ካንቺ ሌላ
ጽዮን ብለናል ነሽ መማፀኛችን
ሞትን አናይም ካለሽ እናታችን /፪/
የከሳሼን ጉልበት ጽናቱን ሰብረሻል
የአዳም ልጅ ከሲኦል ከሞት ወጥቶብሻል
ጣፈጣት ለነፍሴ የማህፀንሽ ፍሬ
ስጠራሽ ኖራለሁ በያሬድ ዝማሬ
ጽዮን ብለናል ነሽ መማፀኛችን
ሞትን አናይም ካለሽ እናታችን /፪/

789. ተወለደችልን

ተወለደችልን ድንግል ማርያም

የነቢያት ትንቢት ሕይወተ አዳም

ሐናና ኢያቄም በጸሎት ሲተጉ

የአምላክን ስጦታ ፀንተው ሲፈልጉ

በሕግ በሥርዓት ሆነው ሲማልዱ

የፀሐይን እናት ሰማይን ወለዱ

አባቶች ነቢያት ያደረጓት ተስፋ

ምልክት የሆነች በሞት እንዳንጠፋ

የቀረችልን ዘር የአምላክ መገኛ

የሕይወት ውሃ ምንጭ ተወለደች ለእኛ

የጥል ምክንያት ብትሆን ሔዋን

በድንግል መወለድ እርቅ ሆነልን

ለአዳም ዘር ሁሉ መድኃኒት ናትና

እናቱን የሰጠን ይድረሰው ምስጋና

790. ተፈጸመ ሃና

ተፈፀመ ሃና በወለትኪ /፪/
ተስፋ ቅዱሳን አበውኪ /፪/
ተፈፀመ ሃና በልጅሽ
የቅዱሳን ተስፋ የአባቶችሽ /፪/

791. ኢያቄም ወለዳ

ኢያቄም ወለዳ ኢያቄም /፪/

ዳዊት ዘመዳ ኢያቄም ወለዳ /፬/

ትርጉም፡- የኢያቄም ልጅ የዳዊት ዘመድ ናት

መዝሙር በእንተ ደብረ ታቦር

792. አማን በአማን

አማን በአማን /፪/
ተሰብሐ በደብረ ታቦር

793. አሐደ ለከ

አሐደ ለከ ወአሐደ ለሙሴ
ወአሐደ ለኤልያስ ንግበር ማሕደረ /፪/

794. ወተወለጠ

ወተወለጠ ራዕዩ በቅድሜሆሙ
ፀአዳ ኮነ /፪/ አልባሲሁኒ ከመ በረድ

795. ታቦር

ታቦር ወአርሞንኤም
በስመ ዚአከ /፬/ ይትፌስሑ

796. ወሪዶሙ

ወሪዶሙ እም ደብረ ታቦር /፪/
እምደብረ ታቦር /፬/ ወሪዶሙ እምደብረ ታቦር

797. ታቦር አበራ

ታቦር አበራ ምድርን ከደናት ደመና
እንቅልፍ የለንም ታላቅ ነጎዳድ ሆኗልና

አነቃን ለምስጋና
ሙሴም የቀደው ሰው ኤልያስ ኃይለኛው
ተገኝተዋል በታቦር ምስክርህ ሆነው
እኛም ከገናናው ክብር የአባቱን ቃል ሰምተናል
በረዶ ሆኗል ልብሱ እፁብ እጹብ ብለናል
ቃል ገብተህልኝ ነበር ልታሳየኝ ክብርህን
ንገሥ ከሞት ቀስቅሰህ አይቼህለሁ አሁን
የእሳት ፈረሶች ያሉህ ተዋጊው የኔ ጌታ
አርሞንኤም ደስ አለው ሲሳራን ስለመታ
እጠብቅሀለሁኝ በምታልፍበት ቆሜ
መብራቶቼን አብርቼ ነጩን ልብስ ተሸልሜ
የዳዊት ልጅ ሆይ ግባ ኢየሱስ ወደ ቤቴ
ጽኒኤል እልሀለሁ ድናለች ሰውነቴ
ሁሉንም ብታከብር ሁሉንም ብትምረው
ማነው ቸርነትህን የሚከለክለው
ጠዋትም የተጠራ አምሽቶም የገባው
ሆነዋል ባለዋጋ ከበዛው ስጦታው
የረዳኸው ይናገር ያሰብከው በሕይወቱ
አቤንኤዜር እያለ ይዘምር በአንደበቱ
በደስታዬም ቀን አለህ አይሃለሁ ከጎኔ
ከእኔ ጋር አልቅሰህል አሳዝኖህ ሐዘኔ

798. እንዲህ አለው ጴጥሮስ

እንዲህ አለው ጴጥሮስ ኢየሱስን
ምስጢር ገሐድ ሲሆን በዚ በተራራ
በአንድ ላይ እንኑር ሦስት ዳስ እንስራ
አንዱን ላንተ አንዱንም ለሙሴ አንዱን ለኤልያስ
ተለወጠ ገጹ ከመ ጽጌሬዳ
ወርዶ ከለላቸው ደመና ፀአዳ
ከሰማይ ቃል መጣ እንደዚህ የሚል
የምወደው ልጄን እርሱን ስሙት ሲል
ኤልያስም ሄደ በሰረገላው
ሙሴም ከመቃብር ወደ መኖሪያው
ስላስደነቃቸው ግሩም ተአምራቱ
ይሕን ምስጢር አይተው ተሰነባበቱ

799. በስመ ዚአከ

በስመ ዚአከ ይትፌሥሑ ዮም /፪/

ታቦር ወአርሞንኤም /፬/

ትርጉም፦ ታቦርና አርሞንኤም በስምህ ዛሬ ደስ ይላቸዋል።

መዝሙር በእንተ ፍልሰታ ለማርያም

800. ድንግል

ድንግል /፪/ ወላዲተ ቃል /፪/
አሚሚትሽ በጥር ነሐሴ መቃብር ድንግል
ያንቺስ ለብቻው ነው ትንሳኤሽ ሲነገር ድንግል
ሥጋሽ በምድር ላይ የታለ እንደ ፍጡር ድንግል
አርጓል ወደ ሰማይ ከክርስቶስ መንበር ድንግል
ሥጋሽን ሲያሳርጉ መላዕከተ ሰማይ ድንግል
ቶማስ በደመና ሲመጣ መንገድ ላይ ድንግል
መግነዝ ተረከበ ለሐዋርት ሊያሳይ ድንግል
ትንሳኤሽን ሽተው ግራ ሲገባቸው ድንግል
ሐዋርያት ጸመው ተገለጽሽላቸው ድንግል
ተቀብራ አልቀረችም ከምድር ከደጇ ድንግል
ወደላይ አረገች እርሷም እንደልጇ ድንግል
ለማየት ሲጓጉ የድንግልን ትንሳኤ ድንግል
እርገቷን አወቁ በብዙ ሱባኤ ድንግል
እናም እንፀልይ ደጃችን እንዝጋ ድንግል
ከወላዲተ አምላክ እንድናገኝ ዋጋ ድንግል

801. ማርያም አረገች

ማርያም አረገች /፪/ ወደ ገነት
የሰማይ መላእክት በደስታ እጀቧት
አረገች ወደ ገነት

መዝሙር በእንተ ቅዱሳን መላዕክት

802. ገብርኤል መልአክ

ገብርኤል መልአክ ወረደ ጎበ ቂርቆስ ወእሙ
ኢየሉጣ /፪/ ቅድስት

ዘአጥፋኦ ለነበልባለ እሳት ዘአድኃኖሙ ለሰማዕት /፪/

ትርጉም፡- ሰማዕታትን ያዳናቸውና የእሳቱን ነበልባል ያጠፋው ገብርኤል ወደ ቂርቆስና እናቱ ቅድስት ኢየሉጣ ወረደ።

803. ፍቁራኒሁ

ፍቁራኒሁ ለአብ ሐራን መተንብላን /፪/

እለ ይስእሉ ምሕረት ለውሉደ ሰብእ ሱራፌል ወኪሩቤል /፪/

ትርጉም፡- አማላጆች ወዳጆች ርኅሩሆች ለሆኑ ለሰው ልጆች ምሕረትን የሚለምኑ የአብ ወዳጆች ሱራፌልና ኪሩቤል ናቸው።

804. ሱራፌል በግርማሆሙ

ሱራፌል በግርማሆሙ ወኪሩቤል በውዳሴሆሙ /፪/

ኅበ አንጻረ ቀዳማዊ የሐውሩ በሠረገላ ይረውጹ /፪/

ትርጉም፡- ሱራፌል በግርማቸው ኪሩቤል በምስጋናቸው በቀዳማዊው ፊት አንፃር በሠረገላ ይሮጣሉ/ይመላለሳሉ/።ቀዳማዊ የሚቀድመው የሌለ ማለት ነው።

805. እልፍ አዕላፋት

እልፍ አዕላፋት ወትዕልፊት
ቅዱሳን ንፁሐን መላእክት
ቆሙ ለአገልግሎት ጸንተው በአንድነት
ቅዱስ /፫/ አምላክ በማለት
ኢዮር ራማ ኤረር የመላዕክት ሐገር
የሣይማኖት ጽናት የእምነት ምስክር
እውነት የታየብሽ የመላዕክት አገር
የሳጥናኤል ምኞት እንደ አበባ ረግፎ
ሚካኤል ተሾመ በእምነት ተደግፎ
ሳጥናኤል ወደቀ ፀጋውን ተገፎ
እንጽና ሲል ገብርኤል ባለንበት ቦታ
በሳጥናኤል ነገድ ነበረ ሁካታ
ግማሹ እየካደ ቀሪው ሲያመነታ
ቅዱሳን መላዕክት በእምነት የፀናችሁ
በታላቅ አክብሮት እናመሰግናችሁ
ስግደት ዘበጸጋ እንስገድላችሁ

806. አንስዕ ኃይለከ

አንስዕ ኃይለከ ወንአ አድኅነነ /፪/

ሚካኤል /፪/ ርድአነ

ሚካኤል /፪/ በጸሎትከ ተማኅጠነ /፪/

ኃይልህን አንሳ መጥተህ አድነን /፪/

ሚካኤል /፪/ ተራዳን

ሚካኤል /፪/ በጸሎትህ ለምንማፀን /፪/

807. ከሚካኤል በቀር

ከሚካኤል በቀር የሚያጽናናኝ የለም
ረዳቴ እርሱ ነው በመከራዬ ቀን
ሐዘኔ እጅግ በዝቶ ከሚካኤል በቀር
ያጽናናኝ ሳይኖር ስደቴ ዘመን
ሰላም ከኔ ርቆ ከሚካኤል በቀር
ጭንቀት አስጠብቦኝ በዙሪያዬ ከቦኝ
ዛሬ ግን አፅናኜ ከሚካኤል በቀር
ሚካኤል ደረሰ ጠላት አፈረልኝ
ሚካኤል ነው የዳዊት ረዳት ከጎልያድ ያዳነው
‹‹ መንፈሳዊ ብርታት ኃይልንም
የሰጠው
ቃልኪዳኑ ግሩም ከሚካኤል በቀር
ዝክሩን ለዘከሩት ስሙንም ለጠሩት
አጋንንት አይቀርቡም ከሚካኤል በቀር
ስዕሉ ባለበት ድርሳኑን ቢደግሙት
በረከት ይገኛል ከሚካኤል በቀር
እርሱን ሲማጸኑት ከለመኑት በእውነት
ሚካኤል ነው በትረ መስቀል ይዞ
የሚጠብቀኝ
‹‹ ከአንበሶች መንጋጋ የሚታደገኝ
በኑሮአችን ሁሉ ከሚካኤል በቀር
እርሱ ይመራናል ፈጥኖ ይረዳናል
ፈርኦንን ድል ነስቶ ከሚካኤል በቀር
ከግብጽ አውጥቶናል በብርሃን መርቶናል
የኤርትራን ባሕር ከሚካኤል በቀር
ከፍሎ እንዳሻገረን ከንአን ገብተናል
ሚካኤል ነው ከበለአም እርግማን እስራኤልን ያዳነው
‹‹ ዛሬም በአዲስ ኪዳን ስሙ የገነነው

808. ሰአሉ አስተምህሩ ለነ

ሚካኤል ወገብርኤል ሱራፌል

ወኪሩቤል ዑራኤል ወሩፋኤል

ብርናኤል አቅናኤል ሱባኤል ወፍናኤል

ሰላታኤል ሰዳታኤል ኤልናኤል መላእክተ ምሕረት

ሰአሉ አስተምህሩ ለነ እስመ በጸሎት

ትንብልናክሙ ትድኅን ወኢትማሰን ሀገር

809. ልዑል ውእቱ

ልዑል ውእቱ ልዑለ መንበር /፬/

ሚካኤል /፪/ ልዑለ መንበር /፪/

ትርጉም፡- ከፍ ከፍ ያለነው መቀመጫውም

ከፍ ከፍ ያለነው ሚካኤል መቀመጫው

ከፍ ከፍ ያለነው

810. ሚካኤል ሊቅ

ሚካኤል ሊቅ ልብሱ ዘመብረቅ /፪/

ዓይኑ ዘርግብ ዓይኑ /፬/ ሚካኤል

ሐመልማለ ወርቅ /፪/

ትርጉም፡- አለቃ የሆነው ሚካኤል ልብሱ መብረቅ ነዉ ዓይኖቹም የርግብ ዓይን ይመስላሉ የሚካኤል የወርቅ ሐመልማል ነው

811. አምላክ እስራኤል

አምላክ እስራኤል ታማኝ ጌታችን

ለእሥራኤል ለሙሴ የሆንከው መድኅን

ፈርያን ቢጸና በትዕቢተ ቢገን

ለእሥራኤል አርበኛ መረጥከው ሙሴን

አማላጅ ነው ሚካኤል /፪/ የአምላክ ባለሟል

ለነሙሴ ለሕዝበ እስራኤል

ፈርያን እንደገና ልቡ ተጸጽቶ

ቢከተላቸውም ጦሩን አስከትቶ

ይመራቸው ነበር ሚካኤል በፋና

ሌሊቱን በብርሃን ቀኑን በደመና

ሙሴ እንደታዘዘው አነሣ በትሩን

እጆቹን ዘረጋ ከፈለው ባሕሩን

እንደ ግንብ ቆመ ባሕረ ኤርትራ

በደረቅ አለፉ እሥራኤል በተራ

812. ኃያል ኃያል

ኃያል ኃያል ሰዳዴ ሳጥናኤል /፪/
ኃያል ገባሬ ኃይል
ባሕራንን የረዳው
ተላፊኖስን ያዳነው /፪/
መልአኩ ሚካኤል ነው /፪/
የሞቱን ደብዳቤ የለወጠው
ከዕደ ረበናት /፪/
ሥስናን ያዳናት /፪/

ሚካኤል መልዓከ ምሕረት
ዲያብሎስን ያዋረድከው
በእሳት ሰይፍ የቀጣኸው /፪/
ሚዛንህ ትክክል ነው /፪/
ሚካኤል ክብርህ ድንቅ ነው
በሐዘን በትካዜ
ያለሁትን ብላቴና /፪/
አጽናናኝ አረጋጋኝ /፪/
ሚካኤል ሊቀ ደብረ ሲና

813. ይበራል በክንፉ

ይበራል በክንፉ ምልጃውም ፈጣን ነው
የአምላክ ስም አለበት ስሙ ሚካኤል ነው
ያሳደገኝ መልአክ ዛሬም ከኔ ጋር ነው /፪/
ከፊቴ ቀደመ ደመናን ዘርግቶ
እንዳልደናቀፍ ጉድባዎቼን ሞልቶ
ዛሬ ላለሁበት ብርቱ ጉልበት ሆነኝ
ሰው ለመባል በቃሁ ሚካኤል ደገፈኝ
በእናቴ እቅፍ ገብቼ መቅደሱ
አለሁ እስከዛሬ አጥሮኝ በመንፈሱ
የሕይወቴን ሰልፎች አለፍኩ ከርሱ ጋራ
ተጽፏል በልቤ የሚካኤል ሥራ
በዙሪያዬ ተክሎ የእሳት ምሶሶውን
ፍቅር እየመገበ አሳደገኝ ልጁን
የአምላኬን ምስጋና ዘውትር እያስጠናኝ
እሱ ነው ሚካኤል በመዝሙር የሞላኝ
ፊት ለፊት ተተክሎ በታናሿ መንደር
ይሰማኝ ነበረ ቅኔው ሲደረደር
የወስደኛል ደጁ እየቀሰቀሰ
ታላቁን በረከት በውስጤ አፈሰሰ
ሴኬምን እንዳላይ ክንፎቹን ጋረደ
መራኝ ወደ ሕይወት መዳኔን ወደደ
የሞአብን ቋንቋ ከአፌ ላይ አጥፍቶ
በፀጋው ቃል ቃኘኝ በበረከት ሞልቶ

814. በአምሳለ ርግብ

በአምሳለ ርግብ ወረደ መልአክ ወረደ /፪/
ወረደ /፬/ ሚካኤል መልአክ ወረደ /፪/

815. ቅዱስ ሚካኤል

ቅዱስ ሚካኤል /፪/ ነፍሴ ሲጨነቅ ሲዝል ስጋዬ
ፈጥነህ ተራዳኝ ዋስ ጠበቃዬ
አንተ ስለሆንክ ሚካኤል
የአምላክ ባለሟል ››
ልመናህ ፈጥኖ ››
ከአምላክ ያቀርባል ››

የዋህ መላክ ነህ አዛኝ ለሰው
ምልጃህ ፈጣን ነው ለምናምነው /፪/
ደቄ የፀናበት ሚካኤል
ባንተ ይድናል
በአደባባይህ
ምስክር ሆኗል
ከቤቱ ወጥቶ የተማጸነ
በቃል ኪዳኑ ሕይወቱ ዳነ
ከአምላክ ተሰጥቶህ ሚካኤል
ክርብር ያበራል
ለጎስቋላው ሰው
መጠጊያ ሆኗል
ትልቅ ትንሹ ደህው ሀብታሙ
ለምኖ አግኝቷል ከአምላክ በስሙ
በብሉይ ኪዳን ሚካኤል
ከአምላክ ተልከህ
ሕዝበ እስራኤልን
ነፃ ያወጣህ
በአዲስ ኪዳንም ድንቅ ስራ አለህ
በታምራትህ ትፈውሳለህ
ባለመድኃኒት ሚካኤል
ያቃተውን
ፈዋሽ ጸበልህ
ሆኖናል ኃይል
እንደ መፃጉዕ ድኅነት አገኘሁ
ፈውሰኸኛል ባንተ ተመካሁ

816. ሐመልማለ ወርቅ

ሐመልማለ ወርቅ /፫/
ሚካኤል /፫/ ልብሱ ዘመብረቅ

817. ሰራዊተ

ሰራዊተ /፪/ መላእክቲሁ
ለመድኃኒዓለም /፪/ ይቀውሙ /፪/

818. ከመ ትባርከነ

ከመ ትባርከነ በመስቀልከ ዘወርቅ /፪/
ተዋነይ በጽድቅ /፬/ ሚካኤል ሐመልማለ ወርቅ

819. ተወከፍ

ተወከፍ ጸሎተነ ውስተ ኖሐ ሰማይ
ከመ መዓዛ ሰናይ /፫/ ሊቀ መላዕክት

820. ባሕራንኒ

ባሕራንኒ ይቤ /፪/ እም ዘነገደ ባሕር
ርኢኩም ለሚካኤል ወሰእንኩ ጠይቆቱ ዘይብል
የሞቱን ደብዳቤ ቅዱስ ሚካኤል
ሚካኤል አጥፍቶ
ባሕራንን አዳነው
በሠርግ ተክቶ
ሰዳዴ ሳጥናኤል
ሊቀ መላዕክት
እኛንም አድነን
ከሲኦል እሳት
ከሊቀ ነቢያት ቅዱስ ሚካኤል
ከነሙሴ ጋራ
ሕዝበ እስራኤልን
ሚካኤል ሲመራ
ቀን ደመና ጥሎ
ሌሊት እያበራ
ተሻገሩ እስራኤል
ሁሉም በየተራ

821. ኦ ሚካኤል

ኦ ሚካኤል /፪/ ሊቀ መላእክት
በኃጢአት እንዳንወድቅ እንዳንሞት
ፈጥነህ ተራዳን አጽናን በእምነት
ለያዕቆብ ነገድ ሚካኤል
ለእስራኤል ››
ጠባቂቸው ነህ ››
መልአከ ኃይል ››
ፍቅርን አድለን ምሕረት
ቅዱስ ሚካኤል የኛ አባት /፪/
ነጸብራቃዊ ሚካኤል
ተክህኖ ልብስህ ››
ሐመልማለ ወርቅ ››
ዓይኑ ዘርግብ ››
ፍቅርን አድለን ምሕረት
ቅዱስ ሚካኤል የኛ አባት /፪/
በስዕልህ ፊት ሚካኤል
እሰግዳለሁኝ ››
ፈጥነህ አረጋጋኝ ››
አለሁ በለኝ ››
ፍቅርን አድለን ምሕረት
ቅዱስ ሚካኤል የኛ አባት /፪/

822. አማላጅ ነው

በፍጡራንና ፈጣሪ መካከል
ድርሻ የተሰጠው ሰውን ለማገልገል
ተራዳኢው መልዓክ ጠባቂ የእስራኤል
የመላዕክት አለቃ ስሙ ነው ሚካኤል
አማላጅ ነው ሚካኤል /፪/ የአምላክ ባለሟል
ለነ ሙሴ ለሕዝበ እስራኤል /፪/

ፈርኦን በእስራኤል ላይ በትዕቢት ተነስቶ
ቢከታተላአቸው ጦሩን አስከትቶ
ይመራቸው ጀመር ሚካኤል በፋና
ሌሊቱን በብርሃን ቀኑን በደመና
ከባሕር ያወጣው ጸጋ ዘአብን
ከአረመኔው ንጉሥ እግዚሐርያን
ከልለህ የጠበቅህ በብዙ ተአምራት
እኛንም ጠብቀን ከበደል ከኃጢአት
በአፎምያ ላይ ሲፎክር ጠላት
ፈጥነህ ደረስከው ሊቀ መላዕክት
እኛንም ጠብቀን ከክፉ መቅሰፍት
ፈጥነህ ድረስልን ሁነን ረዳት
መላኩ ሚካኤል አማላጃችን
እንለምንሀለን እንድትጠብቀን
አምላክ በፍርድ ቀን ፃድቃንን ሲጠራ
ዋስ ጠበቃ ሁነን ሚካኤል አደራ

823. ቅዱስ ሚካኤል

ቅዱስ ሚካኤል ወዳጅ ነህ ለሁሉ
ዛሬም ቆመሀል በኪዳንህ ላሉ
ክንፍህን ዘርጋ ሚካኤል ቅደም ከፊቴ
ምራኝ መንገዱን እንዳይመሽ ልድረስ
ከአባቴ
እንዴት ይገፋል ጎዳናው ላንተ እርዳታ
ጥሜን ቁረጠው በበትርህ ጭንጫውን ምታ
/፪/
ተጠመጠመ ጠላቴ በእሳት ሰንሰለት
የጌታ መልአክ ሚካኤል በሰይፍ ወድቆበት
የለም በቦታው ስመለስ አጥቼዋለሁ
የሚረዳኝን ተሹሞ አይቼዋለሁ /፪/
ከመቃብሩ ድንጋዩን አንከባለህል
ስለረዳኸው ዳንኤል እጅግ ወዶሀል
ይነዋወጻል ባሕሩም አንተ ስትመጣ
እግዚአብሔር ይንገስ ዲያብሎስ መድረሻ
ይጣ /፪/
አለኝ ትዝታ በቤትህ ከልጅነቴ
ስትሳላልኝ እያየሁ ጸንቷል ጉልበቴ
ልዘምር እንጂ ላመስግን ታላቁን ጌታ
አንተን የሰጠኝ ጠባቂ በቀን በማታ /፪/

824. ዓይኑ ዘርግብ

ዓይኑ ዘርግብ ልብሱ ዘመብረቅ
ሐመልማለ ወርቅ /፬/ ሚካኤል

825. የስሙ ትርጓሜ

የስሙ ትርጓሜ ማን እንደ እግዚአብሔር ነው
የሰውን ወደ አምላክ የአምላክን ወደ ሰው
እኛን የሚረዳን ዘወትር በምልጃው
የመላዕክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ነው
ከጉድጓድ ተጥሎ ፍፁም ከሚያስፈራው
ከተራቡ አናብስት ዳንኤልን ያዳንከው
እኛንም ተራዳን ቸል አትበለን
ሰይጣን በተንኮሉ ወጥመድ ሳይጥለን
የክፉ ሰው ስራስ ክፉ ሀሳብ ነውና
በቅንነት መንገድ ከቶ አይሄድምና
የሞቱን ደብዳቤ ለባሕራን ቢሰጠው
ሚካኤል አጥፍቶ በደስታ ለወጠው
ገና ብላቴና ሳለሁ አንድ ፍሬ
ሰው ሁሉ ሲንቀን ምስጋናን ጨምሬ
ጸጋዬን አብዝቶ ያበቃኝ ለዚህ ክብር
የሚካኤል አምላክ ይመስገን እግዚአብሔር

826. ገብርኤል ነው

ገብርኤል ነው በእውነት አስደሳች መልአክ
ትርጓሜው ሰውና አምላክ /፪/
ቂርቆስ ከእናቱ ጋር ወደ እሳት ሲጣሉ
ውኃ ሆነ ጠፋ ነበልባሉ /፪/
ሠለስቱ ደቂቅ ወደ እሳት ሲጣሉ
ውሃ ሆነ ጠፋ ነበልባሉ /፪/

827. ቅዱስ ገብርኤል እርዳን

ቅዱስ ገብርኤል እርዳን ሊቀ መላዕክት /፪/
ልጆችህን አውጣን ከሚነድ እሳት
‹‹ ‹‹ ከዓለም እሳት
ከማይጠፋው እሳት ከዚያ ነበልባል
ከጨለማው ስርዓት ከከፋው ሲኦል
ነፍሳችንን ነጥቆ ሰይጣን እንዳጎዳን
ዋስ ጠበቃ ሁነን ቅዱስ ገብርኤል እርዳን /፪/
ረድኤት በረከትህ ከእኛ እንዳለየን
እንለምንሀለን አደራ እንዳትረቀን
የቀደመው ጠላት ዙሪያችንን ከቧል
ቅዱስ ገብርኤል ድረስ የእግዚአብሔር ባለሟል /፪/
ናቡከደነፆር ምንም ቢቆጣቸው
እሳት አስነድዶ ከዚያ ቢጥላቸው
ከራሳቸው ጸጉር አንዷ እንኳን ሳትጠፋ
ቅዱስ ገብርኤል ደርሶ ሆነላቸው ተስፋ /፪/
ብቸኝነት ከቦን ሐዘን ሲያስጨንቀን
እኛ እንጠራሀለን ቅዱስ ገብርኤል ብለን
በፈጣሪያችን ፊትስለእና ቆመሀል
የነደደብንን እሳት አብርደሀል /፪/
ስልጣንህ ክቡር ነው በአምላክ ፊት
በእውነት
እንሰግድልሀለን የፀጋ ስግደት
ፈጥነህ ምትሰማን ወዳንተ ስንጮህ
የመላዕክት አለቃ ቅዱስ ገብርኤል ነህ /፪/

828. ንቁም በበህላዌነ

ንቁም በበህላዌነ /፪/
እስከ ንረክቦ ለአምላክነ /፪/
ጌታችንን እስክናውቀው በልዕልና
ባለንበት እንፅና
ይህን ብለህ መላዕክትን እንዳረጋጋህ
ቅዱስ ገብርኤል አጽናን በምልጃህ
አጠንክረን በሃማኖት በምግባርም
ከክህደት ጥርጥር አውጣን
ቁሙ በለን በሃይማኖት ለዘወትር
እንድንበቃ ለክብር
ቅዱስ ገብርኤል አረጋጊ አጽናኝ መልአክ
መላእክትን በሰማያት እንጽና ያልክ
ከሃማኖት ልንወጣ ስንባዝን
ናና ባርከን ቅዱስ ገብርኤል ሆይ አጽናን

829. ኃያል ነህ

ኃያል ነህ አንተ ኃያል
ደጉ መላዕክ ገብርኤል /፪/
ይውደቅ ይሸነፍ ጠላት
አንተ ተራዳን በእውነት /፪/
በዱራ ሜዳላይ ገብርኤል
ጣኦት ተዘጋጅቶ ››
ሊያመልኩት ወደዱ ››
አዲስ አዋጅ ወጥቶ ››
ሲድራቅና ሚሳቅ አብድናጎም ጸኑ
ጣኡቱን ረግጠው በእግዚአብሔር አመኑ
ተቆጣ ንጉሡ ገብርኤል
በሦስቱ ህፃናት ››
ጨምሯቸው አለ ››
ወደ እቶን እሳት ››
ከሰማይ ተልኮ ደረሰ መልአኩ
ከሞት አዳናቸው በእሳት ሳነኩ
ከእቶኑ ስር ሆነው ገብርኤል
ዝማሬ ተሞሉ ››
ገፍተው የጣሉዋቸው ››
በእሳቱ ሲበሉ ››
አልተቃጠለችም የራሰቸው ጸጉር
አዩት መኳንንቱ የእግዚአብሔርን ክብር
ናቡከደነጾር ገብርኤል
እጁን በአፉ ጫነ ››
ሠለስቱ ደቂቅን ››
ከእሳት ስላዳነ ››
ይክበር ጌታ አለ የላከ መልአኩን
ሊያመልከው ወደደ ስላየ ማዳኑን

830. እግዚኡ ረሰዮ

እግዚኡ ረሰዮ ለውእቱ ሚካኤል /፪/
አምኩሎሙ መላእክት /፪/ ይትሌዐል መንበሩ

ትርጉም፡- ጌታው ሚካኤልን ከመላእክት ሁሉ መንበሩን ከፍ ከፍ አደረገው።

831. ሊቀ መላእክት

ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል

ሰይጣንን ድል ያደረግህ በፈጣሪ ኃይል

የኃይላት አለቃ የትጎትና መልአክ

እናመስግን አንተን አፎምያን ያዳንክ

ኃያሉ መልአክ ቅዱስ ገብርኤል

ልደትን ያበሠርክ ለማርያም ድንግል

መልአከ ብሥራት መልአከ ብሥራት

መልአከ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል

ፈታሔ ማኅፀን ቅዱስ ሩፋኤል

የሰዎችን ችግር ፈጥነህ ይታቀል

በአንተ አማላጅነት ፈጣሪን ስንለምን

ቶሎ ድረስና ረድኤትህን ስጠን

መጋቤ ብርሃናት ቅዱስ ራጉኤል

ለምስጋና ትጉህ ቀን ሌሊት ሳትል

ሥዕልህ ፊት ቆመን አንተን ስንማፀን
እዘንልንና ገጽህን አብራልን

ቅዱስ ዑራኤል ሊቀ መላእክት

ኢትዮጵያን የባረክህ በድንግል ስደት

መልአከ ሰላም ነህ መልአከ ሰላም

በመስቀልህ ባርካት ይህችን ዓለም

ቅዱስ ፋኑኤል ብርሃናዊ መልአክ
ሰማያዊ ጎብስት ለድንግል የመገብክ
በነፍስ በሥጋ ረኃብ ጠውልገን እንዳንደርቅ
ምልጃህ አይለይን በሲያል እንዳንወድቅ

ባህርና ወንዝ በልክ እንዲሞሉ

ዝናብ የምታሰጥ በዓለም በሙሉ

በኃጢአት እንዳንወድቅ ፍሬ ሳናፈራ

ቅዱስ ሳቁኤል ሆይ ጠብቀን አደራ

832. ሩጎሩጎ መልኣክ

ሩጎሩጎ መልአክ ነህና ለሁሉ ምትራራ /፪/
ገብርኤል አዛኙ አንተ አውጣን ከመከራ /፪/

የሚያሳድዱኝን ገብርኤል
የቆሙ ከፊቴ ››
ጋሻ ይሆነኛል ››
ጠባቂው አባቴ ››
እሳተ ነበልባል ››
ኃያል መላዕክ ነህ ››
ስምህን ሲጠሩ ››
ፈጥነህ ትደርሳለህ ››
በራማ ምትኖር ገብርኤል
የመላዕክት አለቃ ››
አብሳሪ መልአክ ነህ ››
የኛ ዋስ ጠበቃ ››
ቂርቆስና እናቱን ››
አንተ አዳንካቸው ››
ከእግዚአብሔር ተልከህ ››
ከሞት ሰወርካቸው ››
ለነሚሳኤል ገብርኤል
ለነአናንያ ››
ረዳት ሆንካቸው ››
ለነአዛርያ ››
ለኛም መድኃኒት ነህ ››
በእውነት ለለመንህ ››
ሁሌም ትደርሳለህ ››
በአማላጅነትህ ››

833. አማልደን

ገብርኤል አማልደን ከአምላካችን /፪/
እንዳንጠፋ እንዳንሞት በነፍሳችን
አደራህን ቁምልን ከጎናችን /፪/

834. ሚካኤል ሐመልማለ ወርቅ

ሚካኤል ሐመልማለ ልብሱ ዘመብረቅ

ሚካኤል ሐመልማለ ወርቅ የወርቅ ልምላሜ

የወርቅ ልምላሜ ና ና ና ስለምንህ ቆሜ ሚካኤል

ገብርኤል ሊቀመላእክት /፪/

ሠለስቱ ደቂቅን ያወጣህ ከእሳት

በሠለስቱ ደቂቅ ናቡከደነፆር ተቆጣ

እሳቱ ነደደ ነበልባሉ ወጣ

ግን ኃያል ገብርኤል ሊያድናቸው መጣ

ገብርኤል

ሠለስቱ ደቂቅ ይባርክዎ ለእግዚአብሔር

ስቡሕኒ እቱ ወልዑልኒ ውእቱ ብለው

ምስጋና አቀረቡ ከእሳቱ ላይ ሆነው

835. ስዩም በዲበ ኃይላት

ስዩም በዲበ ኃይላት ሩፋኤል ሊቀመላእክት /፪/

በዲበ ኃይላት /፬/
ሩፋኤል ሊቀመላእክት } /፪/

ትርጉም፡- በኃያላን መላእክት ላይ የተሾመ
የመላእክት አለቃ ሩፋኤል ነው።

836. ብቃት ስለሌለህ

ብቃት ስለሌለህ ባትችል ልታያቸው

ብቻህን የተጣልክ ሰዎች ቢመስላቸው

ከአንተ ጋራ ያሉት እጅግ ብዙ ናቸው

ድካም ብቸኝነት የሶርያ ጭፍራ

ችግር ሰይፉን መዞ ከቦ ሲያስፈራራ

አለቀልኝ ብለህ ልቤ ሆይ አትፍራ

ቅዱሳን መላእክት አሉ ከአንተ ጋራ

ተሰደህ ብትሄድ በባቢሎን ማዶ

ኑሮህ ሬት ሲሆን ማዕረግህ ተዋርዶ

በዕንባ ብትዋጥም ጽዮንን አያስብህ

በዙሪያህ ሰፍረዋል መላእክት ሊያጽናኑህ

ዓለም ኢያሪኮ ሰባት ግንብ አጥራ

ኃጢአት ስታደባ ቀስቶቿን ወጥራ

የተሸነፍክና ያለቀ ሲመስልህ

የእግዚአብሔር ሠራዊት በዙሪያህ አሉልህ

837. ሠለስቱ ደቂቅን

ሠለስቱ ደቂቅን ያወጣህ ከእሳት /፪/

እኛንም አድነን /፪/ ሊቀመላእክት

እኛንም አድነን ገብርኤል ሊቀመላእክት

ቂርቆስ እየሱጣን ያወጣህ ከእሳት /፪/

እኛንም አድነን /፪/ ሊቀመላእክት

እኛንም አድነን /፪/ ገብርኤል ሊቀመላእክት

ሠለስቱ ደቂቅን ያወጣህ ከእሳት /፪/

እኛንም አድነን /፪/ ሊቀመላእክት

እኛንም አድነን ገብርኤል ሊቀመላእክት

838. እም እቶነ እሳት

እም እቶነ እሳት /፪/ ዘይነድድ

አንገፈነ በሰፊሐ እድ ሊቀ መላእክት /፪/

ታላቅ መመኪያ ነህ ለሚያምኑብህ ሁሉ
ናዛዜ ጎዙናን /፪/ ገብርኤል ለልዑል መልአከ ኃይሉ

የነበልባል ኃይሉ ሞገሱ ሲበዛ

ለሠለስቱ ደቂቅ የሆንካቸው ቤዛ

(ታላቅ መመኪያ ነህ)

ፈጥነህ የምትደርስ በዕለት ጻሕቅ

ምስጉን ነህ አንተ ከፍ ያልክ በጽድቅ

(ታላቅ መመኪያ ነህ)

ዜናዊ ፍስሐ ለሰው ልጅ ድህነት

የሰላም መልአክ ነህ ሊቀ መላእክት

(ታላቅ መመኪያ ነህ)

በአማላጅነትህ እንኮራለን

እኛ ክርስቲያኖች ደቂቀ ጽዮን

(ታላቅ መመኪያ ነህ)

የግእዙ ትርጉም፡- ከሚነደው የእሳት ነበልባል
የመላእክት አለቃ እጆቹን ዘርግቶ አተረፈን፡፡ በዕለተ ጻሕቅ፡- በጭንቅ ቀን

839. አንስዕ ኃይለከ

አንስዕ ኃይለከ ወንአ አድኅነነ /፪/

ሚካኤል /፪/ ርድአነ
ሚካኤል በጸሎትከ ተማኅፀነ /፪/

ኃይልህን አንሳ መተህ አድነን /፪/

ሚካኤል /፪/ ተራዳን
ሚካኤል /፪/ በፀሎትህ ለምንማፀን /፪/

840. እንደ አናንያ

እንደ አናንያ እንደአዛርያ እንደ ሚሳኤል
አጽናን እኛን /፪/
አጽናን እኛን /፫/ በእምነታችን /፪/

841. ገብርኤል

ገብርኤል አብሠራ ለድንግል ወይቤላ /፪/
ትወለዲ ንጉሥ ገብርኤል ይቤላ /፪/
ትርጉም፡- ለእመቤታችን ገብርኤል አበሠራት
እንዲህም አላት ንጉሥ ትወልጃለሽ

842. አማልደን ስንልህ

አማልደን ስንልህ ስማን እዘንልን /፪/
አጽናን አረጋጋን /፪/ ገብርኤል የእኛ መመኪያ አባታችን

እግዚአብሔር ራሱ ክብርን አቀዳጅቶህ
ለተልእኮ እንድትፈጥን አድርጎ የሾመህ
እንደ ሦስቱ ሕፃናት አንተን እንደጠሩ
ዛሬም አውጣን ገብርኤል ሆይ ከነፍሳችን ጠላት

እምነት አለን እያልን የቀና ምግባር
እባክህን ሊቀመላእክት እንድስት ርዳን
መላእክትን ሁሉ ያረጋጋሀቸው
አንተኮ ነህ ኃያል መልአክ ጽኑ ቁሙ ያልካቸው

እኛስ እናምናለን በአማላጅነትህ
በተሠጠህ በአምላክ ጸጋ ኃይላችን አንተ ነህ
የምሥራች መልአክ ተብለሃልና
ደስ አሰኝን ደስታ ስጠን ተጨንቀናልና

ኢትዮጵያንም ታደግ ተዋሕዶንም ጠብቅ

ሊቀመልአክት በል ቁምልን ሰይፍህንም ታጠቅ
ሠራዊትህ ከበው እነርሱ ያጽናኑን
ዘወትር ሳትርቀን ሰላምን ለግሠን

843. ኦ ገብርኤል

ኦ ገብርኤል መልአክ ናዝዘኒ ወአጽምአኒ ቃልከ /፪/
አይመርየ /፪/ በእንተሰ አሰስኩ ኪያከ /፪/
ትርጉም፡- ቃልህ አረጋጋኝ አጸናኝ ስለዚህ አውቄ
አንተን ፈለኩህ

844. ዉእቱ ሊቆሙ

ዉእቱ ሊቆሙ ለመላእክት ወመላእኮሙ ስሙ
ሚካኤል /፪/ ልብሱ ዘመብረቅ ዓይኑ ዘርግብ ሊቀ
መላእክት /፪/
ትርጉም፡- ለመላእክት አለቃቸዉ እርሱ ነዉ ስሙም
ሚካኤል ነዉ የሚካኤል ልብሱ የመብረቅ ዓይኖቹም
የርግብ ዓይኖች ይመስላሉ

845. ሊቀ መላእክት

ሊቀ መላእክት ሚካኤል መላእከ ምክሩ ለልዑል /፪/
ኃያል /፪/ ሰዳዴ ሳጥናኤል ኃይል ገባሬ ኃይል /፪/
ትርጉም፡- የመላእክት አለቃ ሚካኤል ለልዑል
አማካሪ ነዉ ሰይጣንን ያሳድዳል (ያባርራል)

846. ሚካኤል ስዩም

ሚካኤል ስዩም /፪/ ሊቀ መላእክት /፪/
መዝገበ ርህራሄ /፫/ የዋህ /፪/
ትርጉም፡- የመላእክት አለቃ ሚካኤል የዋህ የርህርሄ
መዝገብ ነዉ።

847. ገብርኤል

አማልደን ከአምላካችን /፪/
እንዳንጠፋ እንዳንሞት በነፍሳችን
አደራህን ቁምልን ከጎናችን /፪/

848. የብርሃናት አለቃ

የብርሃናት አለቃ የጌታ ባለሟል ሊቀ
መላእክት /፪/
ንዓ ራጉኤል /፬/ ራጉኤል መጋቤ
ብርሃናት /፪/ ኸኸ /፪/

ከዋክብትን ልትመግብ ፀሐይን ልትመራ
ሥልጣን የተሠጠህ
ሥራህ የደመቀ ራጉኤል አንተ ነህ /፪/
ራጉኤል መጋቢ ብርሃን /፪/ ኸኸ

አዝርእት አብበው ፈክተው
የሚታዩት እጅጉን ለምልሞው/ኸኸ/ /፪/
በፀሐይ ብርሃን በአንተ አጋዥነት ነው /፪/
ራጉኤል መጋቤ ብርሃን /፪/ ኸኸ

849. ቅዱስ ገብርኤል ርዳን

ቅዱስ ገብርኤል ርዳን ሊቀ መላእክት /፪/
ልጆችህን አውጣን ከሚነድ እሳት
ልጆችህን አውጣን ከዓለም እሳት

ከማይጠፋው እሳት ከዚያ ነበልባል
ከጨለማው ሥርዓት ከክፉ ሲኦል
ነፍሳችንን ነጥቆ ሰይጣን እንዳይጎዳን
ዋስ ጠበቃ ሁነን ቅዱስ ገብርኤል ርዳን /፪/

ረድኤት በረከትን ጸጋህ አይለየን
እንለምንሃለን አደራ እንዳትርቀን
የቀደመው ጠላት ዙሪያችን ከቦናል
ቅዱስ ገብርኤል ድረስ የእግዚአብሔር
ባለሟል /፪/

ናቡከደነጾር ገደል ሲከታች
እሳቱን አንድዶ ከእሳት ቢጥላቸው
ከራሳቸው ፀጉር አንድ እንኳን ሳይጠፋ
ቅዱስ ገብርኤል ደርሶ ሆነላቸው ተስፋ /፪/

ብቸኝነት ከብዶን ሐዘን ሲያስጨንቀን
እኛ እንጠራሃለን ቅዱስ ገብርኤል ብለን
በፈጣሪያችን ፊት ስለእኛ ቆመሀል
የነደደብንን እሳት አብርደሃል /፪/

ሥልጣንህ ግሩም ነው በአምላክህ ፊት
እንሠግድልሀለን የጸጋ ስግደት
ፈጥነህ የምትሰማን ወዳንተ ስንጮህ
የመላእክት አለቃ ቅዱስ ገብርኤል ነህ /፪/

850. ገብርኤል መጽአ

ገብርኤል መጽአ ይርድአነ ወያድኅነነ /፪/
ተፈኒዎ /፪/ እም አርያም /፪/ ከመ
ያድኅነነ /፪/
ገብርኤል መጣ ሊረዳን ሊያድነን /፪/
ተልኮ /፪/ ከሰማይ /፪/ እኛን ሊያድነን

851. ይቀልል

ይቀልል ሩጸቶሙ /፪/
እም ነፍሳት ሑረቶሙ /፪/
ትርጉም፡- ሩጫቸው ከነፋስ ይፈጥናል

852. ገብርኤል ምልአኒ

ገብርኤል ምልአኒ መንፈሰ ልሣን
ለተናብቦ መንፈሰ ልሣን /፪/
ሞጣእተ ብርሃን /፪/ ዘይት ገለብቦ ሞጣእተ
ብርሃን /፪/

853. ራጉኤል ከሰማያት

ራጉኤል ከሰማያት እኽ
በልእልና ወረደ በልእልና /፪/
ፈጣሪያችን አማኑኤል እኽ
ልመናችንን ተቀበል በራጉኤል
ልመናችን ተቀበል በሩፋኤል
ልመናችን ተቀበል በሚካኤል
ልመናችን ተቀበል በገብርኤል
ሚካኤል ከሰማያት እኽ
በልእልና ወረደ በልእልና
ፈጣሪያችን አማኑኤል እኽ
ልመናችን ተቀበል በሚካኤል
ልመናችን ተቀበል በገብርኤል
ልመናችን ተቀበል በኡራኤል
ልመናችን ተቀበል በሳቁኤል
ፈጣሪያችን አማኑኤል እኽ
ልመናችን ተቀበል በራጉኤል
ልመናችን ተቀበል በፋኑኤል
ልመናችን ተቀበል በሚካኤል
ልመናችን ተቀበል በገብርኤል
ገብርኤል ከሰማያት
በልእልና ወረደ በልእልና /፪/
ምልጃውን ሰምተህ የራጉኤልን /፪/
አድነን ጌታ ልጆችህ እንዳንባዝን /፪/
ተስፋ ስናደርግ ምሕረትህን /፪/
ስለ ወዳጅህ ሕዝብህን አድንልን
ስለ ወዳጅህ ኢትዮጵያን ጠብቅልን /፪/

854. ጸሊ ኀበ አምላክ

ጸሊ ኀበ አምላከ ራጉኤል መልአክ
ዓውደ ዓመት ከመ ይትባረክ /፬/
ትርጉም፡-ዓውደ ዓመቱ ይባረክ ዘንድ ራጉኤል
መልአክ ወደ አምላክ ጸልየ/ለምን/

855. ና ና ገብርኤል

ና ና ገብርኤል መልአከ ራማ
ዘውገ ማርያም አሐቲ ድንግል /፪/
ዘዳግመ በሉ እሰይ ዘዳግመ ጽጌ ይበል
አምላለ ኪያሁ ዘይመስል አልቦ ካህን ጥዑመ ልሳን
/፪/

856. ሚካኤል ሐመልማለ ወርቅ

ሚካኤል ሐመልማለ ወርቅ /፪/ ልብሱ ዘመብረቅ /፪/
ሚካኤል ሐመልማለ ወርቅ የወርቅ ልምላሜ /፪/ ና
/ፒ/ ስለምንህ ቆሜ
ገብርኤል ሊቀ መላእክት /፪/
ሠለስቱ ደቂቅን ያወጣ ከእሳት
ሠለስቱ ደቂቅ ይባርክም ለእግዚአብሔር
ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ብለው
ምስጋና አቀረቡ ከእሳቱ ላይ ሆነው
ገብርኤል ሊቀ መላእክት /፪/
ሠለስቱ ደቂቅን ያወጣ ከእሳት
ራጉኤል ሊቀ መላእክት /፪/
እመ ኀበ ላዕለ ወረደ /፪/
መጋቤ ብርሃናት አንሶላዊ ፋና
ራጉኤል ና /ፏ/ አማላጅ ነህና
ራጉኤል ሊቀ መላእክት /፪/
እመ ኀበ ላዕለ ወረደ /፪/
ዑራኤል ሊቀ መላእክት /፪/
ለዕዝራ ያጠጣህ ፅዋዐ ሕይወት
በዓለም ፈተና በስቃይ ኑነኔ
ስባዝን ስጨነቅ ስጠበብ ወይ እኔ
ዑራኤል የእኔ ኃይል ቁምልኝ ከጎኔ
ዑራኤል ሊቀ መላእክት /፪/
ለዕዝራ ያጠጣህ ፅዋዐ ሕይወት

857. አዕርግ ጸሎትነ

አዕርግ ጸኖትነ ውስተ ኑኃ ሰማይ /፪/
ከመ መዓዛ ፀሐይ /፬/ ሊቀ መላእክት /፪/

858. መልአከ ሰላምነ

መልአከ ሰላምነ ሊቀ መላእክት ሚካኤል /፪/
ሰአል ወጸሊ በእንቲአነ አዕርግ ጸሎተነ
ቅድመ መንበሩ ለመድኃኔዓለም
ትርጉም፡-የሰላም መልአክ ቅዱስ ሚካኤል ስለ እኛ
ለምንልን ጸሎታችንንም በመድኃኔዓለም ፊት
አሳርግልን

መዝሙር በእንተ ሰማዕታት

859. ጊዮርጊስ ኃያል

ጊዮርጊስ ኃያል /፪/ መስተጋድል
ኧኽ ገባሬ ተአምር /፪/ ኮከበ ክብር /፪/

860. እምሔሶ ለሄሮድስ

እምሔሶ ለሄሮድስ ይብላዕ መሐላሁ /፪/ እም
ያምትር ርዕሶ ለዮሐንስ /፪/ ዐቢይ ነቢይ /፪/ ሰባኬ
ወንጌል /፬/
ትርጉም፡- ሄሮድስ ዋና ነቢይ የሆነውንና የጥምቀት
ሰባኪ የዮሐንስን አንገት ከሚያስቆርጥ መሐላዉን
ቢበላ ይሻለዉ ነበር

861. ወአንተኒ ሕፃን

ወአንተኒ ሕፃን ነቢየ ልዑል /፬/
አርኩ ለመርዓዊ ትሰመይ /፪/ ነቢየ ልዑል /፪/
ትርጉም፡- አንተ ሕፃን የልዑል ነቢይ የሙሽራው
ክርስቶስ መንገድ ጠራጊ ትባላልህ /ትሰኛለህ/

862. ገድልከ ግሩም

ገድልከ ግሩም ነገርከ ጥዑም /፪/
ጊዮርጊስ /፫/ ንአ በሰላም

863. ኦ ፍጡነ ረድኤት

ኦ ፍጡነ ረድኤት /፪/
የእግዚአብሔር አገልጋይ
ቅዱስ ሰማዕት
ሰላም ላንተ ይሁን ፍጡነ ረድኤት
የልዳው ፀሐይ
በጨካኝ ንሉሥ ፊት ቆምክ አደባባይ
ታማኝ አገልጋይ ነህ ፍጡነ ረድኤት
ስቃይ ያልበገረህ
አክሊልን አገኘህ መከራን ታግሰህ
ለእምነቱ ተጋዳይ ፍጡነ ረድኤት
ታማኝ ወታደር
ቢነገር አያልቅም የተሰጠህ ክብር
ስቃይ ሲያደርሱብህ ፍጡነ ረድኤት
በመታገስህ
ሲወሳ ይኖራ ዘላለም ስምህ
የፈጣሪውን ስም ፍጡነ ረድኤት
ስለመሰከረ
ጊዮርጊስ ሰማዕት በሰይፍ ተመተረ
የስቃይ መሳሪያ ፍጡረ ረድኤት
ያላዘናጋህ
መንፈሳዊ አርበኛ ጊዮርጊስ አንተ ነህ
ለሰማው ይደንቃል ፍጡነ ረድኤት
ያንተ ሰማዕትነት
ምሳሌ ይሆናል ለሁሉም ፍጥረት
ገድልህ ይናገራል ፍጡነ ረድኤት
ክብር እንደተሰጠህ
ጊዜ የማይሽረው ምግባር ሃይማኖትህ

864. ጊዮርጊስ በዚያች ቀን

ጊዮርጊስ በዚያች ቀን ከፈተናው አንፃር
ስለሃይማኖቱ የታየው ምን ነበር
ያመነውን አምላክ አላውቀውም እንዲል
በሥልጣን በገንዘብ እርሱን ለመሸንገል
የዱድያኖስ ጭፍሮች ነገር ሲያሴሩበት
ልቡናው ምን አለ ሲቀርብ ለመሥዋዕት
ስገድ ባሉት ጊዜ ሰው ለሠራው ምስል
ትዝ አለው ጊዮርጊስ የአምላኩ ሕያው ቃል
ከሠለስቱ ደቂቅ ከዳንኤል ጋር
በእሳት ነበልባል ውስጥ ተአምር ሲሠራ
ቂርቆስ ኢየሉጣን ከመቃጠል ዋጅቶ
ያቀዘቀዘውን ፍሉን ውኃ አጥፍቶ
አስታውሷል ጊዮርጊስ ያንን ኃያል ጌታ
መስቀል መሸከሙን በዚያች ጉልጉታ
ጴጥሮስና ጳውሎስ አባቶቹን መስሎ
ሞትን አሸነፈ በእምነት ተጋድሎ
እንድንጸና በእምነት ይህችን ዓለም ንቀን
በሰማዕቱ ምልጃ አምላክ ይጠብቀን

865. አማን በአማን

አማን በአማን /፬/
መርቆሬዎስ ትሩፈ ገድል

866. ሰማእታት የዚህችን

ሰማእታት የዚህችን ዓለም ጣእም በእውነት
ናቁ /፪/
ደማቸውን ስለ እግዚአብሔር አፈሰሱ /፪/
ስለ መንግሥተ ሰማያት መራራ ሞትን
ታገሱ /፬/

867. ዮሐንስ

ዮሐንስ መጥምቀ መለኮት /፪/
በረከትህ ይደር በኛ ሕይወት /፬/

868. ቅዱስ ጊዮርጊስ

ቅዱስ ጊዮርጊስ /፪/
ቅዱሰ ጊዮርጊስ አማለደን /፪/
ከመድኃኔዓለም አስታረቀን /፪/
ፈጣሪ አምላካችን ማረን /፬/
በእውነት ይቅር አለን /፬/

869. ሕፃን መእሙ

ሕፃን ወእሙ /፬/
ክልዔሆሙ ፈጸሙ ገድሎሙ /፬/

870. በእምነታቸው

በእምነታቸው ዳኑ ከዚያ ነበልባል /፪/
አናንያ አዛርያ ሚሳኤል /፪/
ናቡከደነፆር ጨካኙ ንጉሥ
በባቢሎን ሀገር ጣኦት የሚነግሥ
እያለ ሰገዱ አማኙን ሲያምጽ
ወጣቶች ተነሡ በቅናት መንፈስ
አናንያ አዛርያ ሚሳኤል /፪/
ለሠራኸው ጣኦት አንሰግድም እያሉ
በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ልባቸው ሞሉ
የፈጠረን አምላክ ያድናል ሲሉ
አናንያን አዛርያ ሚሳኤል /፪/
ነበልባል ነዲዱ እያቃጠላቸው
በጭካኔ መንፈስ አስወረወራቸው
ገብተው ሲፀልዩ ፍህሙ ሳይነካቸው
መልአኩን ልኮ አበረደላቸው
ገብርኤል /፪/ በመስቀል /፪/
እንደ ሶስቱ ሕፃናት በእምነት ለሚቆም
መልአኩን ይልካል እግዚአብሔር ሊረዳው
እሣቱም ይበርዳል መልአኩን ሲልከው

871. ጊዮርጊስ ብርሃኑን

ጊዮርጊስ ብርሃኑን አበራ /፪/
ዱድያኖስ አፈረ ከጣኡቱ ጋራ
ጊዮርጊስ ብርሃኑን አበራ /፪/

ለዲያብሎስ ያልሠገደ ጀግናው
ጊዮርጊስ
ደግሞ በዓይን ታየ ክብሩ ሲወደስ
ከሞት አፍ ያወጣት ቤሩታይትን
በሰማእቱ ገድል ድል ሆነ ሠይጣን
ቅዱሱ ሰማእት ጊዮርጊስ አባታችን
አሳየ ሥልጣኑን ከሞት እንደሚያድን
መድኃኒት ክርስቶስ የገለጠው ብርሃን
እኛም እንድንድን ከዘመኑ አውሬ
እስቲ እንግለጽለት ክብሩን በዝማሬ
ተዋሕዶ አበራ ደግሞ እንደገና
ደራጎን ድል ሆኖ ሞቶ ቀርቷልና
ለአሸናፊ ጌታ ለእግዚአብሔር ልዑል
ምስጋና እናቅርብ እንበል እልል
ጊዮርጊስ አበራ ብርሃን /፪/
ሰው በላውም አውሬ ሞተ ድራጎን /፪/
ጊዮርጊስ አበራ ብርሃን

872. ምስክርነቱን ገለጸ

ምስክርነቱን ገለጸ ቂርቆስ ሕፃን /፪/
በእሳት ተፈተኖ አለፈኸኸ ፈተና ደስ ይበለን
/፪/
ቂርቆስ ኢየሱጣን ሁለቱም በአንድ ልብ
ምን ጨከኑ /፪/
ተቃቅፈው ሲገቡ ወደ እሳት ጋኑ /፪/
ሕፃኑ እና እናቱ በእሳት ውስጥ ሲሆኙ
ያለ ምንም ፍርሀት /፪/
ገብርኤል ተላከ እነርሱን ለማውጣት /፪/
በርዶና ቀዝቅዞ የእሳቱ ነበልባል
በጌታችን መስቀል /፪/
ሁለቱም ሰማእታት ተጎናጸፉ ድል /፪/

873. መጥምቀ መለኮት

መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ /፪/
መንገድ ጠረገ ለኢየሱስ መምጫው
ሊደርስ
ተክለሃይማኖት በጸሎት /፪/
ተክለሃይማኖት በጸሎት የእኛ አባት
ገብረመንፈስቅዱስ ሐዋርያ /፪/
ከንሒሳ መጥተው ጸለዩላት ለኢትዮጵያ
ዜና ማርቆስ በጽኑ እምነት /፪/
ፀሐይ አቆሙ እንደ ኢያሱ በደብረ
ብስራት /፪/
እመቤታችን ድንግል ማርያም /፪/
ምሕረት አሰጭን ከመለኮት
ከመድኃኔዓለም
መሰቀሉን ይዞ በፈረስ /፪/
ከዘንዶ አስጣላት ቤሩታዊትን ቅዱስ
ጊዮርጊስ

874. መጽሐፈ ዜናሁ ለቂርቆስ

መጽሐፈ ዜናሁ ለቂርቆስ መንፈሳዊ
ወዘመንክሮ ሰላም /፪/
ጸሐፍ ውስተ ልብየ /፪/ እንዘ ትገብር ከለመ
ደመከ አምላካዊ በመስቀል ዘዘነበ /፪/
እንተ ቅዱስ ቂርቆስ ሕፃን ለአምላክ ሆንክ
ምስክር /፪/
በእኛም ልብ ጻፍልን /፪/ የአምላክን ፍቅር
/፪/
በእስክንድሮስ ዘመን ነበርክ ታላቅ
አስተዋይ ሕፃን
አምላክህም ሰጠህ /፪/ የክብር አክሊልን /፪/
ያ ሁሉ መሣሪያ ሣያስፈራህ የመሠከርክ
የአምላክን ክብር
ድንቅ ነው የአምላክ ሥራ /፪/ ለዚህ ሕፃን
ሰጠው እንዲኖር ሣይፈራ /፪/
አትፍሪ እዳልካት እናትህን እኛንም አድነን
ከመከራ /፪/
እንድንድን ርዳን ከዲያብሎስ ጭፍራ
በጽድቅህ አድለን እንኑር በሥራ /፪/

875. ፀሐይ ዘልዳ

ፀሐይ ዘልዳ ኮከብ ዘልዳ /፪/
አድነኒ /፪/ ጊዮርጊስ እሞተ እዳ /፪/
ከሰው ወገን ያለ አድነኒ
ልክ እንደአንተ ያለ ››
ሰባት ዓመት ሙሉ ››
መከራን የቻለ አድነኒ /፪/ ጊዮርጊስ
እሞተ እዳ
በምግባር በሃይማኖት አድነኒ

በሚገባ ተጋድለህ ››
ሰባት አክሊላትን ››
ጌታ የሸለመህ አድነኒ /፪/ ጊዮርጊስ እሞተ
እዳ
ሲበሉ ሲጠጡ አድነኒ
ነገሥታት ከበው ››
በጸሎትህ ጠፋ ››
ወርዶ እሳት በላቸው አድነኒ /፪/
ጊዮርጊስ እሞተ እዳ
ፍጡነ ረድኤት አድነኒ
ጊዮርጊስ ፈጣኑ ››
እኛንም አድነን ››
ከክፉ ሰይጣን አድነኒ /፪/
ጊዮርጊስ እሞተ እዳ
በሞተር ቢፈጩህ አድነኒ
ዱድያኖስ ተስፋቶ ››
አሳፈረው እርሱ ››
ከሞት አስነሥቶ አድነኒ /፪/
ጊዮርጊስ እሞተእዳ

876. ስብሐት ለአብ ወወልድ

ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
/፪/
ዘአንበሩ ብየ አክሊለ ሞገሰ /፪/
መዘምረ እኩን ለጊዮርጊስ /፮/

877. ከመ ፀብል

ዘነፋስ ዘራውሂ ደብረ
ይድረስ /፪/
አማን በአማን ቅዱስ ጊዮርጊስ /፬/
ትርጉም፡- እውነት በእውነት ጊዮርጊስ
ቅዱስ ነው እንደ ነፋስ ትቢያ በይድረስ
ተራራ በተኑት

878. መክብብ

መክብብ ሰማእት አለቃ ቅዱስ ጊዮርጊስ ነው
ከመካከላችን አባርልኝ አርቅልን
አስወግድልን

879. ቅዱስ ጊዮርጊስ

ቅዱስ ጊዮርጊስ አማልደን /፪/ ከመድኃኔአለም
አስታርቀን /፪/
ማረን ይቅር አለን /፪/ አማኑኤል ታረቀን
/፪/

ሹመት ለመፈለግ ቅዱስ ጊዮርጊስ
ነገሥታት ዘንድ ሄዶ ›› ››
ጣኦት ሲያመልኩ አየ ›› ››
አምላኩ ተክዶ ›› ››

ክርስቲያን ነኝ የሚል ቅዱስ ጊዮርጊስ
በዓለም ሁሉ ጠፍቶ ›› ››
እኔ አምናለው አለ ›› ››
የአምላኩን ስም ጠርቶ ›› ››

የዓለም ግዛንግሱ ቅዱስ ጊዮርጊስ
ጸባይዋ ሣይገዛህ ›› ››
ስለ ጌታ ፍቅር ›› ››
ከእናትህ ተለየህ ›› ››

የመፍጫው መሣሪያ ቅዱስ ጊዮርጊስ
በዓይነት ተደቅኖ ›› ››
እኔ አልፈራም አለ ›› ››
በአምላኩ ተማምኖ ›› ››

ተፈጭቶ እና ደቅቆ ቅዱስ ጊዮርጊስ
ደብረ ይድረስ ሣለ ›› ››
እጸዋቱ ሁሉ ›› ››
ጊዮርጊስ ጊዮርጊስ አለ ›› ››

880. ምን ሰማህ ዮሐንስ

ምን ሰማሕ ዮሐንስ በማህጸን ሳለ /፪/
ሕጻን ሆነህ ነቢይ ለክብር የተጠራህ /፪/
እንደ እንቦሳ ጥጃ ያዘዘለህ ደስታ /፪/
ምን ዓይነት ድምጽ ነው ምን ዓይነት ሰላምታ /፪/
በረሀ ያስገባህ ለብዙ ዘመናት
ምን ያለ ራዕይ ነው እንዴት ያለ ብስራት /፪/
እንደ አዲስ ምስጋና ስልቱ የተዋበ
ተደምጦ የማያውቅ ጭራሽ ያልታሰበ /፪/
ከተፈጥሮህ በላይ ያሰገደህ ክብር
እንዴት ቢገባህ ነው የአምላክ እናት ፍቅር /፪/
ሌላ ድምጽ አልሰማም ከእንግድህ በኋላ
ለውጦኛልና የሰላምታ ቃሏ /፪/
ከሴት ከተገኙ ከደቂቀ አዳም
ድንግል ስለሆነ በሕይወቱ ፍጹም /፪/
በማህጸን ሳለ ተመርጦ በጌታ
ለማዳመጥ በቃ የኪዳን ሰላምታ /፪/

881. በተራራማው

በተራራማው በኤፍሬም አገር
ተአምር ተሰማ ኤልሳቤጥ ሰፈር
መካኗ እናት ነቢይ ወለደች
ስትዘምር ሰማን እልል እያለች /፪/
የመካንነቷ ስድብ ቀርቶላታል
ጌታ በማኅጸን ዮሐንስን ፈጥሯል
የደስታዋ ምስጢር የእጁ ስራ ነው
ዘመረች በሀሴት ሁሉ ለሚቻለው
ገረማት ኤልሳቤጥ የጌታዋ ስራ
ምን ብላ ትናገር በምን ቋንቋ ታውራ
እልልታው ደመቀ በኤፍሬም ከተማ
ከፍ አረገች ድምጿን አለም እንዲሰማ
መጣችላት ድንግል ተአምሩን ስትሰማ
አናገራት መንፈስ ተሞላች በግርማ
ህጻኑም ዘለለ ድንግልን ሲሰማ
በድንግል ማኅጸን ጌታን አይቷልና

882. በመንፈስ የሀውር

በመንፈስ የሀውር እም ኃይል ውስተ ኃይል
ካህን /፪/ ወነቢይ /፪/ ዮሐንስ መጥምቅ

883. በማሕጸን ቅኔ

በማህጸን ቅኔ ለማርያም ተሰማ
በተራራማው አገር በኤፍሬም ከተማ
ዮሐንስ ይናገር በረሀ ያደገው
ድንግል ስትናገር ምን እንዳዘለለው
የእናቱ ማህፀን የቅኔ ርስት ሆነች
ድንግል የአምላክ እናት ፊቱ ስለቆመች
በሀሴት ዘለለ ዘመረ በደስታ
ከድንግል ሲወጣ ታላቁ ሰላምታ
በድንግል ማህጸን ስላየ ጌታውን
ከመወለድ ቀድሞ ሰማነው መዝሙሩን
ትንቢቱ ሲፈጸም በሆዷ ሲነግስ
ሰገደ ለአምላኩ የስድስት ወር ጽንስ
ጀመረ ስብከቱን ገና ሳይወለድ
ተፈጥሮ መች ቻለች ነቢዩን ለማገድ
አፉ ተከፈተ በታላቅ ምስጋና
በእናቱ ማኅጸን ድምጽን አሰማና
የዮሐንስ እናት ኤልሳቤጥ ገረማት
ልጇ በማሕፀን ቅኔ ሲቀኝባት
ድምጿን ከፍ አረገች ዓለም እንዲሰማ
ሞላት መንፈስ ቅዱስ ለመዝሙር ለዜማ

884. ሕፃን ቂርቆስ

ሕፃን ቂርቆስ ለፅህርት ዘኢያፋርሆከ
ነጎድጓድ /፪/
ዮም ባርክ ማኅበረከ /፪/ ለእለ አሐዱ አሐዱ /፪/
ትርጉም፡- የእሳቱ ነጎድጓድ ያላስፈራህ
ሕፃኑ ቂርቆስ
ሆይ የእያንዳንዳችንን ማኅበር ዛሬ ባርክ

885. ኦ እስጢፋኖስ ሰማእት

ኦ እስጢፋኖስ ሰማእት /፪/
አክሊልን አገኘህ ከጌታ በእውነት /፪/

የወንጌልን ትምህርት ቀዳሜ ሰማዕት
ስለመገብካቸው ቀዳሜ ሰማዕት
አይሁዶች ወገሩህ ጨክኖ ልባቸው
በድንጋይ ሲወግሩት ቀዳሚሰማዕት
በጣም ተጨነቀ ቀዳሜ ሰማዕት

ለሚወግሩት ሰዎች ይቅርታን
ጠየቀ /፪/

የወንጌል በር ከፋች ቀዳሜ ሰማዕት
የተባልከው ቅዱስ ቀዳሜ ሰማዕት
ተመሠከረልህ ከእውነተኛው ንጉሥ
ሥራህ ያስደስታል ቀዳሜ ሰማዕት
እጅግ ድንቅ ሥራ ቀዳሜ ሰማዕት
በአንተ ተበተነ ወንጌል አዝመራ /፪/

አዝ. . .
የዲቁናን ሥራ ቀዳሜ ሰማዕት
በክብር የፈጸምክ ቀዳሜ ሰማዕት
የሥላሴ ዙፋን ተከፍቶ ያየህ
የድንጋይ እሩምታ ቀዳሜ ሰማዕት
ያላዘናጋህ ቀዳሜ ሰማዕት
ቀዳሚው ሰማዕት እስጢፋኖስ ነህ
/፪/
ቀና ብሎ አየ ቀዳሜ ሰማዕት
ነፍሴን ተቀበለው በማለት ጸለየ
ጌታ ተቀበለው ቀዳሜ ሰማዕት
ቃሉንም ሰማለት ቀዳሜ ሰማዕት
ሰማያዊ አክሊል ወደ እርሱ ላከለት /፪/

886. መአርዓዮ ለቂርቆስ

አርዓዮ ለቂርቆስ ግብራ ለደብተራ ወተናግሮ
ግብራ ለደብተራ /፪/
ብርሃን በደመና /፪/ እሙ እሙ ለሠማእት
እህቶሙለመላእክት /፪/
ትርጉም፡- ለቂርቆስ የድንኳን ሥራ አሳየው
በብርሃን ምሰሶ ተነጋገረው የመላእክት
እህታቸው የሰማእታት
እናታቸው የደመና ብርሃንናት

887. አፀደ ወይን

አፀደ ወይን ዘያፈርህ አስካለ ሕይወት /፪/
ከመ ጽጌሬዳ /፬/ እስጢፋኖስ ምሉአ ፍቅር
ከመ ጽጌረዳ /፪/

888. ሰአለ

ሰአለ ሥረይ ለኃጢአት ለእለ ወገርዎ /፪/
ወይቤ ሥረይ ሎሙ ዘንተ ኃጢአቶሙ /፪/

889. ይቤላ ሕፃን ለእሙ

ይቤላ ሕፃን ለእሙ ኢትፍርሂ እም /፪/
ነበልባለ እሳት /፪/
ለአናንያ ወአዛርያ ወሚሳኤል ዘአድኀኖሙ
ውእቱ ያድኅነነ /፪/
ሕፃኑ እናቱን አላት እናቴ ሆይ አትፍሪ /፪/
የእሳቱን ነበልባል /፪/
አናንያን አዛርያን ሚሳኤልንም ያዳናቸው
እኛንም ያድነናል

890. አምላኮሙ ለክርስቲያን

አምላኮሙ ለክርስቲያን ተመሲሎ ስብኦ
መጽአ ኀቤየ ወይቤላ ቅዱስ ጊዮርጊስ /፪/
አንሰ ኢኮንኩ አምላከ አላ ገብረ አምላከ አነ
/፪/

891. ገባሬ መንክራት

ገባሬ መንክራት ጊዮርጊስ በአቁጽሎ ይቡስ
ዓምድ /፪/
ተራድአነ በገሀድ ተራድአነ /፬/

892. ሰአለ ሥርየተ ኃጢአት

ሰአለ ሥርየተ ኃጢአት ለእለ ወገርዎ /፪/

ወይቤ ሥረይ ሎሙ ዘንተ ኃጢአቶሙ /፬/

ትርጉም፡- ለወገኖቹ የኃጢአት ስርየት ለመነ
ኃጢአታቸውንም ይቅር በላቸው አለ

/ቅዱስ እስጢፋኖስ/

893. እንዘ ይነብር ለአብ በየማኑ

እንዘ ይነብር ለአብ በየማኑ ወይረፍቅ ውስተ ህፅኑ
የማኑ ለአብ /፪/

ርዕየ ወልደ ርዕየ በዓይኑ እስጢፋኖስ /፪/ ምሉዓ
ጥበብ /፪/

ትርጉም፡- ጥበብን የተሞላ እስጢፋኖስ ወልድን በአብ
ቀኝ ተቀምጦ በአብ እቅፍ /ዕሪና/ ሲመሰገን በዓይኑ
አየው

894. ጊዮርጊስ ግሩም

ጊዮርጊስ ግሩም በመንፈስቅዱስ ጎቱም /፪/
መዓዛ ቅዳሴክ ጥዑም ከመ ጽጌ ገዳም
ጊዮርጊስ ግሩም /፪/

895. ጊዜ ዕረፍቱ

ጊዜ ዕረፍቱ ለእስጢፋኖስ /፪/
እም ልዕልና ወረዳ እግዚአብሔር /፬/

መዝሙር በእንተ ፃድቃን

896. ቅዱሳን በሙሉ

ቅዱሳን በሙሉ ከአምላክ አማልዱን

ልንጠፋ ነውና በዝቶ በደላችን /፬/

ጻድቃን ሰማዕታት ንጹሐን ሁላችሁ

ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ዓለምን

ንቃችሁ /፬/
ለሰማያዊ ክብር ለአክሊል የበቃችሁ
ወደ አምላክ አቅርቡ በጽኑ ምልጃችሁ /፬/

ድንግል እናታችን ኪዳነ-ምሕረት

ቅድስት ቅዱሳን የጻድቃን እናት /፬/

ርኅርኅተ ኅሊና አሳስቢ ከልጅሽ

ይቅርታ እንድናገኝ በፍጹም ልመናሽ /፬/

897. ጻድቃን ሰማዕታት

ጻድቃን ሰማዕታት በሙሉ
በአካለ ስጋና <u>በአጸደ ነፍስ</u> /፪/ ያሉ
ከፈጣሪ አማልደው እኛን ያስምራሉ
የእግዚአብሔር ዓይኖቹ ጻድቃንን ከማየት
ጆሮቹም አይርቁም እነሱን ከመስማት
የጻድቅ ሰው ጸሎት ኃይልን ታደርጋለች
በምልጃቸው እንመን አናመንታ በአንዳች
ጊዜያዊው መከራ ሳያሰቅቃቸው
እሳትና ስለት ሳያስፈራራቸው
ሰማያዊ ተስፋ ስለሚታያቸው
በፈተና ሁሉ ጸኑ በእምነታቸው
ኃጥኡ ነዌ አንኳን በሲኦል እያለ
ስለ ወንድሞቹ ምህረት ከለመነ
እናንተማ ጻድቃን በገነት ያላችሁ
ምንኛ ትረዱን አምነን ስንጠራችሁ
ቀዝቃዛ ውሃ እንኳን በፃድቅ ሰዉ ስም
የሚያጠጣ ቢኖር ዋጋው አይጠፋም
ብሎ እንዳስተማረን ጌታ በወንጌል
አምነን እንፈጽመው ዋጋ ያሰጣል

898. ሰዓሉለነ

ሰዓሉለነ ቅዱሳን መላዕክት /፪/
ሰአሉለነ ጻድቃን ሰማዕታት
ሀበ አምላከ ምህረት ሰዓሉለነ
ለምኑልን ቅዱሳን መላዕክት /፪/
ለምኑልን ጻድቃን ሰማዕታት
ወደ አምላከ ምህረት ለምኑልን
አንተ የመረጥከውን ማን ይከሳል
ያጸደቅከውን ማንይወቅሳል
ለሚገባው ክብርን መስጠት
ታዟልና በመጻሕፍት
<u>ያከበርካቸው ባሪያዎችህን</u>
<u>እናከብራለን ቅዱሳንህን</u> /፪/
ሁሉ መዳንን እንዲይዙ
የሚላኩ የሚያግዙ
ሰርክ በፊትህ እየቆሙ
ጥኡም ቅዳሴን እያሰሙ
<u>በምስጋናቸው የሚያከብሩህን</u>
<u>እናከብራለን መላእክትህን</u> /፪/
ጤዛ ልሰው ዳዋ ጥሰው
ዋዕየ ቁሩንም ታግሰው
በየፍርክታው በየዱሩ
ሌጦ ለብሰው እየዞሩ
<u>በጽናታቸው የሚያከብሩህን</u>
<u>እናከብራለን ጻድቃንህ</u> /፪/
እንደሚታረዱ በጎች ሆነው
አንገታቸውን ለሰይፍ ሰጥረው
ስለስምህ እየተጠሉ
ከአንበሳ ጋራ እየታገሉ
በተጋድሎአቸው ያከበሩህን
እናከብራለን ሰማዕታትህን
ከሕያው ቃልህ እየጠቀሱ
መናፍቃንን ድል የነሱ
በገዛ ደምህ የዋጀሀትን
ቤተክርስቲያንን የጠበቋትን
<u>በሕይወታቸው ያስደሰቱህን</u>
<u>እናከብራለን ቅዱሳንህን</u> /፪/

899. ተክለ አብ

ተክለ አብ ተክለ ወልድ ተክለ መንፈስ ቅዱስ /፪/
አቡነ /፪/ ወመምህር አቡነ ወመምህር ተክለሃማኖት

900. ለተክለ ሃይማኖት

ለተክለ ሃይማኖት ጻድቅ መጠነ በዝሐ ሕማሙ
ትዌድሶ ደብረ ሊባኖስ ገዳሙ /፪/
እስመ በውስቴታ ተገብረት
ፍልሰተ ስጋሁ ወአጽሙ
ኢየሱስ ክርስቶስ እንተ ቀደሳ በደሙ
እምነ አድባራት ኩሎን ዘተለአለት በስሙ

901. ገድሉ ተአምራቱ

ገድሉ ተአምራቱ እጅግ ብዙ ነው
ጣኦትን አዋርዶ የተሸለመው
የተዋሕዶ ኮከብ ተክለ ሐዋርያ
አባ ተክለ ሃይማኖት ዘኢትዮጵያ
ዳግማዊ ዮሐንስ ጠፈር የታጠቀ
ንጹህ ባሕታዊ ጠላት ያስጨነቀ
የጸጋ ዘአብ ፍሬ ዛፍ ሆኖ በቀለ
በደብረ ሊባኖስ መናኝ አስጠለለ
ደካማ መስሏቸው በአንድ እግሩ ቢያዩት
ባለ ስድስት ክንፉ ተክልዬ የኛ አባት
እሱስ አንበሳ ነው ትናገር ደብረ አስቦ
ሌግዮን ሲዋረድ ሐፍረት ተከናንቦ
ከካሕናት መካከል ሕሩይ ነው ተክልዬ
መጣሁ ከገዳምህ ልሳለምህ ብዬ
ኢትዮጵያዊው ቅዱስ አባ ተክለሃማኖት
ወልድ ዋሕድ ብለህ ምድሪቷን ቀደስካት
የባረከው ውኃ የረገጥከው መሬት
ገላህ ያረፈበት ሆኗል ጸበል እምነት
ኑና ተመልከቱ ድውያን ሲፈቱ
ይሰብካል ተክልዬ ዛሬም እንደ ጥንቱ

902. ሐዋርው መነኩሴ

ሐዋርያው መነኩሴ የመረጡህ ሥላሴ /፪/
ዋስ ጠበቃ ሆኗል ተክልዬ ለነፍሴ /፪/
ዳሞት ትናገው ያንተን ሐዋርያነት
የወንጌል ገበሬ የጣዖታት ጠላት
ጸሎተኛው ቅዱስ አባ ተክለ ሃይማኖት
ክንፍን የተሸለምክ እንደ ሰማይ መልአክ /፪/
ብራናው ሲገለጽ ገድለ ተክለሃይማኖት
ከሰው ልጅ ልቦና ይወጣል አጋንንት
የቅዳሴው እጣን ሲወጣ ከዋሻው
ምድርን ይባርካል ጸሎተ ምህላው /፪/
የኢትዮጵያን ምድር አረስከው በመስቀል
ጭንጫው ፈራረሰ ተዘራበት ወንጌል
ትናንት የዘራኸው ዛሬ ለእኛ ሆኗል
አምላክ ተክልዬ ብለን ተማጽነናል /፪/
ከሱራፌል ተርታ ቆመህ ስታጥን
ስሉስ ቅዱስ ብለህ ስታመሰግን
ጸሎት ትሩፋትህ ትህትና ስግደትህ
ጾምህ ከፍ አድርጎ ሰማይ አደረሰህ /፪/
ዛፉ ሲመነገል አምላክ የተባለው
ሞተሎሜ ሲያፍር ታላቅ ሰውነኝ ያለው
የተክልዬ ጸሎት ብዙ ነው ምስጢሩ
ስድስት ክንፍ አወጣ ቢሰበር አንድ እግሩ
/፪/

903. ተክለ ሃይማኖት ባሕታዊ

ተክለ ሃይማኖት ባሕታዊ
ምድራዊ ሲሉህ ሰማያዊ
በአደባባዩ ተተክለህል
ተክልዬ መልካሙን ፍሬ አፍርተሃል
ቃልኪዳን አለህ የገነነ
ምህረት የሚያሰጥ የታመነ
በስምህ ውሃ ጠጥተን
ዋጋችን በዝቷል አምላካችን
እኛም ሆነናል ልጆችህ
ማርኮ አስቀርቶን ምግባርህ
በምጃህ ጸሎት ትሩፋት
ቤታችን ሞላ በረከት
ምሕረት ይዘንባል ከሰማይ
በአንድ እግርህ ቆመህ ስትፀልይ
ብዙ ተጋድለህ አትርፈሀል
ያገለገልከው አክብሮሀል
ተሰባበሩ ጣኦታቱ
አምነው ዘመሩ መኳንንቱ
የበረታው ቃል ከአፍህ ወጥቶ
የአምላክ አድርጓል ሁሉን ገዝቶ

904. አባ አቡነ

አባ አቡነ አባ መምህርነ
መምህርነ አባ ተክለ ሃይማኖት
እም አእላፍ ሕሩይ /፪/ ተክለ ሃይማኖት

905. እምገዳመ መንበሩ

አምገዳመ መንበሩ /፪/ ደብረ ሊባኖስ መቃብሩ
ለመካነ ሕይወት /፬/ ይዕቲ ማሕደሮ

906. ግሩማን መላእክት

ሃሌ ሉያ ግሩማን መላእክት ሱራፌል ወኪሩቤል እለ
አክናፊሆሙ ነበልባል /፪/

ወረዱ ዮም ይትበሉከ በብሂል አማን ገብረ መንፈስ
ቅዱስ ገባሬ ኃይል /፪/

ትርጉም፡- ክንፎቻቸው ነበልባል የሆኑ የሚያስፈሩ መላእክት ሱራፌልና ኪሩቤል

ገብረ መንፈስ ቅዱስ በእውነት ተአምረኛ /ገባሬ ኃይል/ ነህ እያሉ ሊቀበሉህ ወረዱ።።

907. አማን በአማን

አማን በአማን /፪/
ኧኸ ተክለ ሃማኖት ጸሐይ

908. ጼና አልባሲሁ

ጼና አልባሲሁ /፪/ ለገብረ መንፈስ ቅዱስ
ከመጼና ስሂን
አልባሲሁ ዘሜላት /፪/ ዘወረደ ውስተ ገነት

909. ለሀገሪትነ ሰላማ

ለሀገሪትነ ሰላማ ኪያከ ተአቅብ
አባ ኦ አባ /፪/ ገብረ መንፈስ ቅዱስ /፪/ አባ

910. ገብረ መንፈስ ቅዱስ

ገብረ መንፈስ ቅዱስ ዘይሰርር በአክናፍ
ሀበ አምደ ወርቅ /፪/ ስሙ ጽሑፍ

911. ኮከብ ብሩህ

ኮከብ ብሩህ ዘሰረቀ እም አቅሌስያ
ቤተክርሲቲያን ዘንሰምያ
ኮኖሙ አበ ለሰብአ ግብጽ ወኢትዮጵያ

912. ገብረ መንፈስ አህጉር

በብዙ አሕጉር የዞርክ የጌታን ወንጌል ያስተማርክ
የዲናን ስርዓት በክብር የፈጸምክ
ብጹዕ ነህ /፪/ እስጢፋኖስ ብጹዕ ነህ

913. መሠረተ ዜማ

መሠረተ ዜማ ወጠነ /፪/ ያሬድ ካህን
ያሬድ /፫/ ያሬድ ካህን /፪/ ጥዑመ ልሳን

914. አቡነ ሀብተ ማርያም

አቡነ ሀብተ ማርም የዓለም ብርሃን ናቸው
ይኸው ለዘለዓለም ያበራል ስራቸው /፪/
ያበራል ሥራቸው

915. አቡነ አረጋዊ

አቡነ አረጋዊ ጻድቁ መነኩሴ
በኃጢአት እንዳትሞት ሕያዊቷ ነፍሴ
ጻድቁ አማልደኝ በቅድመ ሥላሴ /፪/
ከእናት ከአባትህ ፍቅር አቡነ አረጋዊ
አምላክህን መርጠህ ‹‹
መከራ መስቀልን በእውነት ታግሰህል
የእግዚአብሔር ቸርነት ከሞት ሰውሮሀል
ምስጢረ መለኮት አቡነ አረጋዊ
በልብህ ቢመላ ‹‹
አረጋዊ ተባልክ ሳለህ ታናሽ ጨቅላ
ጸጋህ ትደርብን ትሁንልን ጥላ
ከዳሞ ተራራ አቡነ አረጋዊ
ከማህሌት ከተማ ‹‹
የጽዮን ዝማሬን ነፍስህ ብትጠማ
በዘንዶ ተጉዘህ ሰማህ ያንን ዜማ
የሕግ መምህር አቡነ አረጋዊ
በረከት አድለን ‹‹
ከድካም ወደ ኃል በእምነት አሻግረን
ወደጌታ ደስታ በምልጃህ አቅርበን

916. የምዕመናን አባት

የምእመናን አባት አገልጋይ የአምላክ ባለሟል
መርቆሬዎስ /፪/

ተቀበለ ዛሬ /፬/ አክሊለ ሰማዕታት /፪/ ኧኸ

917. ጸለዩ ባስልዮስ ወጎርጎርዮስ

ጸለዩ ባስልዮስ ወጎርጎርዮስ ኀበ ሥዕሉ ለቅዱስ መርቆሬዎስ /፪/

ደነነ ሥዕል /፪/ ዘመርቆሬዎስ ከመ ኦሆ ዘይብል

ወተፈሥሑ ባስልዮስ ወጎርጎርዮስ /፪/

ጸለዩ ባስልዮስና ጎርጎርዮስ ወደ ሥዕሉ ለቅዱስ መርቆሬዎስ /፪/

ዝቅ አለ ሥዕል /፪/ የመርቆሬዎስ አቤት እንደሚል

ተደሰቱ ባስልዮስ ጎርጎርዮስም /፪/

918. ይቤሎ ጴጥሮስ

ይቤሎ ጴጥሮስ በጳውሎስ ጥባዕኬ እጐየ ጳውሎስ /፪/

ወኢትናፍቅ ኢንመውት ዳግመ ዳግመ /፪/

ትርጉም፡- ጴጥሮስ ጳውሎስን ወንድሜ ጳውሎስ ሆይ ጨክን አትጠራጠር ከእንግዲህ ዳግመኛ አንሞትምና አለው

919. ተክለ ሃይማኖት ተወለዱ

ተክለ ሃይማኖት ተወለዱ እሰይ እሰይ /፪/

የዓለም ብርሃን /፪/ የጽድቅ ፀሐይ /፪/ ባለሟሉ የአምላክ አገልጋይ /፪/

920. አረጋዊ ምሉዓ ፍቅር

አረጋዊ ምሉዓ ፍቅር ከመ ጽጌረዳ ዘይወፅእ እም አፉሁ ዕጣነ ቅድስና /፪/

ለገቢረ ሠናይ ዘይወጽዕ ዘይወጽዕ ከመ ማይ ምስለ ገብረ ክርስቶስ /፪/

ትርጉም፡- ከአንደበቱ ከመ ማይ ምስለ ገብረ ክርስቶስ /፪/

/ቃል/ የሚወጣ ፍቅርን የተሞላ አረጋዊ ከገብረክርስቶስ

ጋር ለበጎ ሥራ እንደ ውኃ ይወጣል፡፡

921. ደምፀ ወተሰብከ

ደምፀ ወተሰብከ /፪/ ውስተ ዓለም /፪/

ዜና ምግባሩ ትሩፍ ለአረጋዊ /፬/

922. ሰላም ለክሙ

ሰላም ለክሙ ጻድቃን ወሰማዕታት እለ አእረፍክሙ በሃይማኖት /፪/

መዋዕያነ ዓለም አንትሙ እስመ በብዙኅ ትዕግስት

ለአሉ ቅድመ ፈጣሪ በበኩሉ ሰዓት

ትርጉም፡- በሃይማኖት ሆናችሁ ያረፋችሁ ጻድቃን ሰማዕታት ፍቅር ሰላምታ ይገባችኋል ዓለምን በብዙ ትዕግስት ድል የነሣችሁ እናንተ ኹል ጊዜ በፈጣሪ ፊት ለምኑልን፡፡

923. ዘአጽናእኮሙ

ዘአጽናእኮሙ ለእሙንቱ አበዊነ ለሄኖክ ወኤልያስ /፪/

አንተ አጽንአነ በመንፈስ ቅዱስ /፪/

ያፀናህቸው ለእነርሱ አባቶቻችንን ለሄኖክና ኤልያስ /፪/

አንተ አጽናን በመንፈስ ቅዱስ /፪/

924. ኀዲጎ ብእሲቶ

ኀዲጎ ብእሲቶ መኒኖ መንግሥቶ /፪/

ዘፈለሰ /፫/ መኒኖ መንግስቶ /፪/ ኧኸ

ትርጉም፡ ሚስቱን ትቶ መንግሥቱን ትቶ መነነ /ገብረ ክርስቶስ/

925. ጥምቀት አምጽአ

ጥምቀት አምጽአ ሕፅወ ንግሥት ለእሊአሁ

እምኀበ ፊሊጶስ ድኅረ ተጠምቀ ለሊሁ

ሰላማ አቡነ አምጽአ ለነ በዕድሜሁ ለመድሃኒነ

ምስጢረ ደሙ ወሥጋሁ

ትርጉም፡- የንግሥቲቱ ጃንደረባ በፊልጶስ ዘንድ ራሱ ከተጠመቀ በኋላ ጥምቀትን አመጣልን፤ አባታችን አቡነ ሰላማም በዘመኑ

926. ለባርኮትነ ንኡ

ሰላም ለክሙ እንጦንስ ወመቃርስ አቢብ ሲኖዳ ገብረ መንፈስ ቅዱስ /፪/

ለባርኮትነ ንኡ ውስተ ጽርሐ ዛቲ መቅደስ

ተክለ ሃይማኖት አኖሬዎስ ኤዎስጣቴዎስ /፪/

ሳሙኤል ተክለ አልፋ በብኑዳ ኪሮስ

ትርጉም፡- እንጦንስ መቃርስ አቢብ ሲኖዳ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሰላምታ ይገባችኋል።

ተክለ ሃይማኖት አኖሬዎስና ኤዎስጣቴዎስ ሳሙኤል ተክለ አልፋ በብኑዳ ኪሮስ

ትባርኩን ዘንድ በዚች መቅደስ ኑ።

927. በጽድቅ የሚያምኑብህ

በጽድቅ የሚያምኑብህ ቅዱሳን በሙሉ

ካንተ ባገኙት ኃይል ሁሉን ያደርጋሉ

እስራኤልን መርቶ ሙሴ ከግብፅ ሲያወጣ

ቢከታተላቸው ፈርዖንም በቁጣ

ባሕሩን ከፍሎ ሙሴ ሕዝቡን አሻገረ

ከሠራዊቱ ጋር ፈርዖንም በቁጣ

ባሕሩን ከፍሎ ሙሴ ሕዝቡን አሻገረ

ከሠራዊቱ ጋር ፈርዖን ሰጥሞ ቀረ

ጎልያድ ሲፎክር ተማምኖ በኃይሉ

የሚገጥመው ጠፍቶ ሁሉም ፈርተው ሳሉ

ብላቴናው ዳዊት ከእረኝነት መጥቶ

በአንድ ጠጠር ጣለው በአምላኩ ስም ወጥቶ

የእግዚአብሔርን መንፈስ ደፍረው ሊያታልሉ

ሐናንያና ሚስቱ በሐሰት ሲምሉ

ልባቸውን አውቆ ጴጥሮስ ገሠጻቸው

በሞት ተቀሰፉ አንድ ሆነ ቀብራቸው

ጳውሎስና ሲላስ በእስር ቤት ተጥለው

ሲዘምሩ ሳለ መከራውን ችለው

ተናወጠ ወሕኒው እስከ መሠረቱ

በጸሎታቸው ኃይል ከእስራት ተፈቱ

928. ብርሃናተ ዓለም

ብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ

ጻድቁ አባታችን /፪/ ገብረመንፈስ ቅዱስ /፪/

የመረጣችሁ ፈጣሪያችን አምላካችን

እንድናገኝ ሰላምን አማልዱን እኛን ከፈጣሪያችን /፪/

929. ደም ወማይ

ደም ወማይ ወሀሊብ እምነ ክሳዱ ፈልፈለ /፪/

ሶበ ተከለለ /፪/ ተከለለ ቅዱስ ጊዮርጊስ /፪/

ትርጉም፡- ቅዱስ ጊዮርጊስ በይፍ

አንገቱን በተሰየፈ ጊዜ ደም ውኃና ወተት ፈሰሰ

930. ኮከብ ብሩህ

ኮከብ ብሩህ ቅዱስ ማርቆስ ዘሠረቀ እም እስክንድርያ

ቤተክርስቲያን ዘንሰም /፪/

ኮኖሙ አበ ለሰብአ ግብፅ ወኢትዮጵያ

በከመ ጳውሎስ ሐዋርያ

ትርጉም፡- ከእስክንድር ብሩህ ክርስቲያን የተገኘው ብሩህ ኮከብ የሆነው ቅዱስ ማርቆስ እንደ ጳውሎስ ለኢትዮጵያና ለግብፅ ሰዎች አባት ሆናቸው

931. በብዙ አህጉር

በብዙ አህጉር የዞርክ የጌታን ወንጌል ያስተማርክ /፪/

የዲቁናን ግብር በክብር የፈፀምክ ብፁዕ ነህ

ብፁዕ ነህ እስጢፋኖስ ብፁዕ ነህ

932. ገብረ መንፈስ ቅዱስ

ገብረመንፈስ ቅዱስ የዓለም ብርሃን ናቸው /፪/

ይኸው ለዘላለም ያበራል ሥራቸው /፪/

933. ጻድቃን ቡሩካን

ጻድቃን ቡሩካን ዓለምን ንቃችሁ

የክርስቶስን ፈለግ የተከተላችሁ

በመንግሥተ ሰማይ እጥፍ ነው ዋጋችሁ

ሰአሉ ለነ አሰተምሕሩ ለነ

እስመ በጸሎተ ጻድቃን ትድኅን

ወኢትማስን ሀገር

ቅዳሜ ሰማዕት እስጢፋኖስ ዲያቆን

ወቅዱስ ጊዮርጊስ መክብበ አሚን

ወኢየሉጣ ወቂርቆስ ሕፃን

ገብረመንፈስ ቅዱስ ዘእምአቅሌያስያ

ወተክለሃይማኖት ዘኢትዮጵያ

ወማርቆስ አብ ዘእስክንድርያ

934. ኮከብ ብሩህ ገብረ መንፈስ ቅዱስ

ኮከብ ብሩህ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ዘሠረቀ

እምአቅሌስያ ቤተክርስቲያን ዘንሥምያ

ኮኖሙ አበ ለሰብአ ግብፅ ወኢትዮጵያ

አማን ገብረመንፈስ ቅዱስ ሐዋርያ

ትርጉም፡- ቤተክርስቲያን ብለን ነው ለግብፅና ለኢትዮጵያ ሰዎች አባት ሆናቸው በእውነት ገብረመንፈስ ቅዱስ ሐዋርያ ነው።

935. ወይቤሎሙ

ወይቤሎሙ ሑሩ ወመሀሩ ለዘየአምን /፪/
ወንጌለ መንግሥተ ሰማያት /፬/
በሕይወታችሁ ስበኩ በኑሮአችሁ
ከጽንፍ እሰከ ጽንፍ
በዓለም ዙሪያ አዳርሱ ሳትሰለቹ
ደመና ጠቅሳችሁ እንደወፏ
በኃጢአት ገመድ ተይዞ ለታሰረው
በዓለም ጽልመት ለተዋጠው
የእውነት መንገድ ብርሃን ለጠፋበት
በሁለንተናው ፈንጥቁበት
የጽድቅ እንጆራ በማጣት ለተራበው
የሕይወታችን ውኃ ለተጠማው
ቀቢፀ ተስፋ በልቡ ላደረባት
የወንጌልን ማእድ አቅርቡለት
አርድእተ ወንጌል ካህናት ሊቃውንት
ለተልእኮ የጠራችሁ
ከእውነተኛው ምንጭ ከጌታ ከባሕሩ
ከሕይወትን ውኃ የጠጣችሁ
ወይበሎሙ ሑሩ ወመሐሩ ለዘየአምን /፪/
ወንጌል መንግሥተ ሰማያት /፬/

936. ንዌጥን ዜማ

ንዌጥን ዜማ /፪/
ሊያሬድ ጥኡመ ልሳን /፬/
እንጆምር ዜማውን /፬/
የያሬድን /፪/ ጥኡመ ልሳን /፬/

937. ተነግሮ የማያልቅ

ተነግሮ የማያልቅ ነው ጸጋህ /፪/
በጸሎት የተጋህ የሃይማኖት ፍሬ
ተክለ ሃይማኖት የወንጌል ገበሬ
በወንጌል ብርሃን ሕዝቡን የመራኸው
የኃጢአቱን ባሕር ከፍለህ ያሻገርከው
ኢትዮጲያዊው ሙሴ በመስቀልህ ባርከን
ፍሬ እንድናፈራ ንጹሕ አድርገን /፪/
ሐዲስ ሐዋርያ አባ ተክለሃይማኖት
ወንጌል ያስተማርከው ለክርስቶስ መንግሥት
ጠበልህ እንድምረን ውረድ አባታችን
በእጣንህ መኣዛ ይፈወስ ደዌአችን /፪/
ለማጠን የበቃህ የሥላሴን መንበር
ሰይጣን ከቶም አይደርስ በሄድክበት ሀገር
ለህሙማን ሁሉ የሆንካቸው ፈውስ
ጠብቀን አቡዬ በሥጋም በነፍስ
በጣሙን የበዛ ትሩፋት ምግባርህ
ጸሎትህን ያልተውክ ቢቆረጥ አንድ እግርህ
ምእራፈ ቅዱሳን የወንጌል ገበሬ
እኛንም አድነን ከዚህ አለም አውሬ

938. ለሳዉል ወኬፋ

ለሳዉል ወኬፋ /፪/
አክሊሎሙ ትኩነነ ተስፋ /፬/

939. የአምላክን በረከት

የአምላክን በረከት ጸጋውንም ሸተው
በመከራ ጸኑ ከዲያብሎስ ታግለው
በእምነታቸው ጽናት በእግዚአብሔር ጸጋ
ቅዱሳን አባቶች አግኝተዋል ዋጋ
የእምነቱ ገበሬ ተክለሃይማኖት

በአምላክህ ታምነህ ድል አደረግኽ

ጠላትን

ፈጣሪ የሰጠኽን ረድኤት በረከት

ለእኛም እንዲሠጠን ለምንልን ከአምላክ

የአምላክ ባለሟል ገብረመንፈስቅዱስ
ኢትዮጵያን አስማርካት በጾምና ጸሎት
ታማኝ አገልጋይ ነህ ለኀብረተሰብህ
ልጆችህን አስተምረን እንጓዝ በአንተ እግር
ጻድቁ አባታችን ታማኝ አገልጋይ
አቡነ አረገዊ ደስ ያሰኛል ሥራህ
እንደ አምላክህ ፈቃድ በሕጉ ተመርተህ
በዘንዶ ጀርባ ላይ ደብረ ዳሞ አየንህ
ቅዱስ የሦስት ዓመት ሕፃኑ ቂርቆስ
ገድልህ አስደናቂ የህሙማን ፈውስ
እናትህ ኢየሉጣን በርቺ አይዞሽ እንዳልክ
ልጆችህን ጠብቀን ከዲያብሎስ ተውሣክ

940. የጸጋ ምስጋና

የጸጋ ምስጋና ለሰው አለውና
ለገብረሕይወትም ይገባል ምስጋና
ገብረመንፈስቅዱስ የአለም ብርሃን /፪/
እኛንም አንደአንተ አምላክ ይባርከን /፪/
ጊዜአችን እንደሳር መሆኑን አንርሳ /፪/
እንደ ገብረሕይወት ለጽድቅ እንነሣ /፪/
ማግኘት ከፈለግን የዘለዓለም ሕይወት
ለጽድቅ እንነሣ እንደ ገብረሕይወት

941. ማርቆስ ዘአንበሳ

የወንጌል ገበሬ
በዓለም ላይ ዞረህ የዘራኸው ፍሬ
መጽደቁን ስላየ ጠላት ገብቷልና /፪/
ፍሬ እንደያፈራ መስቀሉን ይዘህና /፪/
ተወከፍ ጸሎተነ ውስተ ኖኅ ሰማይ /፪/
ማርቆስ /፪/ ሰባኬ ወንጌል
የምታመልኩትን ኑ ዛሬ ምረጡ
የምስጋናን መሥዋእት ወደ ኢያሱ አምጡ
የቀለጠውን ወርቅ ጥጃውን ትታችሁ /፪/
እግዚአብሔርን ያዙ ይሁን አምላካችሁ /፪/

942. በድፋረትና

በድፋረትና በትእቢትም በመናቅም /፪/
በጻድቃን ላይ የሚናገሩ /፪/ ክንፈሮች ዲዳ
ይሁኑ /፪/

943. ይትፌስሑ

ይትፌስሑ ጻድቃን የዋሃን ውሉደ
ብርሃን /፪/
በትፍስይት የሀሎ ውስተ አድባር
ትርጉም፡- በምድር የዋሃን የሆኑ የብርሃን
ልጆች

944. ተክለሃይማኖት

ተክለሃይማኖት ፀሐይ የኢትዮጵያ ሲሣይ
ምእራፈ ቅዱሳን /፪/ በነፍስም በስጋ አትለየኝ
የቅዱሳን አርእስት የዋሻው ብርሃን
የጸሎት ባለቤት የነዳያን መድኅን
ገና ስትወለድ አምላክ የመረጠህ
የድውያን እምነት ፈዋሹ አንተነህ /፪/
ገና በሦስት ቀን በሕፃንነትህ
ጌታን አወደሰው ቅዱስ አንደበትህ
ደግሞም እግዚአብሔር አስቦሃልና
በወጣትነትህ ወጣህ ለምነና /፪/
ሌትና ቀን ሳትመርጥ ክረምትና በጋ
ስትጸልይ ውለህ ስትጸልይ ነጋ
በመቆምህ ብዛት አንድ እግርህ ሲነሣ
ጸሎትህን ፈጸምክ ለሥጋ ሳትሣሣ /፪/
ምንኛ ድንቅ ነው ቅዱስ የአንተ ብርታት
ሰባት ዓመት ሙሉ በአንድ እግርህ ጸሎት
የዓለም ግዛንግሷ ሀብቷ ሣይስብህ
ለኢትዮጵያ ጸለይክ ቆመህ በአንድ
እግርህ /፪/
የሃይማኖት ተክል የኢትዮጵያ አባት
ምሕረት ከአምላክ ለሀገርህ አሠጣት
እኛንም አግዘን ጽድቅን እንድንሠራ
በተሠጠህ ሥልጣን ጠብቀን አደራ /፪/

945. ተክለአብ

ተክለአብ ሐዲስ ሐዋርያ /፬/
ሐዲስ ሐዋርያ /፪/ ዘኢትዮጵያ /፪/

946. ዜና ውዳሴክ

ዜና ውዳሴክ ፈጸምኩ /፪/ ተክለሃይማኖት

/፪/ በለኒ አባ ወልድየ በለኒ አባ /፪/
ወልድየ ተክለሃይማኖት /፪/

947. ቅዱሳን አባቶች

ቅዱሳን አባቶች በገዳም ያላችሁ
ሰላምን አሠጡኝ ከፈጣሪ አስታርቃችሁ
በሀገራችን ላይ ይደር በረከት ጸጋችሁ
አምላክ በበደላችን በእኛ እዳይከፋ
ምልጃችሁ አይለየን በኃጢአት እንዳንጠፋ
ሰላም ለእናንተ ይሁን ቅዱሳን አባቶች
ከዓለም ርቃችሁ በጾም ጸሎት የጸናችሁ
በገድል በትሩፋት ዲያብሎስን የረታችሁ
ቅዱሳን አባቶች በእኛ ላይ ይደር ጸጋችሁ
ውርጭ ሀሩሩን ሣትሰለቹ በጸሎት
የጸናችሁ
በረከታችሁ በእኛም ይደር በልጆቻችሁ
ጸጋችሁ ብዙ ነው ጸሎታችሁ ኃይል
ያደርጋል
ከጥፋት ጠብቆ አጋንንትንም ይዋጋል
የእናንተን ጽናት አይቶ እኛንም ታግሶናል
በኃጢአት ስንረታ በምሕረት ጎብኝቶናል

948. ጼና አልባሲሁ

ጼና አልባሲሁ /፪/
ለገብረ መንፈስ ቅዱስ ከመጼና ስሂን /፪/
አልባሲሁ ዘሜላት /፪/
ዘወረደ ውስተ ገነት /፪/
ትርጉም:- የገብረ መንፈስ ቅዱስ ልብሳቸው እንደ
ሸቱ ያማረ ነው ደግሞም ልብሳቸው እንደነጭ ሐር
ነው እርሱም ወደ ገነት የወረደ ነው

949. ያሬድ ማኅሌታይ

ያሬድ ማኅሌታይ ለእግዚአብሔር ካህኑ ስብሐተ
ትንሣኤ
ዘይእዜኑ ያሪት ቶታህኑ ወወንጌል አሳዕኑ /፪/
ትርድአነ ነአ በህየ መካኑ ከመ ፀበል ግዑዛነ ፀርነ
ይኩኑ /፪/
ትርጉም:- የጫማህ ማዘቢያ /ማሰሪያ/ ኦሪት የእግርህ
መጫሚያ ወንጌል የሆነና የትንሣኤን ክብር
የምታስተምር የእግዚአብሔር አገልጋይ ማኅሌታዊ
ያሬድ በዚህ ቦታ ትረዳን ዘንድ ና

950. ሰማየ በአብ

ሰማየ በአብ ወበወልድ አርያመ ወበመንፈስ ቅዱስ
ኀበ ዓረጉ አነ /፪/
ሰማዕኩ እመላአእክት ዝማሬ በአድንኖ ወበአትሕቶ ቦ
ዘያጽሕሱ ወቦ ዘይዜምሩ /፪/
ትርጉም:- በአብ በወልድ በመፈስ ቅዱስም ቸርነት
ሰማይ ወጥቼ ጽርሐ አርያም ደርሼ ከመላእክት
ዝማሬ /ምስጋና/ ሰማሁ ከእነርሱም በዝቅታና
በትኅትና የሚያሸበሽቡ አሉ ዙሪያውንም ቆመው
የሚዘምሩ አሉ

951. በኢትዮጵያ ምድር

በኢትዮጵያ ምድር የዞርክ የዜማን ትምህርት
ያስተማርክ /፪/
የክህነትን ሥራ በክብር የፈጸምክ ብቱዕ ነህ /፪/
ቅዱስ ያሬድ ብጹዕ ነህ /፪/

952. የጻድቃን ከተማ

የጻድቃን ከተማ ሆነች መንግስትህ
አምላክ የፈጠርካት ለወገኖችህ /፪/
የአራዊት ድምጽ የሌሊቱ ግርማ
በትዕግሥት አለፈ ያን ሁሉ ጨለማ /፪/
ሀብት ንብረትን ተድላን ሁሉ ናቁ
መንግስትን ብቻ ለማየት ናፈቁ /፪/
ቅዱሳን እጆችህ ሰውን የፈጠሩ
ለሰው ልጆች ሲሉ በሐብል ታሠሩ /፪/
ይህንን ሁሉ ነፍስ ቅዱሳንም አይተው
በጎዘን አለፈ መላ ሕይወታቸው /፪/
ምሕረትህ የበዛ ቸሩ አምላካችን
በምህረትህ ጎብኛት ኢትዮጵያን /፪/

953. ቅዱሳን በሙሉ

ቅዱሳን በሙሉ ከአምላክ አማልዱን /፪/
ልንጠፋ ነውና በዝቶ በደላችን /፬/
ጻድቃን ሰማእታት ንጹሐን ሁላችሁ /፪/
ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ዓለምን ንቃችሁ /፪/
ለሰማያዊው ክቡር ለአክሊል የበቃችሁ /፪/
ወደ አምላክ አቅርቡም በጽኑ ምልጃችሁ /፬/
ድንግል እናታችን ኪዳነምሕረት /፪/
ቅድስተ ቅዱሳን የጻድቃን እናት /፬/
ርኅርኅተ ኅሊና አሳስቢ ከልጅሽ /፪/
ይቅርታ እንድናገኝ በፍጹም ልመናሽ /፬/

954. ቅዱሳን መስክሩ

ታምሩን ያያችሁ ቅዱሳን መስክሩ
ፍቅሩን ቸርነቱን ለዓለም ንገሩ /፪/
በየዋህ ልቡና ንጹሕ መሥዋዕት
አቤል ግለጽልን ለጽድቅ መሞትን
ኖኅም ተናገረው ለአንተ የታየህን

ዛሬን ብቻ ትተህ ነገን ማሰብህን
ተናገር አብርሐም የአምላክን ሥራ
እንዴት እንደነበር ያኔ ስትጠራ
ልጅህን ያሰጠህ ፍቅሩን ግለጽልን
በእምነት መታዘዝን ለእኛም አስተምረን
ግለጽልን ዮሴፍ እንዴት እንደነበር
ፍትወትን ድል ነስቶ ለሃይማኖት ማደር
ከራስ ደስታ ይልቅ ለወገን መሞትን
አስተምረን ሙሴ ፍቅርና ጽናትን

955. ምስጋና ጀመረ

ምስጋና ጀመረ ብሎ ሃሌ ሉያ
ማኅሌታይ ያሬድ ዘኢትዮጵያ
ምስጋና ጀመረ ብሎ ሃሌ ሉያ
ይበል /፫/ ሃሌ ሉያ
ጥዑመ ልሳን ያሬድ /፫/ ዘኢትዮጵያ
ብሉይን ከሐዲስ ሐዲስን ከብሉይ
አስተባብሮ ይዞ ያሬድ ማኅሌታይ
ምሥጢር ተገልጦለት ከምድር
እስከ ሰማይ
በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ምሥጢር እያስማማ
ምስጋና ጀመረ በእነዚህ ከተማ
ለቅድስት ሥላሴ በሦስት ዓይነት ዜማ
በገና ጸናጽል ሲመታ ከበሮ
ዜማው ሲንቆረቆር በሰው ልጆች ጆሮ
የያሬድ ዝማሬ ያድሳል አዕምሮ
ምእመናን እናቅርብ ለአምላክ ምስጋና
በእዝራ መሰንቆ በዳዊት በገና
ዜማውን ከያሬድ ተምረናልና

956. ጽድቅ ተክለ አልፋ

ጽድቅ ተክለ አልፋ
ጽድቅ ካማናጎ ሌሊተ
ኸኸ ይበል ኸኸ /፪/
ወገድሉ ጸዳል እንደ ኮከብ እንደጨረቃ /፪/
እንደ ቀን ፀሐይ ተክለ አልፋ እንቁ ባሕርይ
ኸኸ ይበል ኸኸ /፪/
ጽድቅ ተ/ሃይማኖት ዘደብሩ ሲና
ወኢቲሣ ግሩም መዋኢ አንበሳ
ኸኸ ይበል ኸኸ /፪/
ጻድቅ ገብረመንፈስ ቅዱስ በምድረ ዝቋላ
ወዛምድረ ከብድ መለኮት መንፈሣዊ /፪/
ነበልባላዊ ባሕረ ገዳማዊ

957. ግሩማን መላእክት

ግሩማን መላእክት /፪/ ሱራፌል ወኪሩቤል /፪/
ወረዱ ዮም ይትቀበሉከ በብሔር አማን /፪/
ገብረመንፈስ ቅዱስ ገባሬ ኃይል /፪/
ትርጉም፡- ኃይልን ተአምርን የምታደርግ ገብረ መንፈስ ቅዱስ
ቅዱስ ሆይ ክንፋቸው በነበልባል የሆነ የሚያስፈሩ
መላእክት ሱራፌልና ኪሩቤል እውነት በማለት ይቀበሉህ ዘንድ ዛሬ ወረዱ

የገባኤ መክፈቻና መዝጊያ መዝሙራት

958. የአማኑኤል እናት

የአማኑኤል እናት መድኃኔዓለም
ገባኤውን ባርኪው ድንግል ማርያም
ገባኤውን ባርኪው /፫/ ድንግል ማርያም

959. ዝማሬ ዳዊትን

ዝማሬ ዳዊትን ተልዕኮ አርድእትን ቅዳሴ
መላእክትን /፪/
የተቀበልክ አምላክ /፬/ የእኛንም ዝማሬ
ተቀበል /፪/

960. ቃልህ ሲነገር ልስማ

ቃልህ ሲነገር ልስማ ጌታ ሆይ እባክህ
ልቤን ክፈተው /፬/ የልድያን ልብ
እንደከፈትከው /፪/

961. ያሰባሰበን

ያሰባሰበን ቸሩ ፈጣሪ ይክበር የሁሉ ጌታ
አምላክ ሰብስቦናል ምስጋናውን እናቅርብ በእልልታ

962. በስምህ ስንጀምር

በስምህ ስንጀምር ጉባኤ ስናደርግ
በመካከላችን ቸርነትን አድርግ /፪/
ልቦናችን ላንተ ተከፍቶ እንድንማር
ጉባኤያችንን ባርክ ሕያው እግዚአብሔር
መከፋፈል ገብቶ በመካከላችን
እንዳይነጣጥለን ሰይጣን ጠላታችን
ምራን አምላካችን እኛን አስተምረን

በተዋሕዶ እምነት እንድንፀና አድርገን
ምስጋናችን ደምቆ አንተ እንድትደሰት
አንደበታችንን ለምስጋና ክፈት
የምስጋና መስዋዕት እንሰዋልህ ጌታ
ሥራህን እናድንቅ እንዘምር በእልልታ
በቅዱስ ቁርባኑ ፍፁም እንዲያፀናን
ሰማያዊ መልአክ ሱራፌል ላክልን

963. የጥበብ መገኛ

የጥበብ መገኛ የሰላም ንጉሥ /፪/
ፊትክን ግለፅልን ቸሩ ክርስቶስ /፪/
በዚህ ባለንበት በረቂቅ ማዕዳችን /፪/
የተማርነው ትምህርት ይፅና በልባችን /፪/
ዘውትር አትለየን ከመሐከላችን /፪/
አሜን ወአሜን ለይኩን ለይኩን /፪/

964. በምህረት በይቅርታ

በምሕረት በይቅርታ ያሰባሰበን ጌታ
ፍቅር ነው ለዘላለም አንደ አምላካችን የለም
የጠላትን ክንድ ሰብሮ ባሕር ከፍሎ አሻግሮ
ምድረ ርስትን ሰጥቶናል በማዕረግ
አቁሞናል
ስንወድቅ እያነሳ በደልን እየረሳ
አባት ሆኖናል በግልጥ ሳይከፋ ሳይለወጥ
ሰርክ አዲስ ነው አዋቂ ማለዳ ተናፋቂ
ነጋ ጠባ ስለኛ የማይደክም የማይተኛ
ሰይጣን አንገቱን ደፋ ርስታችንም ሰፋ
አስገባን ክንዱ ስር ሰበሰበን በፍቅር
የሲና ንዳድ ግለት ከቶ አልሰጠንም ለሞት
ረሀብና ቸነፈር አላስቀረንም ከዱር
ቀኑንም በደመና ሌሊት በብርሃን ፋና
እየከለለ መራን እየመገበን መና
ከሰፈር አውጥቶናል ድንኳኑን ተክሎልናል
በመንፈስ እንሰግዳለን ለስሙ እንገዛለን
ለሞት እንዳንተኛ ዓይናችንን አበራ
ይኸው ተሰብስበናል ወደ ሕይወት ተራራ

965. ኦ አንተሙ

ኦ አንትሙ ሕዝበ ክርስቲያን
በከመ ተጋብዕክሙ በዛቲ እለት
ከማሁ ያስተጋብእክሙ በደብረ ጽዮን ቅድስት
ወበ ኢየሩሳሌም አጋእዚት

966. ጸጋ ነሳዕነ

ጸጋ ነሳዕነ ወሕይወተ ረከብነ
በኃይለ መስቀሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ
በኃይለ መስቀሉ
ኪያዕከ እግዚኦ ነአኩተ
ወንሴብሐከ እግዚአብሔር

967. ኢትግድፈነ

ኢትግድፈነ /፪/ ወኢትመንነነ
አምላከ ሰላም ተራድአነ /፪/
እግዝእትነ /፪/ ነጽሪ ሀቤነ /፪/
ሰላመ ወልድኪ የሀሎ ምስሌነ /፪/

968. አስተምሮናልና

አስተምሮናልና መክሮናልና ገስፆናልና
እግዚአብሔር ይድረሰው ምስጋና /፪/

969. ታቦት እንተ ውስቴታ

ታቦት እንተ ውስቴታ ኦሪት እንተ ውስቴታ
ውቱረ ይኬልልዋ በወርቅ /፪/ ይኬልልዋ

970. አምላካችን

አምላካችን /፪/ በሰላም አሳድረን
ቀኑን በሰላም እንዳዋልከን
የሰላም ሌሊት አድርግልን
እመቤታችን አማላጃችን ተመልከች ወደኛ
የልጅሽ ቸርነት ይሁነን መዳኛ
ያንቺ አማላጅነት አይለየን ከኛ

መዝሙር በእንተ ክረምት

971. ሰማያት ዘምሩ

ዝናማቱም ዘነሙ ወንዞችም ጎረፉ /፪/

የአምላክን ጸጋ እያትረፈረፉ /፪/

ሰማያትም ዘመሩ በልዑል ቃሉ /፪/

የፍጥረታት ሁሉ መጋቢ አንተ ነህ እያለ /፪/

ገበሬም አረሰ ፈጣሪዉን አምኖ /፪/

ዘርንም በተነ በምድር ላይ ከጎተራዉ ዘግኖ /፪/

ደመናትም ዓለምን ይዞራሉ /፪/

በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ዝናምን ሊያድሉ /፪/

በልምላሜ ተዋቡ እፅዋት አትክልቱ /፪/

ፍሬን ይሰጡ ዘንድ አብዝተዉ በጊዜዉ በወቅቱ /፪/

መሬትን ከእርሻ አድርጋ ዉለታ /፪/

የላቡን የወዙን ከፈለች እንዳዘዘ ጌታ /፪/

ድካሙን ጥረቱን አምላክ ተመልክቶ /፪/

እንኳን ፍሬ ሰጠዉ አብዝቶ አድርጎ መቶ /፪/

ዝናምን ለዘር ለልምላሜ ፍሬ /፪/

የሰጠን አምላክ ይመስገን ይክበር በዝማሬ /፪/

የኦሮምኛ ዝማሬዎች

972. ሎላ

ሎላ ፈኖ ኢሳቲን አጀሴ
ፈኖ ኢሳቲን ነሞታ ነጉማ ኑሂሬ /፪/

973. ኮቱ መሌ

ኮቱ መሌ ሚካኤሊ ሂን ደንዴኜ ቆፋኮ
ዳበቹ ደደቤ ሆለታ ሚሊኮ
ማለን ሲቲ ሂማሬ አቱምቲ ኒቤክታ
ዲኒኮ ባዬዳ ሁነዳቱ ነኤገታ
ሲቲን ቦአ ሚካኤል አባኮ
ኩፉፍ ጀዴ ሆለታ ሚሊኮ
ጉቴ ኢራ በኤ ገላኒቺ ሱኒ
ኬሲኮ ጀቀሜ ሶዳን ጉተሙኒ
ኮቱ ማሎ ሚካኤል አባኮ
ገመቲ ርጌ ሂን ሃፉ ቢያኮ
ሆኡካ ሃርካኮ ሲተንኬና አኒ
ሚካኤሊ ማሎ ኢቲ ነን ላተኒ
አኒ ሂን ቤኩ ባየቴ ዲኒኮ
ሂን ገዲሲን ሚካኤል ሀርካኮ

974. ናፍ ኬኒ

ናፍ ኬኒ ዋቀዮ ሰሙፊ ቀልቢ
የሮ ሁንዳ ከን ሲ ያዱ
ሉቦኮስ ናታሲሲ ሌራኬ ቆፋን ከን ገመዱ /፪/

975. ገለተ ዋቃዮ

ገለተ ዋቃዮ ዬሮ ሁንዱማቲ
አከዳዊት አኑ ገርቢቻ ኢሳቲ /፪/
ጎፍታንኮ አማኑኤል ባዬ ናጃለቴ
ሴጣና ሀርካ ዲጋ ኢሳን ናቢታቴ /፪/
ሴጣና ነ ሂንያዲን አና ያ ዲነኮ
ሁምነ ጎፍታን ሞአቹን ዮሚስ ከንኮ /፪/

976. ያ ዋቀዮ

ያዋቀዮ ሲያገለቱ ያዋቀዮ መቃን ኬ ያኡልፋቱ
ለፈ ጀላስ ታናን ሰሚራስ ከን በለሊኡ
ዮ በርባኔ ሂንጂሩ ከን አማ ዋቃ ኬኛ ገኡ
ኢኒ ሁኑዱማራ ጫላ ገለኒ ኢሳ ሀገኡ

977. ጃለሊ ዋቀዮ

ጃለሊ ዋቀዮ ጉያ ጂማታ ፈኖ ኢራቲ ሙለቴራ
ኢየሩሳሌም ኑገልቹዳፍ ቢያ ሀራ /፪/
ኢየሩሳሌም ገሉፍ ጀጀባዳ ዬሮ ሁንዳ ያነሞታ
ዲሀቴራ ዱፋቲን ጎፍታዳ /፪/
ኤኙ ከን ቆጳኤ ኢየሩዳሌም ኢሼሀራ ገሉዳፊ
ቁልቁሎታ ወጂን ሚርጋሳ ዳበቹፊ /፪/

978. ጃለላን ሁንዳ ጎቴ

ጃለላን ሁንዳ ጎቴ ናማ ፈዱሱፍ ፈኖራ ኦልቴ
ባየቴራ ባየቴ ጃለሊኬ /፪/ ያዋቅ ገለተኬ

979. አኒፍ መኪኮ

አኒፍ መኪኮ ዋቀዮ ዋቄሲና /፪/
ኢሳቲ አመኔ አብዲ ጎደኔ
ጎቻ ኢሳ ዱጋ ባና /፪/
ወሪ አማሌቆን ናኖ ኬኛ መርሱን
ኢኒ ሲንሂን ኦልቹ ኤሳ ጂራ ጀቹን
ጎታ ቤከማዳ ኢኖ ዋቅኒ ኬኛ
ሰልጲናን ዶቢሴ ወረ ዲና ኬኛ
ኢሳቲ ሂርከኔ ሁምኒኬኛ ሂን ላፍኔ
ገርጋርሳ ሳቲኒ ዋንትሄዱ ደርቢኔ
መቃሳ ጃጃቹን ኑኒፍ ሆጂ ኬኛ
ዮሙ ሂን ኤራፈኑ ኦልማ ዋቃ ኬኛ
አከ ማርያሚ ኦቦሌቲ ሙሴ
ዋቀዮፍ ሆጀና ኢሳ ኑገሬ
ኢሰራ ከን ሀፊ ከን ቢራ ሂን ቤክኑ
ዋቃ ኦረሞታቲፍ ሀርከ ኬኛ ሂንላኑ
ናሱዳን በቃቴ ዲኒ ሰጋሌሳ
ዬሙ ደገሀሙ ሰሚ ቀቀዌንሳ
ኢሳን ሱን ሁምናፊ ቀቤኛ ሳኒኒ

ኑትገሩ ኒሞና ዮሚዩ ታናኒ

980. ናቢራ ሂን ዳርቢን

ናቢራ ሂን ዳርቢን አደራ ዋቃኮ
ዋቤኩ ሂን ደንዴኜ ጀማዳ ኢጂኮ
አን ዱከናፍ ኢፋ አዳን ባሴ ሂን ቤኩ
ኣገርቱኮ ሳቂ ኢጂኮ ያበነሙ
ጩበማዳ ጀቴ ሂነ ደርቢን ናቢራ
ዲቢናኮ ኢላልቴ ሂን ዲዲን ነዱራ
ጩበማ ፈዩሱን ሲፍ አመላ ኬቲ
ነያዳዱ ኡማማ ሃርካ ኬቲ
ባራ ጂሬኛኮ ያዶዳን ቃባሜ
ጋናማፍ ገልገላ አቢሳ ናዶዋቴ
ጂሬኜ ፎን ኮቲ ቡአ ናቲ ታኤ
ጎፍታ ሲተን ከኔ ሲቱ ሁነዱማ ሞኤ
በረኮ ሁንዱማ ጩቡዳን ደበርሴ
ወንታ ሲቲ ሂን ቶሌ ዋን ባዬ ሆጀዴ
አከ ናፈዩስቱ ገሩ ነን አብደዳ
ገራሚ አከኬ ኤሳቲን አርገዳ

981. ዱአ ኬሳ

ዱአ ኬሳ ኑባስቴ ጃለላ ኬቲን <u>ኑዋምቴ</u> /ፎ/
ገለትኒ ሲፍ ያተኡ /ፎ/ ያ ዋቀዮ /ፎ/

982. ዋቀዮ ኑዳጋሂ

ዋቀዮ ኑዳጋሂ ባዩስኔ ሲከደና
ቶሉማኬ ኑፈ ላዱ ቁልቁሎፍኔ ለሚ ካንኬ ታና

983. ሳጋሌ ጋማቹ ዳጌሲሳ

ሳጋለ ጋማቹ ዳገሰሳ
ዋቀኮቲፍ ገለታነ ዲዬሳ
ኢዩኮ ደገኤ ናፍ ቢርመቴ
ሂርማቱ ዳላሳ ናጎደቴ
ቢያ ለፋኬሳ ኡቱን ጂሩ
ጎፍታንኮ ነዋሜ ከን ናፉሩ
ሴና ኮ ጡራኤ ናፍ ጂጂሬ
ገመዴን ፋርፈዳ ነቲ ቶሌ
ቱፈተማን ቱሬ ከን ገተሜ
ነማ አብዲ ደቤ ኢራንፈተሜ
አቲ ወንተ ጉዳ ናፍ ሆጀቴ
ኩፋቲኮ ኬሳ ኦል ናካስቴ
አን ጩበማ ተኤ ዲጳዩ
ጎፍታንኮ ናነ ዲፍኔ ካተሳዬ
ሃርካ አራራሳ ናፍ ዲሪርሴ
ከራ ኢሳ ፈዩና ና አገርሲሴ

984. ኤጕዳ ኑቲ

ኤጕዳ ኑቲ /ፎ/ ያዋቀዮ ከንሲፉልዱራ ዳባኑ /ፎ/
ከን ካናነ ኑ ገኡ ቁልቁሉማ ሂን ቀብኑ /ፎ/
ያካ ኬኛ ሂን ቤኩ ናምኒ ቶኮ ሲመሌ ያጎፍታ
ዱፍኔ ሲቲሂመና ሲንዶክሲኑ አቲ ሁንዱማ ቤክታ
ኦል ጀቹ ደደብኔ ቦቁ ቡስኔ ባይና ጩቡኒ
ገደደማ ፊዩ አስኑ ዳብዩ ነመ ኑ ጎቹኒ
ኦቶ አቲ ኑኑፊን ኑኑፊኔ መነኬ ኬሳቲ
መቃኬን ጀባኔ ዮና ገኜ አከነማ ሚቲ
መቃኑ ሞጋሱ ያዋቀዮ መቃ ኑቲ ሂን ቀብኔ
ኑዋመቴ ማሌ ጎፍታኬኛ ኑቲዮም ቆጸፍኔ
ኑሌያሲሱዳፍ ሂን በርባኔ አቲ ጎፍታኮ
ረከኔ ዮዱፍኔስ ኑኑፊኔ አቲ ጋፈረኮ
አቲ ኤርጋኑዋምቲ ኑሂንገቲኒ ያዋቅ በዱፊኑ
ገረኬ ኩተዱ ቢያ ለፋ ኑት ገራኬ ሂንዱፍኑ

985. ሉቡን ኮ ዋቀዮፍ

ሉቡንኮ ዋቀዮፍ ኒፋርፈቲ
ዋቀዮ ጋሪኮስ ኒ ያደቲ
ቁልቁሉዳሆ ቁልቁሉ ጀቻ
መቃሳ ኡልፋታ ኒ ፋርፈቲ
ከን ናጋርጋሬስ ኢተን ገመዳ
ዬሮ ረኪናስ ዬሮ ጋማቹ
ጩቡ ኮ ወሊን ከን ነጃስቴ
ገለቴፈቹን ኒቲ ባየቴ
በረሲሳ ከንኮ ከን ዬሮ መራ
ጃቢና ኪያፍ ከን ተኤ ካራ
ጀቺ ኢሳ ጉዳን ለጴኮ ቀሬ
አጀጃ ኢሳፍ ነን ጀዳ ቶሌ
ኢዶ ቁልቁሉዳን ከን ነዳቃተ
ጡሪ አዱኛስ ከን ነራ ዲቂ
ዮሚዩ ሂን ደብኔ ኢሳን አብደዴ
ፈዩና ሉቡስ ኢሳን አርገዴ
ቢታፍ ሚርጋኮ ከን ናፍ አጃጁ
ገዳንቱማኮስ ከን ናፍ ከበጁ
ነጋን ጉታሜ አላፍ መኒኮ
ያ ገለቶሙነ ጀዳ ዋቅኒኮ

986. አከሚን ታሬ

አከሚን ታሬ ጂዴ ቦዳን ኮ ሂን ላሉ
ኤሱማ ሂን ጂሩ ማርያሚ ከን ሲጫሉ
ጀልቀባፍ ዱምኒኮ ሲኢ ሀርሜኮ
ሚልኪን ናፍ ጉዱንፊ ዱማ ጂሬኛኮ /ፎ/
ጃለላፊ ነጋን ደበሜ ጋዲ ባየቱስ
ነሃማቱስ ገራንኮ ባዬ አብሳ ደደቡስ

ዲቤኮፍ ቆሪቻ ናፍ ታቴ አማ ፈዬራ
ገለታን አን ገልመኬ ሴና ሁንዱ ታሬራ
ኢሚማን ኮ ዬቢ አርገቴ አኒስ ጀባዬ
አካ ገዲ ጀዬቲ ዚን ሀፍኔ አማስ ኦልጀዬ
ያዲን አዱኛከና አናፍ ጉፉ ተኡሌ
ኩፌ አከ ዚን ሀፍኔ ሀርሜ ኮ ናፍ ኮቱ አማሌ
ዱራን ዱርሴ አዱኛ ከናፍ ሲፌለቴራ
አዳ ጎዬ ሲኡሜ ጎፍታን ዱበርቶታራ
ኤጋ ኩኖ ዱብሬ ማርያሚ ገለታ አርገዱ
ከን አካኬ ዚን ጂሩ ጀዱ ደሎኒ ሁንዱ

987. ጃለሊ ዋቀዮ

ጃለሊ ዋቀዮ አናፍ ባየቴራ
አንጎ ሙጨማ ኢሳ ቶሳን ናኬኔራ
ጃለላ ኢሳ ጉዳ ፈኖዳን ሙሊሴ
ኢኑምቲ ናዱኤ ዱአራ ነባሴ
ሙጨማኮ ዲሴ ኢሳራ ፈጋናን
አዱኛ ጃለዬ ሂዩማ ፊለናን
ጨቡዳን ቢተሙስ ናዚንዲስኔ ጎፍታ
ና ዬቢሴ መሌ ናዋሜ ጃለላን
ነፈዩሱፍ ጀዬ ባዬ ዲገሜራ
ፊንጪሉኮ ኦብሴ ኦፊቲ ናዋሜራ
ቢታ ሴጣናራ ቢሊሳ ነባሴ
ኡፈታ ኡልፊና ነራቲ ዬቢሴ
ዱአ ኢሳን ኡልፊና ከን ና ጎንፈቺሴ
ዱከና ነባሴ ከን ኢፋ ናኬኔ
አርጁማ ኢሳ ከናፍ ማለን ዲዬፈዳ
ኡማ ሰሚፍ ለፋ ነን ገለቴፈዳ

988. አብዲ ናፍ ተኤ

አብዲ ናፍ ተኤ ዋቅኒኮ
ናፍ ኤቢሴራ ለፈ ጂሬኛኮ
ከን ነቲ ሂናፉስ ኩፊፊሴ
መነኮ ኤቢሴ ሥላሴ
ፊራ ኬረቲ በሂ አዳን በሂ
አባፍ ሀደኬ ዲሲ ቢራ በኢ
ቢያ ሲፍ ቆዬሴራ ከን ቢራ
ዚን ሶዳቲኒ ዋቀኬ ሲወጂን ጂራ
ሰኚኬስ ነንባዩሳ ነን ኤቢሳ
አከጪረቻፊ ኡርጂ ነን ታሲሳ
ጀዬ ዋዳ ናፍ ገሌ ዋቅኒኮ
አኒ ኢሳፈን ቢተማ በረኮ
ነመቶልቼፍ ዚን ሰገዱ ተሱማ
ዚን አርጉ አከ ሥላሴ ቶኩማ
ዋን ዱበቴ ዚን ራዋታ ዚንደገቱ
ገለኒ ዋቃ አብርሃም ሃ ባየቱ
ቤለኤ ኛታ ኬናን ቤሉ ባሳ
ዬቦቴ ቢሻን ኬኔ ዬቡ ባሳ
ኪያ ሚቲ ቀቤኚኮ ጀልቀባ
ጎንቢሳንኮ ዚንዚረቱ ማለን ደባ

989. ጀሬን ሱን

ጀሬን ሱን ፈርደን ሳኒቲን ኑት ገሩ ዋቀኬኛኒ
ጀሬን ሱን አንጎን ሳኒቲን ኑት ገሩ ዋቀ ኬኛኒ
ኒአመና /ፎ/ ኢሳ አብደተሙ ዋቀዮን ቀብና
ጀቁምሲ ጉዳ ወራኒስ ከኤ
ሎልቱ ኦረማቲ ለፍቲ ኡከሜ
ሀሜኛ ቡአ ጉደተኒሌ
አመንቲ ኬኛ ዚንቱቁ ኤኙሌ
ዱአ ከን ካሱ ዋቀዮ ጂራ
ጎፍቲቻ ቀብና አባ ሀራራ
ሎልቱ ባዩናን ጎሊያድ ኤርጌ
ጋቸናፍ ኤቦ ኢረቲ ኤርጌ
ዋቃ ኬኛራ ኤና ሞርሜሌ
ጪረቻ ጢቆን ኢራሳ ጨብሴ
አፋን ኑጉቴ ገለትኒ ጉዳን
ኑቲስ ጀባኔ ዋቀዮ ጎፍታን
ኦቶ አብደተኒ ፈርዬንሳኒቲን
ኑሃርካ ዚን ባኔ ቀቀብኔ ኢረቲ
ዬሮ ዳበተን አፍቱሉማኒ
ኒ ሊቂምፈመን ገላኒቻኒ
ዋኤኬኛሌ ኒዱሜ ጀኔ
ዱአ ኑ ኦልቻ ከን አመነኔ
ሰባ ዋቀዮ ኤኙሌ ዚንቱቁ
ጀቢኒ አንጎሳ አመንቲ ኢሳዳ
ከደና ቆፋን ዳአ ኒዲጋ
ወራና አቆራ ኤኙ ፈጫሳ
ገረ መናቲ አልቤ ዬቢስኔ
ሞኢቻ ኡልፊና ኑቲስ ጎንፊኔ

990. ኩኖ ቦጂአሜ

ኩኖ ቦጂአሜ ሀርካ ኮ ኦል ቀቤ
ወንጌለኬ ዱጋ አዱኛፍ ለሳቤ
ኤኙማኮፍ ጠለያ ባዬ
ኤናን ዬሙ ሂዱፍ ማቲኬ
ሰገሌኬ ናፍ ደበርሲቴ
ኢጃ ጨቡ ኢፋን ጃምሲቴ
ጃለሌኬ አጃኢቡማ
ሲጂበኒስ ዚንገቱ ኤኙማ
ሜሻ ዲንቂ ጀቴ ፊለታ
ጨቡ ጂቡን ናማ ጃለታ
ሲፊለዬ ሱመ ናፍ ጫላ
አባ ነጋ አባ ጃለላ
ናፍገሌራ ሲበሬ አማ
ሁንዬን ጂሩ መርቲኑ ሱማ
ነሙደቱስ ቆርማኒ ሄዱ
ጃለላኬ ናሙ ነዚንዶዉ
ነንፋርፈዳ መቃኬፍ ረቢ

ያሶስኡ መኒ አደቢ

991. ገለታን ዲዬሳ

ጋላታን ዲዬሳ አኒ ዋቃ ናጃላቴፍ /፪/
ዬሙን ደገተሜ ሰና ኢሳ ነያደቴ
ሞቲቺ ሚሲር አጀጃ ባሴ
ሙርቲ ኢሳ ዱአ ኑረቲ ለብሴ
አቲዳ ጎፍታ ኡምቴ ሂን ደገቱ
ኡመማ ኬሳስ ሆምቱ ሰ ሂን ጊቱ
ጂራ አጀስቴ ዱአ ኒካስታ
ለፋፍ ሰሚ ኢራቲ ኤኙ ሲጊታ
ጋፈ ረኪና ለፍቲ ሂን በሪኡ
ዮ በሪኤዩ ኢፋ ሂን ተኡ
ዲቤን ባየናን አቶ ሂን ደገቱ
ሙጫኢሼ ገቴ ኦፍ ኦል ኦልቺቲ
ሲመሌ ጎፍታ ጋሪን ሂን ጂሩ
ኦሶ ነኑፊን ከን ነገርጋሩ
ጂራ አጀሴ ዱብኣ ኒካስቲ
ዮበበሌቴ ኑረቲካቲ
ጀቹን ዱበቴ ኦልኦፍ ቀቡኒ
አንጎን ከን ጎፍታ ተኡ ኦሶ ሂን ያዲን
ዱአፍ ኑዋምኔ ጂሬኛፍ መሌ
ከን ኑ ጉዲሴ ኤኙ ሲመሌ
ጋፈ ረኪና.....

992. ሲመሌ ጎፍታ

ሲመሌ ጎፍታ መዲ ገመቹ
ጨራ ጂሬኛ ሂክኒ ጂራቹ
ሲን ሚልካኤራ ሀዊንኮ መርቱ(ኧ)
ዲኒኮ ባዬ ዱበቴ
አነ ላሉን ኢቲ ኡልፉቴ
አት ገሩ ነራ ደበርቴ
ጃለላኒስ ነዌራርቴ
ዋንጆ ገርቡማ ዶቃ ሀርጫፍቴ
ኢሬኬ ጪማን ጎፍታ ነባቴ
ሆማን ዲኒ በበሮዬ
ከረ ዱአኮት በርባዬ
አቲ ጂርማ ጂሬኛቲ
ሲቲሂርከዬ በሄራቲ
ከዮ ዲናኮ ናፍ ኩኩቴርታ
ዋጆ ሰልጲና ኢቲ ኡዊስቴርታ
ቡልቺቶትን አዱኛ ከና
ወሪዬሮ ደርቤ ኡልፉተን
አርጌራ ኢና ቡረኩ ታአን
አከ ዱዳ ሀርካ ጎፍታን
ጎቺ ኢሳ ዲንቂ ጎፍታን አዳዳ
ኢኒ ኢሱማ ዮሙ ጉዳዳ
ሚቹንኮ ኢኒ ከሌሳ
ጂጂረሜ ሀራ ነዬሳ

ካናን አብደዬ መርቱ
ነሚዱዳፍ አሪፈቱ
አማ ናፍገሌ ሲቱ ናፍ ጫላ
ዶርጎማ ሂን ቀብዱ አኒ ሲንላላ

993. ገለተን ገልቻፊ

ገለታን ገልቻፊ ዋቀኮቲፍ
ቡልቶ ኢሳቲን ሴነ ሰገደ ኢሳፊ
ሃሌ ሃሌሉያ ሃሌሉያ ጀዬ
ኦልማላን ዱበዳ ወንተ ኢኒ ናፍ ጎዬ
ጀባዳ ዋቀዮ ሁንዳ ኒ ደንደአ
ጀቻ ሰጋሌሳን ሁነዱምቱ ኒ ተኣ
ኢሳነን አርገዳ ነጋ መና ኮቲ
አልፋዳፍ ኦሜጋ ኢኒ አብዲ ኮቲ
አፋን ሌንጫ ጨፊ አቢዳን ኒዳምሴ
ጂራታ ኑ ጎዬ ዱአ ኬሳ ባሴ
ሞቲ ሰሚፍ ለፋ ጎፍታን ማልዳደባ
ቂሌንሳ ኬሳሌ ኢኖ ከራ ቀባ
ባኬቲ ጋታሜ ሚዳሜ ቃምኒኮ
ና ዲሴቱ ዳረቤ ናኢላሌ ፊሪኮ
ሱጴ ኦል ነካሴ ጨባኮስ ዲዲቤ
ገለኒ ኢሳፍ ሀተኡ ፉለሳ ነዳቤ
ዲገሳ ቁልቁሉን መለቴፈሜራ
ደሜ ሜጢቆጴ ገለታፍ ከኤራ
ሰገሌ ሞኢቻን ነን ዋማ መቃሳ
በራ ጂሬኛ ኮን ዱበዳ ዋኤሳ

994. ሥላሴፍ ያገለቱ

ሥላሴፍ ያገለቱ /፪/
ኤኙ አከ ኢሳ /፪/ ከን ነመ ጃለቱ
ለፋፍ ሰሚ ኡሜ ከን በራቼ
ሰገሌን ዬበቴ ከንቀጀልቼ
አቢዲፍ ገላኒሳ አጀጀሙ
ገለትኒ ሥላሴፍ ዮሙ ያዱርፈሙ
ኢሳይያስ ኒአርጌ ሰሚረቲ
ዮሙ አቲን ጂደኒ ቁልቁሉ አቲ
ገልገላፍ ገነማፍ መቃ ዋመና
ኡማ ኡመማቲ ሥላሴቲ አመና
ዋቀዮ አባፍ ኢልማ አፉራ ቁልቁሉ
ሰደኒ ዋቀቶኮ አመኔ ከን ሉቡ
ኡመማ ኡሜራቲ ሞኤ ከን ጂራቱ
ሰብኒ ቢያ ለፋ ኒገለቴፈቱ

995. ጀጀባዳ

ጀጀባዳ /፪/ አመንቲ ኬሰኒን ጀጀባዳ
ሶባን ዱጋ በሁ ሂን ደንደአሙ /፪/
ኒአመናስ ኒ አብደና

ኢርገሞታ ዋቃስ ሂን ሲመና
ዬሮ ረኪና ፊስ ዬሮ ጊዲራ
ዬሮ ዲቢናፊስ አብዲን ኑተኡ
ያ ማርያሚ ያጊፍቲኮ ዳበዱ ሚርገኮ
ኢልመኬ ናፍ ካዱ ዋኤ ሉቡኮ /ፎ/

996. ተክለ ሃይማኖት

ተክለሃይማኖት(ኧ) አባኮ /ፎ/
ናፍ ከደዱ ሂን ኢላሊን አቲ ደደቢናኮ /ፎ/
ጀቢና አመንቲኬን አቲ ከን ቤከምቴዳ
ሰባ ቢያ ኬኛፍ አብዲን ሳኒ ሲዳ
አመንቲቲ ኩፍኔ ኑት ኦፍ ደደብኔራ
ኮቱ አባ ኬኛ ሲቲ ቦአ ጂራ
ኤባ ሀርካ ኬ ባዬ በርባኔራ
አባ አመንቲዳ ኑ ደርበቺሴራ
ባራ ሀማ ካና ቆፋ ሂን ደንዬኙ
ኑቀቢ ሀርካ ኬኛ ዬሮ ሲቲ ቦኙ
አዱኛ ኑጂቤ ወጂን ሲርቡዲናን
ኑ ዋመቻ ጂራ አስኮቱ ጀቹዳን
ኑቶ ኦፊ ኬኛ ጃቢና ሂን ቀብኑ
ሲቲ ቦኛ መሌ ወንተ ታኑ ሂን ቤክኑ

997. ማርያም

ማርያም ማርሚን ጂዳ
ጊፍቲኮ አኒሲንዋመዳ
ረኮንኮ መርቲኑ ተራራ
ሁንዱምቱ ሴና ናፍተኤራ
ማርያም ደሎኒ መርቲኑ
›› መቃ ኬ ያዋመን
›› ሲን ደርበኒ ጂሩ
›› ዲጋ ኢልማ ኬቲን
›› ጃለሊኬ አዳ
›› ማልጀዱ አዮኮ
›› ዲፈማ ናፍ ላቴ
›› ጎፍታ ከደቴቶ
›› አርጁማኬ ማራፍ
›› ኬና ሂን ቀቡ አኒ
›› ሀልካኒፊ ጉያ
›› ናንፋርፈዳ አኒ
ማርያም አዳሚፍ ሰኚንሳ
›› ማርያም ያጀዳኒ
›› ሲቲ ሂርካታኒቲ
›› ገነቲ ካንጋላን
›› ዱከኒ ሂንጂሩ
›› ኢፋ ጂሩከንኮ
›› ኤባ ማርያሚቲን
›› ጉታሜ ኬሲኮ
›› ጋማዬን ቡራቃ
›› አኒ አከ ዋቲ
›› ገነቲ ገሉዳፍ
›› አዮኮ ናፍ ጂርቲ
ማርያም ወሪ ሲቲ አብዳቴ
›› ኤችቱ ረከቴ
›› ኦሌ ኦሶ ሂን ቡሲን
›› ፉርማታ አርጋቴ
›› ቂሌ ናፉልዱራ
›› ላሌ ሶዳዱሌ
›› ቢዲሩንኮ ሲኢ
›› ናንካአ ኩፉሌ
›› ዋዳ ፈኖ ጀላ
›› ማርያሚ ጀቹን
›› ኤችምቱ ሂንቃናኡ
›› ሀርሜ ሲካዳቹኒ

998. ሲጋላቴፈና

ሲጋላቴፈና ዱብሮ ማርያሚ
አብዲ ዋን ኑፍ ታቴፍ አከ ኩፍኔ ሂንሀፍኔ /ፎ/
ኦሶ ሰኚ ሲሂን ሀምቢሱ ባቴ
ኢቢዲ አካ ሰዶሚፍ ገሞራ
ደላ ናመ ኛቴ /ፎ/

999. ዱበርቶታ ኬሳ

ዱበርቶታ ኬሳ ፊለተምቴ
ኬና ዋቀዮ ከን አርገቴ /ፎ/
ገመዲ ዬሮ ሁንዱማ /ፎ/
ያማርሚ ያሀደኮ አብዲን ኬኛ ሱማ

1000. ናሞአቴ

ናሞአቴ ጂሬኚኮ ናጀቤሲ ጊፊቲኮ /ፎ/
ዋቢ ታኢ ዳበዱ ሉቡኮፍ
አቲ ታቦታ ሙሴ ኡሌ አሮኒዳ
ሰኚ አዳም ሁነዳፈ አቲ ሃራርሲቱዳ
ያቆቢ ከን አርጌ ፊኖተሉዛቲ
ከዳ ኬኛ ኦል ከንባስቱ ያቦኖ ወረቄቲ
በገና ዳዊቲ ቢፍቱ ከንገነማ
ኢፋ ኬቲን በዬ ዲጹን ደላ ናማ
ሀዳ ቁልቁሎታ ጎንፎ ኡልፊና ሳኒ
ሉቡን ጉበሞታ ፈዬ ኢልማ ኬኒ
ገመዲ ያ ዱርቦ ዬሱ ዋቀዮዳ
ሰኚ ኢጆሌ አዳሚፍ አቲ ሃራርሲቱዳ
ጨቡኮ ነንዳቡ ፉላ ኢልማ ኪቲ
ጉያ ሙርቲ ሰና ዋቢናፍ ተኢ አቲ
ነገርጋሪ ማርያሚ አኒ ዋ ቶኮ ሂን ቀቡ
ፈዱሳን ኢልማኬ ሆማ ሂንደደቡ
ጨቡፍ ና ቆጼሴ ደዳብኒ ፎንኮ
ከደና ኬቲኒ ናጀቤሲ ጊፍቲኮ

1001. የሮ ኢሲን ዱፍተኒ

የሮ ኢሲን ዱፍተኒ /፪/ ማና ዋቃ ኬኛ
ጋማዳ ናሞታ ሲንሲመቲ ማርያም ሀቲ ኬኛ /፪/
ኤጋ ያናሞታ ሉቡ ኬሰን /፪/ ዋቀዮዳፍ ኬና
ማርያም ሀቲ ኬኛ ኑ ጎርሲቲ ካኔ ደጌፈና /፪/
ሐሜኛ ዲሳቲ ኮታሜ /፪/ ያነማ
ዋቀዮ ሐከደኑ ጋለጋላስ /፪/ ጋናማ /፪/

1002. ኦ ማርያሚ

ኦ ማርሚ ኑ ሲጃለና
ኦ ያጊፍቲኮ ኑሲጃለና
ዋን ኑ ዩሴፍ ፈሪ ጂፈኛ
ሀደ አማኑኤል ኑ ሲጃለና
ለጴኮ ዋን ጋሪ ኑ ሲጃለና
ቡርቂሱ ጀልቀቤ
ገለተ ማርያሚ
ዱበቹ ኤገሌ
ኡልፊኒ ኢሼ አዳ
ከናፍ ኒጃለና
ዋቀዮ ሰሚራ ኑ ሲጃለና
ቢዱ ለፋ ኢላሌ
ቁልቁሉማ ኢሼ
ሁንዱመራ ጫሌ
ሀዳ ጎፍታ ኬኛ
ሂክቱ ሂምቴ ኬኛ
ለሊስቱ ሚደግዱ ኑ ሲጃለና
አቢዳን መርፈምቴ
ሙጫሼ ሀመቴ
ኡሌ አሮኒዳ
ከናፍ ኒጃለና

1003. ያ ማርያሚ

ያማርሚ ጊፍቲኮ ያማርያሚ /፪/
ከንሲራ ደለቴ ፈዩሳ ነሞታ
ገለትኒ ሲፍ ሃተኡ ያ ጊፍቲ ኡማምቶታ /፪/
ሁንዱማ ደንዴኜ ከን ኡሜ ሃርካቲ
ነማ ፈዩሱዳፍ ከን ቡሌ ለፋቲ
ከን ኢልማ ኬ ተኤ ኢልማ ዋቀዮቲ
ነጋን ሲፍ ያተኡ ያ ማርያም ያ ጊፍቲ
ኤርገሞኒ ሰሚ ቄዱ ሲቄዲሱ
ማንጉዶኒ ለፋ ኤባ ሲ ኤቢሱ
ያ ሀርሜ ዋቀዮ ጀደኒ ሲ ፋርሱ
ሰገሌ ቶኪቻን ነጋ ሲፍ ዲዩሱ
ገብርኤሊ ኤርገማን ገረኬ ኤርገሜ
ያ ዱርቤ ዱርቡማን ኢልማ ዴሳ ጀዴ
ኤርጋ ጎፍታን ሙጫ ከን ኡፌ ሲቲሂሜ
ነጋን ሲፍ ያተኡ ያ ማርያም ያ ሀርሜ

1004. ያመና ዋቀዮ

ያመነ ዋቀዮ ኡልፊና ቀቤቲ
ኮቱ ኑኤቢሲ ማርያም ቁልቁሌቲ
ከራ በዲኢራ አቲ ኑዴቢሲ
ኢልመኬ ከደዱ ማሎ ኑሀራርሲ
ዱሜሳ ኤሊያስ ከንኢቲን አብደኔ
ቆሪቻ ናሆሚ ከን ኢቲን ፊዩኔ
ሞቲን በረበራ ከን ሂን ጂጂረምኔ
ክርስቶስ ዋቀዮ ሲሀዳ ኑፍ ኬኔ
አርጆምኒ ቢሻኒ መቃኬን ኬነሜ
ሉቡዱኤ ወጂን ዬሙ መዳለምኔ
ፈዩናፍ ተኤራ ኑቲስ ከነ ቤክኔ
ኑደገሂ ጊፍቲ ዬሙ ሲዋመኔ
ኑወጂን ዳበዱ ያጊፍቲ ማርያሚ
ኢልመኬ ኑፍ ከዱ ጂፈኖፍ ኑዋሚ
ኑ ሁምና ሂን ቀብኑ ሰጎደና ሂርኮ
አቲ ኑጀቤሲ ሀደ ጋፈ ረኮ

1005. ኪዳነ ምህረት

ኪዳነ ምሕረት ነ ሂን ዳጋቲኒ
ዮና ገሄራ አራራ ኬቲኒ
ዮሙ ናፍ ሮቡ ዲፈምኒ ሀርካ ኬራ
ዱኩባ ኮራስ ዱጉማ ፈዬራ
ጋራ ላፌቲኮ አቲ ዱጉማ ነመፍ ገዲታ
ነመ ዱአፍ አብዲ ኩቴ ዱፍቴቶ ጀጀቤሲታ
ጎዶኮ ኢሳ ዱከናኤ ደፍቴቶ ኢፋኬ ጉቴ
አን ነማ ሞፋ ኡፈቱ ወየሀራ ነቲ ኡዊስቴ
ሀርከ ነማስ ሂን ኢሳሉ አኖ ለመታ ጊፍቲኮ
መነ ነማስ ሂን ከጀሉ ናፍ ኤቢስቴርታ ጎደኮ/፪/
ኮልፈ ኢሳኒነን ደደቤ ዋራ ዬሮስ ሶሮማኒ
ኢሳኖ ተሳን ሂን ቤከን ቦደሞ ሂዩማ ኢሳኒ
አንገለገሌን ሂን ኢላሉ ዬሮ ኢሳን ናቲ ኮልፈኒ
አከ አቲ ነባስቱ ቤካ ጊፍቲኮ ሲቲ ቦኛኒ
አኩማ ጀዬስ ጊፍቲኮ አቲ ዮም ነኢራፈቴ
ሂዩማኮ ኢሳ ዱሪ ሴና ጎቴ ደበርሲቴ /፪/
ከንኬ ናዲባ ጊፍቲኮ በገን ገርቢቻኬተኤ
ገመቹዳነን ጉተሜ ሲፍ ፋርፈዳ አንአማ ከኤ
ሜሬሬ ሃቲሳ ጀዱ ኢሼኖ ማሊፍ ሂንፈዩስቱ
አኒስ ዬቢሴነን ጀዳ ኢሼኖ ሂን አሪፈቱ
አካሳኒ ዱሪ ሚቲ ደደንደአን ሂን ዱበተኒ
ነፈዩሱሼ አርገኒ አፋሳን ኒቀበተኒ
ማል ጀደኒ ዱበቱሬ ቴላቲን ዬደቢአን
ከነን ኢቲን ቦኑ ሀቲኮ ናፈዩሱሼ አርገኒ

1006. ፎንኮ

ፎንኮ ሉቡኮ ማሊፍ ሚታ(ኧ)
ለጉፍ ከደና ዶርኪቴርታ /፪/
ራፍ በርባዬ ዮ ገበቴ

ከራ አዱኛ ኢራ ዶዶቢቴ
ኤጋ ፎንኮ ተሳ ታቴ /፪/
ገላ ሂራፈቴ ሉቡ ሁቤ
ጎፍታን ና ዋመናን ዶቢ ደቤ
ጉያን ከበጃ ነራ ደርቤ /፪/
ለኪ ፎንኮ አደበዱ
ነሰልጲሱዳፍ ቀልቤፈዱ
ሉቡ ኮፍ ጀዲ ሲሬፈዱ /፪/
ዱጋ ጀሊሰቴ ሶባ ባቴ
ጎፍታ ኡማኬ ኢንራፈቴ
ጉያኬ ዱሜ ሲቲ ዲቴ /፪/

የመስቀል ወረቦች

1007. በዓለ መስቀል

በዓለ መስቀል ክቡር ይትቀደስ ስምከ በኃይለ መስቀልከ ዕፀ መስቀልከ ዘአዕይኮ ለስምከ ስብሐት ለከ ለባሕቲትከ

1008. ርዕዩ

ርዕዩ ዕበዩ ለዕፀ መስቀል ዩም በምድር ተዝካሩ በሰማያት በላዕሉ በሰማያት

1009. እምገቦ ከ ዉኅዝ

እምገቦ ከ ዉኅዘ ነቅዓ ማይ ዘቀደሶ ለፈ ይታይ። ለነዳይ ምስካይ መስቀልከ እግዚኦ ለነዳይ ምስካይ

1010. ደመ ወማየ

ደመ ወማየ አዉኅዘ ለነ ደመ ወማየ ዩም ንዜኑ ዘመስቀል ዕበየ ንዜኑ ዘመስቀል ዕበየ።

1011. እምገቦከ ዉኅዘ

እምገቦከ ዉኅዘ ነቅዓ ማይ ዘቀደሶ ለፈይታይ።

ለነዳይ ምስካይ መስቀልከ እግዚኦ ለነዳይ ምስካይ።

1012. ይቤሎሙ

ይቤሎሙ ኢየሱስ ይቤሎሙ ኢየሱስ ለአይሁድ

እመኑ ብየ ወአመኑ በአቡየ አበርህ በመስቀልየ ለእሊአየ

1013. መስቀል አብርሃ

መስቀል አብርሃ በክዋክብት አሠርገወ ሰማይ።

እምኩሉሰ ፀሐየ አርአየ እግዚአብሔር

የሕዳር 6 ወረቦች

1014. ፀምር ፀዓዳ

ፀምር ፀዓዳ መሶበ ወርቅ እንተ መና መሶበ ወርቅ ።

በትረ አሮን እንተ ሠረፀት እንተ ሠረፀት መሶበ ወርቅ።

1015. ረኃበ ወጽምዓ

ረኃበ ወጽምዓ አዘክሪ ድንግል ረኃበ ወጽምዓ

ምንዳቤ ወኀዘነ አዘክሪ ድንግል ።

1016. አብርሂ አብርሂ

አብርሂ አብርሂ ኢየሩሳሌም

በጽሐ ብርሃንኪ ኢየሩሳሌም ደብረ ሎዛ

1017. ዮም ጸለሉ

ዮም ጸለሉ መላእክት ላዕለ ማርያም ወላዕለ ወልደ ክርስቶስ በደብረ ቁስቋም።

እንዘ ይብሉ ስብሐት ስብሐት በአርያም ስብሐት በአርያም

የሕዳር 21 ወረቦች

1018. ወይቤላ

ወይቤላ ኢተረእይኑ ላህዚአነ እንተ ረከበተነ።

ዕዝራኒ ርእያ ወተናገራ።

1019. እንተ ክርስቶስ

እንተ ክርስቶስ መሠረትኪ ፀሐየ ጽድቅ ያበርህ ለኪ ፀሐየ ጽድቅ ።

ለሰማዕት ሥርጉት በስብሐት ሥርጉት በስብሐት።።

1020. ታቦተ ሕጉ

ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር በካህናት ሕፅርት ወበ መንፈስ ቅዱስ ክልልት

ንጉሥኪ ጽዮን ኢይትመዋዕ ለፀር ወኢየኃድጋ ለሀገር

1021. ሃሌ ሃሌ ሉያ

ሃሌ ሃሌ ሉያ በጾም ወበ ጸሎት

ተመጠወ ሙሴ ኦሪተ አሥሮን ቃላተ

የካቲት 16

1022. አንቲ ዉእቱ

አንቲ ዉእቱ ተስፋሁ ለአዳም እንቲ ዉእቱ

አመ ይሰደድ እምገነት አመ ይሰደድ እምገነት

1023. ኪዳንኪ ኮነ

ኪዳንኪ ኮነ ኪዳንኪ ኮነ ኪዳንኪ ኮነ

ለኃጥአን ቤዛነ ኪዳንኪ ኮነ ለኃጥአን ቤዛነ ኪዳንኪ ኮነ

1024. ይነግሥ ወልድ

ይነግሥ ወልድ በደብረ ጽዮን አመ ይነግሥ ወልድ

ክፍልኒ ድንግል ዕቁም በየማን

1025. አንገርጋሪ

ክነፈ ርግብ በብሩር ዘግቡር ወገበ ዋተሃኒ በሐመልማለ ወርቅ አንቲ ምሥራቅ ወወልድኪ ፀሐየ ጽድቅ ምሥራቅ ደብረ ሎዛ።።

ነሐሴ 16

1026. ደብተራ ፍጽምት

ደብተራ ፍጽምት ዘጻዉሊ ፈለሰት እምዘይበሊ ጎበ ኢይበሊ

በመሰንቆሁ እንዘ የጎሊ ዳዊት አቡሃ ዘወልዳ ወዓሊ።።

1027. ሰላም ለኪ ማርያም

ሰላም ለኪ ማርያም እመ አምላክ ማኅደረ መለኮት

ወልድኪ ወልድኪ ይጼዉዓኪ ዉለተ ሕይወት ወመንግሥተ ክብር

1028. ንዒ ኅቤየ

ንዒ ኅቤየ አንቲ አየ ሠናይት ርግብየ

መዓዛ አፉሃ ከመ ኮል መዓዛ አፉሃ ከመ ኮል

1029. አንገርጋሪ

ትርሢተ ወልድ መለኮት ወፍቅር ኀደረ ላዕሌሃ

ይቤላ ርግብየ ወይቤላ ወደቤላ ሠናይትየ።።

ወረብ በእንተ ቅዱስ ኡራኤል

1030. ሰዓለነ ሊቀ መላእክት

ሰዓለነ ሊቀ መላእክት እምሀበ እግዚአብሔር

ሰአለነ ሊቀ መላእክት

ከመያዝንም ለነ ዝናመ ምኅረት /፪/

1031. ንዒ ሀብየ

ንዒ ሀብየ አድንግል ምስለ ኤልያስ ወኤልሳ ነብይ

ወምስለ እዝራ ሱቱኤል ፅዋዕ ልቦና ዘአስተርዮ ኡራኤል መላእክ

1032. ለከ ይደሉ

ለከ ይደሉ ክቡር ወስብሐት ወስግደት ለከ ይደሉ

እምጎበ መላእክተ ወሰብ እምጎበ መላእክ

1033. ይእቲ እሞሙ

ይእቲ እሞሙ ለሰማዕት ወእቶሙ ወመላእክት

ቃልኪ አዳም ይትመኒ ዘእምአስካለ ወይን

ወረብ በእንተ ቅድስት አርሴማ

1034. አርሴማ ሰማዕት

አርሴማ ሰማዕት ፈለሰት ነያ /፪/

ይእዜኒ ለሰላም ንትልዋ /፪/

1035. አርሴማ ሰማዕት ስርጎት

አርሴማ ሰማዕት ስርጉት በሐይማኖት /፪/

ወበ መንፈስ ቅዱስ ክልልት /፪/

1036. ሃሌሉያ በመዓዛ

ሃሌሉያ በመዓዛ ፍቅርከ ክርስቶስ

ሰማዕትነ ህማማተ ወፃድቃን ኤሊገዳማተ

1037. አድህንኒ ወባልህኒ

አድህንኒ ወባልህኒ በኪዳንኪ በቂኢ

አመወርሐ ጽልመት አብይ ወእሳት በላኢ